# ሚዛን የጠበቀ




## A Balanced Life & Ministry

ከበደ በከሬ

# ሚዛን የጠበቀ ሕይወት እና አገልግሎት

ጸሐፊ:- ከበደ በከሬ

እርማት:- መጋቢ ስሜ ታደሰ

ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1998 ዓ.ም.

# ሚዛን የጠበቀ ሕይወት እና አገልግሎት

A Balanced Life and Ministry

ደህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት ወይም እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

ማስታወሻነቱ ለአራተኛው ልጃችን ለኬና ክበደ ይሁን!

የሽፋን ሥዕል በመጋቢ ይድነቃቸው ለገሠ

ምሥጋና

ከሁሉም በላይ በዘላለም ፍቅሩ ለወደደኝና ለአገልግሎቱ ታማኝ አድርጎ ለቆጠረኝ ለእግዚአብሔር ክብርና ምሥጋና እስከዘላለም ይሁን! ውድ ጊዜያቸውን ስለሰጡኝ ለቤተሰቤ ከፍ ያለ ምሥጋና አቀርባለሁ። ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት የሚያስፈልገኝን መረጃ ለማግኘት ቃለመጠይቅ ሳደርግ ፈቃደኞች ሆነው ልምዳቸውን ላካፈሉኝ ሁሉ እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካችሁ እላለሁ። የመጽሐፉን ረቂቅ በማንበብ ገንቢ አስተያየት ለሰጡኝ ለመጋቢ ተፈራ ጎንፋ፣ ለመጋቢ ይድነቃቸው ለገሠ እንዲሁም የቋንቋ እርማት ላደረጉልኝ ለአቶ በሜ ታደሠ ምሥጋናዬ የላቀ ነው።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP-20 3M

ማውጫ

ገጽ

መግቢያ ........................................ 4

ክፍል አንድ፡ የመንፈሳዊ አገልግሎት ሕይወት

1. ሚዛን የጠበቀ ሕይወት እና አገልግሎት አስፈላጊነት ............ 7
2. የአገልጋይ የትኩረት ቅደም ተከተል ............ 16
3. አገልጋይ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ............ 22
4. የአገልግሎትና የቤተሰብ ግንኙነት ............ 25
   4.1. አገልጋይና የትዳር ጓደኛው ............ 40
   4.2. አገልጋይና ልጆቹ ............ 62
   4.3. አገልጋይ የቤተሰቡን አገልግሎት ለማጠናከር የሚረዱ መልዕክቶች..... 75
5. በአገልግሎት ውስጥ የመልካም ጓደኛ አስፈላጊነት ............ 81
6. የተቃራኒ ጾታ ግንኙነትን በሚዛን ማድረግ ............ 94
7. የአገልግሎትና የጊዜ አጠቃቀም ............ 107
8. በአገልግሎት መዳሸቅን መከላከል ............ 120

ክፍል ሁለት፡ የክርስቲያን ሕይወት

9. ክርስቲያንና ሥራ ............135
10. ሥራን፣ ክርስቲያናዊ ሕይወትና አገልግሎትን በሚዛን መጠበቅ..........159

ዋቤ መጽሐፍት

## መግቢያ

መንፈሳዊ አገልግሎት ሰዎች በእግዚአብሔር ተጠርተው በእርሱ ጸጋ የሚሠሩት ሥራ ነው:: ሥራው በእግዚአብሔር ጸጋ ቢሠራም አድካሚ ሥራ ነው:: በዚህ መንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ የተሰማሩ አገልጋዮች በሁለንተናዊ ሕይወታቸው ማለትም በግል፣ በመንፈሳዊና ማህበራዊ ሕይወታቸውን በማይጎዳ መልኩ አገልግሎቱን ለማከናወን ጥረት ካላደረጉ ሕይወታቸው እንዲሁም አገልግሎታቸው ይጎዳል:: መንፈሳዊ አገልግሎት ፍሬያማ እንዲሆን የእግዚአብሔርን እሳብ ከቃሉ ማወቅና እርሱ እንደሚፈልገው ማገልገል ያስፈልጋል::

እግዚአብሔር በቅድሚያ ማንን እንድናገለግል ይፈልጋል? ይህ ምንም ጥያቄ የሚያስፈልገው አይመስልም:: እግዚአብሔር ከሁሉም በፊት እርሱን እንድናገለግለው ይፈልጋል:: እግዚአብሔርን ማገልገል ማለት ግን ምንድነው? ጌታን አገለገልን ብለን አፋችንን ሞልተን መናገር የምንችለው ምን ስንሠራ ነው? አገልግሎቱስ ከየት ይጀምራል?

እግዚአብሔር ራሳችንን፣ ቤተሰቦቻችንን፣ እርሱ የጠራቸውን ሕዝቡንና ገና ወደ ቤቱ ያልመጡ በውጭ ያሉትን ሰዎች እንድናገለግል ይፈልጋል:: የአገልግሎት ተቀባዮቹ ብዙ ናቸው:: እኛ ራሳችን፣ ቤተሰቦቻችን፣ ምዕመናንና ያላመኑ ሰዎች ናቸው:: ከእነዚህ ተገልጋዮች የመጀመሪያው ትኩረት መደረግ ያለበት በየትኞቹ ላይ ነው? ለማን ቅድሚያ ቢሰጥ እግዚአብሔር የሰጠንን መንፈሳዊ አገልግሎት እንደሚገባ ማገልገል እንችላለን?

ይህ መጽሐፍ ትኩረት ያደረገው በግል ከእግዚአብሔር ጋር ባለን መንፈሳዊ ግንኙነት፣ በቤተሰብና አገልግሎት መካከል ሊኖር በሚገባው ሚዛን ላይ ነው:: እግዚአብሔርን ማገልገል የሚቻለው ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ መንፈሳዊ ተራክቦ በማድረግ ነው:: ከእርሱ ጋር ያለው ግንኙነት ጤናማ ካልሆነ የግል ሕይወት፣ ቤተሰብና አገልግሎት እየተበከለ ይሄዳል:: ቤተሰብ መንፈሳዊ አገልግሎት የሚጀመርበት መሠረትና የሚያድግበት አውድ በመሆኑ ሌሎች ሰዎችን ከማገልገል በፊት የግል ቤተሰብን ማገልገል ተገቢ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ተግባር ነው:: ከቤተሰብ ውጭ ያለው አገልግሎት ፍሬያማ የሚሆነው አገልጋይ ለቤተሰቡ ትኩረት በመስጠት እነርሱን ማገልገል ሲችል ነው:: የሕይወታችው ቋሚ መመሪያ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል አገልግሎት ከቤተሰብ እንደሚጀምር ያስተምረናል:: ስለዚህ ለቤተሰብ ተገቢውን ጊዜ በመስጠት አስፈላጊውን ፍቅርና እንክብካቤ መስጠት ተገቢ ነው::

አገልጋይ ሕይወቱንና አገልግሎቱን ሚዛን በጠበቀ ሁኔታ እየመራ መሆኑን ሊያሳየው የሚችል፣ በሕይወት ውስጥ ተግዳሮት ሊገጥመው የሚደግፈውና በሕይወት ጉዞ አብሮ ሊጓዝ የሚችል ጓደኛ ያስፈልገዋል:: ጓደኛ ለማግኘት ደግሞ አገልጋይ ለማሕበራዊ ግንኙነት ትኩረትና ጊዜ መስጠት ይገባዋል:: ይህ ዝግጅት አገልጋይ ጓደኛ ማግኘቱ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ለአገልጋይ ምን ዓይነት ጓደኛ እንደሚያስፈልገው በስፋት ይዳስሳል::



አገልጋይ በማህበራዊ ግንኙነቱና በአገልግሎት ሁኔታ ከብዙ ዓይነት ሰዎች ጋር ይገናኛል:: አገልጋይ ከሚገናኛቸው ሰዎች መካከል የተቃራኒ ጾታ ይገኙበታል:: አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ማድረግ ይጠበቅበታል? ይህ ግንኙነት ተገቢውን ሚዛን ካልጠበቀ የአገልጋይን ሕይወት፣ ቤተሰብ፣ አገልግሎትና ቤተክርስቲያንን እጅግ ሊጎዳ ይችላል:: ስለዚህ አገልጋይ ሚዛን የጠበቀ ግንኙነት ከተቃራኒ ጾታ ጋር ማድረግ አለበት:: ይህን እንዴት ሊያደርግ እንደሚችል ሰፊ ማብራሪያ ተሰጥቷል::

አገልጋይ በተለያየ የሕይወት ገጽታውና በአገልግሎቱ መካከል ተገቢ የሆነ ሚዛን መጠበቅ ካልቻለ ሕይወቱና አገልግሎቱ እየደከመ ይሄዳል:: ጸጋውና ኃይሉ ተማጥጦ ያልቅና እንደ ተመጠጠ ሸንኩራ ይሆናል:: በአገልግሎት መድከም የሚመጣባቸው መንገዶችና ሁኔታዎች እንዲሁም እንዳይመጣ እንዴት መከላከል እንደሚቻል ተጨባጭ የሆኑ መርሕ አሳቦች ተጠቅሰዋል::

ከዚህም የተነሣ መጽሐፉን ለማዘጋጀት አስፈላጊው ጥናት ተደርጓል:: በተለይ አሁን በቤተክርስቲያን እያገለገሉ ያሉ አገልጋዮች አገልግሎትንና ቤተሰብን በተመለከተ ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ ብዛት ያላቸውን አገልጋዮች እንዲሁም የትዳር ጓደኞቻቸውን በተጨማሪም የአገልጋይ ልጆችና ምዕመናን ስለ አገልጋይ የግል፣ መንፈሳዊ፣ የቤተሰብ ሕይወት፣ ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነትና እጠቃላይ አገልግሎት ምን እንደሚመስል ለማወቅ ለብዙ ሰዎች ቃለመጠይቅ ተደርጓል::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አገልጋይ የሚለው ቃል ወንዶችና ሴቶች አገልጋዮችን ያጠቃልላል:: እግዚአብሔር ወንዶችን እንዲሁም ሴቶችን የጾታ አድልዎ ሳያደርግ ለአገልግሎት ይጠራል::[1]

አገልጋይ ብቻም ሳይሆን እያንዳንዱ የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው ሁሉ ሚዛን የጠበቀ ሕይወት ሊመራ የተገባ ነው:: ሕይወትን በሚዛን መጠበቅ ከሚገለጥባቸው መንገዶች አንዱ በሥራ፣ በግል ሕይወት፣ ለቤተሰብና ለመንፈሳዊ አገልግሎት በሚሰጠው ትኩረትና ጊዜ መካከል ሚዛን በመጠበቅ ነው:: ይህን በተመለከተ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች ለሥራ ሊኖረን የሚገባ አመለካከትና ትጋት፣ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሊኖረን የሚገባ አይታና ሊንሰጠው የሚገባን ትኩረትና ጊዜ ምን መሆን እንዳለበት ጠቃሚ ምክሮች የሚሰጡበትም ሁለት ምዕራፎች በመጨረሻ ላይ ቀርበዋል::

እንግዲህ አንድ አገልጋይ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን መርሆዎች በመከተል ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን መንፈሳዊ ኅብረት በመጠበቅ፣ ቤተሰቡን ማለትም ከሚስቱና ልጆቹ ጋር እንደ መልካም ባልና አባት በመኖር፣ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ከእርሱ ጋር የሚቆም ጓደኛ በማፍራት እንዲሁም በማህበራዊና የአገልግሎት ግንኙነቱ ከሚገጥሙት ተቃራኒ ጾታ ጋር ወሰኑን የጠበቀ ኅብረት በማድረግ እንዲሁም ጸጋውና ኃይሉ እንዳይላሽቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ አገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን ማድረግ ይችላል:: በመጨረሻም አማኞች በዓለም ውስጥ

---

[1] ማስታወሻ:- «አገልጋይ» የሚለው ቃል ሁለቱንም ጾታዎች ያካተተ መሆኑን አትዘንጉ::

አገልጋይ ከቤተሰብ ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረው የሚያጋጥሙት ችግሮች ለቤተሰብ ሊያካፍላቸው ቀላል ሆነው ይታያሉ። ምክንያቱም ቤተሰቡ ሁሉ ከእርሱ ጋር ሆነው ችግሩን ለመሸከምና ለመቅረፍ ጥረት ያደርጋል። በአገልግሎት ውስጥ የሚያገኘው ደስታ ደግሞ የላቀ ይሆናል። ደስታው የአንድ ሰው ብቻ ሳይሆን የቤተሰቡ ሁሉ ይሆናል።

**ለቤተሰብ ትኩረት መስጠት ለፋጣኝ ብድራት ለለማግኘት:-** በአብዛኛው በቂ ጊዜ የሚሰጠው በጣም አስፈላጊ ለተባለ ነገር ነው። በሕይወታችን አስፈላጊ የሆነውን ነገር የምንመዝንበት መሥፈርት የተለያየ ነው። ከእነዚህም አንዱ የሚሠራው ሥራ የሚያመጣው ብድራት ነው። ብድራቱ ጥቂት ነው ወይስ ብዙ እንዲሁም በቶሎ ይገኛል ወይስ ይቆያል የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ እናስባለን። አንዳንዶች ቶሎ ብድራት የማያስገኘው ተግባር ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ ቶሎ ብድራት የሚያስገኘው ሥራ ጠቃሚም ቢሆን ችላ ይሉታል። አገልጋይ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ወይም በሌሎች ሥፍራዎች ተጋብዞ ሊያገለግል ወቅታዊ የሆነ ብድራትን ያገኛል። የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎች ጥሩ የሆነ የምሥጋና ምላሽ ወይም ገንዘብ ሊሰጡት ይችላሉ። ይህ ጊዜያዊ የሆነ ብድራት አገልጋይ ለቤተሰብ ትኩረት እንዳይሰጥ እንቅፋት ይሆንበታል። ቤተሰብን ማገልገል በረጅም ጊዜ ውስጥ ብድራቱን የሚመልስ ሥራ ነው። ስለሆነም ለጊዜያዊ ጥቅም ብሎ ዘላቂ ብድራት ያለው የቤተሰብ አገልግሎት እንዳይጎዳ ተገቢውን ወሰን ማበጀት ይበጃል።

**አገልግሎት ከቤት ውጭ እንደሆነ በመታሰብ:-** በአብዛኛው ሰዎች አገልግሎትን የሚያዩት ከቤተሰብ ውጭ እና ስኬቱም በአደባባይ እንደሆነ ነው። ይህ አመለካከት ደግሞ አገልጋይ ለቤተሰቡ ትኩረት እንዳይሰጥ እንቅፋት ይሆናል። በአገልግሎትና በቤተሰብ መካከል የሚፈጠረውን የሚዛናዊነት ችግር ለመቅረፍ አገልጋይ ሁልጊዜ ራሱን መሆን ይኖርበታል። አገልጋይ በውስጡ የሚያምነውን ለመኖር የሚጨክን ልብ ሊኖረው ይገባል።

**ለአገልጋይ ቤተሰብ ትኩረት ለለማይሰጥ:-** ለቤተክርስቲያን ምዕመናን የሚሰጠው የእረኝነት አገልግሎት እልፍ እልፍ ካልሆነ በስተቀር ለአገልጋይ ቤተሰብ ትኩረት አይሰጥም። እነርሱ የአገልጋይ ቤተሰብ ስለሆኑ ተገቢውን አገልግሎት ያገኛሉ ብሎ ከማሰብና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በቤተክርስቲያን እረኝነት አገልጋዮች ዘንድ እንደ ሌሎች ምዕመናን ስለማይቆጠሩ ችላ ይባላሉ። የአገልጋይ ቤተሰብ እንደሌላው ቤተሰብ ችግር ያለው አይመስልም። እነርሱ ሌሎች ሰዎችንና ቤተሰቦችን ይጠይቃሉ፣ ይመግባሉ፣ ይጠብቃሉ እነርሱ ግን የሚያስብ እምብዛም ነው። ይህ ሲባል ግን ሰዎች እቤታቸው አይመጡም ማለት አይደለም። እቤታቸው የሚመጡ ብዙ ሰዎች አሉ። ነገር ግን እነርሱን ለማገልገል ሳይሆን የራሳቸውን ጉዳይ ይዘው ይመጣሉ። በአገልጋይ መገልገል እንጂ የአገልጋይን ቤተሰብ በሁለንተናቸው ማገልገል አልተለመደም።

አንድ አገልጋይ ለአገልግሎት ሊወጣ ቤተክርስቲያን ለቤተሰቡ እንክብካቤ እንደማታደርግ አምርሮ ይናገር ነበር። «የቤተክርስቲያን መጋቢ በመሆን በተለያዩ የአገልግሎት ደረጃዎች ለ25 ዓመታት አገልግያለሁ። አንዳንድ ጊዜ ለአገልግሎት በቤተክርስቲያን ተልኬ ለሳምንታት እስከ ወራት ድረስ ከቤተሰቤ ተለይቼ በተላኩበት ሥፍራ እቆያለሁ። እብረውኝ የሚያገለግሉ



አገልጋዮችም ሆኑ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ባለቤቴንና ልጆቼን አይጠይቁም። ወደ ቤት ተመልሼ እንዴት እንደቆዩ ስጠይቃቸው ማንም ሰው ሳይጠይቃቸው እንዲሁ እንደከረሙ ሲነግሩኝ መንፈሴ በጣም ያዝናል። ቤተሰቤ ተገቢውን እንክብካቤ በማጣታቸው ማዘን ብቻ ሳይሆን የብቸኝነት ስሜት ይሰማኛል። እጅግ ከባድ የሚሆነው ደግሞ የተሰማኝን ስሜት በቀጥታ መግለጽ አለመቻሌ ነው። ቤተሰቤን ለምን እንዳልጎበኙ ብጠይቃቸው ለራሱ ብቻ የሚያስብ አገልጋይ ነው እንዳይሉኝ ፈርቼ እተዋለሁ። ስለዚህ ቤተሰቤን ለምን እንዳልጠየቁ እንኳ ከራሴ ግምት በስተቀር እነርሱን ጠይቄ አልተረዳሁም። ምክንያቱ ምንም ቢሆን አንድ የማውቀው ነገር ቢኖር የአገልጋይ ቤተሰብ በቤተክርስቲያን ውስጥ ችላ የተባለ ቤተሰብ መሆኑን ነው።»

እንግዲህ የአገልጋይ ቤተሰብ አገልጋዩ በማይኖርበት ወቅት ከሌሎች እንክብካቤ የማያገኙ ከሆኑ ለማን መተው አለባቸው? የቤተሰቡ ተቀዳሚ ባለአደራ የሆነው አገልጋዩ ራሱ አገልግሎቱን በማይበድል ሁኔታ ለቤተሰቡ ተገቢውን ጊዜ መመደብ ይኖርበታል።

**የሌሎች ቤተሰቦች ሸክም መብዛት:-** የአገልጋይ ቤተሰብ ከራሱ ችግርና ተግዳሮት አልፎ የሌሎች ቤተሰቦችን ሸክም ይሸከማል። አገልጋይ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ቤተሰቦች ችግር ይዞ ወደ ቤት የሚመጣ ከሆነ ቤተሰቡ ከራሱም በተጨማሪ የብዙዎችን ቤተሰብ ችግር ይሸከማል። የሌሎች ቤተሰቦች ችግር የአገልጋይን ቤተሰብ ያስጨንቃል። እነርሱም የሌሎችን ቤተሰብ ችግሮች እንደራሳቸው በመቁጠር ይጨነቁበታል። ይህ ደግሞ ከገደብ ሊያልፍ ቤተሰብን የማናጋት ኃይል ይኖረዋል። የሌሎች ሰዎችንና ቤተሰቦችን ችግር መሸከም የግልና የቤተሰብ ሕይወትን እንዳያናጋ ሚዛን መጠበቅ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑ ሊተኮርበት ይገባል።

የእግዚአብሔር ቃል መንፈሳውያን የሆኑ ምዕመናን አገልጋይንም ጨምሮ የሌሎችን ችግር መሸከምና እንደ ወጌሻ የሰዎችን ውስጣዊ ስብራት በመጠገን መፈወስና መመለስ የተሰጣቸው ኃላፊነት መሆኑን በግልጽ ይናገራል (ገላ.6:1-2)። ሆኖም ይህ የሌሎችን ሸክም መሸከምና መጠገኑ ሂደት አገልግሎቱን የሚሰጡትን ሕይወት የሚፈትንና ወደ ኪሣራ የሚያመራቸው ሊሆን አይገባም። መፍትሔው የራስን ሕይወት በሚዛን እየጠበቁ ሌሎችን ማገልገል መቻል ነው።

**የአገልጋይ ቤት እንደ ምዕመናን ቤት መቆጠር:-** በአብዛኛው ምዕመናን የአገልጋይ ቤት እቤታቸው ወይም የቤተክርስቲያን ቤት እንደሆነ በማሰብ የአገልጋይ ቤተሰብ የራሳቸው ነጻነት እንዳይኖራቸው ያደርጋሉ። ይህን አስመልክቶ ሁለት ጸሐፊዎች «የአገልጋይ ቤት የአገልግሎቱ ክፍል ቢሆንም የቤተክርስቲያን ሕንጻ አንድ ክፍል እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል። እርሱና ቤተሰቡ እንደ ማንኛውም የቤተክርስቲያኒቷ አባሎች የግላቸው ነጻነት ሊኖራቸው ይገባቸዋል» በማለት ተናግረዋል።[2] በዚህ አሳብ መሠረት በአገልግሎትና በቤተሰብ መካከል ሚዛን የሚዛባው ምዕመናን ለአገልጋይ ቤተሰብ ጥንቃቄ ባለማድረግ ቤታቸውን እንደ ቤተክርስቲያን ሕንጻ በማሰብ ያለገደብ መጠቀም ሲጀምሩ ነው። ይህ የአገልጋይ ቤት እንደ ልባቸው

---

[2] Sugden, Howard F. and Wiersbe, Warren W. (1980). *Confident Pastoral Leadership*. Chicago, Moody Press, p.141

ያለምንም ፈቃድ ወይም አስቀድሞ ሳያሳውቁ መሄድና በአነርሱ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባትን ያጠቃልላል:: ከዚህ በላይ አገልጋይ ከቤተሰቡ ጋር በሚሆንበት ወቅት ሳያስቡላቸው ጥሪ ማድረግም ሌላው ጣልቃ መግባት ነው:: ለምሳሌ አገልጋይ በዓመት በዓል እንደሌላው ምዕመን ከቤተሰቡ ጋር ማሳለፍ ሲገባው ለአገልግሎት መፈለግ ራስ ወዳድነትና ለአገልጋይ ቤተሰብ አለማሰብን ያመለክታል::

*አገልግሎት ማህበራዊ ግንኙነትን ይገድባል፡-* ከሥራው ባሕርይና ከጊዜ ማጣት የተነሳ አገልጋይ እንደ ፍላጎቱ ማህበራዊ ግንኙነትን ከሚፈልጋቸው ሰዎች ጋር ማድረግ አስቸጋሪ ይሆንበታል:: አገልጋይ ከሚያገለግልበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ውጭ ካሉት ሰዎች የሚገናኝበት ሰፊ ዕድል የለውም:: ከሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ምዕመናን ጋር የሚገናኘው በአገልግሎት ስለሆነ የአገልጋይና ተገልጋይ ግንኙነት እንጂ የጓደኝነት ግንኙነት አይኖረውም:: ይህ ደግሞ የግል ጉዳዩን የሚያካፍለውን ሰው እንዲያጣ ያደርጓል::

*የተቃራኒ ጾታ የፈተና ወጥመድ፡-* ለአንድ መንፈሳዊ አገልጋይ ወጥመድ ሊሆኑ ከሚችሉ ዋና ዋና ነገሮች አንዱ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ነው:: አገልጋይ ተመሳሳይ ብቻ ሳይሆን ተቃራኒ ጾታን ማገልገል ይጠበቅበታል:: በእሁኑ ጊዜ ጥቂት የማይባሉ አገልጋዮች በዚህ ፈተና ውስጥ ወድቀዋል:: አንዳንዶች ቤተክርስቲያን በበደት ውስጥ በነበረችበት ወቅት ትልቅ ዋጋ የከፈሉና ለቤተክርስቲያን እንደ አርበኞች የሚቆጠሩ ናቸው:: ይህ ችግር በሰፋት እንዲጎላ ካደረጉት ነገሮች አንዱ አገልጋይ ወሰንን የጠበቀ ግንኙነት ከተቃራኒ ጾታ ጋር አለማድረግ፣ ፈተናው ሲገጥመው ከአርሱ ጋር ሆኖ ሊረዳው የሚችል የቅርብ መንፈሳዊ ጓደኛ እንዲሁም ምስጢሩን በመጠበቅ እንደ መንፈሳዊ ሞግዚት ሆኖ ሊረዳው የሚችል ሰው አለማግኘት ወይም አለመኖር ነው::

*የአገልጋይ የጊዜ አጠቃቀም ችግር፡-* አገልጋይ ከእውቀት ማነስ ወይም ከቸልተኝነት የተነሳ በጊዜ አጠቃቀም ከፍተኛ ድክመት አለው:: ከዚህም የተነሳ ለግል ሕይወታቸው፣ ለቤተሰብና ለአገልግሎት መስጠት የሚገባቸውን ጊዜ በዕቅድ አይጠቀሙበትም:: በዕቅድ ከመመራት ይልቅ በሁኔታዎች ግፊት በግብታዊነት እንደ ሁኔታው የማድረግ ዝንባሌ ይታይባቸዋል:: አገልጋይ ጊዜውን በዕቅድ ስለማይጠቀም አንዳንድ ጊዜ በአገልግሎት ያለመጠን ይወጠርና ሕይወቱና አገልግሎቱ መዳለም ይጀምራል::

<u>ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ::</u>

*1. በግል፣ በቤተሰብ ሕይወትና በአገልግሎት መካከል ሚዛን መጠበቅ የሚለውን አሳብ እንዴት ትረዳዋለህ?*
*2. በሕይወትህና በአገልግሎትህ መካከል ሚዛን መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን ምን ያህል ትገነዘባለህ?*
*3. እንደ መንፈሳዊ አገልጋይ ሚዛን መጠበቅ ያስፈለገበትን ምክንያቶች ከሕይወትህ ገጠመኞች አንጻር ግለጽ::*
*4. አገልጋይ/ምዕመን/ ሚዛን መጠበቅ የሚያስፈልግባቸው ነጥቦች ምንድናቸው?*



እንግዲህ አገልጋይ በአገልግሎቱ፣ በግል ሕይወቱና በቤተሰቡ መካከል ሚዛን መጠበቅ እንዳለበት ተመልከተናል:: ለመሆኑ አገልጋይ በሕይወቱ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለምን ጉዳይ ነው? የእግዚአብሔር ቃል እገልጋይ በሕይወቱ ለምን ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት ምን ያስተምራል? አገልጋይ በሕይወቱ ቅድሚያ ሊሰጠው ለሚገባው ነገር ቅድሚያ መስጠት ከቻለ ከብዙ አደጋና ጉዳት ራሱን፣ ቤተሰቡንና አገልግሎቱን መጠበቅ እንደሚችል በማመን እነዚህን አገልጋይ ሊከተላቸው የሚገባቸውን ቅደም ተከተሎች በሚቀጥሉት ምዕራፎች እንመለከታለን::

## ምዕራፍ 2

### የአገልጋይ የትኩረት ቅደም ተከተል

አንድ አገልጋይ በሕይወቱ ውስጥ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለምንድነው? ቅድሚያ የሚለው ቃል ትልቅ ሥፍራ ወይም ዋጋ የሚሰጠው እንዲሁም እንገብጋቢና ከሌሎች ነገሮች ይልቅ አስፈላጊ የሆነን ነገር ያመለክታል። አገልጋይ በሕይወቱና በአገልግሎቱ በእርግጠኝነት የሚፈልገውን ነገር የማያውቅ ከሆነ አማራጮች እጅግ ብዙ ስለሆኑ ነገሮችን በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ሊከብደው ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የሚኖሩ ምርጫዎች ከመብዛታቸው የተነሳ ግራ መጋባትን ያስከትላሉ። ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለሚስት ወይስ ለልጆች? ለአገልግሎት ወይስ ለግል ትምህርት? ለጸሎት ወይስ ሕሙማንን ለመጠየቅ? እነዚህና የመሳሰሉት ነገሮች ቀላል ሊመስሉ ቢችሉም ተግባራዊ ለማድረግ ሲነሳ ግን አንዱን ከሌላው ለማስቀደም ፈተና ይሆንበታል።

በመሠረቱ አገልጋይ ትኩረት የሚሰጠው እጅግ አስፈላጊ ነው ብሎ ለሚያምነው ነገር ነው። ጊዜ የሚሰጠው እንደ ጉዳዩ አስፈላጊነት ደረጃ ነው። ጥቂት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አስፈላጊነቱ አናሳ ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ ደግሞ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል። ለነገሮች እንደ አስፈላጊነታቸው ቅደም ተከተል መስጠት አገልጋይ ሕይወቱን በሥርዓት ለመምራትና ጊዜን በሚገባ ለመጠቀም ይረዳል። ነገሮችን እንደ አስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል ለማስቀመጥ ደግሞ መሥፈርቱ የእግዚአብሔር ቃል ሊሆን ይገባል። እግዚአብሔር አገልጋይ ለምን ቅድሚያ እንዲሰጥ ይፈልጋል? አገልጋይ እግዚአብሔር በቅድሚያ እኔ ምን እንድሆን እንዲሁም ምን እንድሠራ ይፈልጋል? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ በቅደም ተከተል መምጣት ያለባቸው ነገሮች ተጠቅሰዋል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው።




እነዚህ ነገሮች እያንዳንዳቸው መሠረታዊና አስፈላጊ ናቸው። በቅደም ተከተላቸው ቢስተናገዱ በእያንዳንዱ መካከል ሥርዓት ያለው ግንኙነት እንዲኖር ያስችላሉ። በቅደም ተከተላቸው መሄባት ሲገኝ የግንኙነት ሥርዓቱን ያበላሻል። የቅደም ተከተሉ መጠበቅ በሕይወትና በአገልግሎት ፍሬያማነት እንዲኖር መንገድን ይከፍታል።



በአንድ አገልጋይ ሕይወት ከሁሉም በማስቀደም ሥፍራ ማግኘት ያለበት እግዚአብሔር ነው። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት የጀመረውና ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ነው። አዳም ብቻውን በነበረበት ወቅት ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ያደርግ ነበር። ሔዋን ከአዳም ከተገኘች በኋላ ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት ጀመረ። በዚህም መንፈሳዊ ግንኙነት ከማህበራዊ ግንኙነት እንደሚቀድም መገንዘብ እንችላለን። ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን መንፈሳዊ ግንኙነት በመልካም ሁኔታ በመጠበቅ ከእርስ በርሳቸውም ጋር ተገቢውን ግንኙነት ሊያደርጉ ይገባቸዋል።

ጌታ ኢየሱስ ሰዎች ከሁሉም ነገር በላይ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቅ እንዲያስቀድሙ መክሮአቸዋል። «ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል» (ማቴ.6:33)። ለሰው ልጆች የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የሆኑ ነገሮች ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ለአማኝ እንዲሁም ለአገልጋይም ያስፈልጋሉ። እነዚህን ነገሮች ለማግኘት መሥራትና መትጋት መልካም ነው። ሆኖም ግን እነዚህን ነገሮች ለማግኘት የሚሠሩትን ሥራዎች የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ አውቆ በእርሱ ከመኖር ማስቀደም ትክክለኛ መንፈሳዊ መርሕ አይደለም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ መረዳት እንጀራ የሚገኝበትን መንገድ ከመፈለግ መቅደም አለበት ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ ባስተማረን ጸሎት ውስጥ የእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ማወቅ ለእንጀራ ከመለመን እንደሚቀድም አስተምሮናል (ማቴ.6-9-10)።

እግዚአብሔር በእርሱ ለሚያምኑት እነርሱ በራሳቸው ጥረት ማግኘ ት የማይችሉትን ትልቅ ነገር የራሱን መንግሥት ከሰጣቸው ቀላል የሆነውን ለእነርሱ የሚያስፈልጋቸውን ምድራዊ ነገሮችንም ለመስጠት ሊታመን ይገባል። ለምድራዊ ኑሮ የሚያስፈልጉ ነገሮች በሰማያዊው በረከት ውስጥ ይገኛሉ። ስለዚህ በቅድሚያ ሰማያዊውን በመፈለግ ምድራዊውን ማግኘት ይቻላል። ሆኖም ግን ሰማያዊው እኛ ማድረግ የማንችለው ነገር ስለሆነ እግዚአብሔር ራሱ በመረጠው መንገድ በነጻ የሰጠን ስጦታ ነው። ይህን ለመቀበል የእኛ ድርሻ ለፈቃዱ መገዛት ነው። ምድራዊውን ግን እኛ በእርሱ ፈቃድ ውስጥ ሆነን መሥራት ይገባናል። እውቀታችንና ጉልበታችንን በማቀናጀት እርሱ በከፈተልን መስክ መትጋት ይጠበቅብናል።

ከመንፈሳዊ መርሕ አኳያ አገልጋይ በሕይወቱ ማስቀደም የሚገባው ነገር የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ነው። ከምንም በላይ በእርሱ ፈቃድ ውስጥ መገኘት አስፈላጊ መሆኑን ያውቃል። ከዚህም የተነሳ ከሌሎች ምድራዊ ነገሮች ሁሉ የሚያስቀድመው የመንግሥቱን ነገር ነው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔር መንግሥት ጉዳይ በሕይወቱ የመጀመሪያ ሥፍራ ይኖረዋል ማለት ነው። አንድ አገልጋይ በቅድሚያ ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ያለውና ይህም ግንኙነት እርካታ ያለውና ዘላቂነት እንዲኖረው ተገቢውን ጊዜና ትኩረት መስጠት ይገባል።

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተጨማሪም እግዚአብሔርን ከሁሉም ነገር በላይ መውደድ አስፈላጊ እንደሆነ «ጌታ አምላክን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም ውደድ» (ማቴ.22:37) በማለት ተናግሯል። ከሁሉም በፊት ራሳችንን ለእግዚአብሔር መስጠት ከዚያም ያለንን ሁሉ ለእርሱ መስጠት ቀዳማይ ተግባር ነው። ከጊዜ አኳያ ሲታሰብም ለእግዚአብሔር በቂ ጊዜ መስጠት ያስፈልጋል። ይህም እግዚአብሔርን

በሚያከበር በሚፈራና በሚታዘዝ ሕይወት መመላለስ፣ ቃሉን ዕለት ዕለት መመገብና ሳያቋርጡ የእርሱን ፊት በጸሎት መፈለግን ያጠቃልላል:: ለራሳችንም ሆነ ለሌሎች አስፈላጊውን ነገር ለማግኘትና ለመስጠት የሚቻለው ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ በማሳለፍ ነው:: እግዚአብሔርን ያላስቀደመ ሕይወትና አገልግሎት በሁሉም ዘርፍ ፍሬያማነትን ያሳጣል:: ስለዚህ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ በመስጠት ከእርሱ ለሕይወትና ለአገልግሎት የሚሆን በቂ ትጥቅ ማግኘት መሠረታዊ ነገር ነው::

ከእግዚአብሔር ቀጥሎ አገልጋይ ለቤተሰቡ ቅድሚያ ሊሰጥ ይገባል:: ቤተሰብ ከአገልግሎት መቅደም እንደሌለበት የሚናገሩ ሰዎች ይኖራሉ:: ይህ አሳብ ግን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም:: ምክንያቱም ቤተሰብ እግዚአብሔር ከመሠረታቸው ተቋማት የመጀመሪያው ማህበራዊ ተቋም ነው:: ቤተሰብ በምሥረታ ከቤተክርስቲያን ይቀድማል:: ይህን በሚገባ ለመረዳት ዘፍጥረት (2:18-25) ማንበብ ይቻላል::

አገልጋይ የቤተሰብ ሰው መሆን ይጠበቅበታል:: ይህ ማለት ከቤተሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ሰው ሊሆን ይገባል:: ቤተሰብ አንድ ሰው ሕይወቱን በጥልቀት ለሌላው የሚያካፍልበት ኅብረት ነው:: ቤተሰብ ሕይወት በቀውስ ውስጥ ብትገባ እንኳ የማረጋጋት ኃይል አለው:: ቤተሰብ በሰው ሕይወት ውስጥ ችግር ሲፈጠር የማምለጫ ዓለት ነው:: ቤተሰብ ሕይወት ኃይል ስታጣ ኃይል የሚሞላበት ማደያ ነው:: ስለዚህ ይህን የመሰለ ኅብረት እያፈረሱ ለአገልግሎት ከፍተኛ ትኩረት መስጠት የኋላ ኋላ መግቢያ ሥፍራን ማፍረስ ነው::

ለቤተሰብ የጊዜን ትራፊ መስጠት አንድ አገልጋይ ለቤተሰብ ያለው ግምት ወይም የሚሰጠው ሥፍራ ዝቅተኛ መሆኑን ያመለክታል:: ምክንያቱም አንድ አገልጋይ ብዙ ጊዜውን የሚሰጠው በጣም ለሚወደውና በሕይወቱ አስፈላጊ ነው ላለው ነገር ነው:: አገልጋይ ለቤተሰቡ ጊዜ የሚሰጠው ወይም ከቤተሰብ ጋር የሚሆነው ጊዜ ሲተርፈው ሳይሆን ያለውን ጊዜ ለእነርሱም በመመደብ ነው::

ለቤተሰብ ቅድሚያ መስጠት አለበት ማለት ቤተክርስቲያንና ቤተሰብ የሚፎካከሩ ሁለት ተቃራኒ ተቋማት እንደሆነ መታሰብ የለበትም:: ቤተሰብና ቤተክርስቲያን የሚቃረኑ ሳይሆኑ እርስ በርስ የሚደጋገፉ ናቸው:: ቤተክርስቲያን የቤተሰብ ስብስብ ናት:: ለቤተሰብ የሚሰጠው ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ ለቤተክርስቲያን መታነጽ የሚውል ነው:: አገልጋይን ጨምሮ እያንዳንዱ የቤተሰብ ኃላፊ ከትዳር ጓደኛውና ከልጆቹ ጋር ተገቢውን ጊዜ ቢያሳልፍ ቤተክርስቲያን ትታነጻለች:: ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ስጠን የሚባለው ከቤተሰብ ውጭ ያሉትን ሰዎች ስናገለግል እንደሆነ ብቻ መቆጠሩ ስህተት ነው:: ስለዚህ አገልጋይ ለእያንዳንዳቸው የሚገባቸውን ጊዜና ጉልበት በመስጠት በሁለቱም ሥፍራ ኃላፊነቱን በተገቢው ሁኔታ መፈጸም ይችላል::

ከቤተሰብ ውስጥም በተለይ ለትዳር ጓደኛው ቅድሚያ መስጠት አለበት:: አንዳንድ አገልጋዮች ከትዳር ጓደኛ ይልቅ ለልጆቻቸው ቅድሚያ መስጠት እንደሚኖርባቸው ያስባሉ:: ይህ ግን ትክክል አይደለም:: በዓለም ካሉ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ለአገልጋይ ቅርብ የሆነች ወዳጅ ሚስቱ ናት:: ይህ ያልገባቸው አገልጋዮች «ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ» የሚለውን የጋብቻን



ምስጢር ቢመረምሩ መገንዘብ ይችላሉ:: አገልጋይ ለልጆቹ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ የሚችለው ሚስቱን ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን በወደደበት ፍቅር ሲወዳት ነው (ኤፌ.5:25):: አንዳንድ አገልጋዮች የጋብቻ ችግር የሚኖራቸው ለሚስቶቻቸው ተገቢውን ቅድሚያ ባለመስጠታቸው ነው::

ለሚስት ፍቅር የሚለው ቃል ትርጉሙ ከእርሷ ጋር ጊዜ ማሳለፍ ነው:: አገልጋይ ለሚስቱ ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ሚስቱን እንደሚወዳት ምንም ያህል ቢናገር ለእርሷ ዘንድ ተቀባይነት የለውም:: አገልጋይም ሆነ ሚስቱ ከትዳር ውጭ ከሌላ ሰው ጋር ወዳጅነት የሚጀምሩት እንዱ ይህ ቅደም ተከተል ሲዛባ በመሆኑ አገልጋይ ለሚስቱ ያለውን ኃላፊነት መዘንጋት የለበትም:: አንድ አገልጋይ ለሚስቱ ተገቢውን ሥፍራ እንደሰጠ የሚያውቀው «ከሚስትህና ከምታገለግላቸው ምዕመናን ማንን አብልጠህ ትወዳለህ?» ተብሎ ሲጠየቅ ሚስቱን ከምዕመናን በላይ እንደሚወድ ሲናገርና በተግባርም ሲያሳይ ነው:: ለምዕመናን የሚሰጠው ፍቅር ከሚስት የተረፈው ሲሆን ይገባል::

አገልጋይ ከሚስቱ ቀጥሎ ለልጆቹ ቅድሚያ መስጠት ይገባዋል:: አገልጋይ ሁለት ዓይነት ልጆች አሉት:: እነርሱም ሥጋዊና መንፈሳዊ ልጆች ናቸው:: ሁለቱም እርሱ እንዲያገለግላቸው የተሰጡት ልጆቹ ናቸው:: ከእነዚህ ከሁለቱ የበለጠ ትኩረት መስጠት ያለበት ለየትኞቹ ልጆቹ ነው?




ሥጋዊ ልጆች ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአገልጋይ የተሰጡ የመጀመሪያ መንጋ ናቸው:: እነዚህን ልጆች በመንከባከብ በእግዚአብሔር ቃል በማሳደግ ሲያድጉ እግዚአብሔርን የሚወዱና ጌታን የሚያገለግሉ እንዲሆኑ ማድረግ ትልቅ አገልግሎት ነው:: ከወላጆቻቸው በተለይም ከቤተሰብ መሪ ተገቢውን ፍቅር በማግኘት ያደጉ ልጆች ሲያድጉ ወደ መጥፎ ተግባር አይሄዱም:: የአገልጋይ መንፈሳዊ ልጆቹ ሌሎች ሊያገለግሉአቸው የሚችሉ ብዙ መንፈሳዊ አባቶች አሉአቸው:: የአገልጋይ ልጆች ግን ያላቸው አንድ አባት ብቻ ነው:: ይህ አባት ደግሞ እነርሱን ማገልገልን ችላ ካላቸው ማንም እርሱን ሊተካላቸው አይችልም::

አገልጋይ ለቤተሰቡ ትኩረት ወይም ቅድሚያ መስጠቱን የሚገልጸው ለእነርሱ በሚሰጠው ጊዜ ነው:: አገልጋይ ለቤተሰቡ በቂ ጊዜ መስጠት ይጠበቅበታል:: ለቤተሰብ በቂ ጊዜ መስጠት አስፈላጊ እንደሆነ ይነገራል:: ነገር ግን ይህ በቂ ጊዜ የሚባለው ምን ያህል ጊዜ ነው? ለቤተሰብ የሚሰጠውስ ጊዜ በቂ መሆኑ ወይም አለመሆኑ የሚለካውስ በምንድነው?

በቂ የሚሰው ቃል አንጻራዊ ነው። ለአንድ ቤተሰብ በቂ የሆነ ጊዜ ለሌላው ቤተሰብ በቂ ላይሆን ይችላል። በቂ ጊዜ የሚባለው ከቤተሰብ ጋር ብዙ ሰዓት ማሳለፍ ብቻ ሳይሆን ቤተሰብ የአገልጋይን መገኘት በሚፈልግበት ወቅት በመገኘት ፍላጎቶቻቸውን ማሟላትን ያመለክታል። አንድ አገልጋይ ከቤተሰብ ጋር ቁምነገር ያለው ነገር ሳይሠራ ከሚያሳልፈው ብዙ ሰዓታት ይልቅ ቤተሰብ የሚደሰትበትና የጋራ የሆነ ነገር በመሥራት የሚያሳልፈው ጥቂት ሰዓት ለቤተሰቡ ጥቅም ይኖረዋል። ስለዚህ በቂ የሚለው አሳብ እንደ ቤተሰቡ ፍላጎት ቤተሰብ ሲፈልግ መገኘትና ለእነርሱ የተመደበውን ጊዜ ደግሞ እንደ ፍላጎታቸው እንዲጠቀሙበት ለጋራ ዓላማ ማዋል መቻል ነው። ከጊዜ ርዝመት ይልቅ ጊዜው በሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

በመጨረሻም አገልጋይ ትኩረት የሚሰጠው በአገልግሎት ላይ ነው። አገልጋይ በውጭ ለሚገኙ ምዕመናን ተገቢውን አገልግሎት መስጠት ያለበት በቤቱ ውስጥ ለሚገኙ ምዕመናን ተገቢውን እንክብካቤ እየሰጠ ሲሆን ነው። አገልጋይ ቤተሰቡን በሚያገለግልበት ወቅት ቤተክርስቲያንን እንዳገለገለ ማሰብ አለበት። ምክንያቱም የተሳካ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ ለቤተክርስቲያን ዕድገት ከፍተኛ አገዛ ያደርጋል። ጥናቶች አገልጋይ ለሌሎች ሰዎችና ምዕመናን ምሳሌ የሚሆን ቤተሰብ በሚኖርበት ሁኔታ እርሱ የሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ሳታቋርጥ እንደምታድግና ፍሬያማ እንደምትሆን ያመለክታሉ።[3]

ስለዚህ አገልጋይ የቤተክርስቲያን አገልግሎት ሚና በዝቶበት በቤቱ ውስጥ ያለችው ቤተክርስቲያን እንድትዳከም እጅ መስጠት የለበትም። እግዚአብሔር አገልጋይን እንዴት ቤተክርስቲያንን እንዳገለገለ እንደሚጠይቅ ሁሉ ቤተሰቡንም እንዴት እንደተንከባከበ ይጠይቀዋል። እግዚአብሔር አገልጋይ ቤተሰቡን ሲያገለግል ደስ ይለዋል።

አገልጋይ በቤተሰብ እንደ ባልና እንደ ወላጅ ውጤት ያለው ሚና መጫወት የሚችለው ጊዜውን መቆጣጠር ሲችል ነው። ጊዜውን መግዛት የማይችል አገልጋይ መሥራት የሚገባውን ሥራ መሥራት አይችልም። ይህን ወደፊት እንመለከታለን።

ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።

1. *በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በተጠቀሰው ቅደም ተከተል መሠረት ለእግዚአብሔር፣ ለቤተሰብና ለአገልግሎት/ሥራ/ ተገቢውን ሥፍራ መስጠቱና አለመስጠቱ በምን ይታወቃል?*
2. *አገልጋይ በሚያገለግልበት ዓውድ ውስጥ የሚገኙ ምዕመናን ከቤተሰብ ይልቅ ለአገልግሎት ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት የሚያምኑ ከሆነ ምን ሊደረግ ይችላል? ይህን ሁኔታ ለመለወጥ አገልጋይ ምን ዓይነት መንገድ መከተል ይኖርበታል?*
3. *አገልጋይ ለአንድ ነገር ቅድሚያ መስጠቱ የሚታወቅባቸው ተጨባጭ የሆኑ መመዘኛዎች ምንድናቸው?*

---

[3] Shawchuck, Norman and Heuser, Roger. *Leading the Congregation: Caring for Yourself While Serving Others.* Nashville, Abingdon Press, 1993, p.115



እንግዲህ አገልጋይ ሊከተላቸው የሚገባቸው ቅደም ተከተሎች ይህን የሚመስሉ ከሆኑ አገልጋይ እያንዳንዳቸውን በዝርዝር በማወቅ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል። አገልጋይ ከሁሉም በላይ በሕይወቱ ቅድሚያ መስጠት ያለበት ለእግዚአብሔር ነው። የግል መንፈሳዊ ሕይወትን መጠበቅ የመጀመሪያው የሕይወት ተልዕኮ ነው። አንድ አገልጋይ ለእግዚአብሔር ቅድሚያ እንዴት ይሰጣል? ለእግዚአብሔር ቅድሚያ መስጠት ያለው ጥቅምስ ምንድነው? አገልጋይ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ተገቢውን እንክብካቤና ጥንቃቄ ማድረጉ በምን ይታወቃል? ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ተከታዩ ምዕራፍ ምላሽ ይኖረዋል።

በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት ቤተሰብን ከመምራትና ከመንከባከብ ጋር የተያያዘ ነው። ከእውድ ልዩነት በስተቀር በመሠረተ አሳብ ደረጃ ሁለቱም ብዙ ልዩነት የላቸውም። አገልጋይ ለሚያገለግላቸው ምዕመናን ተገቢውን እንክብካቤና ጥንቃቄ ለማድረግ ይህን አስቀድሞ ለቤተሰቡ በማድረግ ያሳየ መሆን ይጠበቅበታል። እንደ ጳውሎስ ያሉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ለሚያገለግሉት ምዕመናን እንደ እናትና እንደ አባት እንደሆኑ ተናግረዋል። አገልጋይ በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት ከወላጅነት ሚና ጋር የተያያዘ ነው። ጳውሎስ እንዲህ በማለት ይናገራል:-

> ነገር ግን ሞግዚት(እናት) የራስዋን ልጆች እንደምትንከባከብ በመካከላችሁ የዋሆች ሆነን እንዲሁም አያፈቀርናችሁና የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና (1ተሰ.2:7-8)።

በቤተክርስቲያን ምዕመናንን ማገልገል እናት ለልጆችዋ እንደምትሆን መሆንን ይጠይቃል። እናት ከልጆችዋ ጋር በየዋህነት ትኖራለች። እናት ለልጆችዋ ተንኮልን አታስብም።

እናት ለልጆችዋ ምንም ብድራት ሳትጠብቅ ፍቅር ትሰጣቸዋለች። የእናት ፍቅር ከራስ ወዳድነት የጸዳ ነው። እናት ትወዳለች፣ ፍቅርዋም ንጹሕ ነው። እናት ለልጆችዋ መልካም ልብ አላት። እናት ከመልካም ልብ ጋር መልካም እጅ ወይም ሙያ ቢኖራት ደግሞ ልጆችዋን በተገቢው ሁኔታ መንከባከብ ትችላለች። እናት ለልጆች ምንጊዜም ታስፈልጋለች። ሕጻናት ተወልደው ገና ራሳቸውን በማይችሉበት ወቅትማ እጅግ ታስፈልጋለች። በዚህ ወቅት ሕጻናት ያለእናት የመኖር ተስፋ የላቸውም። እናት ልጆች ራሳቸውን በማይችሉበት ወቅት ትሸከማቸዋለች። ነገር ግን ራሳቸውን ከቻሉ በኋላ እርስዋን ቢረዱአት አትጠላም። ልጆችም የእናታቸውን ብድራት ለመመለስ እናታቸውን መርዳት ይገባቸዋል።

መልካም መንፈሳዊ አገልጋይ ለሚያገለግላቸው ምዕመናን እንደ እናት ነው። ከሁሉም በላይ እነርሱን ይወዳቸዋል። አገልጋይ እንደ ልጆች እናት በቤተሰቡ እነዚህን ነገሮች ከተለማመደ ወደ ቤተክርስቲያን በሚመጣበት ጊዜ በመንፈስ ልጆቹ ለሆኑት ምዕመናን ተገቢውን እንክብካቤ ያደርጋል፣ የሚያገለግላቸውን ምዕመናን በሁኔታዎች ላይ ባልተመሠረተ ፍቅር ይወዳቸዋል። በተለይ ምዕመናን ገና በእምነታቸው አዲስ በሚሆኑበት ጊዜ ክርስቶስ እያሳያቸውና ወተት የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል እየመገባቸው በእምነት ኮትኩቶ ያሳድጋቸዋል። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ከእነርሱ ሊያገኝ የሚገባው ነገር ቢኖርም እንኳ እስኪያድጉ ድረስ በእነርሱ ላይ ሸክም ላለመሆን መብቱን አይጠቀምም። ይሸከማቸዋል እንጂ በምንም በእነርሱ ላይ ሸክም አይሆንም።

እናት ልጆችዋን ከማፍቀርዋ የተነሳ ራስዋን ትቆርሳለች። የእርስዋ መጎዳት ልጆችዋን የሚጠቅም ሆኖ ካገኘች ለእነርሱ መልካም ነገር ለማድረግ አስፈላጊውን ዋጋ ከመክፈል ወደኋላ አትልም።



መልካም አገልጋይ አንደ እናት ለሚያገለግላቸው ምዕመናን ወንጌልን ብቻ ሳይሆን ራሱንም ለእነርሱ ይቆርሳል። ወንጌልን በማስተማር ብቻ ኃላፊነቱን እንደተወጣ አያስብም። ከቤተክርስቲያን የተሰጠውን የሥራ መዘርዝር ማከናወንና ከልብ የሆነ ሕይወትን ማካፈል የተለያዩ ነገሮች ናቸው። አንድ አገልጋይ ከሚያገለግላቸው ምዕመናን ጋር እናት ከልጆችዋ ጋር በተያያዘችበት መንፈስ ካልተያያዘ ሕይወቱን ለእነርሱ አያካፍልም። በአገልጋይ ሕይወት ውስጥ ለምዕመናን ብሎ ዋጋ ለመክፈል ዝግጁነት የሚኖረው አገልጋይ ምዕመናኑን የሚወድ ሲሆንና ክርስቶስ ለእርሱ የከፈለውን መበዋዕትነት ሲረዳ ነው። የአገልጋዩ ዝግጁነት ሲኖር እግዚአብሔር ደግሞ ለምዕመናን ሁለንተናዊ ዕድገት ዋጋ እንዲከፍል የሚያስችለውን ጸጋ ይሰጧል።

አናት ለልጆችዋ ተቆርቋሪ እንደሆነችም ማስተዋል ይቻላል። እናት ለቤተሰብ በተለይም ለልጆችዋ ታስባለች። ለቤተሰቡ ሁለንተናዊ ሕይወት ታስብና ለሁለንተናቸው የሚያስፈልጋቸው ማናቸውም ነገሮች እንዲሟሉላቸው ጥረት ታደርጋለች። «ምንም ቢሆኑ ግድ የለኝም» የሚል ልብ የላትም። ቤተሰቡ ምን ይበላሉ? ምንስ ይጠጣሉ? የትስ ይኖራሉ? ደህንነታቸውስ ምን ያህል አስተማማኝ ነው? ልጆቼ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ምን ያጋጥማቸው ይሆን? እነዚህ የሁልጊዜ ጥያቄዎቿ ናቸው። እናት ልጆችዋን ስታስብ ልብዋ ይንሰፈሰፋል። ሥራ እየሠራች ወይም ከሰዎች ጋር እያወራች ብትሆንም ልብዋ ግን «ልጆቼ! ልጆቼ!» ይላል። በአጠቃላይ ለቤተሰቡ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ነገሮች መኖራቸውንና ቤተሰቡን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮች ደግሞ አለመኖራቸውን ለማረጋገጥ ሁሌም ጥረት ታደርጋለች። ከምንም ነገር በላይ ለቤተሰቡ መልካም ነገር እንዲሆን ከመመኘትም አልፋ ተግባራዊ የሆነ እርምጃ ትወስዳለች።

አናት ልጆችዋን አትረሳም። እናት የወለደችውን ልጅ እንደማትረሳ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ እርሱ ራሱ ሕዝቡን እንደማይረሳ በእናት ምሳሌ «ጡውት ሴት ከማኅፀንዋ ለተወለደ ልጅ እስከማትራራ ድረስ ሕጻንዋን ትረሳ ዘንድ ትችላለችን?» (ኢሳ 49:15) በማለት ተናግሯል። ለሰው በሚገባ ደረጃ እናት የወለደችውን ልጅ እንድትረሳ የሚያስችላት ልብ የላትም። ከእናት ሚና አንዱ የቤተሰብ አባላትን ማስታወስ ነው። የቤተሰብ ቁጥር ብዙ በሆነበት ቤተሰብ ውስጥ እንኳ እናት ልጆችዋን ታስታውሳለች። ማን እንዳለና ማን እንደሌለ በሚገባ ታውቃለች። ብዙ ጊዜ እናት በጣም የምታስበው ከእርስዋ ጋር ላለው ሳይሆን ደህንነቱ እንዴት እንደሆነ ስለማታውቀው ልጅዋ ነው። ከእርስዋ ጋር ላሉት አስፈላጊውን እንክብካቤ እየሰጠች ከአርስዋ ጋር የሌለው ደግሞ እንደነዚኛዎቹ በመልካም ሁኔታ ውስጥ ይሆን ዘንድ ትጨነቃለች። ወላጆች ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባላት ትኩረት ይሰጣሉ። እያንዳንዱ አባል በእነርሱ ዘንድ ዋጋ አለው፣ የማይፈለግ ሰው የለም። የብዙዎች መኖር የሌላውን አለመኖር አይሞላም ወይም አይተካም። እያንዳንዱ ተፈላጊነት አለው።

በተመሳሳይ ሁኔታ መንፈሳዊ አገልጋይም መንፈሳዊ ልጆቹን ሁሉ ማስታወስ ይጠበቅበታል። አገልጋይ መንፈሳዊ ልጆቹ ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ ጥረት ሲያደርግና ይልቁንም በሁለንተናዊ ሕይወታቸው በጤናማ ሁኔታ ውስጥ ያልሆኑትን ተግቶ የሚፈልግና አስፈላጊውን የማዳን እርምጃ የሚወስድ ነው። በጌታ ለወለዳቸውና ላሳደጋቸው መንፈሳዊ ልጆቹ የሚራራ ልብ አለው።

ወደ መንግሥቱ ወደ ክብርሩም ስጠራችሁ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እየመከርንና እያጸናን እየመሰከርንላችሁም አባት ለልጆቹ እንደሚሆን ለእያንዳንዳችሁ እንደሆንን ታውቃላችሁ (1ተሰ.2፡11-12)።

አገልጋይ ሆኖ በቤተክርስቲያን አገልግሎት መስጠት ከአባትነት ሚና ጋርም ተመሳሳይነት አለው። በሐዋርያት ዘመን በነበረችው ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲያገለግሉ የነበሩ አገልጋዮች ለሚያገለግሉት ምዕመናን አባት ለልጆቹ እንደሚሆን እንደሆኑ ተናግረዋል። እንደ አባት ለምዕመናን በጽድቅና ነቀፋ የሌለበት ኑሮ በመኖር ምሳሌ መሆን፣ መምከር፣ በማጽናትና ለእግዚአብሔር መንግሥት ምቹ የሆነ ከጥሪያቸው ጋር የሚመጥን እግዚአብሔርን የሚመስል ሕይወት እንዲኖራቸው ያበረታቱዋቸው ነበር።

አባት ልጆቹን ይመክራቸዋል። አባት ልጆች ፈቃዳቸውን ለመልካም ነገር እንዲሰጡ ከእውቀቱና ከልምዱ ይመክራቸዋል። አባት ለልጆቹ ዓላማ ስላለው እርሱ ወዳቀደላቸው መልካም ግብ እንዲደርሱ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣቸዋል። አገልጋይም እንደ መንፈሳዊ አባት ምዕመናን ፈቃዳቸውን ለእግዚአብሔር በመስጠት እንደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲኖሩ ከቃሉ አኳያ ይመክራቸዋል። በዚህ ምክር ውስጥ ለእነርሱ መልካም አቅጣጫ ማሳየትና ወደ እግዚአብሔር አሳብ ሙላት እንዲደርሱ ማበረታታትና ማደፋፈር ይገኝበታል። አቅጣጫን ማሳየት ብቻ ሳይሆን በዚያ አቅጣጫ ወደ መልካም ግብ እንዲደርሱ ተከታታይነት ያለው ማበረታታት መስጠት ይገባል። ምዕመናን የመምረጥ መብታቸውን ሳይጋፋ ነገር ግን አባታዊ ምክር የሚሰጣቸውን አገልጋይ ሲያገኙ ደስ ይላቸዋል። ለእርሱም ያላቸው ታማኝነት እና በእርሱ ላይ የሚኖራቸው መታመን ይጨምራል።

አባት ልጆችን ያጸናቸዋል። ልጆች በሕይወታቸው መልካም ነገር ሲያጋጥማቸው እንደሚችል ሁሉ የሚያሳዝናቸውና የሚያስፈራቸው በአጠቃላይ ስሜታቸውን ሊጎዳ የሚችል ነገርም ያጋጥማቸዋል። በዚህ ወቅት የሚያጸናቸውን አባት ይፈልጋሉ። አባት ከልጆቹ ጋር ቁጭ ብሎ እነርሱን በመዳመጥና በመረዳት ስሜታቸውን «ሲያክምላቸው» በጣም ደስ ይላቸዋል። ከአባታቸው ጋር ያላቸውም የስሜት መተሳሰር ይጠነክራል። መንፈሳዊ አባትም ለምዕመናን ስሜት አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል። ምዕመናን ሲያዝኑ የሚያጽናናቸው፣ ሲያለቅሱ እንባቸውን የሚያብስ፣ ሲቆስሉ ቁስላቸውን የሚሸፍኑበት ጨርቅ የሚያዘጋጅላቸው ሊሆን ይገባል። ምዕመናን ስሜታቸውን የሚረዳላቸውንና አስፈላጊውን ማጽናናት የሚሰጣቸውን አገልጋይ ይፈልጋሉ። በክርስቶስ የተጽናና አገልጋይ በመከራ ውስጥ ሆነው መጽናናት ለሚፈልጉ ሰዎች መጽናናት ሊሰጣቸው ይችላል። ምክንያቱም የመጽናናት አምላክ ከእርሱ ጋር በመሆኑ ነው (2ቆሮ.4፡4-7)።

አባት ለልጆቹ ይመሰክራል። አባት ልጆቹ በአዕምሮአቸውም የበሰሉና እውነትን የተረዱ እንዲሆኑ እውነትን ያስተምራቸዋል። እውነት የሆነውን ነገር ሳይሸፍን ይነግራቸዋል። ልጆች እውነትን መሸቃቀጥ እንደማይገባቸውና እውነትን አውቀው በእውነት እንዲኖሩ አስፈላጊውን ምስክርነት ይሰጣቸዋል። መንፈሳዊ አባትም የእውነት መስካሪ ነው።



ለሚያገለግላቸው ምዕመናን እውነትን ይመሰክርላቸዋል። ምዕመናን እውነትን አውቀው በእውነት በመኖር በአርነት እንዲመላለሱ ይጥራል። ምዕመናን እውነትን ከመንፈሳዊ አባታቸው ከተረዱ ከዚያ እውነት ፈቀቅ አይሉም። ነገር ግን እውነትን ካላወቁ ሐሰት የሆነውን ለይተው ስለማያውቁ ይቸገራሉ። ስለዚህ ለምዕመናን እውነት የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ከአውዳቸው ጋር በማገናዘብ ማስተማር በሕይወት ዘመናቸው ከእግዚአብሔር ጋር በእምነት እንዲኖሩ የሚያደርጋቸውን መሠረት ይጥላል።

አባት ልጆቹን ሥርዓት በማያስያዝ ያሳድጋል። ይህን የሚያደርገውም ልጆቹን ስለሚወዳቸው ነው (ዕብ.12፡9)። አገልጋይ ልጆቹን እንደሚወድድ አባት ምዕመናን ሥርዓት ባለው ሁኔታ ሕይወታቸውን እንዲመሩ ይረዳቸዋል። ምዕመናን መሄድ ከሚገባቸው መልካም መንገድ ሲስቱ አስፈላጊውን የእርምት እርምጃ እየወሰደ ያቀናቸዋል።

አባት ልጆቹን ሁሉ ይወዳቸዋል (ማቴ.5፡44-45)። ይህ የአባት ፍቅር ከሁኔታዎች በላይ መሆን አለበት። ልጆች እርሱ በሚፈልግበት ሁኔታ ባይሄዱ እንኳ የሚወድ ልብ ሊኖረው ይገባል፣ እንደ አባት በእርሱ አሳብና ፈቃድ የሚሄዱትንና የማይሄዱትን እኩል መውደድም ይጠበቅበታል። ሁለቱም ልጆች በመሆናቸው ከእርሱ ማግኘት የሚገባቸው ፍቅር አለ። በመታዘዝና ባለመታዘዝ ደግሞ ከእርሱ የሚሰጠውን ሽልማት ሳያገኙ ይችላሉ። ልጅ በመሆናቸው ግን የሚታዘዙና የማይታዘዙ ልጆች ከእርሱ የአባት ፍቅር ማግኘት ይገባቸዋል። አንዳንድ ጊዜ የአባት ልብ ለሚታዘዘው ሊያዳላና የማይታዘዘውን ችላ ሊል ይችላል። በቤተሰብ ውስጥ የማይታዘዙ ልጆችን ከሚታዘዙት እኩል መውደድ ከእንካ-በእንካ ፍቅር ማለፍን ግድ ይላል። የልጆቹን ድርጊት ሳይቆጥር እንዲሁ ልጆቹ እንደሆኑ በመገንዘብ መውደድ የሚችል አባት እውነተኛ አባት ነው።

በቤተሰብ ውስጥ ያሉትን ሰዎች ድርጊቶቻቸውን ሳይቆጥር እንዲሁ መውደድና መቀበል የቻለ አባት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ምዕመናን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሊወዳቸውና ተገቢውን እንክብካቤ ሊያደርግላቸው ይችላል። በቤተክርስቲያን ውስጥ የተለያዩ ዓይነት ሰዎች አሉ። አንዳንዶቹ በፈርሃ እግዚአብሔር የሚመላለሱ ሲሆኑ አንዳንዶች ደግሞ ዓመጸኞችና የእግዚአብሔርንም ቃል ሰምተው የማያውቁ የሚመስሉ ናቸው። አገልጋይ የተጠራው ሁሉንም ዓይነት ሰው ለማገልገል ነው። ለእግዚአብሔር ቃልና ለቤተክርስቲያን ወግና ሥርዓት ለመታዘዝ ልባቸውን የማይሰጡትን እንደ ምዕመናን በመቁጠር መቀበል፣ መውደድና ማገልገል አስቸጋሪ ነው። እነዚህን ሰዎች ለመውደድ አገልጋይ በቤተሰቡ ውስጥ ያሉትን ለቤተሰብ ሥርዓት የማይገዙትን የያዘበት ሁኔታ ተጽዕኖ ያደርግበታል። በቤተሰብ ውስጥ ያሉትን የማይታዘዙ ሰዎችን በፍቅር በመያዝ እውነትን እያሳያቸው ወደ መልካም አሳብ መምራት ከቻለ በቤተክርስቲያን ይህን መድገም አያቅተውም። ነገር ግን በቤተሰቡ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ልምምድ ከሌለው ለቤተክርስቲያን መልካምን ነገር ያደርጋል ብሎ መጠበቅ አዳጋች ነው።

አባት የቤተሰብ መሪ ነው። አባት የወለዳቸውን ወይም የሚያሳድጋቸውን ልጆቹን ይመራቸዋል። የቤተሰብ አባላትን በተገቢው መንገድ መምራት መቻል አንዱ የአባት ሚና ነው። አባት ከልጅነት ጀምሮ ልጆች ራሳቸውን ችለው መኖር እስከሚችሉበት ድረስ ሁለንተናዊ የሆነ

ምሪት ይሰጣል:: አባት ልጆች ተወልደው በእግር ለመሄድ ሙከራ ሲያደርጉ የልጆቹን እጆች በመያዝ በእግር መራመድን ያስተምራል:: በዚህ የጀመረው መምራት እንደ ልጆቹ ዕድሜና ብስለት እየተሰጠ ልጆቹን ሙሉ ሰው ወደመሆን ያደርሳል::

በቤተሰብ ውስጥ ልጆቹንና በቤተሰብ ውስጥ ያሉትን ሰዎች በተገቢው መንገድ መምራት የቻለ ሰው በቤተክርስቲያን ውስጥም ስኬታማ የመሪነት ሚና መጫወት ይችላል::

አባት ለልጆች ጥበብን ያስተላልፋል:: የአባት ሌላው ሚና ደግሞ ለልጆች ጥበብን ማስተላለፍ ነው:: መጽሐፈ ምሳሌ ውስጥ የተጠቀሰው ጠቢብ የሆነው ሰው እንደ ወላጅ ሆኖ እርሱን ለሚሰሙት ሰዎች ጥበብን ያስተምራቸዋል:: በእርሱና በተቀባዮቹ መካከል ያለው ግንኙነት የወላጅና የልጆች በሚመስል ሁኔታ ተገልጸዋል:: ወላጆች በዕድሜና በልምድ ያገኙትን መልካም ልምምድና ጥበብን ለልጆቻቸው ያስተላልፋሉ:: ይህም የሚሆነው በመጀመሪያ ልጆች ከልምድና ከተሞክሮ የተገኙትን መልካም እውቀት በመጠቀም ሕይወታቸውን በመልካም ሁኔታ መምራት እንዲችሉ ለማገዝ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ልጆች ከወላጆቻቸው ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ወግና ሥርዓት አውቀው ቀጣይነት ባለው ሁኔታ እንዲኖሩበትና እነርሱም በተራቸው ለቀጣዩ ትውልድ እንዲያስተላልፉት ነው::

መንፈሳዊ አገልግሎትም የማስተላለፍ ወይም የማቃበል አገልግሎት ነው:: የቀደመው ለቀጣዩ ከእግዚአብሔር የተቀበለውንና በሕይወቱ የተለማመደውን መልካም እሴት ለሚመጣው ያስተላልፋል:: አገልጋይ እግዚአብሔርን በዘመኑ ብቻ አገልግሎ የሚያልፍ ሳይሆን ለሚቀጥለው ትውልድም የሚያስተላልፍ ተልዕኮና ራእይ ሲኖረው ይገባል:: በዚህ ሁኔታም አገልግሎቱ ሳይረሳ ከትውልዱ አልፎ ቀጣዩን ትውልድም የሚነካ ይሆናል:: አገልጋይ ማገልገል ያለበት በዘመኑ ያሉትን ሰዎች ቢሆንም ካለበት ዘመን በላይ አሻግሮ ማየት የሚችልና ለትውልዶች የሚያስብ ልብ ያለው የእግዚአብሔር ሰው ሲሆን ይገባል:: አገልጋይ እንደ ወላጅ ለልጆቹ እንዲህ ማሰብ የማይችል ከሆነ ለቤተክርበቲያን ያበባል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው::

እንግዲህ መንፈሳዊ አባት መንፈሳዊ ልጆቹን በመምከር፣ በማጽናት፣ እውነትን በማስተማር፣ በሥርዓት በመምራት፣ የሚጠቅማቸውን የትውልድ ቅሪት ለእነርሱ በማስተላለፍ በእግዚአብሔር ቤት እንዲኖሩ ይረዳቸዋል:: መንፈሳዊ አባት ምዕመናን የእግዚአብሔር መንግሥት አባላት እንደሆኑና እሁን በዚያ መንግሥት ውስጥ ስለሚኖሩ ሕይወታቸውን ለጌታ በመስጠት በእርሱ ፈቃድ ውስጥ ቃሉን በመጠበቅ እንዲመላለሱ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል:: ምዕመናን በበጎ ፈቃድ ለእግዚአብሔር መታዘዝና መታመን ኖሮአቸው እግዚአብሔር ያስቀመጠላቸውን ብድራት ሳይዘነጉ እስከመጨረሻው በእምነት እንዲጓዙ የማድረግ ድርሻው ትልቅ ነው:: መንፈሳዊ አባት ለመንፈሳዊ ልጆቹ የዘላለም ብድራት መኖሩን እንዳይረሱ ሳይታክት ዘወትር ያሳስባቸዋል::



## የአገልጋይ እውነተኛ ማንነት በቤተሰብ እውድ ይታወቃል

የአንድ አገልጋይ ትክክለኛና እውነተኛ ማንነት የሚታወቀው በቤተሰብ እውድ ውስጥ በሚኖረው ሕይወት ነው:: ለቤተሰብ ምስጢር የሚሆን የአገልጋይ የሕይወት ገጽታ አይኖርም:: ቤተሰብ አገልጋይን መልካሙንና መጥፎ የሕይወት ገጽታውን በሚገባ ያውቃል:: አንድ አገልጋይ መንፈሳዊ ሕይወትን በትክክልና በጥልቀት መኖሩ የሚታወቀው በቤተሰቡ ውስጥ በመሆኑ አገልጋይን ከቤተሰብ እውድ ውጭ በትክክል ማወቅ አዳጋች ነው:: አገልጋይ የሚታወቀው በቤተሰብ ውስጥ በሚኖረው አጠቃላይ ሕይወት ነው:: የአንድን አገልጋይ እውነተኛ ገጽታ የሚያውቀው ቤተሰቡ ነው::

በቤተሰብ ውስጥ ጥሩ ምሥክርነት ያለው አገልጋይ በቤተክርስቲያንም መልካም ምሥክርነት ይኖረዋል:: አንድ አገልጋይ በትዳር ጓደኛውና በልጆቹ የሚነቀፍ ከሆነ ራሱን መመርመርና የሚነቀፍበትን ነገር ማስተካከል ይገባዋል:: ምክንያቱም ያ የተነቀፈበት ነገር እውነት ይሆናል:: የቤተሰብ ግምገማ ከቤተክርስቲያን ግምገማ ይልቅ እውነትነት አለው::

ስለዚህ አንድ ሰው ቤተሰቡን በሚገባ መንከባከብና መምራት ካልቻለ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ መንከባከብና መምራት እንደማይቻል መገለጹ የቤተሰብና የቤተክርስቲያን አገልግሎት ተዛማጅነት እንዳላቸው ያሳስበናል:: በአንድ ሰው ቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች ቁጥር በአንጻራዊ መልክ ሲታይ ጥቂት ነው:: እነዚህ ሰዎች ከሰውየው ጋር የተዛመዱ ናቸው:: ሰዎቹም በዕድሜያቸው ከእርሱ ያነሱ ናቸው:: በቤተክርስቲያን ያሉት ሰዎች ቁጥር ከቤተሰብ ካሉቱ ይበልጣሉ፣ የኑሮ ደረጃቸው፣ ትምህርታቸውና ያላቸው የሕይወት ልምምድ የተለያየ ነው:: ከቁጥራቸው መጨመር በተጨማሪም ባሕርያቸውና ዕድሜያቸው የተለያየ ነው:: አንድ ሰው በቤተሰቡ በትንሽ ሥፍራ መምራት ካልቻለ በትልቅ ሥፍራ በቤተክርስቲያንም መምራት አለመቻሉን መተንበይ ይቻላል::

ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የመጀመሪያው የሥልጠና ሥፍራ ቤተሰብ ነው:: በዚህ ዓውድ ስኬታማ የሆነ ሰው ወደ አገልግሎት ይሠማራል:: ጆን ስቶት በቤተሰብ አመራርና በቤተክርስቲያን አገልግሎት መካከል የጠበቀ ቁርኝት እንደለ «ባለትዳር የሆነ መጋቢ ሁለት ቤተሰቦችን ማለትም የራሱንና የእግዚአብሔርን ቤተሰብ ለመምራት የተጠራ አገልጋይ ነው:: የመጀመሪያው ለሁለተኛው የሥልጠና ሥፍራ ነው:: መጋቢዎች በቤተሰቦቻቸው ውስጥ በሥርዓት መምራትን ካልተማሩ በእጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሥርዓት እንዲመሩ መጠበቅ አይቻልም» በማለት ተናግረዋል::[5]

የአገልጋይ ጥሪ በቤተክርስቲያን ውበጥ መንፈሳዊ ሥራዎችን መሥራት ብቻ ሳይሆን አቤት ውበጥም ለቤተሰቡ አስፈላጊ የሆኑትን ኃላፊነቶች መወጣት መሆኑ አገልግሎቱ በሁለት ዋልታዎች መካከል እንደተወጠረ ሰው ያደርጓል:: በቤተክርስቲያን ያለውም አገልግሎት በቤት ውስጥ ያለውም ኃላፊነት ትኩረትን የሚፈልጉ ነገሮች በመሆናቸው ነው:: ሁለቱን በማይጎዳ ሁኔታ ከማገልገል ውጭ ግን ሌላ አማራጭ አይኖረውም::

---

[5] Stott, John (1996). *The Message of I Timothy and Titus.* Inter varsity Press, p.98

አገልጋይ በተለይ አስቀድሞ ቤተሰቡን በሚገባ መምራትን ከተለማመደና በዚህ አገልግሎት ስኬትን ካገኘ ለቤተክርስቲያን አገልግሎት መልካም የሆነ መርሆዎችን እንደተማረ ያስገነዝባል። ከዚህም የተነሳ ነው ቤተሰብ የአገልግሎት የመጀመሪያ የሥልጠና ትምህርት ቤት ነው የተባለው።

የአገልጋይ ቤተሰብ ትንሽ ቤተክርስቲያን ስለሆነች መንጋውን ከመመገቡ በፊት በልቡ ያለውን የእግዚአብሔር መልዕክት አስቀድሞ የሚያቀምሰውና የሚፈትሽበት ቦታ ነው። ለቤተክርስቲያን ምዕመናን ከመስበኩ በፊት የስብከቱ ቀማሾች የቤቱ ሰዎች ይሆናሉ። ይህ ደግሞ ለእርሱም ለቤተሰቡም ጠቃሚ ነው።

አገልግሎት የሚከናወነው በግንኙነት ውስጥ በመሆኑ አንድ ሰው አገልጋይ ለመሆን ከቤተሰቡ ጋር መልካም ግንኙነት የሚገነባ መሆን ይጠበቅበታል። አንድ ሰው ይህን ጉዳይ አስመልክቶ የሚከተለውን ብሰዋል፦

> ክርስቲያናዊ መሪነት ከግንኙነት ጋር የተያያዘ ነው። ቤተሰብ ደግሞ አንድ ሰው በጣም የሚቀርባቸው ሰዎች ያሉበት ኅብረት ነው። ከዚህ ኅብረት ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ካልቻለ ይህ ሰው ከሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በመልካም ሁኔታ ለመያዝ ብቃት የለውም ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመምራት ብቃት አይኖረውም።[6]

አገልግሎት የሚሰጠው ለሰዎች ነው። አገልጋይ የሚያገለግለው ሰዎችን ነው። ሰዎች ደግሞ አገልግሎትን እንዲያገኙና እንዲጠቀሙበት ለማድረግ ከሰዎቹ ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር ይገባል። ሰዎች አገልግሎትን በመቀበል በሕይወታቸው ለመተግበር የሚነሳሱት አገልግሎት የሚሰጣቸው አገልጋይ ከእነርሱ ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረው ነው። አገልጋዩን ከተቀበሉ በኋላ ከእርሱ የሚገኙትን ነገሮች ደግሞ ይቀበላሉ። ስለዚህ መንፈሳዊ አገልግሎትን በተሳካ ሁኔታ ለመስጠት ከተገልጋዮች ጋር መልካም ቅርበትና ግንኙነት መፍጠር መሠረታዊ ነገር እንደሆነ እንገነዘባለን። አንድ አገልጋይ መልካም ግንኙነት መመሥረትን የሚማረው ከቤተሰቡ ነው። በደምና በሥጋ ከሚገናኛቸው የቤት ሰዎች ጋር በመልካም ሁኔታ የሚኖር ሰው ሊሆን ይገባል። ከቤት ሰዎች ጋር በመተማመን ላይ የተመሠረተ ኅብረት ካለው ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት መሥርቶ ማገልገል አያቅተውም። ነገር ግን ከቤት ሰዎች ጋር ጤናማ ግንኙነት ሳይኖረው ከሌሎች ሰዎች ጋር ግንኙነት ለመመሥረት ጥረት ሊያደርግ ይችላል። ሆኖም ላይ ላይ የሆነ ታማኝነት የሌለበት ግንኙነት እንጂ ከልብ የሆነ ግንኙነት መፍጠር አይችልም።

ግንኙነትን መመሥረት መቻል አንዱ ጠንካራ ጎን ቢሆንም የተመሠረተውን ግንኙነት እየገነቡ ማኖርና ወደተሻለ ደረጃ ማሳደግ መቻል ደግሞ ሌላው አስፈላጊ ችሎታ ነው። አገልጋይ ግንኙነት መመሥረት ብቻ ሳይሆን ግንኙነትን ማቆየት የሚችል ሰው ሊሆን ይገባል። ከሚያገለግላቸው ሰዎች ጋር ዘላቂነት ያለው የአገልጋይና የተገልጋይ ግንኙነት መጠበቅ አለበት። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከሰዎች ጋር ሊያጋጩ የሚችሉትን

[6] Fernando, Ajindo (1985). *Leadership Life Style*. Wheaton, IL: Tyndale House Publishers, Inc., p.73



መሠረታዊ ነገሮች በጥንቃቄ መያዝ፣ ብስለት ያለው አዕምሮ፣ የስሜት ስክነት፣ ትዕግስት፣ ከራስ ይልቅ የሌሎችን ሰዎች ጥቅም ማስቀደም፣ ሰዎችን ከበደለ ይቅርታ በመጠየቅ የተበላሸውን ግንኙነት ለማደስ የትሕትና ልብ ያለው መሆን ይገባዋል። እነዚህን ነገሮች ደግሞ የሚያገኘውና የሚያሳድገው በቤተሰብ አውድ ውስጥ በመሆኑም ከቤተሰቡ ጋር እንዴት እንደሚኖር በማወቅ በቤተክርስቲያን ካሉት ምዕመናን ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው እንደሚችል መተንበይ ይቻላል።

አንድ አገልጋይ በቤተሰብ ውስጥ የሚኖረው ሕይወት በቤተክርስቲያን በሚሰጠው አገልግሎት ላይ ከፍተኛ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። አገልጋዩ በቤተሰቡ መልካም የሕይወት ልምምድ ካለው አገልግሎቱ የሠመረ ይሆናል። ይህም የሚሆንበት አንዱ ምክንያት በሕይወት የኖሩት ነገር በቃል ከሚናገሩት ይልቅ በሰዎች ላይ በጎ ተጽዕኖ የማምጣት ኃይል ስለሚኖረው ነው። ስዚህም ማዜር ቴርዛ የተናገሩትን አሳብ መጥቀስ ይቻላል።

> ሰዎች... ከቤተሰብህ ጋር እንዴት እንደምትኖር! በቤተሰብህ ውስጥ ምን ያህል ሰላም እንዳለ እንዲያዩ ፍቀድላቸው። ከዚያ በኋላ ከሕይወትህ እንዲሁም ከልምምድ ስስምትናገር ዓይናቸው ውስጥ ፊት ለፊት እየተመለከትካቸው «መንገዱ ይህ ነው» ማለትን ትችላለህ።[7]

መልካም አገልግሎት ለመስጠት በመልካም ቤተሰብ ውስጥ መኖር ያስፈልጋል። እርካታ ያለው ቤተሰብና አዳጊና መልካም ኅብረት ያለው ቤተክርስቲያን የሚገነቡት ከተመሳሳይ ነገሮች ነው። በሁለቱም ሥፍራዎች ፍቅር፣ እንክብካቤ፣ በሥርዓት መያዝ፣ ዋጋ መክፈል፣ የእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና ጸሎት ይኖራል። አገልጋይ እነዚህን የተጠቀሱትን ነገሮች በቤተሰቡ ውስጥ የሚያከናውናቸው ከሆነ ቤተሰቡ ደስተኛ ቤተሰብ ይሆናል። በቤተክርስቲያንም እነዚህን ነገሮች በሥራ ላይ ሲያውል ተመሳሳይ ሁኔታ ይፈጠራል።

አገልግሎት ከቤት እንደሚጀምር ተመልክተናል። አገልግሎት ከቤት የማይጀምር ከሆነ ጎዶሎ ይሆናል። አገልጋይ በውጭ በሰዎች እየተሞገሰ ነገር ግን ሚስቱና ልጆቹ በእርሱ የሚያማርሩ ከሆነ አገልግሎቱ ፍሬያማ አይሆንም።

የአገልጋይ ቤተሰብ አባላት ለእርስ በርሳቸው ፍቅር፣ ርኅራኄና እንዱ ለሌላው ዋጋ መክፈል የማያሳዩ ከሆኑ ከቤተሰብ ውጭ ለሆኑ ሰዎችና ቤተሰቦች በፍቅርና በርኅራኄ መልካም ምሳሌ ሊሆኑ አይችሉም። ለራሳቸው የሌላቸውን ነገሮች እንዴት ለሌሎች ማካፈል ይችላሉ? በእነርሱ መካከል የማይታየውን ነገር ለሌሎች መስጠት አይችሉም።

አገልግሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ያለው መሆን እንዳለበት የሚያስተምር ጀይ አዳምስ የተባለ ሰው አንድ ሰው ቤተሰቡን በሚገባ መምራት ካልቻለ የእግዚአብሔርን መንጋ መምራት የማይችልበትን አምስት

[7] Quoted in Shawchuck and Heuser, (1993, p. 125)

ምክንያቶችን ጠቅሰዋል::[8] እነዚህም አሳቦች ከላይ የተጠቀሱት ዝርዝር አሳቦችን አጠቃልለው የያዙ በመሆናቸው ጥሩ ማጠቃለያ ይሆናሉ::

- ✓ በቤተሰብም ሆነ በቤተክርስቲያን አገልጋዩ የሚጠቀምባቸው መርሆዎችና ዘዴዎች ተመሳሳይ በመሆናቸው
- ✓ ጥቂት ሰዎችን መምራት ካልቻለ ብዙ ኃላፊነት ያለበትን ኅብረት መምራት አዳጋች ስለሆነ
- ✓ ቤተሰቡን በመምራት ደካማ ከሆነ ብዙ ኃላፊነት ያለውን መንፈሳዊ አገልግሎት በስኬታማ ሁኔታ መምራት ስለሚያስቸግር
- ✓ ቤተሰቡን በሚገባ መምራት ካቃተው ለሚመራው የእግዚአብሔር መንጋ መልካም ምሳሌ መሆን ስለማይችል
- ✓ ቤተሰቡን በሚገባ መምራት ያልቻለ ሰው በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ቅድሚያ በሚሰጠው ነገር ላይ ተገቢ ውጤት ያላስገኘ በመሆኑ በመንፈሳዊ አገልግሎት ላይ ብቃት አይኖረውም (1ጢሞ4:12)

### የቤተሰብ መሪነት መታወቂያዎች

አንድ አገልጋይ ቤተሰቡን በሚገባ እየመራ እንደሆነ በምን ይታወቃል? አገልጋይ ቤተሰቡን በመልካም ሁኔታ እየመራ እንደሆነ ከሚታወቅባቸው ነጥቦች መካከል የሚከተሉት ነጥቦች ይጠቀሳሉ:: እነርሱም:-

- በየዕለቱ ለቤተሰብ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንበትን ነገር የሚያገኝ ሲሆን
- ከሚስቱ ጋር መልካም መግባባት ሲኖረው
- ልጆቹ እርስ በርሳቸውና ከሌሎች ልጆች ጋር በመልካም ሁኔታ መኖር ሲችሉ
- ቤተሰቡ አንድ ላይ በሚሆንበት ወቅት እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚደሰት ሲሆን
- የውጭ ሰው ስለቤተሰቡ መልካምነት ምሥክርነት ሲሰጥ

እስካሁን ድረስ ትኩረት የተሰጠው ባለትዳር የሆነን አገልጋይ በሚመለከት ነው:: ባለትዳር ያልሆነውስ? ያላገባ ሰው ለቤተክርስቲያን መንፈሳዊ መሪነት ወይም አገልግሎት ሲጠራ ቤተሰብን የመምራት ብቃቱ እንዴት ሊታወቅ ይችላል? ለቤተክርስቲያን መሪነት የሚሾም ሰው ያገባና ባለትዳር የሆነ ሰው ቢሆን ይመረጣል:: ምክንያቱም ቤተሰብን መምራት ለቤተክርስቲያን የመሪነት አገልግሎት መታያ ሥፍራ በመሆኑ ነው:: ሆኖም ሰውዬው ያላገባ ከሆነና ሌሎች ለመንፈሳዊ መሪነት ወይም አገልጋይነት የሚያበቁትን መስፈርቶች የሚያሟላ ከሆነ መሾም ይቻላል:: ስለእርሱ የቤተሰብ ሁኔታ ማለትም ከቤተሰብ ጋር እንዴት እንደሚኖር፣ በቤተሰብ ውስጥ ምን ባሕርይ እንዳለው፣ እንደ ልጅ ከቤተሰብ ጋር የነበረው ግንኙነት እንዲሁም አሁን ከሚኖርበት የቅርብ ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙነት በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል::

---

[8] Adams, Jay (1975). *Shepherding God's Flock.* Grand Rapids, MI: Zondervan Publishing House, pp.33-34.



አንድ ሰው በራሱ ቤተሰብ የሚሆነውንና የሚያደርገውን ነገር የሚማረው ከተወለደበትና ካደገበት ቤተሰብ ስለሆነ ሰውዬው ያደገበትን ቤተሰብ ሁኔታ በማጥናት የራሱን ቤተሰብ እንዴት ሊመራ እንደሚችል በጥቂቱም ቢሆን መተንበይ ይቻላል:: ሰው የራሱን ቤተሰብ ሲመሠርት ከቅርብ ሰዎች ጋር ያልነበረውን መልካም ግንኙነት ያመጣል ብሎ ማሰብ አዳጋች ነው:: ስለዚህ ያደገበትን ቤተሰብና ከቅርብ ሰዎች ጋር ያለውን ግንኙ ነት በማለስ ቤተሰብን የመምራት ብቃቱን መመዘን ይቻላል:: ባለትዳር ያልሆነን ሰው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከመጥራት ወይም ከመሾም በፊት የቤተሰብን ሁኔታ ችላ ብሎ በሌሎች መመዘኛዎች ብቻ መፈጸም ሙሉ ጥናት ሳይደረግ ኃላፊነት መስጠት ስለሆነ ችግር ሊያስከትል ይችላል::

እንግዲህ በቤተክርስቲያን የሚሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎትና አገልጋይ በቤተሰብ ውስጥ እንደ ትዳር ጓደኛና እንደ ወላጅ በሚኖረው ሚና መካከል ተወራራሽነት በመኖሩ የአንድ አገልጋይ የአገልግሎት ስኬት የሚለካው እርሱ በቤተሰብ ውስጥ እንደ ትዳር ጓደኛና ወላጅ ሚናውን በሚገባ በማከናወኑ እንዲሁም በቤተሰብ ውስጥ የሚሆናቸውንና የሚያደርጋቸውን መልካም ነገሮች በቤተክርስቲያንም መሆንና ማድረግ ሲችል ነው::

ቤተክርስቲያን አንድን አገልጋይ ለመሾም በምታስብበት ጊዜ ትክክለኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት እንደተቀበለና በሕይወቱ ክርስቶስን ያወቀና የተለማመደ መሆኑን በሚገባ ለመመርመር ጥረት እንደምታደርግ ሁሉ የእርሱን የቤተሰብ ሕይወትም መመዘን አስፈላጊ በመሆኑ እንደ ትዳር ጓደኛና እንደ ወላጅ ምን ዓይነት ሕይወት እንዳለው መፈተሽ ያስፈልጋል::

### ለቤተሰብ ቅድሚያ መስጠት የሚኖረው ጥቅሞች

አንድ አገልጋይ ከአገልግሎት በፊት ለቤተሰብ ቅድሚያ ሲሰጥ ብዙ ትርፍ ያገኛል::

- ✓ ከትዳር ጓደኛው ጋር መልካም ኅብረት ይኖረዋል::
- ✓ ልጆቹን በፍርሃ እግዚአብሔርና ሁለተናዊ ፍላጎቶቻቸውን በማሟላት ለማሳደግ ዕድል ያገኛል::
- ✓ አገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን ያደርጋል:: ምክንያቱም አገልግሎቱ በቤተሰብ ውስጥ ተፈትኖ ያለፈ በመሆኑ ሌሎች እርሱን እንዲከተሉ ያደርጋል::

*በምሳሌነት ሌሎችን ለማስተማር:-* በዚህ ዘመን ዓለም ስለመልካም ጋብቻና ቤተሰብ ምሳሌ የሚሆናትን እየፈለገች ትገኛለች:: ጋብቻና ቤተሰብ በተለያዩ ተጽዕኖዎች ሲፈራርስ ማየት የተለመደ ሆኗል:: ሰዎች አንዳንድ ጊዜም በእግዚአብሔር አናምናለን የሚሉ ምዕመናን ጭምር ለትክክለኛ ቤተሰብ ምንነት ግራ እንደገባቸው ማስተዋል ከባድ አይደለም:: በአካባቢያችን በባልና ሚስት መካከል በሚፈጠረው አለመግባባትና በሌሎችም አናሳ ምክንያቶች ፍች እንደ ቀላል ነገር በመቁጠር እንደ አማራጭ መፍትሔ እየሆነ ይገኛል:: ወላጆች ልጆቻቸውን ከመውደድና ከመንከባከብ ይልቅ ያንገላቱአቸዋል:: ልጆችም ወላጆቻቸውን ከማክበርና ከመታዘዝ ይልቅ በእነርሱ ላይ ይነሱና ይንቁአቸዋል:: ከትዳር ውጭ

ልጆችን መውሰድና በነጠሳ ወሳጅነት ልጆችን ማሳደግ እንደ አማራጭ እየታየ ይገኛል።

ለዚህ ችግር መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉት በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ምዕመናን ናቸው። ምዕመናን መልካም ትዳርና ቤተሰብ እንዲኖራቸው ደግሞ አገልጋይ ስለመልካም ትዳርና ቤተሰብ ማስተማር አስፈላጊ ነው። ይህ የማስተማር አገልግሎት ግን ፍሬያማ የሚሆነው አገልጋዩ መልካም ቤተሰብ መገንባት በመቻል ለሌሎች ምሳሌ ሊሆን ነው። ብዙዎች ስለመልካም ትዳርና ቤተሰብ ለማስተማር እውቀት ሊኖራቸው ይችላሉ። ነገር ግን ትምህርቱ በምሳሌነት ሲሆን የበለጠ ኃይል ይኖረዋል። አገልጋይ የሚኖረው ሕይወት በራሱ የተዋጣለት ስብከት ነው። አካባቢው በችግር ውስጥ እያለ ወንጌል የሰውን ሕይወትና ቤተሰብ ለውጦ መልካም ቤተሰብ እንዲኖራቸው ካደረገ ይህ ወንጌል ለሰው ልጆች ጥቅም እንደሆነ የሚናገር ሕያው ምስክር ነው። የአገልጋይ መልካም ቤተሰብ በኅብረተሰቡ ውስጥ የሚያበራ ብርሃን ይሆናል። ወንጌል የግል ሕይወት ብቻ ሳይሆን የቤተሰብንም ሕይወት መለወጥ እንደሚችል ያሳያል።

በአውዳችን የአገልጋይ እውነተኛ የቤተሰብ ሁኔታ ለውጭ ሰዎች እምብዛም የሚታይ አይደለም። አንዳንድ አገልጋዮች በቤተሰብ ያላቸው ትክክለኛ ሁኔታ በተለይም ከሚስቶቻቸውና ልጆቻቸው ጋር ያላቸው መልካም ያልሆነ ግንኙነት በሌሎች ሰዎች ዘንድ እንዳይታወቅባቸው ለመደበቅ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ። የግል ችግራቸውን ለራሳቸው በመያዝ በሰዎች ዘንድ መልካም ግንኙነት እንዳላቸው አድርገው ይቀርባሉ። በሰዎች ፊት ይጫወታሉ፣ ይስቃሉ፣ በመከባበር ይነጋገራሉ ነገር ግን ለብቻቸው ሲሆኑ ንትርክ ይጀምራሉ። ሁለት ተቃራኒ ሕይወት አላቸው። በሰዎች ዘንድ የሚታወቅና ከሰዎች የተሰወረ የሕይወት ገጽታ አላቸው።

ይህ አስመሳይነት ግን ዘለቄታ አይኖረውም። አንዳንዶች ማስመሰላቸው በእግዚአብሔር ፊት መልካም እንዳልሆነና ለእነርሱም ጥቅም እንደሌለው ያውቁታል። ሆኖም የቤተሰባቸውን ደካም ጎን ለሚያገለግሉት ሕዝብ መግለጽ በእነርሱ ዘንድ ያላቸው ተሰሚነትና ክብር ስለሚጎዳባቸው ይህን መንገድ ይጠቀማሉ። የቤተሰብ ገመናቸው ወደ ውጭ ከወጣ ምዕመናን እነርሱን በጸሎት ከማገዝ ይልቅ እነርሱን መንቀፍና በእነርሱ ላይ መፍረድ ይጀምራሉ። ይህ ሕዝቡ አገልጋይ ፍጹም ሰው እንደሆነ ከማሰብ የተነሳ የመጣ አስተሳሰብ ሊሆን አገልጋይ ራሱን ካሳወቀና ትክክለኛ ማንነቱን ለሚያገለግለው ሕዝብ ለመግለጥ እርምጃ ካልወሰደ የእነርሱን ደረጃ ለማሟላት ከሆነው በላይ ሆኖ ራሱን እንዲያቀርብ የሚጋብዝ ስለሆነ አደገኛ ነው። አገልጋይ የምዕመኑን ነቀፋና ፍርድ በመፍራት የቤተሰብ ችግሩን አምቆ ይኖራል። ከጊዜ በኋላ በባልና ሚስት መካከል የተፈጠረውና የታመቀው ችግር ቀስ በቀስ እያደገ ይሄድና ትዳራቸውን አደጋ ላይ ይጥላል። በአገልጋይና ሚስቱ መካከል መፋታት ባይታይም እንኳ ሁለቱም በማይመች ትዳር ውስጥ ታስረው ይኖራሉ።

በቤተሰብ አመራርና አያያዙ አገልጋይ ለሚመራቸውና ለሚያገለግላቸው ምዕመናን ምሳሌ መሆን አለበት። ከእርሱ ጋር አብረው የሚያገለግሉ፣ እርሱ የሚያገለግላቸው ምዕመናንና ጌታን ያላመኑ ሰዎች አገልጋዩ ከአገልግሎቱ በፊት ለቤተሰቡ ቅድሚያ እንደሚሰጥና



እንደሚከባከብ በመገንዘብ እንደ እርሱ በማድረግ እንዲማረኩ የሚያደርግ ሲሆን ይህ ምሳሌነቱ በሌሎች ላይ በጎ የሆነ ተጽዕኖ ያሳድራል።

## የእግዚአብሔር ሰዎች ምሳሌነት

ሙሴ ሚስት ያገባውና ትዳርን የያዘው መጻተኛ ሆኖ ይኖርበት ከነበረው ከምድያም ምድረ በዳ ነበር። ሙሴ ከዚያው ሲፓራን አገባት። ከዚያም ከእርስዋ ሁለት ወንድ ልጆችን ወለደ። ሙሴ በአማቱ ቤት እየኖረ ለአርባ ዓመት በጎቹን ይጠብቅ ነበር። ከንጉሥ ቤተመንግሥት ለኮበለለው ሰው የተገኘው የሥራ መስክ በግ ጠባቂነት ነው። ይህኛ ሥራውንም እየሠራ ከቤተሰቡ ጋር ይኖር ነበር።

ሙሴ በምድያም ምድረ በዳ በበግ ጥበቃ ላይ ተሠማርቶ ሳለ በግብጽ የነበሩ የእስራኤል ልጆች ግን በባርነት ሥር ይማቅቁ ነበር። ከባርነት ቀንበር የተነሳ ሕዝቡ ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔር አለቀሱ። እግዚአብሔርም ከአባቶቻቸው ጋር የገባውን ቃልኪዳን አስቦና ከባርነት ሊያወጣቸው ወሰነ። ለዚህም አገልግሎት ሙሴን ጠራው። ሙሴ በበግ ጥበቃ ላይ በነበረበት ወቅት እግዚአብሔር ወደ ግብጽ ሄዶ በባርነት ሥር ያሉትን ወንድሞቹን ነጻ እንዲያወጣ ጠራው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር ብዙ ከተሟገተ በኋላ ጥሪውን ተቀበለ።

ሙሴ ከእግዚአብሔር ዘንድ ትልቅ አደራና ተልዕኮ ተቀብሎ በግ ሲጠብቅ ውሎ ወደ ቤት ተመለሰ። እቤት እንደ ደረሰም ለማን ቀድሞ እንደተናገረ ባይገለጽም ከአማቱ ጋር ግን ተነጋገረ። ሙሴ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ለአማቱ መናገሩ አልተጻፈም። ሆኖም «እስከ ዛሬ በሕይወት እንዳሉ እይ ዘንድ ተመልሼ ወደ ግብጽ ወደ ወንድሞቼ ልሂድ እለው» (ዘጸ 4፡18)። ሙሴ ከግብጽ ከወጣ አርባ ዓመት ሲሆነው እንዴት በዚህ ጊዜ ይህ ወደ ግብጽ የመሄዱ አሳብ እንደ መጣለት አማቱ ሳይጠይቀው አይቀርም። ሙሴ ተገቢውን መልስ በመስጠት ከአማቱ ፈቃድ አገኘ።

ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር የተገናኘ ሰው ቢሆንም አማቱን አልናቀውም። እንደ ቀድሞ ዘመናት በተረጋጋ መንፈስ አናገረውና ለማድረግ ሳሰበው ነገር ስምምነትን ፈለገ። አቀራረቡ ስላልተሰወጠበት ለሙሴ ፈቃድ ሰጠ። አማቱ ባይስማማበት ኖሮ ቢያንስ ሚስቱ ከእርሱ ጋር እንዳትሄድ ማድረግ ይችል ነበር።

ይህን ብቻ ሳይሆን ሙሴ ሚስቱንና ልጆቹን በምድያም ምድረ በዳ በተወለዱበትና ባደጉበት፣ ለሕይወታቸው ዋስትና ይኖራቸዋል ተብሎ በሚገመተው ሥፍራ ትቶአቸው ወደ ግብጽ አልተመለሰም። ነገር ግን ሙሴ «ሚስቱንና ልጆቹን ወስደ በአህያ ላይም አስቀመጫቸው ወደ ግብጽም አገር ተመለሰ» (ዘጸ.4፡20)። ሙሴ እግዚአብሔር እንዴት እንደተገናኘውና ምን ዓይነት ተልዕኮ እንደሰጠው ሳይነግራቸው ከመሬት ተነስቶ «ተነሱ አህያ ላይ ውጡ» እንዳላላቸው መገመት አዳጋች አይሆንም። የሙሴ ሚስትና ልጆቹ ጥያቄዎችን ሳይጠይቁ አልቀሩም። ሙሴም ለእነርሱ ሊገባቸው በሚችል መንገድ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ተልዕኮ ማስረዳት በመቻሉ ከሙሴ ጋር አብረው ለመውጣት እንደተስማሙ ይታመናል።

ሙሴ በእግዚአብሔር ጥሪ የእርሱን ተልዕኮ ያውም የእስራኤልን ሕዝብ ከባርነት ለማውጣት ወደ ግብጽ ቤተሰቡን ይዞ ሄደ፡፡ ይህ ጉዞ እንኳን ለቤተሰቡ ለሙሴ ለራሱም አስጊ ነበር፡፡ ሆኖም ሙሴ ከቤተሰቡ ለመለየት አልፈለገም፡፡ እግዚአብሔር ለጠራው አገልግሎት ከቤተሰቡ ጋር ሄደ፡፡

በእግዚአብሔር ተጠርቶ በመንግሥቱ አገልግሎት ላይ የተሰማሩ አገልጋዮች ስለቤተሰብ ከሙሴ የሚማሩት ብዙ ቁምነገሮች አሉ፡፡ ከእነርሱም ጥቂቶቹ፡-

- ✓ ለመንፈሳዊ አገልግሎት ከመውጣት ቀደም ብሎ የእግዚአብሔርን ጥሪ ለቤተሰብ ማሳወቅና የቤተሰብን ስምምነት ለማግኘት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግን
- ✓ የእግዚአብሔርን ሥራ ለመሥራት ወደተላኩበት ሥፍራ የራስን ቤተሰብ ይዞ መሄድን
- ✓ በአገልግሎት ምክንያት ከቤተሰብ ተለይቶ ሩቅ በታ ለረጅም ጊዜ አለመቆየትን
- ✓ የእግዚአብሔር ሥራ የሚከናወንበት ሥፍራ ወይም የተልዕኮው በታ ሁኔታ ለቤተሰብ ለሚስትና ለልጆች አስቸጋሪ ከሆነ በተለይም ልጆች በዕድሜያቸው ትናንሽ ከሆኑ ለተወሰነ ጊዜ ሚስት ከልጆች ጋር ለደህንነታቸው በማያሰጋ ሥፍራ ማኖርን (ዘጸ18:2 ይመልከቱ)

በሀገራችን የነበሩና ያሉ የእምነት አባቶችና እናቶች ቤተሰቦቻቸውን በሚገባ በመንከባከብ ምሳሌነት አልተውልንም፡፡ ከብዙዎቹ የተማርነው ከቤተሰብ አገልግሎት እንደሚቀድምና ቤተሰብን በአገልግሎት ስም መስዋዕት ማድረግን ነው፡፡ ስሌሎች ሰዎች ወንጌልን ለማድረስ ብዙ ዋጋ ሲከፍሉ ለቤተሰቦቻቸው ግን ምንም ትኩረት አላደረጉም፡፡ ከእኛስ ምዕመናን ስለቤተሰብ ምን ይማራሉ? የእኛ ቤተሰብ በችግር እየታመሰ እንዴት ጋብቻና ቤተሰብ በእግዚአብሔር አሳብና ዕቅድ እንዲሄድ ለማስተማርና በጎ ተጽዕኖ በሌሎች ላይ ማምጣት እንችላለን? እኛ መልካም ቤተሰብ ሳይኖረን የምናገለግላቸው ሰዎች መልካም ቤተሰብ እንዲመሠርቱ ለማስተማርና ለመምከር እንዴት ድፍረት ይኖረናል? በቤተሰብ መፍረስ ለተቸገረች ዓለም ጨው ለመሆን ከተፈለገ እግዚአብሔርን የምናገለግል አገልጋዮች ሁሉ የራሳችንን ቤተሰብ እንደ እግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ለመምራትና ለመያዝ እርምጃ መውሰድና ምሳሌ በሚሆን ሕይወታችን ሌሎች ሰዎች እንዲከተሉን ማድረግ ይገባል፡፡

<u>ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ፡፡</u>

1. *በዓውድህ አንድ ሰው መልካም ቤተሰብ አለው የሚባለው ምን ዓይነት መሥፈርት ሲያሟላ ነው? ከዚህ አኳያ የአገልጋይ ቤተሰብ እንዴት ይታያል?*
2. *አንድ አገልጋይ ቤተሰቡን በተገቢው ሁኔታ እየመራ እንዳልሆነ ቢታወቅ የአገልጋዩና የቤተክርስቲያን ኃላፊነት ምን ሊሆን ይችላል?*
3. *በሕይወትህ አንድ መንፈሳዊ ሰው ቤተሰቡን እንዴት መያዝ እንዳለበት ምሳሌ የሆኑልህ ሰዎች አሉ? ከእነርሱ ስለቤተሰብ አመራር ምን ተማርክ?*



እንግዲህ በቤተሰብና በአገልግሎት መካከል ይህን ያህል መተሳሰር ካለ ለቤተሰብ ተገቢውን ሥፍራ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ አያከራክርም፡፡ ቤተሰብ ሲባል ደግሞ ብዙ አባላትን ያቀፈ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል፡፡ በቤተሰብ ውስጥ የትዳር ጓደኛ እንዲሁም ልጆች ይኖራሉ፡፡ ከአባላቱ አኳያስ ሲታይ ቅድሚያ ለማን መስጠት አለበት? መቼም የትዳር ጓደኛ ከልጆች በፊት መቅደም እንዳለባት መገመት አያዳግትም፡፡ አገልጋይ ከሚስቱ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው ይገባል? እንደ ክርስቲያን ባል ብቻ ሳይሆን እንደ አገልጋይ ባል ምን ሊያደርግላት ይገባል? ሚስትስ እንደ አገልጋይ ሚስት ለባልዋ ምን ማድረግ ይጠበቅባታል? ሁለቱ እንዴት አድርገው ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን የጥሪ ተልዕኮ ተግባራዊ ማድረግ ይችላሉ? በዚህ ርዕስ ዙሪያ የሚነሱ የተለያዩ ጉዳዮች እንደሚኖሩ ያታወቀ ነው፡፡ የሚቀጥለው ምዕራፍ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ሰፋ ያለ ዳሰሳ ያደርጋል፡፡

## 4.1. አገልጋይና የትዳር ጓደኛው

ለአገልጋይ ከእግዚእብሔር በመቀጠል ትኩረት ማግኘት ያለበት የትዳር ጓደኛው ናት:: መልካም የትዳር ጓደኛን የሚሰጥ እግዚአብሔር ነው:: አገልጋይ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ሚስቱን መውደድና ለእርስዋ አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅበታል:: እርስዋ የእርሱ ሥጋ ናት:: ከሰዎች ሁሉ ይልቅ ለእርሱ እጅግ በጣም ቅርብ የሆነች ሰው ሚስቱ ስለሆነች ከሰው ልጆች ሁሉ እርስዋን በጣም ሲወዳት ይገባል:: ለሰው ልጅ ያለው ፍቅሩ የሚለካው እርሱ ሚስቱን በሚወዳት ፍቅር ልክ ነው:: ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ናቸው (ዘፍ.2:24) ስለሚልና ባል ሚስቱን የማይወድ ከሆነ የራሱንም ሥጋ እንደማይወድ ስለሚናገር ነው (ኤፌ.5:33)::

አገልጋይ ለቤተሰቡ በተለይም ለትዳር ጓደኛው ተገቢውን ጊዜ የማይሰጥ ከሆነ ትዳራቸው ሲጎዳ ይችላል:: አገልጋይም እንደማንኛውም ባለትዳር መልካም ትዳር ለመገንባት አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈል ይጠበቅበታል:: እርሱ አገልጋይ ስለሆነ ብቻ ትዳሩ በተዓምር አይገነባም:: የትዳር ግንኙነትን መገንባት ደግሞ ባልና ሚስት ጊዜ ወስደው አንድ ላይ የሚሆኑበትን ሁኔታ እንዲፈጥሩ የግድ ይላል::

የአገልጋይ ሚስቶች አገልግሎትን በተመለከተ ሁለት ተቃራኒ የሆነ አመለካከት አላቸው:: የመጀመሪያው አዎንታዊ የሆነ አመለካከት ነው:: ይኼውም የእገልጋይ ሚስት መሆን ማለት እግዚአብሔርን ለማገልገል ከፍተኛ ዕድል እንደሆነ በማሰብ አገልግሎት ዋጋ ቢያስከፍልም ከእግዚአብሔር ዘንድ መልካም ብድራት ያለው ሥራ እንደሆነ መመልከት ነው:: እግዚአብሔርን ማገልገል መልካም እንደሆነ የሚያስቡ የአገልጋይ ሚስቶች ስለአገልግሎት መጥፎ ነገር ሲናገሩ እምብዛም አይሰማም::

ሁለተኛ ደግሞ አሉታዊ የሆነ አመለካከት ነው:: በዚህ ውስጥ የሚመደቡ የአገልጋይ ሚስቶች ደግሞ አገልግሎት ማለት ባልንና ቤተሰብን የሚለይ ሥራ እንደሆነ ይቆጥራሉ:: ከዚህም የተነሳ ባል ለቤተሰብ ጊዜ በሚያጣበት ወቅት «እኔ እኮ እንዲህ መሆኑን ባውቅ ኖሮ አላገባሁም ነበር» ይላሉ:: ስለአገልግሎት ከማማረራቸውም የተነሳ ሌሎች እህቶች አገልጋዮችን እንዳያገቡ ቅስቀሳ ያደርጋሉ:: አገልጋይ ለቤተሰብ ጊዜ ካለመስጠቱ የተነሳ አገልግሎት መልካም እንዳልሆነ በማሰብ ከራሳቸው አልፎ ሌሎች ሴቶች ስለአገልግሎት ጥሩ አይታ እንዳይኖራቸው ማድረግ በውስጣቸው ያለው ምሬት ከፍተኛ መሆኑን ያሳያል::

ማርታ መጋቢ ታዬን ያገባችው አገልጋይ መሆኑን እያወቀች ነበር:: አገልጋይ ማለት የትዳር ጓደኛና ምዕመናን በጋራ የሚጠቀሙበት ሰው መሆኑን ያወቀችው ከብዙ ውጣውረዶች በኋላ እንደሆነ ትናገራለች:: «ታዬ አገልጋይ ቢሆንም የእኔ ባል ብቻ እንደሆነ አስብ ነበር:: ሆኖም በተግባር ሲታይ እርሱን ከእኔ ጋር የሚጋሩት ብዙ ሰዎች ናቸው:: ብዙ ሰዎች በጋራ በንብረትነት የያዙት ዕቃ ይመስላል:: የሚኖረው እኔ ቤት ነው ነገር ግን ማንም ሲፈልግ የሚጠቀምበት ዕቃ ነው:: ባሌ የእኔ ብቻ አለመሆኑን በተግባር ስመለከት በጣም አስቆጣኝ:: ግን ማድረግ የምችለው ነገር ስላልነበረኝ የግድ ሆኖብኝ ተቀበልኩት:: አሁንም ቢሆን አንዳንድ ጊዜ እኔ



ስፈልገው ሌሎችም በተመሳሳይ ጊዜ ሲፈልጉት ያስቆጣኛል:: ቁምነገሩ የጋራ ንብረትን እንዴት በጋራ መጠቀም እንደሚቻል ማወቁ ላይ እንደሆነ ተረድቻለሁ::»

ከላይ ለተጠቀሱት ነባራዊ ችግሮች መፍትሔ ሲመጣ የሚችለው አገልጋይ ቤተሰብ ቅድሚያ ሲሰጠው እንደሚገባ ሲያውቅና ለተግባራዊነቱም እርምጃ ሲወስድ ነው:: እንደ መንፈሳዊ መሪ ይህ ለእርሱ ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዱ አማኝ የሚያስፈልገው ነገር መሆኑን ማስተማር ይጠበቅበታል:: ከዚያም የራሱን ቤተሰብ በሚገባ በመንከባከብ የሚያገለግላቸው አማኞች የእርሱን ምሳሌነት እንዲከተሉት ማድረግ አለበት::

አገልጋይ መልካም የትዳር ሕይወት ሲኖረው የሚያገለግላቸው ምዕመናን መልካም የትዳር ሕይወት እንዲኖራቸው ሲረዳቸው ይችላል:: ምዕመናን የትዳር ችግር ካላቸው እንዴት አድርገው መልካም ትምህርት መገንባት እንደሚችሉ ሲመክራቸውና መልካሙን መንገድ ሲያሳያቸው ይችላል:: ለምዕመናን በትምህርት ብቻ ሳይሆን ከትዳር ጓደኛው ጋር ባለው መልካም ግንኙነት ጥሩ ምሳሌ ይሆንላቸዋል:: እርሱን በመከተል ሌሎች ባለትዳሮችም ከትዳር ጓደኛቸው ጋር መልካም ግንኙነት እንዲመሠርቱ በጎ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል:: ከሁሉም በላይ ደግሞ አገልጋይ ከትዳር ጓደኛው ጋር ጥሩ ኅብረት ካለው ሁለንተናዊ ፍላጎቶቹ ስለሚሟሉለት እርካታና ደስታ ያገኛል:: ይህ ደግሞ በአገልግሎቱ እርካታ እንዲያገኝ አስተዋጽኦ ያኖረዋል::

አገልጋይና ሚስቱ መልካም ግንኙነት የሚኖራቸው የእግዚአብሔር ቃል ስለባልና ሚስት ግንኙነት የሚያስተምረውን ትምህርት በሕይወታቸው ተግባራዊ ሲያደርጉ ብቻ ነው:: እነዚህም የግንኙነት መመሪያዎች በ(ኤፌ.5:21-33፣ ቆላ.3:18-20፣ 1ጴጥ.3:1-7) ላይ ተጠቅሰዋል:: አገልጋይ እንደ ባል ሚስቱን መውደድ እንዲሁም ሚስት ለባልዋ መገዛት ይኖርባታል:: ይህን ሲያደርጉ እነርሱ የሚያገለግሉአቸው ምዕመናን ከሕይወታቸው መልካም ምሳሌነት ይማራሉ::

አገልጋይና ሚስቱ ግንኙነታቸውን እንደ እግዚአብሔር ቃል በማድረግ ወደ እግዚአብሔር አሳብ ለማደግ እንዲሁም አገልግሎታቸውን በስኬት ለማከናወን የበኩላቸውን ሚና መተግበር ይኖርባቸዋል::

### የአገልጋይ ሚስት ከባልዋ ምን ትጠብቃለች?

የአገልጋይ ሚስት እንደ ማንኛውም ሚስት አንድ ባል ለሚስቱ ማድረግ የሚጠበቅበትን ነገር እንዲያደርግላት ትጠብቃለች:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ አገልጋይ ሚስቱ ከእርሱ የምትጠብቃቸው ነገሮች አሉ:: ከእነዚህም የሚከተሉት ይጠቀሳሉ:: እነርሱም:-

*መንፈሳዊ እንክብካቤ:-* አገልጋይ የሆነ ባል በማግባትዋ የእርስዋ መንፈሳዊ ጥያቄዎች ምላሽ እንደሚያገኙ ታስባለች:: በተለይ አገልጋዩ ከእርስዋ ይልቅ በመንፈሳዊ ሕይወቱ የበሰለ ከሆነ በመንፈሳዊ ነገር ከእርሱ የምትጠብቀው ነገር ብዙ ይሆናል:: ብዙ እህቶች አገልጋይን ማግባት ከሚፈልጉበት ምክንያቶች አንዱ በእርሱ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት

በመማረክ ነው። እርሱን ቢያገቡ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው መንፈሳዊ ኅብረት እንደሚያድግላቸው ያስባሉ።

ገነት አገልጋይን ለማግባት ከፍተኛ ምኞት ነበራት። «አገልጋዮች ሲያገለግሉ ሳያቸው በጣም ደስ ይለኛል። ወደፊት አገልጋይን አገባለሁ የሚል ምኞት ስለነበረኝ እግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ባል እንዲሰጠኝ እጸልይ ነበር። አገልጋይ ባገባ መንፈሳዊ በረከት ከሚቀዳበት ምንጭ እንደምጠጋ አስብ ነበር። እንደተመኘሁትና እንደጸለይኩበት አልቀረልኝም አንድ የምወደው አገልጋይ ለትዳር ጠየቀኝ። እውነት አልመሰለኝም። ተስማምተን ተጋባን። አገኛለሁ ብዬ ያሰብኩት ግን አልሆነም። እርሱ ቀኑን ሁሉ አገልግሎት ውሎ ይመጣና ከእኔ ጋር መጫወት፣ ማውራት እንዲሁም የባልና ሚስትን የፍቅር ሥራ መሥራት ይፈልጋል። እኔ ደግሞ ቃሉን እንዲያስተምረኝና እንድንጸልይ እፈልጋለሁ። ያልጠበኩት ነገር ሲሆን በጣም አዘንኩኝ። ሆኖም ከጊዜ በኋላ እርሱ ለእኔ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን ባሌም እንደሆነ ተረዳሁ። ከዚያ በኋላ ነገሮችን በሚዛን ለመጠበቅ እንሞክራለን።»

አንዳንድ ጊዜ ሚስት ከባል የምትጠብቀው ነገር በተለይም በመንፈሳዊ እንክብካቤ ከፍተኛ ይሆንና እንዲሁም ባልዋን እንደ አገልጋይ ብቻ በማየት የተጠበቀው ነገር ሳይገኝ ሲቀር ተስፋ ትቆርጣለች። ስለዚህ የአገልጋይ ሚስት ሲታገባውም ሆነ ካገባች በኋላ ባልዋ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን ባልም እንደሆነ በመረዳት ከመንፈሳዊ ነገር ውጭ ሌሎች ነገሮችንም ማድረግ እንደሚያስፈልግ መጠበቅ ለግንኙነት መታነጽ ይረዳል።

*የምሽት አገልግሎት መተው፡-* ሚስት ከአገልግሎት በጣም ሳይመሽ ወደ ቤት መጥቶ የቤተሰብ አምልኮ እንዲያደርግላቸው፣ ቃል እንዲያካፍላቸውና እንዲጸልይላቸው ትፈልጋለች። አገልጋይ ያልሆኑ ክርስቲያኖች ቤት ውስጥ ማታ ማታ ባሎች መንፈሳዊ ፕሮግራም ሲያደርጉ ስለሚያዩና ስለሚሰሙ በአገልጋይ ቤት ውስጥም ተመሳሳይ ነገር እንዲደረግ ፍላጎት አለ። ማታ ከቤተሰቡ ጋር እራት እንዲበላ ትፈልጋለች። በአብዛኛው ቤተሰብ ውስጥ ባልና ሚስት እና ልጆች አንድ ላይ ምግብ ለመብላት ዕድል ያላቸው ማታ ነው። የአገልጋይ ቤተሰብ ይህን በጣም ይናፍቃል። ሆኖም ብዙ ስብሰባዎች የሚካሄዱት በማታ ስለሆነ አገልጋይ ቶሎ ወደ ቤት አይገባም። ከዚህም የተነሳ ሚስትና ቤተሰቡ አገልጋዩ መቼ ይሆን ከእኛ ጋር እራት የሚበላው የሚል ናፍቆት አላቸው።

- ✓ የአገልጋይ ሚስት ባልዋ ከቤተሰብ ተለይቶ በሳምንት ሦስትና ከዚያ በላይ ቀናት እዳር ጸሎት ወይም ፕሮግራም እያለ ከቤተሰብ ተለይቶ ውጭ እንዳያድር ትፈልጋለች።
- ✓ በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ እንድትሳተፍ እንዲያበረታታት ትፈልጋለች። ብቻውን የሚያገለግል ሳይሆን ሚስቱም ከእርሱ ጋር በመሆን እግዚአብሔር በሰጣት መንፈሳዊ ስጦታ እግዚአብሔርን እንድታገለግል እንዲያደፋፍራትና ሁኔታዎችን እንዲያመቻችላት ትሻለች።
- ✓ ባልዋ እርስዋን እንደሚወዳት በቃልና በተግባር እንዲያሳያት ትፈልጋለች። የአገልጋይ ሚስት ለባልዋ ከቤተክርስቲያን አገልግሎት እንደምትበልጥ እንዲቀበልና ከእርስዋ ጋር ጊዜ እንዲያሳልፍና ሁለቱም ደስ የሚላቸውን ነገሮች እንዲሠሩ ትፈልጋለች።



### ሰዎች ከአገልጋይ ሚስት ምን ይጠብቃሉ?

የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ መሆን ተግዳሮትም አለው። ሌሎች ባለትዳሮች የማያጋጥማቸው ተግዳሮት ይገጥማታል። የአገልጋይ ሚስት እንደ ሌሎች ሴት ምዕመናን አትታይም። በቤተክርስቲያን እርስዋ ከሌሎች ሴቶች የተለየች እንደሆነች ያስባሉ። የአገልጋይ ሚስት መሆን ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ ካሉት ሴቶች ሁሉ ይልቅ የታላቁ የእግዚአብሔር አገልጋይ ሚስት መሆን ማለት ስለሆነ በመንፈሳዊ ነገር እርስዋ ያላት ተደማጭነት ከፍተኛ ነው። ምዕመናን አገልጋይ ከሆነው ባልዋ ውስጥ ስለሚያዩዋት ያከብሩአታል። እርስዋን በአገልጋዩ ዓይን ስለሚመለከትዋት በሰዎች ዘንድ ያላት ሞገስ ትልቅ ነው።

መልካም ሕይወት በመኖር በሌሎች ሴቶች ላይ በጎ ተጽዕኖ ለማሳደር ያላት ዕድል ከፍተኛ ነው። ሌሎች የእርስዋን መልካም አርዓያ እንዲከተሉ በሕይወትዋ የመጥራት ኃይል ይኖራታል። በአንጻሩ ደግሞ መልካም ያልሆነ ሕይወት የምትኖር ከሆነ የሚኖራት ክፉ ምሳሌነት ከፍተኛ ይሆናል። ስለዚህ የአገልጋይ ሚስት እንደ ሌሎች ክርስቲያን ሴቶች በነጻነት መኖር አትችልም። በሁሉ ነገር ጥንቃቄ የተሞላበት አካሄድ ሊኖራት ይገባል። እርስዋ በሰዎች ዘንድ ያላት ሥፍራ ከፍተኛ በመሆኑ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የምታደርጋቸው ጥቃቅን ስህተቶች በምዕመናን ዘንድ አሉታዊ ተጽዕኖ አላቸው።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ወይም ውጭ ያሉ ሰዎች ስለአገልጋይ ሚስት የራሳቸው የሆነ ሥዕል አላቸው። ሰዎች ከአገልጋይ ሚስት የሚጠብቁት መልካም ባህርያትና ተግባራት አሉ። ምዕመናን ከአገልጋይ ሚስት ከሚጠብቁት መልካም ነገሮች የሚከተሉት ነገሮች የሚጠቀሱ ናቸው። እነርሱም፡-

የአገልጋይ ሚስት ዘወትር አምልኮና መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን እንድትካፈልና በመንፈስም የተነቃቃች እማኝ እንድትሆን ይጠበቃል። ይህም ማለት ስትጸልይ ወይም ስታመልክ በመንፈስ የምትሆን፣ በመንፈስ የምትነቃቃና ሌሎች ሰዎችንም ለአምልኮ የምታነሳሳ፣ ለመንፈሳዊ ነገር ቅንዓትና ትጋት እንዳላት በግልጽ የሚታይባት እንድትሆን ይጠበቃል። ሆኖም ግን የአገልጋይ ሚስት በመሆንዋ ብቻ ከሌሎች ይልቅ መንፈሳዊ እንደሆነች በማሰብ የምትኮራ ዓይነት ከሆነች ምዕመናን በተለይ እህቶች ይጠሉአታል።

- ✓ ለሰዎች ፍቅር ያላትና ፍቅርዋንም በድርጊት የምትገልጽ
- ✓ ሰዎችን ሰላምታ የምትጠይቅና ሰላምታ ስትጠይቅም በፊትዋ ላይ ለሰዎች ያላት መልካም አሳብና ፍቅር የሚነበብባት እንድትሆን ትጠበቃለች።
- ✓ ለተቸገሩ ሰዎች በተለይም በቤተክርስቲያን ውስጥ ላሉ ሰዎች የምትራራና የእናትነት ርኅራኄ ያላትና ካላት ለማካፈል ዝግጁ የሆነች

እንግዳ ተቀባይ በተለይም የእግዚአብሔር አገልጋዮችን በመቀበል ሳይሰለቻት የምታስተናግድና ይህም የእርስዋ አገልግሎት እንደሆነ የምትቀበል መሆን እንዳለበት ይጠበቅባታል። ከዚህም በተጨማሪ አንድ ጊዜ ያገኘቻቸውን ሰዎች ፊትና ስም ሳትረሳ በመጥራት ሰላምታ መስጠት

ለዎችን እንዳማትረሳ ስለሚያስቆጥር ለእርስዎ ያላቸውን አክብሮት እንዲጨምሩ ያደርጋል።

- ✓ በአለባበስዎ የተቀደሰች ማለትም በአውዳችን ፋሽን የማትከተል ነገር ግን ራስዎን ያልጣለች ልከኛ የሆነ ልብስ የምትለብስ፣
- ✓ ለዎችን ሁሉ በእኩል ዓይን የምትመለከትና ከሰዎች ሁሉ ጋር መልካም ግንኙነት ያላት። አንዳንዶችን በመቅረብ ሌሎችን ደግሞ የማታገልል አንዲትሆን ይጠበቃል። በተለይ በኑሮ ጥሩ የሚባል ደረጃ ላይ ካሉት ሴቶች ጋር መልካም ግንኙነት ኖሮአት በዝቅተኛ የኅብረተሰብ ደረጃ ላይ ያሉትን ሴቶች ደግሞ የማትቀርብ ከሆነ ሰዎች አይወዱአትም።
- ✓ በንግግርዋ ለዎችን የማትበድልና የማታሳዝን፣
- ✓ በሁሉ ነገር ታማኝ የሆነች። የአገልጋይ ሚስት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳ በመግባት ቃልዋን መጠበቅ ባትችል ለዎች «አንቺ የአገልጋይ ሚስት አይደለሽም ወይ?» ይሉአታል። የአገልጋይ ሚስት በምንም ሁኔታ ውስጥ ታማኝ መሆኗ ይጠብቃሉ።

ምዕመናን ከአገልጋይ ሚስት የሚጠብቁትን ነገሮች ከየት አገኙ? ብሎ መጠየቅ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት ጠቃሚ ነው። አንዳንዶች ከዚህ በፊት አነርሱ የሚያውቁአት የአገልጋይ ሚስት ከነበራት ባሕርይ፣ ተግባርና አገልግሎት ይሆናል። በአብዛኛው ከዚህ በፊት በዚያች አጥቢያ ቤተክርስቲያን ባስትዳር የነበረ አገልጋይ ካለ የአርሱን ሚስት ሁኔታ የሚወዱ ከሆኑ አዲስ የመጣችም አገልጋይ ሚስት እንደ ቀድሞዋ እንድትሆንላቸው ይፈልጋሉ። የቀደመችውን የማይወዱ ከሆኑ ደግሞ ይህች አዲስዋ የአገልጋይ ሚስት ደግሞ መልካም ነገር እንደምታደርግላቸው በማሰብ ምኞታቸውን ይናገራሉ። የአገልጋይ ሚስት ለዎች ከእርስዋ የሚጠብቁትን ነገር ሲነግሩአት የቀደመችውን የአገልጋይ ሚስት ከመተቸት ይልቅ ከእርስዋ ስህተት በመማር መልካም የሆነውን ነገር ለማድረግ ብትዘጋጅ የተሻለ ለውጥ ማምጣት ትችላለች።

ሌሎች ደግሞ በቤተክርስቲያን ውስጥ ካላቸው ጉድለት አኳያ የአገልጋይ ሚስት የአጥቢያይቷን ክፍተት እንድትሞላ በማሰብ እንዲህ ብትሆን ወይም ብታደርግ ብለው ይናገራሉ። ለምሳሌ የልጆች ሰንበት ትምህርት አስተባባሪ፣ የሴቶች አገልግሎት አስተባባሪ እና የመሳሰሉት የአገልግሎት ክፍተቶች ሲኖሩ እርስዋ ይህን ክፍተት እንድትሸፍንላቸው ይፈልጋሉ። የአገልጋይ ሚስት እግዚአብሔር በሰጣት ስጦታ አንጻር እንጂ በአጥቢያ ያለውን የአገልግሎት ክፍተት ለመሙላት ብቻ ከገባችበት መልካም አይሆንም። ምክንያቱም ፍሬያማ የሆነ አገልግሎት መስጠት ስለማትችልና ከዚህም የተነሳ ምዕመናን ስለአገልግሎትዋ በሚኖራቸው አመለካከት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያመጣል። አርስዋም የልብ መነሳሳት ሳይኖራት በግፊት የገባችበት አገልግሎት ስለሚሆን እርካታና ደስታ ላታገኝበት ትችላለች።

ሰዎች በለአገልጋይ ሚስት ያላቸው አመለካከትና አስተሳሰብ ሁሉ ትክክል ወይም ተጨባጭ ነው ማለት አይቻልም። አንዳንዶች የአገልጋይ ሚስት ማለት ፍጹም ሴት እንደሆነች በማሰብ በሁሉ ነገር ከእርስዋ ፍጹምነትን ይጠብቃሉ። የአገልጋይ ሚስት ደግሞ ለዎች ለእርስዋ ያላቸውን ግምት ማሟላት አትችልም። እንዴት ፍጹም መሆን ትችላለች?



ይህ ግምት የአገልጋይ ሚስት የለዎችን ግምት ለማሟላት መሆን ከምትችለው በላይ ለመሆን ጥረት እንድታደርግ ያደርጋታል። በዚህ ፈተና ውስጥ ከገባች ደግሞ ፍጹም ለመሆን ስለማትችል የውስጥዋን ደብቃ አስመሳይ መሆን ትጀምራለች። ይህ ደግሞ የበለደኛነት ስሜት እንዲሰማት ያደርጋታል። ያልሆነችውን እንደሆነች አድርጋ ራስዋን ስለምታቀርብ ሕሊናዋ ይወቅሳታል። ካልሆነ ደግሞ ከብዙ መከራ በኋላ መጨረሻ ላይ አለመቻልዋን መረዳትዋ አይቀርም።

የለዎችን ግምት ማሟላት እንደማትችል ከመጀመሪያው በማወቅ ትክክለኛ ማንነትዋን ለለዎች ማሳየት መቻል መልካም አማራጭ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ ለዎች የተለያዩ ስለሆኑ እያንዳንዱ ምዕመን ከአገልጋይ ሚስት የሚጠብቀው ነገር የተለያየ ነው። ስለዚህ የሰዎችን ግምት ለመድረስና እነርሱን ለማስደሰት ከመጣር ይልቅ በጌታ ፊት ግልጽነት ባለው ሕይወት በመኖር ለሰዎች የሆኑትን ሆነው መቅረብ የተሻለ ነው።

የአገልጋይ ሚስት ስኬት የምታገኘው ሰዎችን ለማስደሰት በምታደርገው ጥረት መጠን ሳይሆን ራስዋን ለመሆን በምታደርገው ጥረት ነው። ሰዎችን ሁሉ ለማስደሰት ጥረት ማድረግ ለሰዎች ሁሉ መጫወቻ ዕቃ በመሆን የእግዚአብሔርን አሳብ ሳትረዳና ሳታደርግ እንድትቀር ያደርጋታል። የአገልጋይ ሚስት ሰዎችን ሁሉ ማስደሰት ባትችልም እንኳ ሰዎችን ሁሉ በክርስቶስ ፍቅር መውደድና መቀበል መለማመድ ትችላለች። ይህን ደግሞ ለማድረግ በክርስቶስ ፍቅር የተነካችና የተሞላች ልትሆን ይገባታል። በዚህም መልክ በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን የተለያየ ባሕርይ ያላቸውን ሰዎች መውደድና እንደማንነታቸው ለመቻል ጸጋ ይኖራታል።

### የአገልጋይ ሚስት ተግዳሮቶች

የአገልጋይ የትዳር ጓደኛ መሆን መልካም ነገር እንዳለው ሁሉ ተግዳሮትም አለው። በመልካም ጎን ሲታሰብ እግዚአብሔርን ከሚያገለግል ሰው ጋር ተጣምሮ ከእርሱ ጋር እግዚአብሔርን ለማገልገል ዕድል ማግኘት መታደል ነው። አገልጋይና የትዳር ጓደኛው ባልና ሚስት ሆነው በትዳር ከመጣመር አልፎ በእግዚአብሔር አገልግሎት እንደ አገልጋይም ይጣመራሉ። ይህ ደግሞ የሕይወት ዓላማቸው አንድ እንዲሆን ስለሚያደርግ ሁለቱን የበለጠ ሊያቀራርብ ይችላል።

የአገልጋይ ሚስት ለብቸኝነት ስሜት የተጋለጠች ናት። የብቸኝነት መንስኤዎች የተለያዩ ናቸው። የመጀመሪያው ባልዋ ከሚያገለግልበት አጥቢያ ቤተክርስቲያን መልካም ጓደኛ ማግኘት አለመቻል ነው። እንደ ሌሎች ሚስቶች ከሌሎች ሴቶች ጋር ግንኙነት ለማድረግና ጓደኝነት መመሥረት ቀላል አይደለም። የምታገለግላቸው ሴቶች ቢኖሩም ከእነርሱ ጋር የሚገናኙት በአገልግሎት ስለሆነ የቅርብ ጓደኝነት መመሥረት ይከብዳታል። ሴቶቹም ለእርስዋ ያላቸው ግምት ከአነርሱ ጋር በነጻነት በጓደኝነት ደረጃ እንዳትቀርብ ያደርጋታል። ሴቶቹም የልባቸውን ለአርስዋ ለመናገር ሊፈርዋት ይችላሉ። በስንት መከራ ጓደኛ ከመሠረተች በኋላ ደግሞ የአገልጋይ ቤተሰብ በአገልግሎት ምክንያት ወደ ሌላ ሥፍራ ሲሄድ ወይም ሌላኛው ቤተሰብ ወደ ሌላ ሥፍራ ሲሄድ ሲለያዩ ይታያል።

ሌሎች መንስኤዎች ደግሞ ባልዋ አገልግሎቱን ምሥጢራዊ በማድረግ ስለሚያገለግለው አገልግሎት ለእርስዋ የማይነግራትና እርስዋ ለአገልግሎቱ ባይታወር መሆን፣ ባልዋ ከሚያገለግላቸው ምዕመናን ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመመሥረት ሚስቱን ከረሳት ወይም ከእርስዋ ጋር ያለው የስሜት መጣበቀ እየላለ መሄድ፣ እንደ አገልጋይ ሚስትነትዋ ከምዕመናን ነቀፋና ትችት የሚበዛባት መሆን፣ ባልዋን ከመደገፍና ከእርሱ ጋር አብራው ከማገልገል ይልቅ በፉክክር መንፈስ ውስጥ ገብታ መቅናት መጀመር እና የመሳሰሉት ነገሮች ሊታዩ ይችላሉ።

የቤተሰብንም ኃላፊነት በከፍተኛ ደረጃ የምትሸከመው የአገልጋይ ሚስት ናት። አገልጋይ በአገልግሎት ምክንያት ከቤት ውጭ በሚሆንበት ጊዜ ቤተሰብን መምራትና ልጆችን ማሳደግ የእርስዋ ኃላፊነት ይሆናል። በተለይ የአገልጋይ የኑሮ ደረጃ ዝቅተኛ በሆነበት አካባቢ የአገልጋይ ሚስት የቤት ውስጥ ሥራ በመሥራት ብቻ ሳይሆን ለኑሮ በማሰብ የምትጨነቀው ጭንቀት ከፍተኛ ነው። ባልዋ አገልግሎቱን ተው እንዳትለው በእግዚአብሔር ፊት ቃል ገብተው ተቀብለዋል። የኑሮው ችግር ደግሞ እንዳለ አለ። የአገልጋይ ሚስት እንደማንኛውም ሰው «እግዚአብሔር ሆይ ለምን ይህ ሆነ?» ትላለች። ነገር ግን በልብዋ እንጂ ለሰዎች አውጥታ አትናገርም። ምክንያቱም እንዲህ ማለት ከእርስዋ አይጠበቅም። ስለዚህ ችግርዋን በልብዋ ተሸክማ ከውጭ ለላማዊ ሚስት መስላ ትኖራለች፣ ከዚህ የበለጠ ብቸኝነት ምን አለ?

የአገልጋይ ሚስት ከሌሎች ሚስቶች የበለጠ በሰዎች መካድን ትለማመዳለች። እንደ አገልጋይ ሚስት ሰዎችን ማመንና ማገልገል ስለሚጠበቅባት ለሰዎች ተገቢውን አገልግሎት ትሰጣለች። ለሰዎች ዋጋ በመክፈል ካገለገለች በኋላ ከተገልጋዮቹ የምታገኘው ብድራት ለእንድ መልካም ላደረገ ሰው የሚገባ ሳይሆን ለጠላት የሚሰጥ ምላሽ ይሆናል። በዚህም ልብዋ ይሰበራል። ወዳጆች ናቸው ብላ የያዘቻቸው ሰዎች ሳይታወቅ ከቁም ነገር በማይገቡ ነገሮች ሊከሰዋት ወይም ስምዋን ሊያጠፉ እንዲሁም ሊክዱዋት ይችላሉ። ጮሌዎቹ ደግሞ የእርስዋን መንፈሳዊነት በመጠቀም የራሳቸውን ጥቅም ለማግኘት እንደ መሣሪያ ሊጠቀሙባት ይችላሉ። ከእነዚህ ሰዎች ጋር በሰላም ለመኖር እርቅ እንዲደረግ ብትፈልግ እንኳ ፈቃደኞች ባለመሆን ስሜትዋ እንዲጎዳ ያደርጋሉ። የአገልጋይ ሚስት የማይከዳ መልካም ጓደኛ ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ በማሰብ ከሰዎች ጋር በበጎ ሕሊና ለመኖር ጥረት ካላደረገች ከአገልግሎት እንድትወጣ የሚያደርጉ ብዙ ጉዳዮች ይኖራሉ።

በምዕራፍ አንድ ውስጥ ምዕመናን የአገልጋይን ቤት እንደራሳቸው ቤት በመቁጠር ቤተሰቡ የግል ጊዜ እንዳይኖራቸው እንቅፋት እንደሚሆኑ ተመልክተናል። ይህ ሁኔታ ወሰን እንዲኖረው ማድረግ መልካም ቢሆንም የአገልጋይ ቤተሰብ በተለይም የግል ሕይወት እንዲኖራቸው የምትፈልገው ሚስት ዋጋ መክፈልዋ አይቀርም። ምዕመናን የአገልጋይ ቤተሰብ የግል ሕይወታቸው ውስጥ ጣልቃ የሚገቡባቸው መንገዶች፡-

- ✓ በተለይ ችግር ውስጥ የወደቁ ምዕመናን ሌሊት እነርሱ በእንቅልፍ ላይ እያሉ የስልክ ጥሪ ያደርጉላቸዋል። አገልጋዩና ቤተሰቡ በእንቅልፍ ላይ ስለሚሆኑ ከምንረብሻቸው እስኪነጋ ድረስ እንጠብቅ ብለው ሳያስቡ ይጠሩታል።



- ✓ እራት ለመብላት ወይም ለመተኛት ዝግጅት እያደረጉ አንዱ የቤተክርስቲያን መሪ ወይም ሽማግሌ ስልክ ደውሎ ለብዙ ደቂቃዎች ወይም ለሰዓት ያወራል። በፊታቸው የቀረበ ምግብ ካለ ምግቡን እያዩ እጃቸው ይደርቃል ወይም ባልዋ ስልክ እያነጋገረ ብሉ ብሎ በምልክት ያሳያቸዋል። ይህ ለሚስት ፈተና ነው።
- ✓ ቤተሰብ አንድ ፕሮግራም ኖሮአቸው አገልጋይ ዕረፍት ለመውጣት ሊጠይቅ «አሁን እንዲህ ዓይነት አገልግሎት ወይም ጉዳይ ስለሚኖር ወደፊት ብትወጣ ምን ይመስላል?» ይባላል። ይህ በማንኛውም መሥሪያ ቤት ሊያጋጥም የሚችል ጉዳይ ቢሆንም በቤተክርስቲያን ጎልቶ ይታያል።
- ✓ በበዓላት ቀናት አገልጋይ ከምንጊዜውም በላይ በአገልግሎት በጣም ስለሚወጠር ከቤተሰቡ ጋር ለማሳለፍ ይቸገራል። የባል በአገልግሎት መጠመድና ለሚስቱ ምቹ አለመሆን በመካከላቸው ለግጭት መፈጠር ምክንያት ይሆናል። በዓል በመጣ ቁጥር ሚስት «እስቲ ዘንድሮ በዓልን አንድ ላይ እንድናከብር ፕሮግራም አትያዝ» ትለዋለች። ሆኖም ከአቅም በላይ በሆነ መልኩ የተለመደው ነገር ይደገማል።

ስለዚህ የአገልጋይ ሚስት እነዚህን ሁኔታዎች እንዴት ማስተናገድ ይጠበቅባታል? አገልግሎት የግል ወይም የቤተሰብ ምኞት የሚያሳጣና ዋጋ የሚያስከፍል ሥራ መሆኑን በማመን በተቻለ መጠን መታገስና መቻል መልካም ነው። ከዚህም ባሻገር የቤተሰብን ፕሮግራሞች በዓልም ቢሆን በተለዋጭ ቀናት ማድረግ የተሻለ መፍትሔ ነው።

አገልግሎት በአገልጋይ ሚስት ላይ የሚያመጣቸው ሌሎች ተግዳሮቶችም አሉ። ከእነዚህም በቤተክርስቲያን ከሚገኙ ሴቶች መካከል መልካም ጓደኛ ማጣት፣ የኢኮኖሚ ችግር (ለአገልጋይ ከቤተክርስቲያን የሚሰጠው ቀለብ ቤተሰብን ማስተዳደር አለመቻል)፣ የአንዳንድ ኃይለኛ ሴቶች ባልዋን እንደሚፈልጉት ማሽከርከርና የጥገኝነት ስሜት በተጨማሪ ይጠቀሳሉ።

### የአገልጋይ ሚስት ተግዳሮቶችን የምትቋቋምባቸው መንገዶች

የአገልጋይ ሚስት የባልዋን ጥሪ እንደ ራስዋ ጥሪ አድርጋ ከተቀበለችና ከእርሱ ጋር በአገልግሎት ከተሰለፈች አንድ የሕይወት ዓላማ ይኖራታል። «ምን ልሁን?» «ምን ልሥራ?» በማለት ግራ መጋባት ውስጥ አትገባም። የሕይወት ዋጋ ቢስነት ሳይሰማት ከባልዋ ጋር እግዚአብሔርን በማገልገል ትርጉም ያለው ሕይወት መምራት ትችላለች። ይህ ግንዛቤ ግን በቀላሉ የሚገኝ ሳይሆን «የአገልጋይ ሚስት በመሆኔ እግዚአብሔር በሕይወቴ መሥራት የሚፈልገው ነገር ምንድነው?» በማለት በመጠየቅና የእርሱን ፈቃድ ለማወቅ ጥረት ካደረገች በኋላ ነው። እግዚአብሔር በሕይወትዋ ያለውን ዓላማ ከተረዳች ግን ለአንድ ዓላማ ራስዋን በመስጠት ትኖራለች። በሕይወትዋ ዘመን ማድረግ የሚገባትን አንድ ነገር ማወቅና ለዚያ ራስን መስጠት ለሕይወት ትርጉም ከመስጠቱም ባሻገር ዓላማው ለኬታማ እንዲሆን የራሱ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በአገልግሎት ውስጥ ሰዎች በእግዚአብሔር መገኘት ተነክተው ሕይወታቸው ሊለወጥና ሊታደስ ማየት ያስደስታል። እግዚአብሔር

ተገቢውን እገዛ ለእርሱ ማድረግ ይጠበቅባታል። የአገልጋይ ሚስት እንደ ሌሎች ሚስቶች ሁሉ መልካም ሚስት ለባልዋ ማድረግ የሚገባትን ነገሮች ሁሉ ታደርጋለች። ከአገልግሎት ጋር በተያያዘ መልኩ ግን እንደ ጓደኛ ለእርሱ ማድረግ ከምትችላቸው ነገሮች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፡-

**የባልዋን አገልግሎት በመቀበልና በማክበር፡-** የአገልጋይ ሚስት እንደ ትዳር ጓደኛ የባልዋን አገልግሎት ከተቀበለችና ካከበረች ከእርሱ ጋር መልካም ግንኙነት ከመመሥረትም አልፎ እርሱ አገልግሎቱን በሚገባ እንዲያከናውን ድጋፍ ትሆነዋለች። አገልጋይ እንደማንኛውም ባል ሥራውን/አገልግሎቱን/ ይወዳል። ከዚህም የተነሳ ብዙ ጊዜውን ለአገልግሎቱ ይሰጣል። አገልጋዩ ከአገልግሎቱ ጋር በጣም ሊጣበቅ ደስ ይለዋል፣ እርካታ ያገኛል። ሚስት ማንኛውም ባል ሥራውን እንደሚወድ ሁሉ አገልጋይ የሆነ ባልም አገልግሎቱን እንደሚወድ ማወቅዋ በመካከላቸው ግጭት እንዳይፈጠር ይከላከላል። ከዚህ አልፎ እርሱ ለአገልግሎቱ በቂ ጊዜ በመስጠት መሥራት ስለሚችል ስኬታማ ይሆናል።

አገልጋይ በአገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን ሚስት እንደ ትዳር ጓደኛው እርሱንና አገልግሎቱን በመቀበል የተቻላትን ድጋፍ ሁሉ ስታደርግ እርሱ የበለጠ ደስተኛና ፍሬያማ ይሆናል። አገልጋይ እግዚአብሔር መሣሪያው አድርጎ የሚጠቀምበትና ኃይሉን የሚገልጥበት መሆኑን ለእርሱ ቅርብ ከሆኑ ሰዎች በተለይም ከሚስቱ ሲሰማ ነፍሱ በሐሴት ትሞላለች፣ እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠውንም ስጦታ በከፍተኛ ደረጃ ያወጣል። በአገልግሎቱ ፍሬያማ መሆኑ ደግሞ ደስተኛ አገልጋይ ብቻ ሳይሆን ደስተኛ ባልና አባት እንዲሆን ያደርጓል። ስለዚህ የባልን አገልግሎት መደገፍ በተዘዋዋሪ መንገድ ትዳርን አስደሳች ለማድረግ መሥራት ነው።

**ለአገልጋዩ መጸለይ፡-** ለባሏ የአገልግሎት ስኬት በእግዚአብሔር ፊት በመጸለይ በመንፈስ ከእርሱ ጋር በመቆም የእርሱን አገልግሎት በመደገፍ ፍሬያማ አገልግሎት እንዲሰጥ የበኩልዋን ድርሻ ታበረክታለች። አገልጋይ የሚያገለግላቸው ብዙ ሰዎች ቢኖሩትም ለእርሱ አገልግሎት ስኬት የሚጸልዩ ግን ጥቂት ሰዎች ናቸው። በለዚህ የአገልጋይ ሚስት በዚህ ክፍተት ብትቆም የአገልግሎቱ ፍሬ የሁለቱም ይሆናል። ባልዋን በጸሎት በመደገፍዋም ከጌታ ዘንድ በሰዎች ዘንድ ያልተጠበቀ እጅግ ታላቅ ብድራት ይኖራታል።

**የአገልጋዩን ደካማ ጎን በመሸፈን፡-** የአገልጋይ ሚስት በባሏ ደካማ ጎን በኩል በመቆም ለእርሱ ያላትን ወዳጅነት ትገልጻለች። አገልጋይ በብዙ ሰዎች ዘንድ ሊታወቅና ብዙ ሰዎች የእርሱ ወዳጆች ሊመስሉ ይችላሉ። ሆኖም እንደ አገልጋይ ያለ «ብቸኛ» ሰው የለም። ብዙዎች በእርሱ ፊት ስለእርሱ መልካም ነገሮች ይነግሩታል። የእርሱን ደካማ ጎን በመንገር ወንድም «ይህችን ነገር ብታስተካክል በተሻለ ሁኔታ ጌታን ማገልገል ትችላለህ» የሚለው አይገኝም፣ ቢገኝም አልፎ አልፎ ነው። የአገልጋይን ደካማ ጎን በትክክል ማወቅ የምትችል ሚስት ስለሆነች ሚስት መልካምና ትክክለኛ የሆነ ሂስ ለእርሱ በመስጠት ስህተቱን በማረም አሁን ካለበት የተሻለ አገልጋይ በመሆን መልካም አገልግሎት መስጠት እንዲችል ማድረግ ይጠበቅባታል።



የአገልጋይ ሚስት ለባልዋ ገንቢ ሂስ በምትሰጥበት ጊዜ ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ካላደረገች ግንኙነታቸውን ሊያበላሽ ይችላል። ሚስት ሂስ ለመስጠት በምታስብበት ወቅት የሚከተሉትን ነጥቦች ማስተዋል ይኖርባታል።

- ✓ አገልጋዩ በቂ እረፍት እንዳገኘ ማረጋገጥ
- ✓ ሌሎች ሰዎች በአካባቢ አለመኖራቸውንና ለመነጋገር በቂ ጊዜ መኖሩን ማወቅ
- ✓ መልካም የሆኑ ወይም የአገልጋዩን ጠንካራ ጎኖች በማስቀደም መጀመር
- ✓ በአንድ ጊዜ ከአንድ ነጥብ በላይ አለመንሳት፣ ሌሎች የሚነሱ ጉዳዮች ካሉ ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍና ሁኔታዎች ሲመቻቹ መነጋገር
- ✓ ሂስን በፍቅር፣ በትሕትና በጨዋነት መንፈስ ማቅረብ

**የቤተክርስቲያንን ምስጢር በመጠበቅ፡-** የአገልጋይ ሚስት የሰዎችንና የቤተክርስቲያንን ምሥጢር በመጠበቅ ታማኝ ልትሆን ይገባታል። ባል ለሚስቱ ምሥጢር ሊያካፍላት ወይም አብረው በሚያገለግሉበት ወቅት የሰዎችን ገመና እንዲሁም በምሥጢር ሊያዝ የሚገባውን የቤተክርስቲያን ነገር በመጠበቅ ታማኝነቷን ማሳየት ይኖርበታል። አንዳንድ የአገልጋይ ሚስቶች ምሥጢርን በማውጣት የባሎቻቸውን አገልግሎት ሲያበላሹ ይታያል። ምሥጢር በመጠበቅ የአገልጋይን አገልግሎት የማታስነቅፍ ሚስት እርሷ እውነተኛ ወዳጅ ነች። አገልጋይ የልቡን አሳብ ለሚስቱ ለማካፈል «ምሥጢር ቢታወጣስ?» ብሎ የማይፈራት የትዳር ጓደኛ እርሷ የእግዚአብሔር ሥጦታ ነች። አገልጋይ ምን ያህል የቤተክርስቲያንን ምስጢር ለሚስቱ መንገር አለበት? የቤተክርስቲያን ምሥጢር የሚባለውስ ምንድነው? ይህን እያንዳንዱ ባለትዳር የሆነ አገልጋይ እንደ ዓውዱ ሊመልሰው የሚገባ ጥያቄ ነው። ከትዳር ጓደኛ የሚደበቅ ምስጢር ምናልባት የግለሰቦች የግል ታሪክ ካልሆነ በስተቀር ምን መደበቅ እንዳለበት ወጥ የሆነ መመሪያ ማውጣት ያዳግታል።

**በአገልጋዩ በመጠንቀቅ፡-** የአገልጋይ ሚስት ባልዋ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመራ ካህን እንደሆነ ከተረዳች ለባልዋ ሁለንተናዊ ሕይወት በተለይም መንፈሱንና ስሜቱን ሊረብሽ የሚችል ነገር በእርስዋ በኩል ወደ እርሱ እንዳይመጣ ትከላከላለች። አገልጋይን ማሳዘን ወይም መጉዳት ማለት እርሱ የሚያገለግላቸውን ሰዎች ማሳዘን ወይም መጉዳት ማለት ነው። አገልጋይ ከቤት ልቡ አዝኖ ከወጣ አገልግሎቱን በሚገባ ማገልገል አይችልም። እርሱን የሚያዩ ሰዎችም ከፊቱ የሚያነቡት ሐዘንን ነው። ከሚስቱ በኩል በሕይወቱ ላይ የተደረጉ መልካም ያልሆኑ ነገሮች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በአገልግሎቱ ላይ ይንጸባረቃሉ። ስለዚህ የአገልጋይ ሚስት መንጋውን እንደምትጎዳ በማሰብ ለአገልጋዩ በተቻለ መጠን ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባታል። ይህ ግን ከባልዋ ጋር ጥበብና ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ አለመግባባቶችን መያዝ እንዳለባት ለማሳሰብ እንጂ በውስጥዋ ምንም መልካም ያልሆነ ነገር ሊሰማት አይገባም ማለት አይደለም።

የአገልጋይ ሚስት ባልዋ የተሻለ ግንዛቤ ለማግኘት በሚፈልግበት ጉዳይ ላይ ከእርሱ ጋር በመነጋገርና አሳብ በመስጠት እርሱን ማገዝ ትችላለች።

ኃይል ቀላል አይደለም። ስለዚህ አገልጋይ ተመጣጣኝ ምግብ ማግኘት ይኖርበታል። ይህ በኢኮኖሚ አቅም ላይ የተመሠረተ ቢሆንም አቅም በፈቀደ መጠን ተመጣጣኝ ምግብ ማዘጋጀት ይቻላል። የአገልጋይ ሚስት ለባልዋ በማሰብ ተመጣጣኝ ምግብ እንዲሁም አገልጋዩ የሚወደውን ምግብ የምታዘጋጅለት ከሆነ ምግቡን በሚገባ ከመብላቱም በላይ ሚስቱ ለእርሱ በማሰብዋ ደስ ይለዋል፣ ለእርሰዋም ያለው ፍቅር እያደገ ይሄዳል።

በአጠቃላይ የአገልጋይ ሚስት ቤትዋን በጥበብ በመያዝ ባልዋን ማስደሰት ትችላለች። ቤተሰብዋን እንደ መልካምና ትጉ ሚስት በማቀናጀት በመልካም ሥራዋ ብርሃንዋ ለባልዋ እንዲሁም ለሌሎች ሰዎች እንዲታይ የማድረግ ዕድል አላት። እቤት በምትሆንበት ጊዜ ባልዋን በብዙ መንገዶች ማገዝ ትችላለች። ከእነዚህ መንገዶች ቤትዋን በንጽሕና መያዝ፣ አቅም በፈቀደ መጠን ተመጣጣኝ ምግብ በማዘጋጀት፣ገንቢ የሆነ ጫወታ/ንግግር/ ከእርሱ ጋር በማድረግ፣ ራሱን ሊጎዳው የሚችል የአመጋገብ ሥርዓት ካለው ራሱን እንዲገዛ በመምከርና በመሳሰሉት መርዳት ትችላለች።

### 3. የአገልጋይ ሚስት በቤተክርስቲያን

የአገልጋይ ሚስት በቤተክርስቲያን ሊኖራት ስለሚገባው ሚና ሁለት ዓይነት አመለካከቶች ይታያሉ። የመጀመሪያው የአገልጋይ ሚስት ከበስተጀርባ ሆና አገልግሎቱን መደገፍ የሚል ሲሆን በዚህም አሳብ የአገልጋይ ሚስት ዋና ተግባርዋ ቤተሰብን በመንከባከብና እርሱን አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች መደገፍ ነው። የአገልጋይ ሚስት ይህን ከተቀበለች በአብዛኛው ሥራዋ በአገልጋዩ ፍሬያማነት እንጂ በቀጥታ አይታይም። ይህን አመለካከት የተቀበሉ የአገልጋይ ሚስቶች ወይም ይህ አመለካከት በነገሠበት ቤተክርስቲያናት ውስጥ የሚያገለግሉ አገልጋይ ሚስቶች ባሎቻቸው ለአገልግሎት ሲሾሙ እንኳ ከእነርሱ ጋር ሆነው «መሾምን» አይፈልጉም።

ይህ አመለካከት የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎን አለው። ጠንካራ ጎኑ የአገልጋይ ሚስት የባልዋ ደጀን በመሆን ለአገልግሎቱ ስኬት አስፈላጊ የሆነውን ነገር ታደርግለታለች። የእርስዋ ሥራ በአደባባይ ባይታይም ቤተሰብን በመንከባከብና ሌሎች ኃላፊነቶችን በመሸከም አገልጋዩ ትኩረቱን በአገልግሎቱ ላይ እንዲያደርግ ታደርጋለች። በዚህ መልኩ የአገልጋይ ሚስት በቤተክርስቲያን ውስጥ እንደ አገልጋይ ሳይሆን እንደ አገልጋይ ሚስት ትታያለች። በፊት ለፊት የማትታይ የባልዋ ኃይል ነች። የዚህ አመለካከት ደካማ ጎን ደግሞ ሚስት እግዚአብሔር በውስጥዋ ያስቀመጠውን ስጦታ እንዳትገልጥ እንቅፋት ይሆናል። ከዚህ አመለካከት ሥር ሴቶች በአገልግሎት አደባባይ መውጣት አይገባቸውም የሚል ሥነመለኮታዊና ባሕላዊ ግንዛቤ እንዳለ ማስተዋል ይቻላል።

ሁለተኛው አመለካከት ደግሞ የአገልጋይ ሚስት በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሔር በሰጣት ጸጋ ከእርሱ ጋር ሆና ማገልገል አለባት የሚል ነው። አገልጋይ ለአገልግሎት ሲጠራ ሚስቱም አብራ እንደተጠራች ይታሰባል። ምንም እንኳ ለእርስዋ ቀለብ ባይሰፈርላትም በቤተክርስቲያን አገልግሎት ውስጥ በትጋት እንድትሳተፍ ይጠበቃል። የአገልጋይ ሚስት በተለያዩ መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ላይ የማትገኝና የማትካፈል ወይም የማታገለግል ከሆነች ሌሎች ሴቶች «እርስዋ ለምንድነው ፕሮግራም የማትመጣው ወይም የማታገለግለው?» እያሉ ይጠይቃሉ።



በመንፈሳዊ አገልግሎቶች ውስጥ በተሳትፎም ይሁን በማገልገል የአገልጋይ ሚስት አለመገኘት አንዳንዶችን ቅር ያሰኛቸዋል። ይህም ሚዛኑን ካልጠበቀ ማለትም የአገልጋይ ሚስት በቤተክርስቲያን አገልግሎት በብዛት ከተጠመደች ማን ለቤተሰባቸው ተገቢውን እንክብካቤ መስጠት ይችላል? የሚል ጥያቄን ያስነሳል። ስለዚህ ቤተሰብም ሳይጎዳ አስፈላጊ በሆኑት የቤተክርስቲያን አገልግሎቶች ውስጥ ደግሞ በመሳተፍ የበኩልዋን ድርሻ ማበርከት ትችላለች።

የአገልጋይ ሚስት ባልዋ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን አባል የሆነችና መልካም ኅብረት ያላት መሆን ይኖርባታል። የአገልጋይ ሚስት ከባሏ ጋር እንድታገለግል በቤተክርስቲያን ካልተጠራች በስተቀር በቤተክርስቲያን ብዙ ኃላፊነት ውስጥ ባትገባ ይመረጣል። ምክንያቱም ለቤተሰብ ያላትን ጊዜ ሊወስድባት ስለሚችልና አንዳንድ ጊዜ ብዙ ኃላፊነቶችን ከያዘች ባልዋና እርሷ የቤተክርስቲያንን ኃላፊነቶች እንደተቆጣጠሩ ተደርጎ ሊታሰብ ስለሚችል ነው። አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በቅንነት ለእግዚአብሔር ብለው በትጋት ሲያገለግሉ የሚሰጣቸው ትርጉም አሉታዊ ሊሆን ስለሚችል ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ ማገልገል ያስፈልጋታል።

የአገልጋይ ሚስት በቤተክርስቲያን በምን መልክ ማገልገል እንዳለባት እርሷ ያለችበት ዓውድ ሊወስን ቢችልም የሚከተሉትን አሳቦች እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል። እነርሱም፦

ለሴቶች መልካም ምሳሌ መሆን፦ በቤተሰቧ መልካም ሚስትና ጥሩ እናት በመሆን በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚገኙ ሴቶች ጥሩ ምሳሌ በመሆን እነርሱን በተግባር ማስተማር ትችላለች። መልካም ሚስት መሆን እንዴት እንደሚቻል በምትኖረው ኑሮ በማሳየት ወደ እግዚአብሔር አሳብ ልትመራቸው ሰፊ ዕድል አላት።

የአገልጋይ ሚስት መልካም ምሳሌ ሊሆን የሚችል ሕይወት ሲኖራት ሰዎች የእርስዋን ሕይወት በማየት አገልጋዩን ያከብሩታል። ሚስቱ መልካም ያልሆነ ሕይወት ካላት ሰዎች ለአገልጋዩ ያላቸው ግምት ይቀንሳል። በሚስቱ ሕይወት ደስ የማይሰኙ ከሆኑ አገልጋዩን ከመናቅም አልፎ አገልግሎቱንም ላለመቀበል ክስ ሲያቀርቡ ይታያሉ። አገልጋይ እንዲከብር ወይም እንዲዋረድ የማድረግ ኃይል ያለው በሚስቱ ሕይወት ዘንድ ነው። በሚስቱ ዘንድ መልካም ነገር ካለ አገልጋይ በአደባባይ ክብር ያገኛል። እርስዋ ግን መልካም ምስክርነት ያለው ሕይወት ከሌላት በአደባባይ ውርደቱን ይከናነባል። ሚስት መልካም ነገር ከሌላት ወይም አንድን መጥፎ ነገር ከሠራች ባልዋ የሆነው አገልጋይ እንዲህ እንድታደርግ እንዳዘዛት ተደርጎ ይቆጠራል።

ይህ የሚያሳየው ምዕመናን የአገልጋይ ሚስትን ሕይወት ምን ያህል እንደሚከታተሉ ያሳያል። በዚህ ሁኔታ የአገልጋይ ሚስት መልካም ሕይወት ቢኖራት በሰዎች ላይ ከፍተኛ በጎ ተጽዕኖ ማሳደር ትችላለች። ከዚህም በተጨማሪ ሚስት ባልዋን ማገዝ ከምትችልባቸው መንገዶች አንዱ መልካም ምስክርነት ያለውን ሕይወት በመኖር እንደሆነ ያሳየናል።

ቃሉን ማስተማር፡- እንደ አስፈላጊነቱና እንደ ችሎታዋ ለልጆች፣ ለወጣቶች ወይም ለአዋቂዎች ማስተማር ትችላለች። በአብዛኛው የአገልጋይ ሚስት እህቶችን በስብከትም ሆነ በትምህርት እንድታገለግል ይፈለጋል። እህቶችም ሕይወትዋን የሚወዱ ሲሆኑ እርስዋ እንድታገለግላቸው ይፈልጋሉ።

ሴቶችን ማማከር፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሴቶች በማማከር ባሏን በሚገባ ማገዝ ትችላለች። በአንዳንድ ሁኔታዎች ሴቶች ምሥጢራቸውን ለወንድ አገልጋይ ከመናገር ይልቅ ለአገልጋይ ሚስት መንገር ይቀላቸዋል። የአገልጋይ ሚስት ሰዎችን ለማማከር የሚያስችል ብቃት ካላት የባሏን አገልግሎት በማማከር በኩል በመደገፍ ከፍተኛ ድርሻ ታበረክታለች።

ከአገልጋዩ ጋር በማገልገል፡- እንደ አስፈላጊነቱ ባሏ ለመጋቢነት ጉብኝት በሚወጣበት ጊዜ ከእርሱ ጋር በመሄድ ማገልገል ትችላለች። አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ ከሚስቱ ጋር በመሆን ጉብኝት ሲያደርግ የበለጠ ማገልገል ይችላል። ለምሳሌ አዲስ ጋብቻ የመሠረቱ ባልና ሚስት ሲጎበኝ፣ ወጣቶችንና ያላገቡ ሴቶችን ሲጎበኝ፣ አገልጋይ እንዲጎበኛቸው ጥያቄ የሚያቀርቡ ተቃራኒ ጾታዎች ሲኖሩ አገልጋይ ከሚስቱ ጋር ቢጎበኛቸው ለአገልግሎት ስኬትና ከፈተና ለመጠበቅ ይረዳል።

ቤተክርስቲያን ባልን ለወንጌል አገልግሎት ስትጠራ ለሚስትም ማሰብ ይጠበቅባታል። ባልና ሚስት እንዴት ቢሰማሩ የበለጠ እግዚአብሔርን ማገልገልና ቤተሰባቸውን በተገቢው ሁኔታ መምራት እንደሚችሉ ማሰብ አስፈላጊ ነው። በሀገራችን ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት በአብዛኛው የተለመደው ባል ወይም ሚስትን ለአገልግሎት መጥራት እንጂ ሁለቱን አንድ ላይ መጥራት አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር አይታይም። ባልና ሚስት አንድ ላይ ለአገልግሎት ቢሠማሩ አንዳቸው ብቻ ከሚጠሩ ይልቅ የተሻለ አገልግሎት መስጠት የሚችሉበት ሁኔታ እንዳለ ቢታወቅና ይህ አሠራር ቢለመድ መልካም እንደሆነ ይታሰባል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባልና ሚስት ሆነው ሲያገለግሉ የነበሩ ጥንዶችን እናገኛለን። ከእነርሱም ውስጥ አቂላና ጵርስቅላ ተጠቃሽ ናቸው። እነዚህ ባልና ሚስት መቼ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳመኑ ባይታወቅም ምናልባት በበዓለ አምሳ ዕለት ኢየሩሳሌም ከነበሩና ወደ ኢጣሊያ ከተመለሱ አይሁዳውያን ወንጌልን ሰምተው አምነው እንደሆነ ይታሰባል።

በሮም ከተማ በተነሳባቸው ስደት ምክንያት ወደ ቆሮንቶስ ከተማ መጥተው ነበር። በዚያም ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር ተገናኙ። ከጳውሎስም ጋር ድንኳን እየሰፉ መንፈሳዊ አገልግሎትን ይሰጡ ነበር (የሐዋ.18:2-3)። ከጳውሎስ ጋርም እየዞሩ ወንጌልን ያበተምሩ ነበር (የሐዋ.18:18)። ከጳውሎስም ሲለዩ አገልግሎታቸውን አላቋረጡም። አጵሎስ የሚባል የወንጌል አስተማሪንም በጌታ ያሳደጉት እነርሱ ነበሩ (የሐዋ.18:26)። በእነርሱም ቤት እየተሰበሰቡ ጌታን የሚያመልኩ ምዕመናን እንደነበሩ እንመለከታለን (1ቆሮ.16:19፣ 2ጢሞ.4:19)።



## አገልጋይ ሚስቱን እንዴት መያዝ አለበት?

አንድ አገልጋይ በአገልግሎቱ ስኬታማ የሚሆነው በቤት ውስጥ እንደ ባል ከትዳር ጓደኛው ጋር መልካም ግንኙነት ሲኖረው ነው። ባል እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው በመሆኑ ለሚስቱም ፍቅር ሲኖረው ይጠበቅበታል። ለሚስቱ ያለው ፍቅር እርሱ ለክርስቶስ ካለው ፍቅር ነው የሚመነጨው። ባል ሚስቱን በሁኔታዎች ላይ ባልተመሠረተ ፍቅር መውደድ የሚችለው እርሱ ራሱ በሁኔታዎች ላይ ያልተመሠረተውን የእግዚአብሔርን ፍቅር በሕይወቱ ከተለማመደ ነው። አገልጋይ በሕይወቱና በአገልግሎቱ ከሚያጋጥመው እንዲሁም በቤት ውስጥ ካለው ኃላፊነትና ጫና አልፎ ሚስቱን መውደድ የሚችለው የእግዚአብሔር ፍቅር በሕይወቱ በሙላት ሲፈስ ነው። እርሱ የሚያገለግለው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእርሱ ያሳየውን በሰው ነፍስ የሚተመነውን ፍቅር ሲረዳ ነው። ይህን ፍቅር በሚገባ ሲረዳ በሕይወቱ በተግባር ለማሳየት የመጀመሪያው ሥፍራ የትዳር ጓደኛውን እንደ ራሱ ነፍስ መውደድ ነው።

ሐዋርያው ጴጥሮስ ባሎች ከሚስቶቻቸው ጋር በማስተዋል እንዲኖሩ ያስተምራቸዋል (1ጴጥ.3:7)። ማንኛውም ክርስቲያን የሆነ ባል ከሚስቱ ጋር በእንዲህ መልኩ መኖር ቢያስፈልግም አገልጋይ ግን ይህን በተግባር በማሳየት ሌሎች ባሎች ምሳሌውን እንዲከተሉ ለማድረግ ከሌሎች በበለጠ ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል። የአገልጋይ ሚስት ብዙ ጫና ያለባት ሴት ስለሆነች እርሷ ያለችበትን ሁኔታ በሚገባ የሚረዳላትን ሰው ትፈልጋለች። እንዲህ ለማድረግ ከባሏ የተሻለ ሰው ማንም የለም። ባል ይህን ማድረጉ ሚስት ባሏ እንደሚወዳት እንድትረዳ ያደርጋታል።

አገልጋይ ሚስቱ በቤተክርስቲያን ወይም በሌሎች ሰዎች ፊት ሞገስ እንድታገኝ ሊረዳት የሚችል ልዩ ችሎታ ባይኖራትም እርሷን የሚያፈቅራትና በውስጧ የተቀመጠውን እምቅ ችሎታዋን እንድታወጣና እንድትጠቀምበት የሚያበረታታት ሲሆን ይገባል። ፍቅር ደካማውን በመንከባከብና በመኮትኮት ወደ ተሻለ ሁኔታ እንዲያደግ የማድረግ ችሎታ አለው። በሕይወቷ ውስጥ ያለው ጸጋ የሚለቀቀው ባሏ ሲወዳትና ሲረዳት ነው። ስለዚህ አገልጋይ ሚስቱን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለመቀበል ዘወትር ራሱን ማዘጋጀትና ማለስለስ ይኖርበታል።

እንደ አገልጋይ ባል ሚስቱን የእግዚአብሔርን ቃል ማስተማር ይጠበቅበታል። ይህም ከእርስዋ ጋር በሚያደርገው ማንኛውም ግንኙነት ውስጥ በሚነጋገሩበት ወቅትና በሕይወቱ ምሳሌነት ሲሆን ፍሬያማ ይሆናል። በመንፈሳዊ ነገር ብቻ ሳይሆን አገልጋይ እንደ ባል በሥራም ሚስቱን ቢያግዛት የተሻለ ግንኙነት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በቤት ውስጥ ማድረግ የሚችላቸውን ነገሮች መሥራት መልካም ነው። አንድ መጋቢ «በትሕትና በቤት ውስጥ ማድረግ የምችለውን ነገር መሥራት ይገባኛል። አልጋ ማንጠፍ፣ እቤት መወልወልና ልብስ ማጠብ እችላለሁ። ስለዚህ ሚስቴን በዚህ አግዛታለሁ። በተለይ ሠራተኛ እቤት በማትኖርበት ወቅት ይህን አደርጋለሁ» ብሏል። መጋቢ ካህን ቢሆንም እቤቱ ውስጥ ግን ካህን ብቻ ሳይሆን የትዳር ጓደኛ እንደሆነ ካወቀ ለሚስቱ ተገቢውን እገዛ ያደርጋል። መጋቢ ይህን ማድረጉ ደግሞ በሌሎች ባሎች ላይ የሚኖረው በጎ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም።

## አገልጋይ ለሚስቱ ምን ያህል ጊዜ መስጠት አለበት?

በመሠረተ አሳብ ደረጃ ሚስት ከአገልግሎት በፊት መምጣት እንዳለባት ተመልክተናል። አንዳንድ የአገልጋይ ሚስቶች ባሎቻቸው ከአገልግሎት ይልቅ ለእነርሱ ጊዜ እንዲሰጡ መጠየቅ እንደሚያስፈራቸው ይናገራሉ። እንደ ዛሬ አገልግሎት ከመብዛቱ በፊት የእግዚአብሔር ጥሪ ለእርሱ ሲመጣ ባልና ሚስት አንድ ላይ ሆነው እግዚአብሔር እርሱን ለጠራው አገልግሎት በር እንዲከፍትለት በትጋት ሲጸልዩ ኖረው የአገልግሎት በር ተከፍቶ ሲገኝ ደግሞ «ከአገልግሎት ይልቅ ለእኔ ጊዜ ስጠኝ» ብሎ መጠየቅ ተገቢነቱ አይታያቸውም። እነዚህ እህቶች ከባሎቻቸው ጋር ጊዜ ቢያሳልፉ ደስ ይላቸዋል። ነገር ግን ለባሎቻቸው አገልግሎት ሲበዛላቸው የእነርሱን ጊዜ ለራሳቸው መውሰድ እግዚአብሔርን ማሳዘንና አገልግሎትን መበደል እንደሆነ ያስባሉ።

ብዙዎቹ የአገልጋይ ሚስቶች ለአገልጋይ ባሎቻቸው አገልግሎት ሲበዛ ደስ ይላቸዋል። በተለይ አገልግሎቱ ከአጥቢያ ዘለል ሲሆንና ዝናንና ጥቅምን የሚያስገኝ ሲሆን ለአገልግሎቱ አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣሉ። ነገር ግን ከአገልጋይ ባሎቻቸው አንድ የሚፈልጉት ነገር አለ። ይኼውም ባሎቻቸው የአገልግሎታቸውን ዝርዝር ሁኔታ ማለትም የትና መቼ እንዲሁም ምን ዓይነት አገልግሎት እንዳላቸው አስቀድሞ ለእነርሱ እንዲነግሩአቸው ይፈልጋሉ። ባሎቻቸው ዝም ብለው በፈለጉበት ጊዜ የፈለጉበት ቦታ «አገልግሎት አለኝ» ብለው እንዲሄዱ አይፈልጉም። ይህ አገልጋዮች በአጥቢያ ያላቸውን አገልግሎት ዝርዝር ለቤተሰቦቻቸው መናገር እንዲሁም ከአጥቢያ ውጭ የሚመጣላቸውን የአገልግሎት ጥሪ ደግሞ አስቀድሞ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በመነጋገር እንዲይዙ ያሳስባቸዋል። አገልጋዮች በአገልግሎታቸው ውስጥ ቤተሰቦቻቸውን ቢያሳትፉ ቤተሰብ ለአገልግሎታቸው እንቅፋት ከመሆን ይልቅ ድጋፍ ሰጪ ይሆናል። ስለዚህ አገልጋዮች አገልግሎትን እንደ ግል ሥራቸው መውሰድ የለባቸውም። ነገር ግን አገልግሎት የቤተሰቡ ጭምር እንደሆነ በመረዳት ከእነርሱ ጋር በመነጋገር አገልግሎትን ማቀድና መተግበር ፍሬያማነትን ያመጣል።

አገልጋይ ከቤተሰቡ ይልቅ ለአገልግሎት ብዙ ጊዜውን በሚሰጥበትና ቤተሰቡን ችላ በሚልበት ወቅት ሚስት ጥሩ ያልሆነ ስሜት ሲሰማት ይችላል። «ለምንድነው እርሱን ያገባሁት?» «ልጆችን እርሱ ላይ ጥዬ ብሄድስ?» «እንዲያው እግዚአብሔር ባይጠራው ኖሮ!» እያለች በውስጧ ልታጉረመርም ትችላለች። ባሏን ብትወድም አገልግሎትን ግን ወደ መጥላት አዝማሚያ ትመጣለች። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ከገባች ምን ማድረግ ይኖርባታል?

የመጀመሪያው ሚስት ስለአገልግሎት ምንነት መሠረታዊ ግንዛቤ ማግኘት ይኖርባታል። አገልጋይ የአገልግሎት ሰዓቱን በመሰወጥ ለቤተሰብ ጊዜ መስጠት ቢጠበቅበትም መሰወጥ የማይችላቸው መሠረታዊ ሁኔታዎች እንደሚኖሩ ማስተዋል መልካም ነው። ሚስት አገልጋይ የሆነው ባሏ ለቤተሰብ ጊዜ እንዲሰጥ መጠየቅ መብቷ ነው፣ ከእርሱ ጋር በመሆን መወሰን ይችላሉ። ነገር ግን እግዚአብሔርን ማገልገል ብዙጊዜን የሚጠይቅና አድካሚ የሆነ የሥራ መስክ መሆኑ መታወቅ አለበት። ይህ ብቻ ሳይሆን አንዳንድ ጊዜ አገልጋይ የቤተክርስቲያን ንብረት እንደሆነ ይታሰብና ሁሉም እንደ «ዕቃ» ሲጠቀሙበት ይፈልጋሉ። የቤተክርስቲያን



መሪዎችና ምዕመናን አገልጋይ የራሱን ሕይወትና ቤተሰብ በተገቢው ሁኔታ ለመምራት የራሱ ጊዜ ሊኖረው እንደሚገባው እምብዛም የሚገነዘቡ አይመስልም። «አስቸኳይ ጉዳይ አለ» ይባልና ከቤት ተጠርቶ ይወጣል። ከዚያም ከሰዓታት በኋላ ይመለሳል አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ቀናትም ሲቆይ ይችላል። በዚህ ወቅት ለቤተሰብ በተያዘው ፕሮግራም ላይ መገኘት አይችልም።

ስለዚህ የአገልጋይ ሚስት ባሏ የሚያገለግልበትን ዓውድ ማለትም የቤተክርስቲያንን አሠራርና አመለካከት ማጤን ተገቢ ነው። በአንድ ቤተክርስቲያን አንድ አገልጋይ ለሙሉጊዜ የወንጌል አገልግሎት ሲጠራ ሚስቱ ቃል ኪዳን ከምትገባበት ነጥቦች አንዱ «ሰው በሚያስፈልግሽ ጉዳይ ሁሉ ባለቤትሽ ከአቅም በላይ በሆነ አገልግሎት ተጠምዶ በአጠገብሽ ባይገኝ አንዳንዴም የወንጌል አገልግሎት እንዲህ ዓይነት ባሕርይ እንዳለው በመረዳት በእግዚአብሔር ፊት ላለማጉረምረምና ላለመበሳጨት ቃል ትገቢያለሽ?» ይላል።

አንድ ጊዜ አንድ በሙሉጊዜ ሲያገለግል የነበረን አገልጋይ የመጋቢነት ሹመት ለመፈጸም የመጨረሻ ቃለመጠይቅ ለእርሱና ለሚስቱ እንድናደርግ ቤተክርስቲያን ትልከናለች። ከዚያም ከላይ የተጠቀሰውን ጥያቄ ሚስት ስትጠየቅ «አዎን ቃል እገባለሁ» ብላ መለሰች። እኔም በውስጤ በጣም ደነገጥኩና «ጥያቄው በደንብ ገብቶሻል?» ብዬ ጠየቋት። የእኔ ጥያቄ ትንሽ ሁሉንም ግራ አጋባቸው። በውስጣቸው ምን ማለቱ ነው? ቤተክርስቲያን ለላከችው ጥያቄ እንዴት እምቢ ይባላል ወይም ይህ ሰው አዲስ ቢሆን ነው ሳይሉ እንዳልቀሩ እገምታለሁ። ከዚያም ጥያቄው ከአገልግሎትና ከቤተሰብ ማን ይቀድማል ማለት መሰለኝ አልኩኝና ዝም አልኩ። ሚስትም አገልግሎት ከቤተሰብ መቅደም አለበት በማለት ምሳሌዎችን መጥቀስ ጀመረች።

ቤተክርስቲያንም ይህን ጥያቄ ስታወጣው ያሰበችበት አይመስልም። ምክንያቱም «ከአቅም በላይ በሆነ አገልግሎት» የሚለው አሳብ ምን ማለት ነው? አንድ ሰው ከአቅም በላይ ለሆነው ነገርስ እዎንታዊ ምላሽ ለመስጠት እንዴት ቃል ኪዳን ሲገባ ይጠበቅበታል? አንዳንድ አገልጋዮች የእነርሱን መገኘት የሚያስፈልግ የቤተሰብ ጉዳይ እያለ ለአገልግሎት ይሄዳሉ። ለምሳሌ የባለቤታቸው መውለጃ ወራት መቀራቡን እያወቁ እርሰዋን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት ለአገልግሎት ራቅ ወዳለ ሥፍራ ይሄዳሉ። ይህ እንዲሁ ሲታይ የእምነት ነገር ሊመስል ይችላል። በእርግጥ የባል መኖርና አለመኖር ሳይሆን የእግዚአሔብር መገኘት ትልቅ መፍትሔ እንደሚሰጥ የታወቀ ነው። ሆኖም ባል እንዲህ በመሰሉት ወሳኝ ጊዜያት ከሚስቱ ጋር የማይሆን ከሆነ መቼ ነው ከእርስዋ ጋር የሚሆነው? ምናልባት የቸልተኝነት ሥራ እንዳይሆን ያሰፈራል።

ሚስት ከላይ ለተጠየቀው ጥያቄ አዎን ማለት ማድረግ የማትችለውን ነገር ለማድረግ ቃል መግባትዋን ያሳያል። ምክንያቱም ሁኔታው ከአቅምዋ በላይ ሆኖ ሳትበሳጭና ሳታጉረምርም አትቀርም። የገባችሁን ቃል ኪዳን ስታስብ ደግሞ የሕሊና ወቀሳ ይሰማትና ታዝናለች። ስለዚህ ባልዋ በፈታኝ ወቅቶች ከእርስዋ ጋር እንዲሆን እንደምትፈልግ በግልጥ መናገር የተሻለ ነው።

የአገልጋይ ሚስት ትኩረት መሆን ያለበት አገልጋይ በአገልግሎትና ቤተሰብ መካከል ሊኖር የሚገባውን ሚዛን እንዴት መጠበቅ እንደሚችል እርሱን መደገፍና መርዳት እንጂ እግዚአብሔር እንዲያከናውን ከጠራው ታላቅ የወንጌል አገልግሎት ጥሪ ወደኋላ እንዲመለስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ ማድረግ መሆን የለበትም:: በሰዎች ዘንድ ግን አንድ የተሳሳተ ግምት እንዳለ መመልከት ይቻላል:: አገልግሎት ከቤተሰብ ሕይወት መቅደም እንዳለበት የሚያስቡ ምዕመናን ብዙ ናቸው:: ራሳቸውን መንፈሳዊ አድርገው ስለሚቆጥሩ እግዚአብሔርን ማገልገል መንፈሳዊ፣ ነገር ግን ለቤተሰብ ቅድሚያ መስጠት ሥጋዊ መስሎ ይታያቸዋል:: ይህ የእነርሱ አስተሳሰብ እንጂ መንፈሳዊ የሆነው የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረው ትምህርት አይደለም::

ሁለተኛው የአገልጋይ ሚስት የተሰማትን ስሜት መግለጽ የምትችልበት ሁኔታ መፈጠር አለበት:: ስሜት በተገቢው መንገድ ካልተገለጸ ራሷንና ሌሎች ሰዎችን ሊጎዳ በሚችልበት ሁኔታ ሊገለጽ ስለሚችል ለባሏና አገልግሎቱ ያላትን በሜት እንድትገልጽ ማድረጉ መልካም ነው:: ሚስት ስሜቷን መግለጽ አስፈላጊ ቢሆንም ባሏን ከመውቀስና ከመኮነን ይልቅ የተሰማትን ስሜት መግለጽ ብትችል ጥሩ ነው:: ባሏን መውቀስ ለምሳሌ «አንተማ አገልግሎትን እግብተሃል» «ለሌሎች ሰዎች የምታሳየውን ፍቅር ምነው ብታቀምስን?» ብሎ ማለት ባል የእርሷን ስሜት ከማዳመጥ ይልቅ ራሱን መከላከል ይጀምራል:: ስለዚህ ስሜቷን ስትገልጽ ባል በሙሉ ትኩረት እንዲያዳምጣት በሚያስችል መልኩ ቢሆን የተሻለ ይሆናል:: «ሰዎች እንደሚፈልጉህ እኛም አንተን እንፈልጋለን» «ለቤተሰብ ጊዜ በማትሰጥበት ጊዜ ችላ እንደተባልን እሰማናል» «አንተን ፈልገን ሳናገኝህ ስንቀር ቅር ይለናል፣ ስሜታችንም ይጎዳል» ማለት አገልጋዩ ራሱን እንዲመረመር ይረደዋል::

ሦስተኛው አገልጋይ የቤተሰብ ቀናትን በአጀንዳው ላይ እንዲይዝ ማድረግና ሚስት ባሏ በአገልግሎትና ቤተሰብ መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቁን ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ማሳሰብና አብረው ጊዜ በመውሰድ መገምገም ቢችሉ ችግር ከመፈጠሩ በፊት ሁኔታዎችን ቶሎ ማስተካከል ይችላሉ:: ለቤተሰብ የሚሰጠውን ጊዜ ለማሻሻል ተከታታይነት ያለው ግምገማ እጅግ አስፈላጊ ነው::

ቤተሰብ ጤናማ ኅብረት ቢኖራቸው ማለትም ባልና ሚበት በቃልኪዳን ጋብቻ ተሳስረው በፍቅር የሚኖሩ ሊሆኑ እንዲሁም ከልጆቻቸው ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖራቸው ቤተክርስቲያን ደስተኛ ትሆናለች፣ ትርጉም ያለው ኅብረት ይኖራታል:: በባልና ሚስት እንዲሁም ወላጆችና ልጆች መካከል መልካም ግንኙነት ሊኖራቸው ያለምንም መሳሳት ሌሎችን ለማገልገል ራሳቸውን ይሰጣሉ::

<u>ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ</u>

1. *አንድ አገልጋይ የትዳር ጓደኛውን ፈቃድ አምቢ ማለት ያለበት መቼና ለምን ጉዳይ ነው?*
2. *ሰዎች ከትዳር አጋራቸው (ባል ከሚስቱ፣ ሚስትም ከባልዋ) ምን ይጠብቃሉ?*



3. *የትዳር አጋር የአገልጋይን አገልግሎት በሙሉ ልብ እንዲደግፍ/እንድትደግፍ/ ለማድረግ አገልጋይ የሆነው ወገን ምን ማድረግ ይገባል ትላለህ/ሽ?*
4. *ባልና ሚስት አብረው በሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልግሎት ውስጥ ተሠማርተው ቢያገለግሉ ያለው አዎንታዊና አሉታዊ ጎን ምንድነው?*

እንግዲህ አገልጋይ ከሚስቱ ጋር መልካም ግንኙነት ሲኖረዉ አንድ ባል ለሚስቱ ማድረግ የሚጠበቅበትን ሁሉ ካደረገ እንዲሁም አንደ አገልጋይ ተገቢ ሚናውን ከተጫወተና በተለይም ከእርበዋ ጋር በጋራ ለማገልገል በጎ ልብ ካለው ደስተኛ ቤተሰብ ሊኖረው ይችላል:: የቤተሰብ ግንባታ ከሚስት ጋር መልካም ግንኙነት ይጀመራል እንጂ በዚህ አያበቃም:: አገልጋይ ከልጆቹም ጋር እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ግንኙነት በመመሥረት ልጆቹን በመልካም ሥነምግባር እንጾ ማሳደግ ይጠበቅበታል:: ከዚህ ዓላማ አንጻር አንድ አገልጋይ ልጆቹን እንዴት መያዝ እንዳለበት፣ ምዕመናን ከአገልጋይ ልጆች የሚጠብቁአቸው ነገሮች፣ አንዳንድ ጊዜ የአገልጋይ ልጆች ከሌሎች ልጆች ይልቅ ከፉዎች ሆነው ለቤተሰቡ፣ ለቤተክርስቲያንና ለሕብረተሰቡ የሐዘን ምንጭ የሚሆኑባቸው ምክንያቶችንና መከላከል የሚቻልባቸውን መንገዶች በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን::

የቤተክርስቲያን መሪዎች ልጆች ኃጢአት ፈጽመው ሲገኙ ከቤተክርስቲያን እንዳይገለጹ እንደሚደረግ ዓይነት ይሆንን? አባት አገልጋይ ከሆኑ ልጆቹ ክፉ ነገር ሠርተው ኃጢአታቸው በሕዝቡ ሁሉ ዘንድ ቢሰማም ከቤተክርስቲያን ኅብረትና አገልግሎት እንዳይባረሩ ለማድረግ መሸፋፈን ይቻላል።

ነገር ግን የሕያው እግዚአብሔርን ጣልቃ ገብነት ማን መከላከል ይችላል? ዔሊ ልጆቹን ከአገልግሎት ለማባረር ድፍረት ባያገኝም እግዚአብሔር ግን የመገናኛ ድንኳኑን ያረከሱትን የዔሊን ልጆች ለማስወገድ ተነሳ። እግዚአብሔር በዔሊ ልጆች ላይ ፈረደ፣ ከዔሊም ቤት ሰዎችን ለክህነት አገልግሎት እንደማያስነሳ ተናገረ። የዔሊ ልጆች መጨረሻቸው ሞት ሆነ። አባታቸው የልጆቹን መሞት ሲሰማ ወድቆ ሞተ። ካህኑ በእግዚአብሔር የተነቀፈበት ዋናው ጉዳይ የእርሱ ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉና እርግማን የሚያመጣ ነገር እንደሚሠሩ አውቆ አለመከልከሉ ነበር (1ሳሙ 3:13)።

መቼም መልካም አባት ልጆቹን ይወዳል። ለልጆቹ ያለው ፍቅር ደግሞ እነርሱ በእግዚአብሔር ፊት መልካም ያልሆነ ነገር በሚያደርጉበት ጊዜ እንዳይገስጻቸውና እንዳይመልሳቸው የሚያደርግ ከሆነ ለእርሱም ሆነ ለልጆቹ መልካም ውጤት እንደማይኖረው ከዔሊ ሕይወት እንማራለን። በእግዚአብሔር ቤት እስኪያረጁ ድረስ ዕድሜ ልክ ማገልገል ቤተሰብን በተለይም ልጆችን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተዋወቅ ለእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ በማዘጋጀት እርሱን በጽድቅና በቅድስና እንዲያገለግሉ የማያደርግና ለመንግሥቱ የማያበቃ ከሆነ ዘላለማዊ ፍሬ የሌለው ጥረት ይሆናል። እግዚአብሔርን እያገለገሉ የልጆችንም መንፈሳዊ ሕይወትና ኑሮ መከታተል ከጸጸት ያድናል።

አንድ አገልጋይ ልጆቹን እንዴት መያዝ እንዳለበት ከዔሊ መማር የሚችላቸው ቁም ነገሮች አሉ። ከእነዚህም የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

- ✓ የአገልጋይ ልጆች ከአገልጋይ በመወለዳቸው ብቻ መልካም እምነት አይኖራቸውም። የመንፈሳዊ ወላጆች እምነት በዘር ወደ ልጆች አይተላለፍም። ስለዚህ አገልጋይ ልጆቹ ከእግዚአብሔር ጋር የግል ኅብረት እንዲኖራቸው እንዲሁም በተግባር ላይ የተመሠረተ የእግዚአብሔር እውቀት እንዲኖራቸው ተገቢውን ወላጃዊ ክትትል ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን
- ✓ አገልጋይ ልጆቹን መውደዱ መልካም ቢሆንም ልጆች ኃጢአት ሠርተው እግዚአብሔርንና ቤተክርስቲያንን በሚያሳዝኑበት ጊዜ ዝም ከማለት ወይም ከሚገባ በታች የሆነ ምክር ከመስጠት ይልቅ ተመጣጣኝ የሆነ የእርምት እርምጃ መውሰድ ልጆቹንም ከማዳን ወይም ከማትረፍ አኳያ መልካም መሆኑን
- ✓ አገልጋይ ልጆቹ በሕይወታቸውም ሆነ በአገልግሎታቸው በምን ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ፣ ከሰዎች ጋር በተለይ ደግሞ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስል ሳያቋርጥ መከታተልና አስፈላጊውን ምክር መስጠት ወደ ክፉ ነገር እንዳይገቡ የሚከላከል መሆኑን



- ✓ አገልጋይ ልጆቹ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአት ፈጽመው ከተገኙ መገሰጽና ወደፊት ተመሳሳይ ድርጊት እንዳይፈጽሙ መከልከል (ለምሳሌ የሚያገለግሉ ከሆነ ከአገልግሎት ማገድ) አስፈላጊ መሆኑን
- ✓ አገልጋይ ልጆቹ በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ፊት በደል ፈጽመው እያየ ሳይገስጻቸው መተው ለጊዜው ልጆቹን የወደዳቸው ቢያስመስልም በእርግጥ ሲታይ እንዲህ ማድረግ ልጆችን ለእግዚአብሔር ፍርድ አሳልፎ መስጠት መሆኑን
- ✓ የአገልጋይ ልጆች መልካም አለመሆን የአገልጋይን ሕይወትና አገልግሎት ክፉኛ ይጎዳል። ከዚህም የተነሳ እግዚአብሔር ከቤተሰቡ ጋር ለመሥራት ያሰበው ዕቅድ ተግባራዊ እንዳይሆን እንቅፋት መሆኑን መመልከት ይቻላል።

የሳሙኤል ልጆች (1ሳሙ.8:2-3)። ሳሙኤል ከልጅነቱ ጀምሮ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ያደገና እግዚአብሔርን ማገልገል ገና ከልጅነቱ የጀመረ ሰው ነበር። ሳሙኤል ያደገው በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ቢሆንም ከእርሱ ጋር የነበሩ የካህን ልጆች ግን ፈሪሃ እግዚአብሔር ያልነበራቸው ነበሩ። ሆኖም ሳሙኤል አካባቢውንና እኩዮቹን ሳይሆን እግዚአብሔርን በመፍራት በመንፈሳዊ ሕይወቱ አደገ። ከዚያም ከእግዚአብሔር ጋር በግሉ መገናኘት ጀመረ። ሳሙኤል እግዚአብሔር ካህኑ ዔሊ ከእግዚአብሔር ይልቅ ልጆቹን በማክበሩ ያስተላለፈበትን ፍርድ የተቀበለና ለካህኑ ለዔሊ የተናገረ አገልጋይ ነበር። ከእርሱ ጋር ያሉምንም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያገለግሉ የነበሩ የካህን ልጆች እንዴት እንደሞቱ ያየና የሚመሰክር ሰው በመሆኑ ለሚወልዳቸው ልጆቹ ትልቅ ትኩረት እንደሚያደርግ ተስፋ ይደረጋል።

በሳሙኤል የሕይወት ፍጻሜ የሚታየው ግን የዚህ አሳብ ተቃራኒ የሆነ ነገር ነው። ሳሙኤል ልጆቹ እንደ ዔሊ ልጆች እንዳይሆኑ ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል ተብሎ ቢጠበቅም የእርሱም ልጆች ዕድል ፈንታ እግዚአብሔርንና ሕዝቡን ደስ የሚያሰኝ አልነበረም። የእግዚአብሔር ቃልና መገለጥ ብርቅ በነበረበት ከእግዚአብሔር መገለጥ የሚመጣለት፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ የሚያከብሩትና እርሱ የሚናገረው ቃል በምድር ላይ የማይወድቅበት እውነኛ አገልጋይ ነበር። ሆኖም ልጆቹ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ ልጆች እግዚአብሔርን የሚያከብሩና የሚፈሩ እንዲሁም ሕዝቡን በታማኝነት የሚያገለግሉ አልነበሩም። ሳሙኤል ልጆቹ መንፈሳዊ አገልግሎት እንዲያገለግሉ አላስቀመጣቸውም። ነገር ግን በእስራኤል ላይ ፈራጆች አደረጋቸው። ልጆቹ ግን ከሕዝቡ ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ጥቅም በማስቀደም ከሕዝቡ ጉቦ በመቀበል ፍርድን ማጣመም ጀመሩ። የእስራኤል ሕዝብ ይህን ተመለከተና ወደ ሳሙኤል መጥተው «ልጆችህ አንተን መተካት አልቻሉምና ለእኛ የሚፈርድልን ንጉሥ እንደ አሕዛብ ሹምልን» አሉት። እስራኤል በንጉሥ መተዳደርን የመረጠውና የጀመረው የአገልጋይ ልጆች በተለይም የሳሙኤል ልጆች እንደ አባታቸው መልካም የእግዚአብሔርና የሕዝብ አገልጋይ ባለመሆናቸው ነበር።

ከሳሙኤል ወላጅነት አንድ አገልጋይ ሊማራቸው የሚችላቸው የወላጅነት መርሆዎች አሉ። ከእነዚህ የሚከተሉት ይገኙበታል።

- ✓ ልጆች ከመልካም የእግዚአብሔር አገልጋይ በመወለዳቸው ብቻ ተገቢው መንፈሳዊ እንክብካቤና ክትትል ሳይደረግላቸው ፈሪሃ

እግዚአብሔር ያላቸው ስለማይሆኑ አገልጋይ ለልጆቹ መንፈሳዊ እንክብካቤ መስጠት አለበት::

- ✓ አገልጋይ ልጆቹ እርሱ ባደገበት ሁኔታ እንደሚያድጉ በማሰብ ማድረግ የሚገባጡን ወላጃዊ ኃላፊነት ችላ ማለት ያልተጠበቀ ክፉ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል መገንዘብ አስፈላጊ ነው::
- ✓ አገልጋይ ልጆቹ እንደ እርሱ በአካባቢ ያሉትን ፈተናዎች ተቋቁመው መልካም ልጆች ይሆናሉ ብሎ መጠበቅ የለበትም::
- ✓ አገልጋይ ልጆቹን ለአገልግሎት ከመመደቡ በፊት ልጆቹ ምን ያህል የእግዚአብሔር ነገር በሕይወታቸው በርጾ እንደገባና ክርስቲያናዊ ሥነምግባርን በሕይወታቸው ምን ያህል እየተለማመዱ እንደሆነ በቅድሚያ ማወቅ ያስፈልጋል::
- ✓ የአገልጋይ ልጆች በሕይወታቸውም ሆነ በአገልግሎታቸው ከአባታቸው ጋር ሲነጻጸሩ ከእርሱ አንሰው ሳይሆን በልጠውና ተሽለው እንዲገኙ በማሰብ ተገቢውን እንክብካቤ መስጠት በአገልጋዩ የተጀመረው የእግዚአብሔር ሥራ ሳይቋረጥ እንዲሄድ ያደርጋል::

የዳዊት ልጆች፡- ዳዊት በእግዚአብሔር ዘንድ ልቡ መልካም የሆነና የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ በማወቅ በሕይወቱ ለመተግበር የሚጥር የእግዚአብሔር ሰው እንደነበር ቃሉ ይነግረናል:: ዳዊት የእግዚአብሔር ሰው ቢሆንም ዳሩ ግን ብዙ ሚስቶችን በማግባቱ እግዚአብሔር ጋብቻን ሲመሠርት አንድ ለአንድ ያቀደውን ዕቅድ ተግባራዊ አላደረገም:: ከሚስቶቹም ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወልዷል:: ከተለያዩ ሚስቶች የተወለዱትን ልጆች አንድ ላይ ማሳደግና መምራት ከአንዲት ሚስት የተወለዱትን ልጆች ከማሳደግና ከመምራት የበለጠ ጊዜ፣ ትኩረትና ኃላፊነትን ይጠይቃል::

ዳዊት ግን ንጉሥ በመሆኑ ብዙ ሥራ የሚበዛበት ሰው ነበር:: ስለሆነም ልጆቹን በግል አያውቃቸውም:: ልጆቹ እያንዳንዳቸው ያላቸውን ባሕርያት እንዲሁም ጠንካራና ደካማ ጎናቸው ምን እንደሆነ ለይቶ አያውቅም:: የንጉሥ ቤት በመሆኑም ከልጆቹ ጋር የሚገናኘው አልፎ አልፎ ነበር:: ዘወትር ማታ ማታ ከልጆቹ ጋር እራት ለመብላት ጊዜ አልነበረውም:: እንኳን ለልጆቹ ለሚስቶቹም ጊዜ እንዳለው ማሰብ ያስቸግራል::

አንድ ጊዜ አምኖን የሚባለው የበኩር ልጁ በአባቱ በኩል እህቱ የሆነችውን ትዕማርን ወደዳትና በፍቅር ተይዞ በጓደኛው ተመክሮ ታሞ ተኛ:: ከዚያም የንጉሥ ልጅ መታመም ለዳዊት ይነገረውና ዳዊት ልጁን ለማየት ወደ እልፍኙ ይመጣል:: ንጉሥ ዳዊት ሊጠይቀው በመጣ ጊዜ አምኖን እህቱ መጥታ እንጎቻ እንዲትሠራለት ንጉሡ እንዲፈቅድለት ጠየቀው:: ዳዊት ምንም ሳያስብበት ትዕማር ወደ ወንድምዋ እንዲትሄድ አዘዛት::

ዳዊት እንደ አባት ምንም ሥራ ቢበዛበትም ልጁ እንደ ታመመ በሰማ ጊዜ ለማየት መጥቶ ነበር:: ነገር ግን ሕመሙ ምን እንደሆነ፣ መቼ እንደጀመረውና ምን መድኃኒት ሊሆንለት እንደሚችል አልጠየቀውም:: ምናልባት እነዚህን ጥያቄዎች መጠየቅ የነበረበት የጤና ባለሙያ ነው ማለት ይቻላል:: ሆኖም አምኖን ለንጉሡ ካቀረበው ጥያቄ አኳያ እነዚህ ጥያቄዎች መጠየቅ ነበረባቸው:: በተለይ አምኖን «እህቴ ትዕማር እንድትምጣና እኔ



እያየሁ ሁለት እንጎቻ እንድታደርግልኝ፣ ከእጅዋም እንድበላ እለምንሃለሁ» (2ሳሙ.13:6) ማለቱን ወጣቶች ምን ሊያደርጉ እንደሚችሉ የሚጠረጥር አባት «ይህ ለምን ተፈለገ?» ብሎ መጠየቅ የሚገባ ነገር ይመስላል:: የእርሱን ሕመምና ትዕማር የምትሠራውን እንጎቻ ምን አገናኘው? ዳዊት አስተዋይና የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት ሰው ቢሆንም የልጁን ማመልከቻ በጥሞና ያጤነው አይመስልም::

ትዕማር አባትዋ ስላዘዛት ወንድምዋ ታምሞ ወደ ተኛበት ክፍል ገብታ እንጎቻውን አዘጋጀች:: ለእርሱም ሰጠችው:: እርሱ ግን የሠራችውን እንጎቻ ሳይሆን እርስዋን ለሰፈጋት እቤት ውስጥ የነበሩትን ሰዎች ወደ ውጭ አስወጥቶ ደፈራት:: ማስተዋል በጎደለው በአባትዋ ቀዕዛዝ ወደ ወንድምዋ ቤት ሄዳ በገዛ ወንድምዋ ተደፈረች:: ንጉሥ ዳዊት «ይህን ነገር ሁሉ በሰማ ጊዜ እጅግ ተቆጣ ነገር ግን የበኩር ልጅ ነበረና ስለወደደው የልጁን የአምኖን ነፍስ አላሳዘነም» (2ሳሙ.13:21)::

ዳዊት ይህ ነውረኛ የሆነ አስጸያፊ ድርጊት በቤተሰቡ ውስጥ መፈጸሙ እጅግ አስቆጥቶት ነበር:: ነገር ግን ከቁጣ ያለፈ የእርምት ወይም የቅጣት እርምጃ በአምኖን ላይ አልተወሰደም:: ንጉሡ ለምን ያለምንም ቅጣት ተወው? ይህን አስጸያፊ የሆነ ድርጊት የፈጸመው የበኩር ልጁ ስለነበር ዳዊት እርሱን ማሳዘዝን አልፈለገም:: ምናልባት ዳዊት ራሱ በዝሙት ቅሌት ውስጥ ገብቶ ከቤርሳቤህ ጋር ያመነዘረና ባልዋንም ያስገደለ ሰው ስለነበር በሕሊናው ውስጥ ያለው የበደለኛነት ስሜት ትክክለኛ ፍርድ እንዳይሰጥ አድርጎት ይሆናል::

ዳዊት ምንም ቢሆን እንደ ንጉሥና እንደ አባት ተገቢውን ፍርድ መስጠት ይጠበቅበት ነበር:: በዳዩን በመውደድ ላለማሳዘን ብሎ ተበዳዩዋን ችላ ማለቱ የአባትነት ፍቅሩ ሚዛናዊ አለመሆኑን ያመለክታል:: ዳዊት እንደ አባት የሴት ልጁን መብት አልጠበቀም:: እንዲህ ዓይነት በደል የፈጸመ ሰው በሙሴ ሕግ መሠረት ...ፍርድ ይገባው ነበር:: በዳዊት ቤተሰብ ውስጥ በደል ተገኘ:: በዳይና ተበዳይ ተፈጠሩ:: ይህ ደግሞ መፍትሔ ካልተገኘለት በደሉ እንዲቀጥል ለማድረግ የሚያስችል አምቅ ኃይል ነበር:: በዚህ ጉዳይ የተጎዳች ትዕማር ብቻ ሳትሆን ቤተሰቡ ሁሉ ነው:: በቤተሰብ መካከል መከፋፈል ሆኗል:: ለምሳሌ አቤሴሎም አምኖን በልቡ ስለጠላው ክፉም ሆነ መልካም አላናገረውም:: ስለዚህ ዳዊት እንደ አባትና መሪ ቤተሰቡን አንድ ላይ በመሰብሰብ የእርቅና ፍትሕ ሥራ መሥራት ነበረበት:: ሆኖም ዳዊት ለዚህ ጉዳይ ትኩረት አልሰጠም ወይም ጊዜ አላገኘም::

ዳዊት ተገቢውን ፍርድ ባለመስጠት ችላ ማለቱና በዳዩ እንዲሁ ምንም ነገር እንዳላደረገ ሰው መኖሩ በበደሉ የተጎዱትን ወገኖች በተለይም አቤሴሎምን እጅግ አስቆጥቶታል:: ሆኖም ቁጣውን በልቡ በመያዝ ወንድሙን ለመበቀል ጊዜ መፈለግ ጀመረ:: አባትና ንጉሥ መዳኘት ያልቻለውን ነገር ተበዳዮች በራሳቸው መንገድ ፍትሕ የመሰላቸውን ነገር ለማድረግ ተነሱ:: አቤሴሎም ይህ በደል ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በኋላ በጎቹን ይሸልት ስለነበር ግብዣ አድርጎ አባቱንና ቤተሰቡን ሁሉ ጠራቸው:: አባቱ ግን በልጁ ላይ ላለመከበድ ለመሄድ አልፈለገም:: ሆኖም ልጆቹና አምኖን እንዲሄዱ ፈቀደ:: አቤሴሎም በግብዣ ላይ እያለ ወንድሙን አምኖን አስገደለ:: በዚህም የእህቱን የትዕማርን በደል ተበቀለ እንዲሁም አልጋ ወራሽ ለመሆን የሚያስችለውን ዕድል ለራሱ አመቻቸ:: አቤሴሎም የእህቱ

ጉዳይ ችላ በመባሉና ፍትሐዊ ፍርድ ባለመስጠቱ ወንድሙን በመግደል ዐመጹን ጀመረ:: ከዚያም የአባቱን መንግሥት ለመገልበጥ ብዙ ሙከራዎችን አደረገ:: ከአባቱም ቁባቶች ጋር በአደባባይ በመተኛት ከአባቱ ጋር ያለውን ግንኙነት አቋረጠ::

ዳዊት አባት ከመሆንም አልፎ ሀገርን የሚመራ ንጉሥ ነበር:: ነገር ግን ቤተሰቡን በተገቢው መንገድ ለመምራት የተሳነው የእግዚአብሔር ባሪያ ነበር:: ከዳዊት የቤተሰብ መሪነት የምንማራቸው ብዙ ነገሮች አሉ:: ከእነዚህም ጥቂቶቹ:-

- ✓ የልጆችን ባሕርይና ፍላጎታቸውን ለማወቅ ክትትል ማድረግ መልካም መሆኑን
- ✓ ልጆች እንዲደረግላቸው ለሚጠይቁት ነገሮች ቶሎ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ ጊዜ ወስዶ ጉዳዩን ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመልከት
- ✓ ለልጆች በሕይወት መልካም ምሳሌ መሆን:: ልጆች የወላጆቻቸውን ፈለግ ይከተላሉ:: ወላጆች የእግዚአብሔር ሰዎች ሆነው ኃጢአት ከሠሩ ልጆቻቸው ኃጢአት ሲሠሩ በእነርሱ ላይ የእርምት እርምጃ ለመውሰድ ድፍረት ያጣሉ::
- ✓ በልጆች መካከል የጾታ አድልዎ አለማድረግ:: ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን በእኩል ዓይን ማየት ለሁለቱም ተገቢውን እንክብካቤ መስጠትና ሲያጠፉም ተገቢውን የእርምት እርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል::
- ✓ በቤተሰብ ውስጥ በደል ሲፈጸም ጉዳዩ ወደቂም በቀል እንዳያመራ በጊዜው የእርቅና የፈውስ ሁኔታን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው::
- ✓ በውጭ አገልግሎት የሚያስመሰግን ታሪካዊ ሥራ ሠርቶ በቤተሰብ ኃላፊነት ግን መውደቅ የማታ ማታ ውርደትን ያስከትላል::

ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ሳይሆን አሁን በዘመናችን ከሚታየው ሁኔታ አንዳንድ የአገልጋይ ልጆች እንደተጠበቁ ያህል እግዚአብሔርንና ወላጆቻቸውን የሚያስደስት ሕይወት የላቸውም:: በአብዛኛው የአገልጋይ ልጆችን የሚፈታተነው የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት ነው:: ለዚህም ሁለት ምሳሌዎችን መመልከት ይቻላል::

★★ ★

ታደለች የአንድ ቤተክርስቲያን አገልጋይ ልጅ ናት:: አባትዋ ብዙ ጊዜ ከመደበኛ ሥራው ውጭ የሚያሳልፈው ምዕመናንን በመጎብኘት፣ የተጣሉ ሰዎችን በማስታረቅ፣ የቤተክርስቲያን የመሪዎች ስብሰባዎችን በመካፈል፣ ወንጌል በማስተማርና በተለያዩ አዳር ፕሮግራሞች ነው:: «ከሥራው ይመለሳል ብለን ስንጠብቅ እናታችን 'እራት ብሉ አባታችሁ ዛሬ አንድ ቦታ ለአገልግሎት ሄዷል ትለናለች:: ጧት ትምህርት ቤት እንሄዳለን:: ከትምህርት ቤት ስንመለስ አባታችን ለአገልግሎት ሌላ ቦታ እንደሄደ ይነገረናል:: አንዳንድ ጊዜ የአባታችንን ፊት ሳናይ ሳምንት እንቆያለን:: አባታችን ዐመሉ ጥሩ ነው:: እናታችን ደግሞ ትቆጣናለች:: ብዙ ጊዜ ትቆጣና በዱላ ትደበድበናለች:: እንዲሁ እየሆነ ከአባቴ ጋር ብዙም ግንኙነት ሳይኖረኝ የወጣትነት ጊዜ መጣ:: አንድ በትምህርት ቤት አብሮኝ የሚማር ወጣት ለፍቅር ግንኙነት ጠየቀኝ:: በመጀመሪያ ይህን



እንደማላደርግ ብነግረውም በፍቅር አባበለኝ:: ከዚያም ባደርገውስ የሚል እሳብ ደጋግሞ መጣብኝ:: እናቴን በጣም ስለምፈራት ለእርስዋ መንገር አልፈለኩም:: አባቴ እንደሆን መወለዴን እንጂ እንዴት እንዳደኩም የሚያውቅ አይመስለኝም:: እርሱ የወለዳቸው ሌሎች ልጆች ያሉት ነው የሚመስለኝ:: እንደ ወደደኝ የነገረኝ ወጣት ማባበሉን ገፋበት:: እኔም አንድ ቀን ስሜቴ አሸነፈኝና የፍቅር ግንኙነት አደረግን::

«ይህ ያደረኩት ነገር ኃጢአት እንደሆነ ስለተሰማኝ በጣም አዘንኩኝ:: ቤተክርስቲያን ስሄድና የእግዚአብሔርን ቃል ስሰማ ከፍተኛ የበደለኝነት ስሜት ይሰማኛል:: ሆኖም ያን ጓደኛዬን ሳየሁ የፍቅር ግንኙ ነታችን ኃጢአት መሆኑ ይቀርና ስፈጸም የምሰማኝ ደስ ደስ የሚል ስሜት ብቻ ይታየኛል:: ስለዚህ ሳላቋርጥ ግንኙነቱን ቀጠልኩ:: ይህ ሁሉ ሲሆን አንድም የቤተሰብ አባል አያውቅም ነበር:: ከጥቂት ወራት በኋላ ማርገዜን አወኩኝ:: እርጉዝ እንደሆንኩ ስረዳ የተሰማኝን የሐዘንና የተስፋ መቁረጥ ስሜት በቃላት መግለጽ ይከብደኛል:: ከዚያም የወላጆቼን ፊት ማየት አይገባኝም ብዬ ትምህርቴን አቋርጬ ከአካባቢው ተሰወርኩ:: ማንም ሰምንና እንዴት እንደተሰወርኩ አያውቅም ነበር:: ወላጆቼ በጣም ደነገጡ:: እኔን ቢፈልጉ ከየት ያግኙኝ? እኔ ሰው ቤት በሠራተኛነት ገባሁና ልጄን ወለድኩ:: እኔን ያስጠጉኝ ሰዎች የወላጆቼን አድራሻ ወስደው ያለሁበትን ቦታ ለወላጆቼ ነገሩአቸው:: እነርሱም መቼም ልጃቸው ነኝና መጥተው ወደ ቤት ወሰዱኝ:: ወላጆቼ፣ ወንድሞቼና እህቶቼ እንዲሁም ቤተክርስቲያን አዘኑብኝ:: አባቴ እንደ ቀድሞ ጊዜያት በድፍረት ማገልገል አልቻለም:: የእኔም ሕይወት ከዚህ በኋላ መስመር ይይዝ እንደሆን አላውቅም::»

★★ ★

ተሾመ የአንድ ወንጌላዊ ልጅ ነው:: አባቱ በአካባቢው ከሚጠቀሱ የቤተክርስቲያን መሥራቶች አንዱ እንደሆነ ይጠቀሳል:: የተሾመ አባት የማይገባበት የአገልግሎት መስክ የለም:: የእርሱ ግማሽ የመኖሪያ አድራሻ ቤተክርስቲያን ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: እናቱ ደግሞ ብዙጊዜ ሙሉ ጤንነት አይሰማትም:: ሆኖም ለቤተሰቡ አስፈላጊውን እንክብካቤ ለማድረግ ጥረት ታደርጋለች:: ተሾመ የአባቱ ሁለተኛ ልጅ ነው:: የተሾመ ታላቅ ወንድም እኩዮቹ ከሆኑት ካላመኑ ወጣቶች ጋር ብዙጊዜ ስለሚያሳልፍ ዘፈን በጣም ከመውደዱ የተነሳ ቤተክርስቲያን መሄድን አቁሟል:: «ወላጆቻችን ቤት በማይኖሩበት ወቅት ዘፈን እያመጣ ቴፕ ውስጥ ያስገባና ዘፈን ያስደምጠናል:: ተው አባቴ ይቆጣል ስንለው አይሰማንም:: እኔ ቤተክርስቲያን እሄዳለሁ:: ከምዕመናን ጋርም ቅርበት ነበረኝ:: ስለዚህ ጥሩ ልጅ ይሉኛል:: ሆኖም ግን የክርስትና እምነት ምን እንደሆነ በግል የገባኝ ነገር አልነበረም:: ለእኔ ደስ የሚለኝ መዝሙሩና ማህበራዊ ኑሮው ነው:: የእኛ ቤት ብዙ ሰዎች ስለሚመጡ ከእነርሱ ጋር መጫወት ደስ ይለኝ ነበር::

«ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ስገባ ከተለያዩ ቦታ ከመጡ ወጣት ተማሪዎች ጋር ተዋወቁ:: ሳቅ ስለማበዛ ጓደኛ ለማፍራት ብዙም አልቸገርም ነበር:: በትምህርትም ትንሽ ጎበዝ ስለነበርኩ ሴቶች እስጠናን እያሉ ይቀርቡኝ ጀመር:: እኔ በደስታ አስጠናቸው ነበር:: በዚሁ ሁኔታ እያለን ከአንዷ ሴት ልጅ ጋር ግንኙነታችን እየጠነከረ ሄደ:: ከዚያም የፍቅር ግንኙ ነት አደረግን:: ይህን ግንኙነታችንን የሚያውቁ ልጆች ስለነበሩ ወሬው

ቤተክርስቲያን መሪዎች ዘንድ ደረሰ። እነርሱም ያደረኩት ነገር እውነት እንደሆነ ለማወቅ አነጋገሩኝ። እኔ በግልጽ ነገርኩአቸው። ከሳምንት በኋላ ከቤተክርስቲያን ኅብረት እንዳገለሉኝ ነገሩኝ። አባቴም ሁኔታውን ሲሰማ እንዴት ልጄን ከቤተክርስቲያን ኅብረት ያገላሉ በማለት ተቆጣ። የአባቴን ከእኔ ጋር መሆን ሳውቅ በጣም ደስ አለኝና ከጓደኛዬ ጋር ያለኝን ግንኙነት ቀጠልኩ። የፍቅር ግንኙነቱ ከፍተኛ ስለነበር ለትምህርት የነበረኝ መነሳሳትም ቀነሰ። በዚሁ ሳለሁ የኮሌጅ መግቢያ ፈተና መጣ፣ ተፈተንኩ። ነገር ግን ኮሌጅ የሚያስገባኝ ነጥብ አላገኘሁም። አሁን ወደ አዕምሮዬ ስሰመለስ አባቴ አገልጋይ ቢሆንም ለእኔ ሕይወት ግን ማድረግ የሚገባውን አባታዊ ግዴታ የተወጣ አይመስለኝም። እርሱ ያገለገላቸው ወላጆች ልጆቻቸውን በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋ በጥሩ ሁኔታ አሳድገዋል። አገልጋይነቱ ለሌሎች እንጂ ለእኛ አልጠቀመንም።»

ይህ መራራ ፍሬ ግን እንዴት ሊመጣ ቻለ ብሎ መጠየቅ ጥሩ ነው። ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሆኑ የሚችሉ ብዙ አሳቦች ሊኖሩ ይችላሉ። ከእነዚህም ጥቂቶቹ፦

- ✓ ወላጆቻቸው ለአገልግሎት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው ልጆቻቸውን ችላ በማለታቸው ልጆች ቤተክርስቲያን ወይም አገልግሎት ወላጆቻቸውን እንደቀሙባቸው በማሰብ በማዘናቸው
- ✓ ወላጆች በአደባባይ እንጂ በቤተሰብ ውስጥ መልካም ባሕርይና ተግባር ስለማይኖራቸው
- ✓ ወላጆች ልጆቻቸውን እግዚአብሔር እንደሚያሳድጋቸው በማሰብ የበኩላቸውን ኃላፊነት ባለመወጣታቸው
- ✓ ወላጆች በአገልግሎት ከገጠማቸው ችግርና ተግዳሮት የተነሳ ወደ ቤት ሲሄዱ በቤተሰብ ፊት በተለይም በልጆች ፊት ብሶታቸውንና የተጎዱበትን ነገር የሚናገሩ ከሆነ ልጆች ስለእምነትና ስለአገልግሎት ጥላቻ ያድርባቸውና በተቃራኒው መንገድ ሊሄዱ ይችላሉ።
- ✓ ወላጆቻቸው በጌታ ፍቅርና ምክር ልጆቻቸውን ስላላሳደጉአቸው ልጆቹ በወላጆቻቸው ከዚያም በእግዚአብሔር ላይ ያምጻሉ
- ✓ ሁሉም የአገልጋይ ልጆች እንደ ሌሎች ምዕመናን ልጆች እንደሆኑ አያስቡም። ሌሎች ልጆች እንደ ልጆች ለመሆን ነጻነት ሲኖራቸው የአገልጋይ ልጆች ግን እንዲሁ ዓይነት ነጻነት የላቸውም። ምዕመናን «አንተ እኮ የአገልጋይ ልጅ ነህ» «አንቺ እኮ የአገልጋይ ልጅ ነሽ» ይባላሉ። ይህ ደግሞ ከሌሎች ልጆች ልዩ ሆነው እንዲታዩ ስለሚያደርጋቸው ያስቆጣቸዋል፣ እንዲሆኑ ከሚጠበቁት ሁኔታ ውጭ ለመሆን ይፈተናሉ። ከአገልጋይ ልጆች የተሻለ ባሕርይ መጠበቅ ትክክል ነውን? በመሠረቱ የአገልጋይ ልጆች ከሌሎች ምዕመናን ልጆች የተሻሉ እንደሆኑ መገመት አግባብ አይደለም።

በእርግጥ አገልጋይ እንደ ሌሎች ወላጆች ከልጆቹ ጋር ለመሆን ጊዜ ሊያጥረው እንደሚችል ቢታወቅም ዋናው ችግር የጊዜ እጥረት ሳይሆን ለልጆች ትኩረት አለመስጠት እንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም። አንዳንድ አገልጋዮች ያላቸውን ጊዜ ከልጆቻቸው ጋር በጥሩ ሁኔታ ይጠቀሙበታል። ልጆች አባታቸውን በግል የሚያገኙት በሳምንት አንድ ቀን ቢሆንም ግን ከአባታቸው ጋር መልካም ግንኙነት እንዳላቸው ያስባሉ።

★★ ★



ደረጀ የአጥቢያ ቤተክርስቲያን መጋቢ ነው። በቤተክርስቲያኒቷ ደንብ መሠረት አንድ የሙሉጊዜ አገልጋይ በሳምንት አንድ ቀን እንዲያርፍ ይፈቀድለታል። ይህም አገልጋዮች ቅዳሜና እሁድ በአገልግሎት ላይ ስለሚውሉ እንዲያርፉ እንዲሁም ለሳምንቱ አገልግሎታቸው አዕምሮአቸውን እንዲሰበስቡ ለማገዝ ታስቦ ነው። በዚሁ መሠረት መጋቢ ደረጀ አንድ ቀን እቤቱ ይሆናል። ሚስቱ ሥራ ትሄዳለች፣ ልጆች ደግሞ ትምህርት ቤት ይሄዳሉ። ልጆቹ ከትምህርት ቤት እስኪመለሱ ድረስ እርሱ ይጸልያል ቃሉንም ያነባል። ልጆቹ ከትምህርት ቤት ከአባታቸው ጋር ለመጫወት ጓጉተው ይመጣሉ። ያን ቀን በር የሚከፍትላቸው እርሱ ነው። በር ከፍቶላቸው ቦርሳዎቻቸውን ከእነርሱ ተቀብሎ እጆቻቸውን ይዞ ወደ ቤት ያስገባቸዋል። ከዚያም ምሳ ይሰጣቸውና አብሮአቸው ይበላል። ከምሳ በኋላ የቤት ሥራዎቻቸውን እንዲሠሩ ያግዛቸዋል፣ በሳምንቱ ውስጥ ከተማሩት ትምህርት ያልገባቸውን ነገር ይጠይቃቸውና ያስረዳቸዋል።

እነዚህን ነገሮች ሲጨርሱ አብሮ መጫወት ይጀምራሉ። መጋቢ ቢሆንም ከልጆቹ ጋር እነርሱ መጫወት የሚፈልጉትን ነገር ከእነርሱ ጋር ይጫወታል። አብረው ሲጫወቱ ደግሞ ስለተለያዩ ነገሮች ያወራሉ። ልጆቹ በትምህርት ቤት የገጠሙአቸውን ነገሮች ያወሩለታል። አንዱ ሲጨርስ ሌላው ያወራል። ጥያቄዎችንም ይጠይቁታል። እነርሱ የሚያወሩትን በማዳመጥ እስተያየቱን ይሰጣል፣ ለጥያቄዎቻቸውም መልስ ይሰጣል። በዚህ ጊዜ ልጆቹ ደስ ይለኛሉ። መጋቢ ደረጀ ከልጆቹ ጋር በዚህ ሁኔታ በማሳለፍ ከእነርሱ ጋር አብሮ መኖሩን እያሳያቸው ነው። አሁን ልጆቹ የእርሱን የእረፍት ቀን በጉጉት ይጠብቃሉ። በሌሎች ቀናት ከሚያገኛቸው በተጨማሪ እንዲህ ዓይነት ዕቅድ ማዘጋጀቱ ለመጋቢ ደረጀና ለልጆቹ መልካም ሆኗል።

ልጆችን በመልካም መንገድ መምራት ማታና ጧት መንፈሳዊ ፕሮግራሞች በማድረግ እንደሆነ መታሰብ የለበትም። መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን ማድረግ አስፈላጊ ነው። ሆኖም ብቻውን ልጆችን ወደ ተገቢው ግብ አይመሩቸውም። እንደ ወላጅ ከልጆች ጋር ጊዜ ወስዶ እንደ መጋቢ ደረጀ አብሮአቸው መጫወት፣ እነርሱ የሚናገሩትን ነገሮች ማዳመጥና በአዕምሮአቸው ውስጥ ያሉትን ጥያቄዎች እንዲጠይቁ በመፍቀድ ተገቢውን መልስ መስጠት ያስፈልጋል። በልጆች ላይ በጎ ተጽዕኖ የሚኖረው ወላጆች ወግና ሥርዓት ከጠበቀው ግንኙነት ውጭ ከእነርሱ ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ ነው። ልጆች በእርግጥ የወላጆቻቸውን ትክክለኛ ማንነት የሚያውቁት እነርሱ ቃል ሲያካፍሉ ወይም ሲጸልዩ ሳይሆን ከእነርሱ ጋር ሲጫወቱ ነው። ወላጆች ከእነርሱ ጋር ሲጫወቱ የሚያደርጉትና የሚሆኑት ነገሮች የልጆቹን ሕይወት በከፍተኛ ሁኔታ ይቀርጻል። ስለዚህ አገልጋይ ከመደበኛ መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ውጭ ከልጆች ጋር ቢያንስ በሳምንት አንድ ቀን አብሮአቸው ቢሆን የተሻለ ነው።

አገልጋይ ለልጆቹ ምን ያህል ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልገው የሚያውቀው እንዴት እንዳደገ ሲገመግም ነው። እስቲ ለትንሽ ጊዜ ውስድና ወላጆችህ እንዴት እንዳሳደጉህ አስብ። ወላጆችህ መልካም ወላጆች ነበሩ? ካልሆኑ ዛሬ አንተ ስለእነርሱ ወላጅነት ያለህ ትዝታ ጥሩ አይደለም ማለት ነው። ያንተ ልጆች ሲያድጉ «ከአባታችን ባልተወለድን ኖሮ!» እንዲሉ ትፈልጋለህን? የማትፈልግ ከሆንህ ለልጆች ዛሬውኑ ትኩረት ስጥ። ልጆች በቀብር ሥርዓትህ ላይ ስለአንተ ወላጅነት እንዲናገሩ ቢጠየቁና ቢናገሩ ምን

ይናገራሉ ብለህ ታስባለህ? በአዕምሮህ የሚመጣው መልካም ያልሆነ አሳብ ከሆነ ለማስተካከል ዛሬውኑ መልካም እርምጃ ውሰድ።

እንግዲህ ለአገልግሎት ብቃት መኖሩ ከሚታወቅባቸውና ለአገልግሎት ለኬት ከሚያበቁ ነገሮች አንዱ ልጆችን በተገቢ መንገድ ማሳደግ መቻል ነው። አገልጋይ መልካም ሥነምግባር የሌላቸው ልጆች ካሉት በቤተክርስቲያንና በአካባቢው ማሕበረሰብ ውስጥ ለሚኖሩ ልጆች ክፉ ምሳሌ ከመሆናቸውም በላይ አገልጋዩ ለአገልግሎት አለመብቃቱን የሚመሠክሩ ተጨባጭ ማስረጃዎች ናቸው።

ስለዚህ አገልጋይ ከአገልግሎት በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ ቢኖር ቤተሰቡን ነው። ቤተሰብን ከአገልግሎት ማስቀደም መጽሐፍ ቅዱሳዊና ለአገልግሎት ፍሬያማነትም አስፈላጊ ሆኖ እየታመነበት አገልጋይ ለቤተሰብ አስፈላጊውን ትኩረት እንዳይሰጥ የሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች ቢኖሩም ተግዳሮቶቹን በመቋቋም ለቤተሰብ አስፈላጊውን ትኩረት ለመስጠት የሚረዱ ጠቃሚ አሳቦች አሉ። የሚቀጥለው ክፍል በእነዚህ አሳቦች ላይ ትኩረት ያደርጋል።

<u>ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።</u>

1. *በዓውዳችሁ የአገልጋይ ልጆች ምን ዓይነት ባሕርይ አላቸው? ለምች እንዴት ይገልጹአቸዋል?*
2. *የአገልጋይ ልጆች ምን መልካም ዕድል አላቸው? የአገልጋይ ልጆች በመሆናቸውስ የሚያጋጥሙአቸው ተግዳሮቶች ምንድናቸው?*
3. *አገልጋይ ለልጆቹ ተገቢውን እንክብካቤ እንዳይሰጥ ተግዳሮት የሚሆኑባቸው ነገሮች ምንድናቸው? እነዚህን እንዴት መከላከል ወይም ማስወገድ ይቻላል?*
4. *የአገልጋይ ልጆች መልካም ልጆች እንዲሆኑ ቤተክርስቲያን ምን ዓይነት ሚና መጫወት ይኖርባታል?*

እንግዲህ አገልጋይ ከትዳር ጓደኛው በመቀጠል ለልጆቹ ተገቢውን ጊዜ፣ ትኩረትና እንክብባኬ በመስጠት በሁለንተናዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ ከአንድ መንፈሳዊ ወላጅ የሚጠበቀውን ኃላፊነት መወጣት ይጠበቅበታል። በአገልግሎት በማሳበብ ልጆችን ችላ ማለት ልጆች ወደማይፈለግ አቅጣጫ እንዲሄዱ በማድረግ የራሳቸውን ሕይወት ይጎዳሉ፣ የአገልጋይን አገልግሎት ያበላሻል እንዲሁም ለቤተክርስቲያንና ለኅብረተሰብ የማይጠቅም ትውልድ እንዲፈጠር ያደርጋል። ስለዚህ ልጆችን በመልካም ሁኔታ ኮትኩቶ ማሳደግ የመንፈሳዊ አገልግሎት አንዱ ክፍል መሆኑ ሊታወቅና ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።



### 4.3. አገልጋይ የቤተሰብ አገልግሎት ለማጠናከር የሚረዱ መልዕክቶች

የቤተሰብ ሕይወት ማጠናከር እንዲሁ በተዓምር የሚፈጠር ሳይሆን ሰብዓዊ ኃላፊነት ያለበት ሥራ ነው። ቤተሰብ በጥበብና በማስተዋል ተመስርቶ ይጸናል። አገልጋይ ለቤተሰብ ተገቢውን ትኩረት ለማድረግ ቤተሰብን ሊያጠናክር የሚችል እንክብካቤ ለመስጠት ጠቃሚ የሆኑትን አሳቦች ማወቅ አስፈላጊ ነው። ከእነዚህ ጠቃሚ አሳቦች መካከል የሚከተሉት አሳቦች የሚጠቀሱ ናቸው። እነርሱም:-

*ቤተሰብን የተመለከተ ዓላማ መንደፍ-* አንድ ድርጅት ለምን እንደተቋቋመ ዓላማ እንደሚያስፈልገው ሁሉ አንድ ቤተሰብም የራሱ የሆነ ዓላማ ሊኖረው ይገባል። ቤተሰብ የሚኖርለትን ግልጽ ዓላማ ካለውና እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ከተስማማበት በአንድነት ዓላማውን ለመተግበር ይነሳሉ። ይህ ዓላማ ከግብ እንዲደርስ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ከማስቻልም በላይ ቤተሰብ በአንድነት ተሳስሮ እንዲኖር ያግዛል። የአገልጋይ ቤተሰብ እንደ ቤተሰብ አንድ ላይ የሚኖሩት ለምንድነው? ለምሳሌ ያህል አንድ ቤተሰብ ሊኖረው የሚችለው ዓላማ:-

1. በታማኝነት፣ ፍቅር፣ መከባበርና ሰብዓዊ እኩልነት ላይ የተመሠረተ ዘላቂነት ያለውን ጠንካራ ግንኙነት መመሥረት (ኤፌ. 5:22-23፣ 1ጴጥ.3:7)። ቤተሰብ ከምንም በላይ ትኩረት መስጠት ያለበት ለመልካም ግንኙነት ነው። ቤተሰብ የሚሠራቸው ነገሮች መምጣት ያለባቸው በቤተሰብ ውስጥ ያሉት አባላት መልካም ግንኙነትና ዋስትና ሲያገኝ ነው። ቤተሰቡ እርስ በርስ ያላቸውን መልካም ግንኙነት የሚጎዳ ማንኛውም ነገር በምንም መልኩ መደረግ የለበትም። እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል የሚሆነውንና የሚያደርገውን ነገር የሚያየው ነገሩ በቤተሰብ ግንኙነት ላይ ከሚያመጣው ተጽዕኖ አንጻር ነው።

2. ክርስቶስን ማዕከላዊ ያደረገ የቤተሰብ ዘይቤ በመገንባት ልጆችን በሥርዓትና በጌታ ማሳደግ (ዘዳ.6:4-9)። ክርስቲያናዊ ቤተሰብ በተለይ ደግሞ የአገልጋይ ቤተሰብ ክርስቶስን ማዕከላዊ ያደረገ ሕይወት ሊኖረው ይገባል። ልጆች ባሉበት ቤተሰብ ውስጥ ደግሞ ለልጆች መልካምና ተገቢ እንክብካቤ እንዲሁም የእርምት እርምጃ በመውሰድ የጌታን ፍቅር በማሳየት በግላቸው እግዚአብሔርን በልምምድ እንዲያውቁ መርዳት የክርስቲያናዊ ቤተሰብ ኃላፊነት ነው።

3. እግዚአብሔርን ከሚያመልኩት ክርስቲያናዊ ቤተሰቦች ጋር መልካም ኅብረት ማድረግ (ዕብ.10:25)። የእግዚአብሔር ቃል ምዕመናን ከሌሎች ጋር ኅብረት እንዲያደርጉ ይመክራል። ይህ ደግሞ እርስ በርስ ለመተናነጽና ለመጠባበቅ ይረዳል። ወላጆች ከወላጆች ጋር ግንኙነት ሲያደርጉ ልጆች ደግሞ ከልጆች ጋር ግንኙነት ያደርጋሉ። በዚህም ቤተክርስቲያን የመልካም ክርስቲያናዊ ቤተሰቦች ስብስብ እንድትሆን ያደርጋል።

4. በኅብረተሰብ ውስጥ ለሚገኙት ቤተሰቦች ምስክር መሆን (የሐዋ.1:8)። እያንዳንዱ በጌታ የሆነ ሰው እንዲሁም ክርስቲያናዊ ቤተሰቦች ለጌታ ኢየሱስ ምስክሮች እንዲሆኑ ታዘዋል። እያንዳንዱ ቤተሰብ የክርስቶስን መልካምነት በቤቱ ከመለማመዳቸው የተነሳ በሕይወታቸው የሚታየው መልካም

ፍሬዎች ለሌሎች ቤተሰቦች «ክርስቶስ ቤተሰብን ያማረ መልካም ፍሬ ያደርጋል» ብሎ ይናገራል። ይህ እንዲሆን ደግሞ ክርስቶስን የሚመስል ሕይወት መኖርና በአካባቢ ለሚገኙ ቤተሰቦች ብርሃን መሆን ያስፈልጋል።

*የቤተሰብ ጊዜን ማክበር፡-* ዕለታዊና ሳምንታዊ የቤተሰብ ጊዜያትን አስቀድሞ በማቀድ ሁሉም የቤተሰብ አባላት አገልጋዩንም ጨምሮ እንዲያከብሩ ኃላፊነትን መስጠት አስፈላጊ ነው።

*የቤተሰብን ጊዜና ሥራዎች አብሮ ማቀድ፡-* ከቤተሰብ ጋር የሚሠሩትን ሥራዎች ማቀድ መልካም ነው። አገልጋይና የትዳር ጓደኛው፣ ወላጅና ልጆች አብረው በሚሆኑበት ወቅት ምን መሥራት እንዳለባቸው ቢያቅዱ መልካም ነው። ባልና ሚስት ከልጆች ተለይተው አብረው ሲሆኑ በጋራ ምን መሥራት ያስደስታቸዋል? ምንስ ግንኙነታቸውን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደግ ይችላል? ወላጆችስ ከልጆቻቸው ጋር ምን መሥራትን ወይም ጊዜያቸውን በምን ላይ ማዋል ይፈልጋሉ? ልጆችስ ከወላጆች ጋር ሲሆኑ ከወላጆቻቸው ጋር ምን መሥራትን ይፈልጋሉ? እነዚህ ነገሮች ቢታወቁ ጊዜያቸውን በሚገባ ለመጠቀም ይረዳቸዋል።

*ቅድሚያ ለምን እንደሚሰጥ ማወቅ፡-* በአገልግሎትና በሕይወት መሠረታዊና ከጥሪ ጋር ለተያያዙ ነገሮች ቅድሚያ መስጠትን መለማመድ አስፈላጊ ነው። አገልጋይ ሊሠራቸው የሚችላቸው ሥራዎች ወይም አገልግሎቶች ሊኖሩ ቢችሉም አገልጋይ ለየትኛው ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት በሚገባ መለየትና ቅድሚያ ሊሰጡ የሚገባቸውን በተገቢው መንገድ ማከናወን ይኖርበታል። በአገልጋይ ሕይወት ቅድሚያ ሊኖራቸው የሚገባቸው ነገሮች በቅደም ተከተል በምዕራፍ ሁለት ውስጥ ተጠቅሰዋል። እነርሱም እግዚአብሔር፣ የትዳር ጓደኛ፣ ልጆችና አገልግሎት ናቸው።

አገልጋይ በዚህ መልክ ቅድሚያ መስጠት ለሚገባው ነገሮች ቅድሚያ ሲሰጥ ለሚያገለግላቸው የቤተክርስቲያን ምዕመናን መልካም ምሳሌን ይተዋል። አገልጋይ ከቤተሰብ ጋር የሚኖረው መልካም ግንኙነት ለምዕመናን የጋብቻና ቤተሰብ ችግር አዎንታዊ ተጽዕኖ አለው። አገልጋይ በቃል ከሚያስተምረው ትምህርት ይልቅ ከቤተሰብ ጋር የሚኖረው ሕይወት የላቀ መልዕክት አለው። ስለዚህ አገልጋይ ቤተሰቡን በመንከባከብና ቅድሚያ ለእነርሱ በመስጠት ሌሎች ባሎቻቸው እንዲሁ እንዲያደርጉ ማሳየት ይጠበቅበታል።

*የቤተሰብ መንፈሳዊ ፕሮግራም ማቀድና ለዚያም ታማኝ መሆን፡-* የቤተሰብ መንፈሳዊ አቋም መልካም ሲሆን በመካከላቸው የሚኖረው ግንኙ ነት መልካም ይሆናል።

የቤተሰብ አምልኮ ጊዜ ማክበር ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ ነው። የቤተሰብ አምልኮ የቤተሰብ መሠውያ ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን መሠውያ የእግዚአብሔር ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር የሚገናኙበትና እርሱን የሚያመልኩበት ሥፍራ ነው። በዚያን ዘመን መሠውያ የአምልኮ ሥፍራ ነበር (ዘፍ.12:8)። ቤተሰብ የመጀመሪያ የአምልኮ ስፍራ ነው። ይህንንም አምልኮ በቀደሚትነት የሚመራው አባት ነው። አባት ቤተሰቡ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ምን ዓይነት ደረጃ እንዳላቸው መገምገም ይጠበቅበታል።



እግዚአብሔርን በሚያመልክ በአገልጋይ ቤተሰብ ውስጥ ከቤታ የራቁ አባላት ሊኖሩ ይችላሉ (ዘፍ.35:2-15)።

አገልጋይ ችግር ወደ ቤተሰቡ ከገባ በኋላ ለማስወገድ ከመጣር ይልቅ ለጌታ ክብር የማይሰጥ አሳብና ድርጊት ወደ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል እንዳይገባ የመከላከያ ትምህርት መስጠት ተገቢ ነው። አገልጋይ እንደ ቤተሰብ እረኛ ለቤተሰቡ መንፈሳዊ ሕይወት ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች አስቀድሞ በማየት መከላከል ይጠበቅበታል።

የቤተሰብ መሪ የሆነው አገልጋይ ከውጭ ካለው አገልግሎትና የሥራ ጫና በተጨማሪ የቤተሰቡንም መንፈሳዊ ሕይወት የሚከታተል ሰው መሆን ይጠበቅበታል። በውጭ እንደሚያገለግል ቤተሰቡንም የሚያገለግል መሪ ሊሆን ይገባል። ንጉሥ ዳዊት ከሕዝቡ ጋር እግዚአብሔርን ሲያመልክ ከቆየ በኋላ ማታ ወደ ቤቱ ተመልሶ እግዚአብሔርን ከቤተሰቡ ጋር ለማምለክ እንዳሰበ እናነባለን (2ሳሙ.6:20)።

ማንኛውም አገልጋይ እንደ ቤተሰብ መሪ በውጭ በሚሰጠው አገልግሎት ወይም የሥራ ጫና በማመካኘት ለቤተሰቡ ተገቢውን መንፈሳዊ እንክብካቤ መስጠት እንዳልቻለ ማሳበብ አይችልም። የቤተሰብን መንፈሳዊ ሕይወት መገንባት ቅድሚያ የሚሰጠው አገልግሎት ነው። መልካም መጋቢ መሆን ከቤት ይጀምራል። የእግዚአብሔር ቃል አንድ ሰው ለመጋቢነት እንዲሾም ከሚያበቁት መስፈርቶች አንዱ ቤተሰብን እንደሚገባ ማስተዳደር መቻሉ እንደሆነ ተመልክተናል (1ጢሞ.3:4)። ይህን ኃላፊነት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት አይችልም። ቤተሰብን መመገብ የመጀመሪያ የእግዚአብሔር አገልጋይ ኃላፊነት መሆኑ ታውቆ አገልጋዮች ወይም በውጭ ሥራ የተጠመዱ ወላጆች ለቤተሰቦቻቸው ትኩረት መስጠት አለባቸው።

ይህ የማይሆን ከሆነ ከጊዜ በኋላ የቤተሰባቸው ሁኔታ መጥፎ ይሆንና የውጭ አገልግሎታቸውን ያሰድባል። ይህም ብቻ ሳይሆን በቤተሰቡ መጥፎ አካሄድ የእግዚአብሔር ስም በሌሎች ዘንድ ይሰደባል። ከዚህም ባሻገር ሌሎችን ሰዎች አገልግለን ለመንግሥተ ሰማያት አዘጋጅተን ቤተሰቦቻችን ግን ለዚህ መልካም ነገር ሳናዘጋጃቸው ብንቀር ምንኛ የሚያሳዝን ነው! ከዚህ ዓለም የእኛ ነው ከምንለው ይዘን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የምንገባው ልጆቻችን ብቻ እንደሆነ ማስተዋል ይገባናል።

የቤተሰብ አምልኮ የቤተሰብ አባላትን አንድ ላይ የማጣበቅ ኃይል አለው። ቤተሰብን አንድ ላይ ከሚያይዙ ነገሮች ዋነኛው የቤተሰብ አምልኮ ነው። ቤተሰብ አንድ ላይ ሲጸልይ ልባቸው ይያያዛል። በአሁኑ ዘመን የቤተሰብን አንድነት መጠበቅ አስቸጋሪ የሆነበት ወቅት ነው። ለዚህ መፍትሔው የቤተሰብ በኅብረት አንድ ላይ ሆኖ መጸለይ ነው።

*ለቤተሰብ የማይፈጸም ተስፋ አለመግባት፡-* አገልጋይ ከቤተሰቡ ጋር የሚያቅደው ማድረግ የሚችለውን ብቻ መሆኑ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። በስሜት ተነሳስቶ የተለየ ነገር ለማድረግ ማቀድ ተፈጻሚነት አይኖረውም። ከዚህ ይልቅ የሚሻለው በየዕለቱ ጥቂትን ነገር በታማኝነት እያከናወኑ ቀስ በቀስ ወደታለመበት መልካም ግብ ለመድረስ መጓዝ ነው። ለምሳሌ የማራቶን ሩጫን መቶ ሜትር ርቀት በሚሮጥበት ፍጥነት በመሮጥ እንኳን

ይበልጥ ያሳድጋል። የፍሬያማነት ምስጢሩ ሌሎች በተመሳሳይ አገልግሎት ላይ ከተሠማሩት ጋር በኅብረትና በወዳጅነት መሥራት በመቻል ውስጥ ይገኛል።

ጓደኛ ሕይወት የበለጠ ውበት እንዲኖራት ያሞርዳል። ጓደኛ የቅርብ ሰው ስለሆነ የአገልጋይን ሕይወት ከማንም ሰው በላይ ያውቃል። የአገልጋይን ደካማና ጠንካራ ጎን በሚገባ ጠንቅቆ ያውቃል። በቅርበቱ በመጠቀም አገልጋይ ደካማ ጎኑን በማሻሻል የተሻለ የእግዚአብሔር ሰው እንዲሆን በምክርና በምሳሌያዊ ሕይወት በመታገዝ ይቀርጸዋል። ጓደኛ ጓደኛውን በሚስልበት ሁኔታ ሁልጊዜ ቀላል አይሆንም። በመካከላቸው የሚያሻክር ነገር ሊፈጠር ይችላል። ሆኖም በመካከላቸው ካለው ፍቅርና መቀባበል የተነሳ አሁን ከሚፈጠረው ግጭት ይልቅ ወደፊት ሊገኝ የሚችለውን ፍሬ ከሩቅ በማየትና የጓደኛም ዓላማ ለበጎና ለተሻለ ነገር ለማብቃት እንደሆነ ስለሚታሰብ መቀራረጽ ይኖራል። ከዚህም የተነሳ ነው መልካም ጓደኛ ያላቸው አገልጋዮች ከዛሬ ነገ እየተሻሉ የሚሄዱት። ሰዎች ዛሬ በእነርሱ ላይ የሚያየውን ስህተት እንደገና በሕይወታቸውና በአገልግሎታቸው አያይም። ስለዚህ ጓደኛ የሕይወት መስታወት በመሆን አገልጋይ ራሱን እንዲያይ የሚያደርግ የቅርብ ሰው ነው (ምሳ.27:17)።

ጓደኛ እውነትን በመናገር ይገስጻል እንጂ እውነት ባልሆነ ነገር አይሸነግልም (ምሳ.27:5-6)። አገልጋይን እውነትን በመናገር በፍቅር የሚገስጹ ሰዎች እምብዛም አይገኙም። ሰዎች አገልጋይ የሆነውንና ያደረገውን ነገር በተለይ የማይቀበሉ ከሆኑ እንዲሁ ከላይ ላይ እየተናገሩ ይተዋሉ እንጂ በልባቸው የሚሰማቸውን ቅሬታ ወይም ተቃውሞ አያቀርቡም። በአንደበታቸው ከእርሱ ጋር የሆኑ መስለው በልባቸው ግን ከእርሱ ጋር ሳይሆኑ ይቀራሉ። በአንደበታቸው «አገልግሎትህ መልካም ነው» ሲሉ በልባቸው ደግሞ በተቃራኒው «አገልግሎትህ መልካም አይደለም ስለዚህ አልቀበልም» የሚል አቋም ይኖራቸዋል። ጓደኛ ግን እንዲህ አያደርግም። የጓደኛ አንደበትና ልብ አንድ ነው። ጓደኛ ስለአገልጋዩ ሕይወትና አገልግሎት በልቡ የሚሰማውን ነገር በማካፈል የተሳሳተ ከሆነ ከክፉ መንገዱ እንዲመለስ ይመክረዋል። መልካም ያልሆነ ነገር በሕይወቱ እንዲሁም በአገልግሎቱ የሚነቀፍበት ነገር ካለ እንዲያስተካክለው የበኩሉን ጥረት ያደርጋል እንጂ «ጥሩ ነህ» እያለው እስኪወድቅ ድረስ አይጠብቅም። ወዳጅ እውነትን በመናገር ይመክራል እንጂ በለስላሳ አንደበት እየተናገረ በመሸንገል ለውድቀት አያደርስም። ይህ በእውነት ላይ የተመሠረተ ምክር ደግሞ ሕይወትን ያቀናል፣ አገልግሎትም እንዲሳካ ያደርጋል።

አገልጋይ ከትዳር ጓደኛው ሌላ ለምን ጓደኛ አስፈለገው? የትዳር ጓደኛ የምትሰጠው ድጋፍና እገዛ መኖሩ የታወቀ ነው። ሆኖም ከትዳር ጓደኛ ውጭ የሆነ ሰው ስለአገልጋዩ የሚያያቸው ጉድለቶችና ነገሮች ይኖራሉ። ከአገልጋይ ጋር ተመሳሳይ ጾታ ያለው ሰው ለምሳሌ ወንድ ስለወንድ የሚረዳው ነገር እንዲሁም ልምምድ ይኖራል። የትዳር ጓደኛ አገልጋይ ስለሆነው ባልዋ የማትረዳውን ነገር ሌላው ወንድ መረዳት የሚችለው ነገር ይኖራል። ከዚህ በተጨማሪ አገልጋይ በአንዳንድ ሁኔታዎች ለትዳር ጓደኛው ማካፈል የሚፈራቸው፣ ቢያካፍላትም ችግር ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮች በመኖራቸው ለምሳሌ አገልጋዩ በወሲብ ተፈትኖ በወሲብ እንደተፈተነ ለሚስቱ ቢነግራት ችግር ሊፈጠር ይችላል። (ይህ ሁኔታ እንደ አገልጋዩና የትዳር ጓደኛው ሁለንተናዊ ብስለትና የግልጽነታቸው ደረጃ ሊለያይ



ይችላል)። ስለዚህ ከትዳር ጓደኛ ውጭ ሌላ ተመሳሳይ ጾታ ጓደኛ መያዝ ጠቃሚነት አለው።

## በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ የጓደኝነት ምሳሌዎች

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጓደኝነት የተጠቀሱ ምሳሌዎች አሉ። አንዳንዱ ታሪኮች የከፋ ጓደኝነት አስከፊነትን የሚናገሩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ መልካም ጓደኛ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራሉ። መልካም ጓደኝነትን ከሚያሳዩ ታሪኮች መካከል ጥቂቶቹን እንመለከታለን።

**ኑኃሚንና ሩት፡-** በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለመልካም ጓደኝነት ከተነገሩ ታሪኮች መካከል የኑኃሚንና የሩት ታሪክ ይገኝበታል። ኑኃሚን በነበረችበት ሥፍራ ረሃብና ችግር በመከሰቱ እህል ወዳለበት ባዕድ ሀገር ከባልዋና ልጆችዋ ጋር ሄደች። በዚያች ሀገርም ልጆችዋ ሚስቶችን አገቡ። ከቆይታ በኋላ ባልዋና ልጆችዋ ሞቱባት። ከዚያም ኑኃሚን በሀገርዋ መልካም የጥጋብ ዘመን እንደመጣ ስምታ ወደ ሀገርዋ ለመመለስ ተነሳች። ኑኃሚን ከብዙ ሰዎች ጋር ብትወጣም አሁን ያላትን ነገር አጥታለች። ልብዋ በሐዘን ቆዝሟል፣ መንፈስዋ ተሰብሯል። ኑኃሚን ወደ ሀገርዋ ለመመለስ ስትነሳ የልጆችዋ ሚስቶች ከእርስዋ ጋር ለመሄድ ተነሱ። ሆኖም ኑኃሚን ከእርስዋ ጋር እንዲሄዱ ፈቃደኛ አልነበረችም።

ኑኃሚን የልጆችዋ ሚስቶች ከእርስዋ ጋር ወደ ሀገርዋ እንዳይሄዱ ያልፈለገችው ለምን ነበር? ኑኃሚን ለእነርሱ ከማሰብ የተነሳ እንደሆነ መረዳት እንችላለን። እርስዋ የባዕድ ሀገር ኑሮ ምን እንደሚመስል ስላየች እነርሱም ወደ ቤተልሔምም መጥተው በዚያ ዓይነት ሕይወት ውስጥ እንዲገቡ አልፈለገችም። ኑኃሚን ስለወደፊቱ ምንም ተስፋ አልነበራትም። ያለችበት መከራና ሐዘን ወደፊት መልካም ነገር ማግኘት እንደምትችል ተስፋ እንዳታደርግ እንቅፋት ሆኖባታል። እርስዋ ምንም ተስፋ ስለማይታያት ሴቶቹም ከእርስዋ ጋር በመሄድ መከራና ችግር ውስጥ እንዳይገቡ አሰበች። ኑኃሚን ሴቶቹ እርስዋ ያጣቻቸውን መልካም ነገሮች ትዳር፣ ልጆች፣ ዋስትና እና የቤተሰብ ሕይወት እንዲኖራቸው ትፈልግ ነበር። በዚያን ዘመን ለሴት ልጅ አግብቶ ትዳር መያዝ ትልቅ ክብር ነው። ሴት ያለባልዋ ምንም ክብርና በማህበረሰቡ ውስጥ ተቀባይነት አልነበራትም እንዲሁም ባልዋን አጣች ማለት ሥራም ስለማይኖራት በኢኮኖሚ አጅግ ትጎዳለች።

ይህ ለሌሎች በጎ ከማሰብ የመነጨ አሳብ በመሆኑ መልካም ነው። እንደ ጓደኛ ኑኃሚን ለልጆችዋ ሚስቶች ያሰበችውም አሳብ ከእርስዋ ጋር መከራ እንዳይቀበሉ ነገር ግን ዕድሜያቸው ገና በመሆኑ አግብተው ልጆች ወልደው በምድራቸው ሕይወታቸውን እንዲቀጥሉ ነበር። «እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል» ዓይነት አመለካከት አልነበራትም። ኑኃሚን ለራስዋ ጥቅም ብቻ ብላ የሴቶቹ የወደፊት ሕይወት እንዲበላሽ አልፈለገችም። እነርሱ ከእርስዋ እንዲለዩ የፈለገችው ለእነርሱ ከማሰብ አኳያ ነው። ኑኃሚን ሁኔታውን የተመለከተችው ከራስዋ ሳይሆን ከሴቶቹ አቅጣጫ ነው። የሴቶቹ ከእርስዋ ጋር መሄድ «ለእኔ ምን ያህል ይጠቅመኛል?» ሳይሆን «እነርሱን ምን ያህል ይጎዳቸዋል?» የሚለውን ነበር የተመለከተችው።

ቢሆንም ዳዊትን ከመደገፍ ወደኋላ አላለም። የዮናታንና የዳዊት ጓደኝነት በእኩል የጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ አልነበረም።

የዮናታንና የዳዊት ጓደኝነት በቃልኪዳን ላይ የተመሠረተ ነበር። ዮናታን በምንም ሁኔታ ውስጥ ቢሆን ለዳዊት ታማኝ እንደሚሆን ገልጾለታል። ሆኖም ዳዊት ንጉሥ በሚሆንበት ጊዜ እርሱ በሕይወት ሊኖር ተገቢውን ሥፍራ እንዲሰጠው እንዲሁም ቤተሰቡንም ጭምር እንዲያስብ ቃልኪዳን እንዲገባለት ፈልጓል። ዮናታን በዳዊት ንጉሥ መሆን ላይ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነበር።

አገልጋይ ለለጓደኝነት ከሩትና ኑኃሚን እንዲሁም ከዳዊትና ከዮናታን መልካም የወዳጅነት ግንኙነት ምን መማር ይችላል? ከእነዚህ ታሪኮች አገልጋይ ለለጓደኝነት ብዙ መማር እንደሚችል የታወቀ ቢሆንም ጥቂት እሳቦችን መጥቀሱ ለግንዛቤ ይረዳል። እነዚህም:-

☞ አገልጋይ ጓደኛው ለመሆን ያሰበው ሰው ካለ ከእርሱ ጋር ቢሆን ምን ሊያገኝ፣ ምን ሊያጣና ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍለው እንዲሁም ከእርሱ ጋር በመወዳጀት ሊሰጠው የሚችለው ጥቅም ምን እንደሆነ ማወቅ ይኖርበታል። አገልጋይ ከእርሱ መልካም ነገር ለማግኘት ብቻ ከእርሱ ጋር መወዳጀት ከሚፈልግ ሰው ጋር ከመወዳጀት መጠንቀቅ ይሻለዋል። በጓደኝነት ውስጥ ለመቀበል ከሚመጣ ይልቅ ለመስጠት ተዘጋጅቶና ወስኖ የሚመጣ ጓደኛ ጠቃሚ ነው።

☞ ሰዎች ለጓደኝነት ሊቀርቡ ምናልባት ከአገልጋይ ለማግኘት የሚፈልጉት ነገር ኖሮአቸው ወይም በይሉኝታ ተይዞ ከአገልጋይ ጋር ለመሆን አስበው ሊሆን ይችላል። ጥቅም ብቻ ፈልገው አገልጋይን የሚጠጉ ሰዎች መኖራቸው የታወቀ ነው። በተለይ አገልጋይ አውቅና ያለው ከሆነ ሰዎች ለራሳቸው ጥቅም ብለው ጠጋ ጠጋ ማለትን ያበዛሉ። አንዳንዶች ደግሞ አገልጋይን የሚቀርቡ ሰዎች ሆነው ግን የቅርብ ጓደኛ መሆን አይፈልጉም ይሆናል። ከእርሱ ጋር ያላቸውን ግንኙነት አቋርጦ ሌላ ወዳጅነት ከሌሎች ጋር ለመጀመር ይሉኝታ ይይዛቸውና በልባቸው ሙሉ ሳይፈቅዱ አብሮ ለመሄድ ያስባሉ። ስለዚህ አገልጋይ ሰዎቹ ውሳኔያቸውን እንደገና እንዲያጤኑት ዕድል ቢሰጣቸው የተሻለ ነው። የአገልጋይ ጓደኛ መሆን ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ መበዋዕትነትን የሚጠይቅ መሆኑ መግለጽ መልካም ነው። ይህን ከአገልጋይ ከሰሙ በኋላ በጓደኝነት መጽናት ከፈለጉ ምናልባት ውሳኔያቸው የጸና ይሆናል።

☞ በአብዛኛው አገልጋይ በማህበረሰቡ ውስጥ እምብዛም ተቀባይነት ያለው ሰው አይደለም። በምዕመናን ዘንድ አገልግሎቱ ፍሬያማ ከሆነ ምናልባት ብዙዎች ሊወዱት ይችላሉ። ምዕመናንም ቢሆን በአገልጋይ መገልገልን እንጂ ለእርሱ ቀርበው የእርሱ ጓደኛ ለመሆን ሊፈልጉ አይታዩም። ለዚህም የተለያዩ ነገሮች እንደ ምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል አገልጋይ ተንቀሳቃሽ ስለሆነ ከእርሱ ጋር ጓደኝነት ቢመሠረት እንደማይዘልቅ ስለሚያውቁ፣ አገልጋይን በጣም መንፈሳዊ አድርጎ ስለሚያስቡ ከምዕመናን ጋር እንደ ሌሎች ሰዎች ጓደኛ ለመመሥረት ፈቃደኛ ይሆናል ብለው ስለማይገምቱ፣ አገልጋይ ከምዕመናን ጋር የሚገናኘው 'በአገልግሎት ለለሆነ የጠለቀ ግንኙነት ከሰዎች ጋር ለማድረግ ጊዜ አይኖረውም ወይም ሁኔታዎች አይመቻቹም ... የሚሉ የሚጠቀሱ ናቸው።



☞ አገልጋይ በብዙ ሰዎች ዘንድ ታዋቂነትንና ዝናን ያተረፈ እንኳ ቢሆንም ጓደኛ ያስፈልጓል። በብዙ ሰዎች መታወቅ ማለት የብዙ ሰዎች ጓደኛ መሆን ወይም በሰዎች ዘንድ ታዋቂ የሆነ አገልጋይ የቅርብ ጓደኞች አሉት ማለት አይደለም። የታወቀ አገልጋይ ብዙ አድናቂዎችና ተከታዮች ሊኖሩት ይችላሉ። የታወቀ አገልጋይ ከሌሎች ልቆ ስለሚወጣ ከሌሎች ጋር የሚገናኝበት ሁኔታና ጊዜም አያገኝም። ይህ ብቻ ሳይሆን በፊት ከእርሱ ጋር የነበሩ ሰዎች አሁን እርሱ የደረሰበት ሁኔታ ውስጥ መምጣት ስለማይችሉ ራሳቸውን አሳንሰው ስለሚመለከቱ ወይም እርሱ አሁን አይፈልገንም ከሚል ግምታዊ አስተሳሰብ የተነሳ ከእርሱ መራቅ ይጀምራሉ። አገልጋዩ አሁን ከታዋቂነቱ የተነሳ ከተገናኛቸው ሰዎች ጋር የቅርብ ጓደኝነት ለመመሥረት ላያምናቸው ይችላል። ከእርሱ ዙሪያ ያሉ ሰዎች ማንነትና ባሕርይ ምን እንደሆነ እስኪያውቅ ድረስ ጊዜን ይጠይቃል። በለሆነም የታወቀ አገልጋይ መልካም ጓደኛ ለማግኘት ይቸገራል።

☞ በመልካም ጊዜ አገልጋይን ለጓደኝነት ከሚፈልግ ሰው ይልቅ በመከራ ወቅት ከእርሱ ጋር ለመሆን ፍላጎት ያለው ሰው የጸና እውነተኛ ጓደኛ ይሆናል። ብዙዎች አገልጋይ በጥሩ ሁኔታ ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ ከእርሱ ጋር ለመሆን ይፈልጋሉ። ለራሳቸው ጥቅም ፍለጋ ከተሳካለት ሰው ወይም ከሀብታም ወይም ከታወቀ አገልጋይ ጋር ወዳጅነት የሚፈልጉ ብዙዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ያ የሚፈልጉት ሰው በችግር ውስጥ ሊሆን አይፈልጉትም። በችግር ጊዜ አብሮ የሚሆን ግን ከአገልጋዩ አንድ ነገር ለማግኘት ሳይሆን ለእርሱ ከማሰብና እርሱን ለመርዳት ከሚመነጭ ፍላጎት ነው። ስለዚህ እነዚህ ሰዎች የአንድ መልካም ጓደኛ ባሕርይ በማሳየታቸው መልካምና ዘላቂ ጓደኞች የመሆን ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።

☞ ከንጹሕ ልብ በመነጨ ፍቅርና ርኅራኄ የሚደረግ በግል ጥቅም ላይ ያላነጣጠረ ምርጫ ወይም ድርጊት ያልታሰበ መልካም ብድራት ይዞ መምጣቱ አይቀርም። ለለዚህ የዛሬውን ጥቅም በመተው ለወደፊት የሚጠቅም ነገር የሚታይበት ከሆነ አብሮ መሆን መልካም ነው። አንድ ሰው ወደፊት ጠቃሚ ሰው ሊሆን እንደሚችል እንዴት ይታወቃል? ይህን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር መሆኑን በመረዳት እንዲሁም ከእርሱ ማንነት በመነሳት መገመት ይቻላል። እግዚአብሔር አብሮት ያለ ሰውና በማንነቱ ደግሞ ፍቅር፣ ርኅራኄ፣ ጽኑ እምነት፣ ትጋት፣ ታማኝነት እና የመሳሰሉት ባሕርያት ያሉት ሰው ለፍሬያማነት የሚያበቃው እምቅ ነገር እንዳለው ማሰብ ይቻላል። ከዚህ ሰው ጋር መሆን ለወደፊት ለመጠቀም ብቻ ሳይሆን እንዲህ ዓይነት እምቅ ችሎታ ያለው ሰው ችሎታውን በተግባር እንዲያሳይና እርሱና ሌሎች ሰዎችም እንዲጠቀሙበት ለማገዝም ነው። ሁለተኛው ዓላማ የተቀደሰና እግዚአብሔር የሚወደው ዓይነት ዓላማ ነው። ከሌላው ለመጠቀም ሳይሆን ሌላውን ለማሳደግና ብዙዎች እንዲባረኩበት የራስን ድርሻ መወጣት እጅግ መልካም ሥራ ነው።

☞ ከሁለቱ ወዳጅነት አንድ አገልጋይ በለጓደኝነት ምን ይማራል? ሁለት ሰዎች በሚገናኙበት ወቅት በውበጣቸው ከሌላው ጋር እንዲሳሳቡ የሚያደርጋቸው ነገር መኖሩን በልባቸው ውስጥ ይሰማቸዋል። ሰውየውን ሲያዩና ሲያዳምጡት ልባቸውን የሚነካ ነገርና አንድ የሚያደርጋቸውን ነገር ያገኛሉ።

☞ በፍቅር የተሞላና ሌሳውን የሚንከባከብ ልብ ሰዎችን አንድ ላይ የማስተሳሰር ኃይል አለው። አንዱ እግዚአብሔር በሌላው ውስጥ ያስቀመጠውን ጸጋና እግዚአብሔር በሕይወቱ ለማከናወን የሚፈልገውን ዓላማ ሲረዳ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም የተቻለውን ያህል ጥረት የሚያደርግ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ የራሱን ጥቅም በመተው እግዚአብሔር የመረጠውን ሰው ወደ እግዚአብሔር አሳብ የሚያደርስ እውነተኛ ጓደኛ ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው። እንዲህ ዓይነት ሰው የራሱን ነገር በመተው ጓደኛውን ማሳደግና ወደ እግዚአብሔር አሳብ ሙላት ማድረስን እንደ ተልዕኮ አድርጎ ይቀበላል። ይህ እግዚአብሔር አገልጋዮቹ በዚህ ዓለም ውጣ ውረድ ተስፋ ቆርጠው ፈቃዱን ሳይፈጽሙ እንዳይቀሩ የሚያበረታቸው ሰዎች ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነት ጓደኛ እንዲሰጥ መጸለይ አስፈላጊ ነው።

☞ ሁለት ሰዎች ጓደኝነት እንዲመሠርቱ በሁለቱ መካከል የግድ ሙሉ መመሳሰል መኖር የለበትም። በሁለቱ መካከል ሊያቀራርባቸው የሚችል ልዩነት ቢኖር መልካም ይሆናል። አንዱ ከሌላው በአንድ ነገር የተሻለ መሆኑ ይመረጣል። ለጓደኝነት የሚታሰበው ሰው ከፈላጊው በባሕርይም አንድ ደረጃ ከፍ ያለና ከእርሱ በልጦ የሚገኝ ሲሆን ሌላውን ወደ እርሱ መሳብና ወደ ላይ ማሳደግ ይችላል። በማንኛውም ሁኔታ በባሕርይ ሆነ በሌላ ነገር አነስተኛ ከሆነ ጋር መጎዳኘት ወደ ታች ሊስብ ስለሚችል ጥንቃቄ ማድረግ ይመረጣል። ስለዚህ ጓደኛ አንዱ ደሃ በሆነባቸው ነገሮች እርሱ ደግሞ ሀብታም ቢሆን የሚደጋገፍ ይሆናል።

☞ አንድ አገልጋይ ጓደኛ በሚፈልግበት ጊዜ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ያለበት ያ ሰው እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው መሆኑን ማረጋገጥ ነው። በሁለት ጓደኛሞች መካከል እግዚአብሔር እንደ ምስክር ሆኖ ሲኖር ሁለቱም ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላቸው ሲሆኑ ጓደኝነታቸው ሰበን ይሆናል።

☞ በጓደኝነት ውስጥ ታማኝነትን ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነገር ሊፈጠር ይችላል። አንዱ ከሌሎች የቅርብ ሰዎች ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ በእነርሱና በጓደኛው መካከል ለማን ይበልጥ ታማኝ እንደሚሆን ሊፈተን ይችላል። ዮናታን ከአባቱ ከሳኦልና ከጓደኛው ከዳዊት ለማን ታማኝ መሆን ነበረበት? ታማኝነት በጓደኝነት ውስጥ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ባሕርይ ነው። ታማኝ የሆነ ጓደኛ ለራሱ አይኖርም። ታማኝ ሰው በሁኔታዎች ግፊት አይለወጥም፣ ከሌላው ጋር የገባውን ቃል ኪዳን ያከብራል። የገባውን ቃልኪዳን ከሚያፈርስ ይልቅ ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል የቆረጠ ልብ አለው። በሁለት ቡድኖች መካከል «ለማን ታማኝ ልሁን?» የሚል ጥያቄ ሲነሳ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው ሰው እውነትና ጽድቅ ያለበትን መንገድ ይከተላል። የእግዚአብሔርን አሳብና ፈቃድ በማወቅ የታማኝነትን ጥያቄ ይፈታል። ታማኝ ሰው ሁኔታውን ከእግዚአብሔር ቃልና ፈቃድ አንጻር በማየት ለጓደኛው ያለውን ታማኝነት ይገልጻል። ከሰዎች ጥቅም ለማግኘት ብሎ ታማኝነቱን በመሸጥ ጓደኛውን ለከፉ አሳልፎ አይሰጥም።

ምናልባት ከእግዚአብሔር ፈቃድ አንጻር ሲታይ ከጓደኛው ጋር የገባውን ቃልኪዳን ማፍረስ የሚጠበቅበት ከሆነ የጓደኝነት ግንኙነቱን ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመታዘዝ ብሎ መተው እንደሚፈልግ አስቀድሞ በመናገር ጓደኛው ተገቢውን እርምጃ እንዲወስድ በመርዳት ማቋረጥ ይችላል። በዚህ ሁኔታ ከጓደኛው በኩል ሊደርስበት የሚችል ዋጋ መክፈል ሊመጣበት ይችላል።



ሆኖም በምንም መልኩ ታማኝ እንደሚሆን ለጓደኛው ገልጾለት ጓደኛው ከእርሱ ጋር እንዳለ እየመሰለው ጓደኛውን የሚጎዳ ነገር እንዲመጣበት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ፍጹም አይገባም። ታማኝ ወዳጅ እንዲህ የሚያደርግ ልብ የለውም።

☞ ለጓደኛ መልካም ሲሆን አለመቅናት ግን ደስ መሰኘት፣ ለራስ ደግሞ መልካም ነገር ሲሆን ጓደኛን አለመርሳት የጸና ቃልኪዳን ምልክት ነው።

ኢየሱስና ወዳጆቹ፡- ኢየሱስ በምድር ላይ ይመላለስ በነበረበት ወቅት የቅርብ ወዳጆች ነበሩት። እርሱ ለግንኙነት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጥ ነበር። ከእነዚህ ወዳጆቹ ጋር ብዙ ጊዜ ያሳልፍ ነበር። ከሕዝቡ ጋር የአገልግሎት ግንኙነት ቢኖረውም ከቅርብ ወዳጆቹ ጋር ደግሞ የቅርብ ግንኙነት ያደርግ ነበር።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሁም የክርስትና እምነት ጀማሪ ሆኖ እያለ ለቅርብ ወዳጆቹ ግልጽ ነበር። ብዙ የሃይማኖት መሪዎች ራሳቸውን በሚገባ ለተከታዮቻቸው እንዲሁም ለሚቀርቡአቸው ሰዎችም ጭምር ለመግለጽ ይፈራሉ። ኢየሱስ ግን ከደቀመዛሙርቱ ጋር በመሆን እርሱ የሚሆነውንና የሚያደርገውን ነገር እንዲያዩ ዕድል ይሰጣቸው ነበር። እርሱ ከእነርሱ የተሰወረ ሕይወት አልነበረውም። እንደ ጓደኛ ከእነርሱ የሚደብቀው ነገር አልነበረም። እነርሱ ስለእርሱና ስለትምህርቱ ማወቅ የሚችሉትን ያህል ግልጽ ሆኖላቸው ነበር።

ኢየሱስ በቃልና በተግባር ከደቀመዛሙርቱ ጋር የወዳጅነት ግንኙነት ነበረው። ከኃጢአት በስተቀር እነርሱ በሚኖሩበት ዓውድ ውስጥ ራሱን አስገብቶ መልካሙንም ሆነ ክፉውን ከእነርሱ ጋር አሳልፏል። ኢየሱስ ከእነዚህ ወዳጆቹ ጋር ይበላ፣ ይጠጣ፣ ይጓዝ፣ ይነጋገር፣ ጥያቄ ይጠይቅ፣ መልስ ይሰጥ፣ ያዝን፣ ይተክዝ ... ነበር (ማቴ.17:18፣ ማር.5:37፣ ማር.14:33)።

ኢየሱስ ከደቀመዛሙርቱ ጋር የነበረው ግንኙነት የጌታና አገልጋይ ሳይሆን የጓደኛምነት ግንኙነት ነበር (ዮሐ. 15:15)። ኢየሱስ እነርሱን ወደ ሕይወቱ አስገብቶአቸው ራሱን ገለጠላቸው። ከዚያም እርሱ ራሱ ወደ ሕይወታቸው ውስጥ ጠልቆ ገባ። ከዚህም የተነሳ እርሱ ከእነርሱ በተለየበት ጊዜ ከእርሱ ውጭ ሌላ ነገር ማሰብ አልቻሉም። ሁለንተናዊ ሕይወታቸው በውድ ወዳጃቸው በኢየሱስ ተወረሰ። የእርሱን ተልዕኮ ከግብ ከማድረስ ሌላ ምንም ዓላማ እንደሌላቸው በመግለጽ ለዚሁ ተልዕኮ መሳካት የራሳቸውን ድርሻ በማድረግ ለእርሱ ከብር ዋጋ ከፈሉ።

ኢየሱስ ከወዳጆቹ ጋር ከነበረው ግንኙነት አንድ አገልጋይ ስለጓደኝነት ምን ጠቃሚ የሆነ ቁም ነገሮችን ሊማር ይችላል? አገልጋይ ምንም ያህል በአገልግሎቱ የተሳካለት ቢመስለውና ብዙ ተከታዮች ቢኖሩትም ከጥቂት ሰዎች ጋር በጣም የጠበቀ ግንኙነት በማድረግ ማህበራዊ ፍላጎቱን ሊያሟላ ይችላል። ከጥቂት ወዳጆች ጋር ጠንካራ ኅብረት ማድረግ ሰዎቹ ለአገልጋዩ ዓላማና ተልዕኮ መስጠት እንዲኖራቸውም በጎ ተጽዕኖ ለማድረግ ዕድል ይሰጣል። በወዳጆች ሕይወት ውስጥ ሥፍራ ለማግኘት በጣም ዓይነተኛ የሆነው መንገድ ራስን ለእነርሱ ገልጾ ማሳየት ነው። ወዳጆች የአገልጋይን ሕይወት በሁሉም ሥፍራ አይተው በቃል በሚናገረውና በተግባር በሚኖረው

የሕይወት ገጽታ መካከል ምንም ልዩነት ካላዩ ሕይወታቸው ተንክተው ስአገልጋዩ ጋር ስመሰለፍ ራሳቸውን ይሰጣሉ፡፡ ስለዚህ አገልጋይ ጠንካራ ወዳጆችን ለማፍራት ግልጽ የሆነ ሕይወት ሊኖረው ይገባል፡፡

## ጓደኛ አለህ ወይ?

አገልጋይ ጓደኛ እንዳለው ለመፈተሽ ራሱን ሊጠይቅ የሚገባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ እስቲ ቆም በልና ለእነዚህ ጥያቄዎች የምትሰጠውን መልስ በሚገባ አስብ፡፡

- ✓ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ብትሆን ቶሎ ይደርስልኛል ብለህ የምታስበው ሰው አለ?
- ✓ እንደምትመጣ ሳትነግራቸው በፈለግህበት ጊዜ እቤታቸው መሄድ የምትችልባቸው ቤተሰቦች አሉ?
- ✓ ከአንተ ጋር ለመዝናናት የሚችል የቅርብ ሰው አለ?
- ✓ ገንዘብ ቢያስፈልግህና ባይኖርህ ሊያበድርልህ የሚችል ሰው አለ?
- ✓ የቤተሰብህ ችግር አይቶ ምንም ሳይጠየቅ በተጨባጭ መንገድ ሊረዳህ የሚችል የቅርብ ሰው አለ?

ከእነዚህ ጥያቄዎች ለብዙዎቹ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ያልቻለ አገልጋይ ጓደኛ እንደሌለው ማወቅ ይችላል፡፡

## የመልካም ጓደኝነት ጠንቆች

ለመልካም ጓደኝነት እንቅፋት የሚሆኑ ብዙ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከእነዚህም አንዱ ፍርሃት ነው፡፡ አገልጋይ ለሰዎች በተለይም በአጥቢያው ውስጥ ዘወትር ከሚያገለግላቸው ምዕመናን ጋር በመቅረብ ራሱን ለእነርሱ መግለጥን ይፈራል፡፡ ለምን ይፈራል? እነዚህ ሰዎች የአገልጋይን ገመና ካወቁ በኋላ ለእርሱ የነበራቸው መልካም አመለካከት፣ ይሰጡት የነበረውን ክብርና ሥፍራ ቀርቶ ሊጠሉት ይችላሉ፡፡ ሰዎች «እወቁኝና ናቁኝ» እንደሚሉት አባባል የእርሱን ትክክለኛ ማንነት ሲያውቁት ሲንቁት እንደሚችሉ በመፍራት ከሰዎች ጋር የቀረበ ግንኙነት ላለመመሥረት ይወስናል፡፡

«ሰዎች የእኔን ትክክለኛ ማንነት በተይለም የእኔን ደካማ ጎን ቢያውቁ ያገልሉኛል፣ ይንቁኛል» ብሎ የሚያስብ አገልጋይ ከሰዎች ጋር በሚገናኝበት ጊዜ ስለሌሎች ጉዳዮች እንጂ ስለራሱ ሁኔታ ማውራት አይፈልግም፡፡ በዚህ ከሌሎች ጋር ያለውን ርቀት ቀስ በቀስ እየራቃቸው ይሄዳል፡፡ ሰዎችን ወደ ሕይወቱ ለማስገባት ፈቃደኛ አይሆንም፡፡ አንዳንድ ሰዎች እቤታቸው ወዳጆቻቸውን መጋበዝ አይፈልጉም፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ወዳጆቻቸውን መጋበዝ ስለማይፈልጉ ሳይሆን ሰዎቹ እቤት መጥተው እቤት ውስጥ ያለውን ነገር እንዲሁም በቤት ውስጥ ያላቸውን ሕይወት በማየት እንዳይገምቱአቸው ነው፡፡ ከቤታቸው ሁኔታ በመነሳት ስለማንነታቸው በመረዳት እንዳይንቁአቸው በመስጋት ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አገልጋይም ወደ ሕይወቱ ውስጥ ሰዎችን ለማበጠጋት የማይፈልገው ወደ ሕይወቱ ውስጠኛው ክፍል ቢገቡ ድካሜን ያውቁና ተቀባይነት አጣለሁ ስሚል ስጋት ነው፡፡



ስዚህ ፍርሃት መንስኤው የአገልጋይ በራስ የመተማመን መንፈስ ማጣት ነው፡፡ ስለዚህ አገልጋይ ከሰዎች ጋር ጉድለትና ድካሚ ይታወቅብኝ ይሆን በሚል ፍርሃት እንዳይመላለስ በራስ የመተማመን መንፈስ ማሳደግ ያስፈልገዋል፡፡ አገልጋዩ ራሱን መቀበል ይኖርበታል፡፡ ራሱን ለመቀበል ደግሞ መለወጥ የሚችላቸውንና መለወጥ የማይችላቸውን ነገሮች ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ መለወጥ የሚችለውን ነገር በመለወጥ እንዲሁም መለወጥ የማይችለውን ነገር ደግሞ በመቀበል በእግዚአብሔር ጸጋ በመታመን መኖርን መለማመድ መልካም እርምጃ ነው፡፡ ከራስ ፍጹምነትን መጠበቅ ሳይሆን ወደ ክርስቶስ ፍጹም ሙላት ለመድረስ ዘወትር ማደግ ተፈላጊ እንደሆነ መረዳት ራስን ለመቀበል ይረዳል፡፡ አገልጋይ ሰዎችን በሚቀርብበት ጊዜ በአንድ ጊዜ የሕይወቱን ደካማ ጎን መግለጽ አይጠበቅበትም፡፡ ሰዎችን ቀርቦ የሚታመኑ ዓይነት ሆኖ ካገኛቸውና በጥቃቅን ነገሮች ታማኝነታቸውንና ግልጽነታቸውን ከፈተሸ በኋላ ራሱን ትንሽ በትንሹ እየገለጠላቸው መሄድ ይችላል፡፡

ምስጢር ማውጣት፡- ሰዎች ጓደኛሞች መሆናቸውን ከሚመሰክሩ ነገሮች አንዱ መሠረታዊ ነገር በሁለቱ መካከል ምሥጢር መጠበቁ ነው፡፡ አገልጋይ አንዱን ጓደኛዬ ነው ብሎ ምሥጢር ሲነግረው ያ ሰው ደግሞ ለሦስተኛ ሰው አሳልፎ ከነገረው ምሥጢሩ በሦስት ሰዎች ታወቀ ማለት ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ምሥጢር መሆኑ ይቀራል፡፡ ወሬው በአካባቢው እንደተዳረሰ መገመት አዳጋች አይሆንም፡፡ ስለዚህ ጓደኛ ምሥጢር አውጥቶ ከተገኘ በፍቅር ለማቅናት መምከር አስፈላጊ ሲሆን በዚህ ምክር ከድርጊቱ የማይመለስ ከሆነ ግንኙነቱን በመልካም ሁኔታ በመጠበቅ ጓደኝነቱን ግን ማቋረጥ አስፈላጊ ነው፡፡ ምሥጢር በጓደኛ በኩል ወጥቶ አገልጋይን የሚጎዳ ነገር ሲመጣ የሚያስከትለው የስሜት ጉዳት ከፍተኛ ይሆናል (ምሳ.16:28፤ 17:9)፡፡

የዳዊት ወዳጆች የነበሩ ሰዎች ከእርሱ ጋር እንዳሉ በማስመሰል በስውር ግን እርሱን መግደል ለሚፈልገው ለንጉሥ ሳኦል ዳዊት ያለበትን ቦታ ሲነግሩት ዳዊት እጅግ አዝኖ ነበር (መዝ.55:12-14)፡፡

ራስወዳድነት፡- በግንኙነት ውስጥ የራሱን ጥቅም ብቻ ለማስከበር የሚፈልግ ሰው መልካም ጓደኛ መሆን አይችልም፡፡ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ያለው ሰው ጓደኝነት መመሥረት ቢችልም እንኳን ግንኙነቱን ማቆየት አይችልም፡፡ ምክንያቱም ጓደኝነት ቢያንስ በዝቅተኛ ደረጃ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሠረታዊ የጓደኝነት ግንኙነት ውስጥ ተመጣጣኝ የሆነ ሰጥቶ መቀበል ይኖራል፡፡ በመልካም ጓደኝነት በተለይ ደግሞ በእግዚአብሔር ሰዎች ጓደኝነት ውስጥ ደግሞ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሰዎች ጥቅም በሚሆነው ነገር ዋጋ በመክፈል ማለትም የራስን ጥቅም ወደኋላ በመተው ጓደኛን ይበልጥ ማሳደግ ይታያል፡፡ በስዚህ አገልጋይ ጓደኝነትን ለመመሥረትና ለማቆየት ከፈለገ ከራስ ወዳድነት የነጻ መሆን ይገበዋል፡፡

ጊዜ ማጣት፡- ወዳጅነት ለመመሥረት ጊዜ አለመስጠት፣ በአገልግሎት በመወጠር፣ ገንዘብ ለማግኘት በሥራ በመታሠር፣ በትምህርት ራስን ለማሻሻል በትምህርት መያዝ... እነዚህን ለማግኘት ትኩረት በመስጠት ስለጓደኛ ለማሰብ ጊዜ ስለማያገኙ ጓደኛ ሳያፈሩ ይቆያሉ፡፡

## ለጓደኝነት የሚያስፈልጉ መልካም ባሕርያት

እገልጋይ ጓደኛ ሲመረጥ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል። ምክንያቱም ጓደኛ በመልካም ወይም በመጥፎ ጎን በሕይወትና በአገልግሎት ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላል (ምሳ.12:26)። ለጓደኝነት አስፈላጊ ከሆኑት ባሕርያት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም፦

**ፍቅር፦** ሰዎች ኅብረት እንዲፈጥሩ የሚያደርጉ የተለያዩ ጉዳዮች ይኖራሉ። አንዳንዶች በጋራ አንድ ዓላማ ለመፈጸም ብለው ኅብረትን ይፈጥራሉ። አንዳንዶች ደግሞ የማይዋደዱ ሆነው ነገር ግን በጋራ ሁለቱም የማይፈልጉትን ነገር ለማስወገድ ግንባር ይፈጥራሉ። ሌሎችም ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ። በማንኛውም ምክንያት ከሚፈጠሩ ግንኙነቶችና ኅብረቶች ይልቅ በፍቅር ላይ የተመሠረተው ግንኙነት ዘላቂነት ይኖረዋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለጓደኝነት የተመለከትናቸው ታሪኮች ውስጥ ጓደኝነታቸው የተጀመረው በምንም ነገር ላይ ባልተመሠረተ እውነተኛ መውደድ ነበር። ከዚህም የተነሳ መጨረሻው እጅግ ያማረ መሆን ችሏል።

**ግልጽነት፦** የሆኑትን ሆኖ መገኘት፣ ከጓደኛ ራስን አለመደበቅ፣ ለጓደኛ ግልጽ መሆን፣ ከሌሎች የተሰወረውን በግርዶሽ ውስጥ ያለውን የሕይወት ገጽታ መግለጽ- ሰዎች የሕይወታችንን መጥፎ ገጽታ ሲያዩ ወይም ሲያውቁ ለእኛ የነበራቸው ተቀባይነትና አመለካከት ይለወጣል። ጓደኛ ግን ይህን ለሰዎች ያልተገለጠውን የሕይወታችንን ገጽታ እንዲያይ ስንፈቅድለት ከቀድሞ የበለጠ ያከብረናል። የሕይወታችንን ስውር ገጽታ ማሳየት የምንፈልገው በጣም ለምንወደውና ለምናምነው ሰው ነው። ለዚህ ሰው ያለምንም ፍርሃት አሳባችንንና ስሜታችንን ምን ይሰናል ብለን ሳንሳብ እንገልጻለን። ስንዴውን ከእርክንዳድ መለየት አያስፈልገንም። እርሱ ራሱ ወንፍት እለው። እኛ ማለት የፈለግነውን ነገር መረዳት ይችላል።

ሆኖም ሙሉ ግልጽነት የማይቻል ነው። ልብስ መልበስ ያስፈለገው ለተለያዩ ምክንያቶች ቢሆንም ከእነዚህ አንዱ ለሰዎች ሲታዩ የማይገቡአቸውን የሰውነታችንን ክፍል ከሌሎች እይታ ለመሸፈን ነው። አንድ ሰው እርቃኑን ሲሆን ሰዎች ይስቁበታል። የቅርብ ሰዎችም ቢሆኑ ግራ ይገባቸዋል፣ በእርሱ ሥራ ሲያፍሩበት ይችላሉ። ሆኖም ከትዳር ጓደኛው ጋር ሲሆን ምንም የሰውነቱን አካል ላይደብቅ ይችላል። በተመሳሳይ መልኩ ሰው ውስጣዊ ሕይወቱን በሚገልጥበት ጊዜ አውዱንና ሰዎቹ ምን ዓይነት ቅርበት እንዳላቸው ማየቱና በጥበብ ማድረጉ የተሻለ ነው። አንዳንድ ጊዜ ሙሉ ግልጽነት መልካም ቢሆንም በውብጣቸው የሚሰማቸውን አሳብና ስሜት ያለምንም ወሰን የሚገልጡ ሰዎች ራሳቸውን የመግዛት ችግር እንዳላቸው መገመትም ይቻላል።

እንግዲህ አገልጋይ በሕይወቱ ለማደግና በአገልግሎቱ ፍሬያማ እንዲሆን በፈታኝ ሁኔታዎች ከእርሱ ጋር ሆኖ የሚደግፈው እንዲሁም ስኬትን በሚያገኝበትና በድል ስሜት በሚሆንበትም ጊዜ ከጎኑ ሆኖ እግዚአብሔር ያደረገለትን እንዲያስታውስ የሚረዳው ጓደኛ ያስፈልገዋል። ስለዚህ አገልጋይ ፈሪሃ እግዚአብሔር ያለው፣ ታማኝ፣ እርሱን ወደ ተሻለ የሕይወትና የአገልግሎት ደረጃ ሊመራ የሚችል፣ የተሰጠ፣ ጥቅም ፈላጊ ያልሆነ... ጓደኛ ለማግኘት እግዚአብሔርን መጠየቅ እና የግል ጥረትም ማድረግ ተገቢ ነው።



ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።

1. *በሕይወትህ ጓደኛ እንደሚያስፈልግህ እጅግ ያስብክበት ጊዜ ይኖራልን? ጓደኛ እንደሚያስፈልግህ ያሳሰበህ ጉዳይ ምን ነበር?*
2. *ጓደኛ በማጣትህ የተጎዳህበትን እንዲሁም ጓደኛ ስላለህ የተጠቀምክበትን ሁኔታዎች ታስታውሳለህን? እስቲ ይህን ለሌሎች ሰዎች አካፍል።*
3. *በሕይወትህ ጓደኛ እንዳታገኝ ያገዱህ ወይም እንዲታገኝ ያገዙ የግል ባሕርያትን ዘርዝራቸው። እነዚህን እንዴት ለማሻሻል ታስባለህ?*

እንግዲህ መልካም ጓደኝነት ለሕይወትና አገልግሎት ፍሬያማነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ያበረክታል። አገልጋይ ጓደኝነት ለመመሥረት ወይም ከሰዎች ሁሉ ጋር በመልካም ግንኙነት ለመኖርና ለማገልገል ጥረት በሚያደርግበት ጊዜ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ሊኖረው የሚገባውን የግንኙነት ሁኔታ ማጤን ይኖርበታል። አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለው ግንኙነት ሚዛኑን ካልጠበቀ መንፈሳዊ ሕይወቱንና አገልግሎቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሊሆን ይችላል። ስለዚህ አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው ይገባል? አገልጋይ በወሲብ ፈተና እንዲወድቅ ሊያደርጉ የሚችሉ ሁኔታዎችስ ምንድናቸው? አገልጋይ በወሲብ ፈተና እንዳይወድቅስ ምን ዓይነት እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል? አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ቢወድቅስ ምን ቢያደርግ የተሻለ ይሆናል? እነዚህንና የመሳሰሉትን አሳቦች በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን።

## ምዕራፍ 6

### የተቃራኒ ጾታ ግንኙነትን በሚዛን ማድረግ

አገልጋይ በቤተክርስቲያን ውስጥ በሚያገለግልበት ወቅት ከብዙ ዓይነት ሰዎች ጋር ይገናኛል:: ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ከተቃራኒ ጾታ መገናኘት ነው:: አገልጋይ በአደባባይ በመስበክና በማስተማር እንደሚያገለግል ሁሉ በግል ምዕመናንን በመጎብኘት፣ በማማከር፣ ከእነርሱ ጋር በግል ጊዜ ወስዶ በመጸለይ ያገለግላል:: አገልጋይ በተለይ በግል ከምዕመናን ጋር በሚያሳልፍበት ወቅት በተቃራኒ ጾታ ፈተና ሊጠመድ የሚችልባቸው እያሌ ሁኔታዎች ይኖራሉ::

በአብዛኛው መንፈሳዊ አገልግሎት የሚሰጡ አገልጋዮች በቤተክርስቲያን ውበጥ የሚታዩትን የተለያዩ የግልና የጋራ ችግሮች ሲያወሩ ይደመጣሉ:: ሆኖም አልፎ አልፎ ካሳጋጠመ በስተቀር ብዙ አገልጋዮች በተቃራኒ ጾታ ፈተና ያጋጠማቸውን ፈተና ሲናገሩ አይደመጡም:: የአገልጋዮችን በተቃራኒ ጾታ መፈተን አስማውራት ችግሩ እንደሌለ አያመለክትም:: ይልቁንም ችግሩ እንዳለና አገልጋዮች ግን ማውራት የማይፈልጉት ጉዳይ እንደሆነ መመልከት ይቻላል:: አገልጋዮች በተቃራኒ ጾታ መፈተናቸውን ለመናገር የሚፈሩባቸው ምክንያቶች ምንድናቸው? መንፈሳዊ አገልጋዮች ይህን አጀንዳ ማንሳት ከማይፈልጉባቸው ምክንያቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:: እነርሱም:-

- ✓ መንፈሳዊ ሰው በተለይም የእግዚአብሔር አገልጋይ የሆነ ሰው የወሲብ ስሜትም እንደሌለው መታሰብ
- ✓ አገልጋዩ ሥጋዊ ምኞቱን ገና ያልገደለ ሥጋዊ ሰው እንደሆነ ስለሚያስገምተው መንፈሳዊ ስመባል ብቻ ችግሩን መደበቅ
- ✓ መንፈሳዊ አገልጋይ ስሜቱን በመግዛት ከእግዚአብሔር ጋር መጨረስ አለበት እንጂ ይህን ጉድ ወደ ውጭ ማውጣት እንደሌለበት መገመት
- ✓ አገልጋዮች እንዲሁም የቤተክርበቲያን መሪዎች ይህን እንደ ነውር ስለሚያዩ ችግሩን ሲናገር አገልግሎቱ በአደጋ ላይ ሲወድቅ እንዲሁም በእነርሱ ዘንድ ያለው ተቀባይነት ሲቀንስ እንደሚችል ማሰብ
- ✓ የሰሙት ሰዎች ምሥጢሩን ለሌሎች ሰዎች በተለይም ለትዳር ጓደኛ ቸው መናገር እንደሚችሉ መስጋት
- ✓ በዚህ ጉዳይ አገልጋይን ሊረዱ የሚችሉ የበሰሉ ሰዎች በአካባቢው አለመኖራቸውና የመሳሰሉት ናቸው::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱና ሌሎችም ተመሳሳይ ምክንያቶች አገልጋዮች ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያላቸውን የግንኙነት ችግር አስመነጋገራቸውን እንዲሁም ቤተክርበቲያንም በዚህ ጉዳይ ላይ ግልጽ ትምህርት አለመሰጠቷን ያመለክታሉ:: ከዚህም የተነሳ ጥቂት የማይባሉ አገልጋዮች በተለያዩ ሥፍራዎች በዚህ ፈተና ወድቀው ሕይወታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲሁም በቤተክርስቲያን ስምና በምዕመናን ላይ ትልቅ መንፈሳዊና ሥነልቦናዊ ጉዳት አድርስዋል::

አገልጋይ ከሰዎች ሁሉ ጋር መልካም ግንኙነት ሊኖረው ይገባል:: ሐዋርያው ጳውሎስ ስጢሞቴዎስ «ሽማግሌ የሆነውን አትግሥጸው፣ እርሱን ግን እንደ አባት፣ ጎበዞችን እንደ ወንድሞች፣ የሽመገሉትን ሴቶች



እንደ እናቶች፣ ቆነጃጅቱን እንደ እኅቶች በፍጹም ንጽሕና ለምናቸው» (1ጢሞ.5:1-2) በማለት ከወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ከዕድሜያ እኩያ ደግሞ ከታላላቆችና ከታናናሾች ጋር ምን ዓይነት ግንኙነት ሊኖረው እንደሚገባው ይመክረዋል:: ስለዚህ ዝምታውን ሰብሮ ለችግሩ አማራጭ መንገድ መፈለግ መልካም ይሆናል::

አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ሊኖረው በለሚገባ ግንኙነትና እንዴት ራሱን ተገቢ ካልሆነ የተቃራኒ ጾታ ግንኙነት መጠበቅ እንደሚችል ከማየታችን በፊት አንዳንድ ቅድመ አሳቦችን መጥቀስ ለግንዛቤ ይረዳል::

- ✓ አገልጋይ ከወሲብ ፈተና ራሱን የመከላከል የተፈጥሮ ወይም መንፈሳዊ ክትባት አልወሰደም:: ስለዚህ ማንኛውም አገልጋይ በወሲብ ሊፈተን ይችላል:: ማንም ጥሩ መንፈሳዊ አገልጋይ ነው የሚባለው አገልጋይ ሁሉ ለወሲብ ፈተና የተጋለጠ ነው::
- ✓ የወሲብ ፈተና ሁልጊዜ ከሴት በኩል ይጀምራል ማለት ስህተት ነው:: ሴት ዘወትር ሰይጣን ተጠቅሞ ወንድን ወይም አገልጋይን የሚፈትንበት መሣሪያ ነው ብሎ ማሰብ ስህተት ነው:: የወሲብ ፈተና በአገልጋይም በሴትዋም ሊጀምር ይችላል::
- ✓ መንፈሳዊ አገልግሎት መከታ በማድረግ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጭ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ተገቢ ያልሆነ ግንኙነት የሚፈልጉ አገልጋዮች ይኖራሉ:: ብዙ ሴቶችን በዝሙት ኃጢአት የጣሉ አገልጋዮች እንዳሉ ግልጽ ነው::
- ✓ መንፈሳዊ አገልግሎት እንፈልጋለን በማለትም ሌላ ስውር ዓላማ ያላቸው ሴቶችም እንዳሉ ግልጥ ነው:: አገልጋዮችን ለማጥመድ የተሰለፉ እና የጣሉ ሴቶችም እንደሚኖሩ ማወቅ አስፈላጊ ነው::
- ✓ በማንኛውም ምክንያትና መንገድ አገልጋይ ከምዕመናን ጋር የሚፈጸመው የወሲብ ግንኙነት ኃጢአት ነው::
- ✓ አገልጋይ ስለወሲብ ፈተና በማወቅ አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድረግ አለመቻልና ቸልተኛ መሆን ኃላፊነትን በትክክል ያስመወጣት ምልክት ነው::
- ✓ በአገልግሎት ግንኙነት ውስጥ ተገቢውን የግንኙነት ርቀት ወይም ወሰን መጠብቅ ያለበት አገልጋዩ ነው:: አገልጋዩ በምንም መንገድ ለሚፈጸመው የሥነምግባር ጉድለት በቅድሚያ ተጠያቂ ነው:: አገልጋዩ አስቀድሞ ተገቢውን የማምለጫ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል::
- ✓ አገልጋይ ከሚያገለግላቸው ምዕመናን ጋር በወሲብ ኃጢአት ቢወድቅ የሚወሰድበት የእርምት እርምጃ ከፍተኛ ይሆናል:: ምክንያቱም አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን ምዕመናንን የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነትና ሥልጣን ተሰጥቶት ሥልጣኑን አለአግባብ በመጠቀምና ኃላፊነቱን በመዘንጋት ምዕመናንን የሚጎዳ ተግባር በመፈጸሙ ነው (ማቴ18:6)::

እነዚህ መሠረታዊ የሆኑ ነጥቦችን መረዳት ቀጥለው በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱትን አሳቦች ለመገንዘብ እገዛ ከማድረጉም በላይ አንዳንድ በሕዝቡ ዘንድ ያሉትን ትክክለኛ ያልሆኑ አስተሳሰቦችን ለማስተካከል ይረዳል::

ሳይቆርጥ እርሱን ለመመለስ ጸጋ፣ ጥበብና እውቀቱ ያለው ሰው አገልጋዩን እየሞረደ የተሻለ አገልጋይ ሆኖ እንዲወጣ ከዚህ ውድቀት ሊያወጣው ይችላል::

## አገልጋይ በዝሙት ላለመውደቅ እንዴት መከላከል ይችላል?

አገልጋይ ምዕመናን በኃጢአት እንዳይወድቁ ራሳቸውን የሚጠብቁበትን መንገዶች እንደሚያሳያቸው ሁሉ ራሱም በኃጢአት በተለይም ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት ችግር እንዳይመጣበት ራሱን መጠበቅ የሚችልባቸውን መንገዶች መቀየስ ይኖርበታል:: ከእነዚህም የመከላከያ መንገዶች አንዳንዶች ከዚህ በታች ተጠቅሰዋል:: እነርሱም:-

**ራስን ማወቅ:-** አገልጋይ ራሱን ማወቅ ከዝሙት ኃጢአት እንዲከላከል ይረዳዋል:: አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት ምን ጠንካራና ደካማ ጎን እንዳለው ካወቀ ራሱን ለደካማ ጎኑ በማያጋልጥ ሁኔታ መመላለስ ይችላል:: አገልጋይ ሰው እንደሆነና በዚህ ፈተና እንደማንኛውም ሰው መፈተን እንደሚችል ሲቀበል ይገባል:: «እኔ በዚህ ፈተና አልወድቅም» በማለት በራስ መተማመን ማብዛት የማያዛልቅ ወቅታዊ መፍክር ብቻ ሆኖ የሚቀርበት ሁኔታ ሲመጣ ይችላል:: ስለዚህ «ከዝሙት ሽሽ» በሚለው መርሕ አሳብ መሠረት እየኖረ በጥበብና በማስተዋል በእግዚአብሔር ላይ ታምኖ ማገልገል መልካም ነው::

**አገልጋይ የትዳር ሕይወቱን በሚገባ ማጠናከር:-** ይህ ከፈተና ባያድንም በፈተና ከመጡደቅ ሊጠብቅ ይችላል:: አገልጋይ የሚፈልገው ፍላጎት በተለይም በተቃራኒ ጾታ በኩል ሲሟላለት የሚገባው ፍላጎት ከተሟላለት ቢፈተንም የመቋቋም ኃይል ያገኛል:: «ይህ እኔ ያጣሁት ነገር ስለሆነ በዚህ በኩል ማግኘት አለብኝ» ብሎ በፈተናው ውስጥ ጭልጥ ብሎ አይገባም::

**ከተቃራኒ ጾታ ጋር ያለውን ግንኙነት በገደብ ማድረግ::** የሴት ወዳጅ አለመሆን አስፈላጊ ነው:: ተቃራኒ ዋልታዎች እንደሚሳሳቡ ሁሉ ተቃራኒ ጾታዎችም የመሳሳብ ኃይል በመካከላቸው ስለሚኖር ተገቢ ያልሆነ መቀራረብ አለማድረግ ይረዳል:: ከወንዶች ይልቅ ከሴቶች ጋር ለመሆን የሚፈልግ አገልጋይ ለምን እንዲህ እንደሚያደርግ ራሱን ሊጠይቅ ይገባል:: የሴት ወዳጅ የሆነ አገልጋይ ወሰኑን ጠብቆ ከሚሄድ አገልጋይ ይልቅ በወሲብ ፈተና የመውደቁ ዕድል ከፍተኛ ነው:: በተጨማሪም ከተቃራኒ ጾታ ጋር ወሲብ ነክ የሆኑ ቀልዶችንና ጫወታዎችን ማስወገድም ያስፈልጋል:: ከአገልጋይ እንደበት የማያንጹ ወሲባዊ የሆኑ ቀልዶች፣ አስተያየቶችና ንግግሮች መሰማት የለባቸውም:: አገልጋይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ትክክለኛ የአገልግሎት ወሰን ሊያከብር ይገባል::

**አንድ አገልጋይ ከእግዚአብሔርና ከቤተክርስቲያን የተሰጠው የአገልግሎት ኃላፊነት ምን ያህል ታላቅና ክብር እንደሆነ ዘወትር ማሰብ:-** እግዚአብሔር የሰጠው መንፈሳዊ አገልግሎትና ለዚህም አገልግሎት መጠራት ትልቅ ክብር ነው:: እግዚአብሔር ብቃት የሌለውን ሰው ጠርቶ በምሕረቱ ብቻ የታላቁ ጌታ አገልጋይ እንዲሆን እንዳደረገው ዘወትር በማሰብ ይህን ታላቅ ክብር ያለውን ነገር ሊያዋርድ ከሚችል ከማንኛውም ክፉ ነገር ለመሸሽ ያስችላል:: የጥሪው ታላቅነት በውስጡ የሞላው ከሆነ አሳቡ የተያዘው በዚያ ስለሆነ ለዚህ ርካሽ ለሆነው ኃጢአት ራሱን አይሰጥም::



**ጊዜያዊ የስሜት እርካታ ብሎ የራስን እምነትና አገልግሎት ማቃለል የሕሊና ጠባሳ ጥሎ እንደሚያልፍ ማሰብ:-** የወሲብ ኃጢአት መፈጸም በሕይወት፣ በቤተሰብና በአገልግሎት ላይ ሊያስከትል የሚችለው ጉዳት እጅግ ከፍተኛ ነው:: ስለዚህ እንደ መንፈሳዊ እንዲሁም እንደ ባለአዕምሮ በሰከነ ሁኔታ በማሰብ ውጤቱን ማነጻጸር ወደዚህ ዓይነት ድርጊት ሊያመራ ከሚችል ሁኔታ እንዲርቅ ያግዟል::

**እግዚአብሔር ራስን የመግዛት ጸጋን እንዲጨምር መጸለይ:-** አገልጋይን ከፈተና ወጥመድ ሊያስመልጥ የሚችል እግዚአብሔር እንዳለና ከተጠየቀ ጸጋውን ሊሰጥ ዝግጁ መሆኑን ምንጊዜም ሊረሳ አይገባም:: ቁምነገሩ የወሲብ ፈተና ሲጀምር በግልጽ ለእግዚአብሔር ሁኔታውን በመግለጽ ራስን የመግዛት ጸጋ እንዲሰጥ መለመን አስፈላጊ ነው:: ሆኖም ግን በዚህ ላይ መረሳት የሌለበት አንድ ነጥብ አለ:: ይኸውም እግዚአብሔር ራሱ አገልጋዩን ጎትቶ ካለበት ሁኔታ እንዲያወጣው ብቻ መጠበቅ የራስን ድርሻ መዘንጋት ነው:: በእርግጥ እግዚአብሔር ራስን የመግዛት መንፈስ ይሰጣል:: ሆኖም አገልጋይ በወሲብ ሲፈተን ከዚያ ሁኔታ በመሸሽ ራሱን መርዳት ይችላል:: ስለዚህ አገልጋይ አያውቀ በወሲብ ፈተና ውስጥ ሊያስገባው በሚችል ሁኔታ ውስጥ ቁጭ ብሎ «እግዚአብሔር ሆይ አድነኝ» ማለት አባቶች «መንገድ ዳር አድሮ ጌታ ሆይ በሰላም አሳድረኝ» እንደሚሉት ከንቱ ጸሎት ነው:: ስለሆነም አገልጋይ እግዚአብሔርን እየለመነ እንዲሁም ራሱንም የሚያድንበትን መንገድ መፈለግ እንደሚገባው መርሳት የለበትም::

**ሰይጣን የአገልጋይን ሕይወትና አገልግሎት ለማጥፋት የሚጠቀምበት መንገድ መሆኑን በማወቅ ይህ ሁኔታ ሲመጣ አጥብቆ መዋጋት:-** አገልጋይ በዝሙት ኃጢአት ከወደቀ ተመልሶ እግዚአብሔርን እንደገና ለማገልገል ያለው ድፍረት አነስተኛ ነው:: በኅብረተሰቡ ዘንድ በዝሙት ኃጢአት መውደቅ እጅግ አስከፊ በደል ተደርጎ ስለሚቆጠር አገልጋይ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው ምስክርነት ስለሚበላሽ ያለው ተቀባይነት በአንድ ጊዜ ይወርዳል:: ሰይጣን ይህን ስለሚያውቅ እግዚአብሔር በሕይወታቸው የሚጠቀምባቸውን አገልጋዮች በዚህ ወጥመድ ውስጥ ለማስገባት ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል:: ሰይጣን ኃጢአቱ የሚያስከትለውን ጉዳት ሸፍኖ አሁን አገልጋዩ ሊያገኝ የሚችለውን ጊዜያዊ ደስታ ያሳየዋል:: አገልጋዩ በዚህ የሰይጣን ሽንገላ ከወደቀ በኋላ ደግሞ እጅግ ከፉ የተባለ ኃጢአት እንደፈጸመ በማሳየት ራሱን እንዲጠላ፣ እግዚአብሔር እንደማይቀበለውና ቤተክርስቲያንም እንደምትጸየፈው በማሳየት በበደለኛነት ስሜት ተይዞ ያለይቅርታ እንዲኖር ለማድረግ ጥረት ያደርጋል:: ስለዚህ አገልጋይ ሆይ! ሰይጣን የሚያቀርብልህ ይህ ጊዜያዊ ደስታ የሚገድል መርዝ መሆኑን በመገንዘብ ሳለመጠጣት የሚመጣበትን መንገድ አጥብቀህ ጠብቅና ተዋጋው!

**የቅርብ ጓደኛ ወይም መንፈሳዊ ሞግዚት ካለ ለእርሱ በማካፈል ምክር ማግኘት:-** አገልጋይ ጓደኛ ከሚያስፈልግበት ምክንያቶች አንዱ ከተቃራኒ ጾታ ጋር ባለው ግንኙነት የወሲብ ፈተና ሲያጋጥም ሁኔታውን በማካፈል ምክር ለማግኘት ነው:: አገልጋይ ለእርሱ ቅርብ ለሆነው ታማኝ ጓደኛው ወይም ለመንፈሳዊ ሞግዚቱ ምሥጢሩን ቢያካፍል የተጸነሰው ኃጢአት እንዳይወለድ ለመከላከል ይረዳል:: ይህ ጓደኛ ወይም መንፈሳዊ ሞግዚት ከአገልጋዩ ጋር አብሮ ይጸልያል እንዲሁም መውሰድ የሚገባውን አማራጭ መንገዶች ያሳየዋል:: አገልጋዩም አስቀድሞ በመናገሩ ራሱን ለጓደኛው

ችሏል። እርሱ ከልደት እስከ እርገቱ ድረስ ጊዜን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል አሳይቷል (ዮሐ. 9:4፣ 17:4፣ 7:6፣ 12:23.27፣ 13:1፣ 17:1)

## የጊዜ አጠቃቀም መርሆዎች

ጊዜን በሚገባ ለመጠቀም አንዳንድ መርሆዎችን ማወቅ ይጠቅማል። ከእነዚህም መርሆዎች መካከል የሚከተሉት አሳቦች ለአገልጋይ ጠቃሚ ናቸው። ስለዚህ እያንዳንዱ አገልጋይ ከችግሩ አኳያ የሚስማማውን መርሕ አሳብ በመቀበል ጊዜውን ፍሬ ሲያስገኝ በሚያስችለው በተሻለ ሁኔታ መጠቀም ይችላል።

### *1. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ*

እግዚአብሔር በዚህ ዓለም አማኞች በተለይም በአገልጋዮች በኩል ሲፈጽም የሚፈልገው ሥራ አለው። ይህ እግዚአብሔር ልጆቹና አገልጋዮች እንዲሠሩት የሚፈልጋቸው ነገሮች በቃሉ ውስጥ ተጠቅሰዋል። በቃሉ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ማድረግ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው። ሆኖም አንድ ሰው ሁሉን ነገር ማድረግ አይችልም። እግዚአብሔር በእያንዳንዱ አማኝና አገልጋይ መሥራት የሚፈልገው ነገር አለው። ስለዚህ «ለእኔ እንደ አገልጋይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ምንድነው? አሁን ባለሁበት ሁኔታ እግዚአብሔር ምን እንዲሠራ ይፈልጋል?» የሚለውን ጥያቄ በመመለስ የእግዚአብሔርን አሳብ ማወቅ ይቻላል። ይህ አንድ አገልጋይ እንዲሠራው የተሰጠው አገልግሎት የሕይወት ዓላማው ይሆናል። አገልጋዩ መኖር የሚጀምረው ለዚህ እግዚአብሔር ላሳየው ዓላማ ይሆናል ማለት ነው።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ለሕይወት አቅጣጫን ስለሚሰጥ ጊዜን በተገቢው ሁኔታ ለተገቢው ሥራ ማዋል ይቻላል። ከእግዚአብሔር የሕይወት አቅጣጫ ያገኘ አገልጋይ ያገኘውን ሥራ ከመሥራት ይልቅ እግዚአብሔር እንዲሠራ ያሳየውን ሥራ ይሠራል። እርሱ በየዕለቱ የሚሠራው ሥራ ሁሉ እግዚአብሔር ወዳሳየው ግብ የሚመራው ይሆናል። አገልግሎት የሚለጠው ከዓላማው አኳያ በማየት ነው። ከዓላማው ጋር ግንኙነት ለሌለው ሥራ ቅድሚያና ትኩረት አይሰጥም። ጊዜውን የሚጠቀመው እግዚአብሔር በልቡ ያስቀመጠውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ነው።

### *2. ራስን መግዛት*

አንድ አገልጋይ ጊዜውን በሚገባ ለመጠቀም ቢፈልግ ራሱን ሥርዓት ባለው ሁኔታ መምራት መጀመር ይኖርበታል። አገልጋይ ጊዜን መቆጣጠር አይችልም። መቆጣጠር የሚችለው ራሱን ብቻ ነው። ጊዜ ስጦታ ስለሆነ አገልጋይ መቆጣጠር የሚችለው ጉዳይ አይደለም። ጊዜን መጨመር፣ መቀነስ፣ ወደፊት ማሳለፍ፣ ወደኋላ መመለስ ፈጽሞ የማይቻል ነው። ነገር ግን አሁን ያለችውን ጊዜ መጠቀም የሚችልበትን ሁኔታ መፍጠር ይችላል። ይህም የሚሆነው ራስን በመግዛት በአስፈላጊ ወቅት አስፈላጊውን ነገር ለመሥራት በሚያስችል ሥርዓት ያለውን ሕይወት በመስማመድ ነው።



ጊዜን ፍሬያማ በሆነ መስክ ለመጠቀም ራስን ለሥርዓት በማስገዛት ራስን ማሰልጠንን ይጠይቃል። ብዙዎች ጊዜና ችሎታ እያላቸው ራሳቸውን በመግዛት አንድ የተወሰነን ሥራ በጥሞና በተከታታይ መሥራት ባለመቻላቸው በአገልግሎታቸው የሚጠበቅባቸውን ያህል ስኬታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል። በቅርብ ጊዜ አንድ በሀገራችን ደረጃ ጥሩ ትምህርት ያለው ሰው «አንተ እንዴት ነው እስካሁን አንድ የሚታይና ለትውልድ የሚተርፍ ሥራ ያልሠራኸው?» ተብሎ ሲጠየቅ «እግሮቼን ከወንበር ጋር ካላሠሩኝ በስተቀር አንድ ቦታ ለረጅም ጊዜ ተቀምጬ አንድን ነገር መሥራት አልችልም» በማለት መናገሩ ትዝ ይለኛል። ለአንድ ነገር ትኩረት ሰጥቶ ጊዜን በአንድ በተወሰነ ነገር ላይ ማዋል ራስን መግዛትን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። በአገልግሎታቸው ዓላማ ያላቸውና ራሳቸውን በመግዛት ለዓላማቸው የተሰጡ አገልጋዮች ከሰዎች የላቀ ችሎታ ባይኖራቸውም ባላቸው ነገር ብዙ ሰዎችን እንዲሁም የሚቀጥለውንም ትውልድ ሲያገለግሉ የሚችሉ ሥራዎችን መሥራት ይችላሉ።

### *3. ብድራት/ስኬት/ በአልግሎት ብዛት አለመሆኑን ማወቅ*

በእግዚአብሔር መንግሥት አንድ አገልጋይ ብድራት የሚያገኘው ባገለገለው የጊዜ መጠን አይደለም (ማቴ.20:1-16)። እግዚአብሔር ከጧት እስከ ማታ ድረስ በአገልግሎት መጠመድን ሳይሆን እርሱ እንዲሠራ የሚፈልገውን ሥራ መሥራትና የተሠራው ሥራ ጥራት ያለው መሆኑን ነው። የእግዚአብሔር ትኩረት ለሥራው የዋለው ጊዜ ላይ ሳይሆን የእርሱ አሳብ መከናወኑ ላይ ነው።

በአገልግሎት ስኬታማ ለመሆን በትጋት መሥራት አስፈላጊ ነው። ያለትጋት ስኬት አይገኝም። ዳተኛና ታካች ሰው ስኬታማ መሆን አይችልም። ሆኖም ግን እንደ ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ትጋት ወይም ትጉህ ሠራተኛ መሆን ለብቻው ወደ ስኬት አያደርስም። ስኬት በእግዚአብሔርና በሰው የጋራ ሥራ ይገኛል። አገልጋይ የራሱን ድርሻ ሲያከናውን እግዚአብሔርም የራሱን ድርሻ ያበረክታል። አገልጋይ ሰው ማድረግ የሚገባውን ነገር ያደርጋል። አገልጋይ ዘሩን ይዘራል፣ እግዚአብሔር ያበቅላል፣ አገልጋይ ይኮተኩታል እንዲሁም ውኃ ያጠጣል፣ እግዚአብሔር ያሳድጋል እንዲሁም ፍሬ እንዲያፈራ ያደርጋል። ሁለቱም በጋራ በመሥራት መልካም ፍሬ ያገኛሉ (1ቆሮ.3:5-9)። አገልጋይ በትጋት ሳይሠራ እንዲሁም እግዚአብሔር ሳይባርከው ስኬትን አያገኝም (ምሳ.23:4፣ መክ.11:6)። እግዚአብሔር ግን የሚባርከው በትጋት የሚሠራውን አገልጋይ ነው።

### *4. ከመጠን በላይ በሥራ አለመጠመድ*

መሥራት የሚገባቸውን ነገሮች የማይሠሩ አገልጋዮች እንዳሉ ከመጠን በላይ በአልግሎት ተጠምዶ ለሌላ ነገር እንዲሁም ለቤተሰቦቻቸው ጊዜ የሌላቸው አገልጋዮች ሞልተዋል። ብዙ አገልጋዮች በሳምንት አንድ ሠራተኛ መሥራት ከሚገባው እርባ ሰዓት በላይ ይሠራሉ። አገልጋዮች በአገልግሎት የሚጠመዱባቸው ምክንያቶች የተለያዩ ናቸው። አንዳንዶቹ ምክንያቶች ከራሳቸው ከአገልጋዮቹ የሚመነጩ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከውጭ ተጽዕኖ የሚመጡ ናቸው። እነርሱም፡-

- ✓ ለሥራው ትኩረት ወይም ክብደት አለመስጠት ወይም ሥራው ቶሎ እንዲሠራ የሚያስገድድ ሁኔታ አለመኖር ነው::
- ✓ ሥራው መሠራት የሚገባው ነገር ሆኖ እያለ ሥራውን መርሳት - አገልጋዮች መሥራት የሚገባቸውን ሥራ የሚረሱት ከሆነ ከሥራው ጋር የተያያዘ የሆነ ችግር መኖሩን ያመለክታል:: አንዳንድ የሥነልቦና ባለሙያዎች ሰዎች አንድን ነገር የሚረሱት ነገሩ ለእነርሱ እርካታ ወይም ደስታ ስለማይሰጣቸው እንደሆነ ይናገራሉ:: በዚህ መሠረት አገልጋዮች የተሰጣቸውን ሥራ የሚረሱት ሥራውን ስለማይወዱት ወይም ሥራውን በመሥራት የሚያገኙት መልካም ነገር እንደሌለ በመገመት ይሆናል::
- ✓ ሥራው ከባድና አስቸጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ቶሎ ከመጀመር ይልቅ ያቆዩታል:: ሥራውን ከመፍራት የተነሳ መሥራት እንዳለባቸው እያወቁ ግን ሳይሠሩ ይቆያሉ::
- ✓ በሁለት እሳብ መወጠር ማለትም ሥራውን ልሥራው ወይስ ልተወው የሚል የሚያመነታ ልብ ካላቸው ሥራውን በጊዜው አይጀምሩትም:: ሥራን በወቅቱ ለመሥራት ውሳኔ ማድረግን ይጠይቃል::

እነዚህና ሌሎች ምክንያቶች በሚኖሩበት ወቅት ሥራዎችን እንዴት በወቅቱ መሥራት ይቻላል? ተገቢውን ሥራ በተገቢው ወቅት ለመሥራት የሚረዱ እንዳንድ ጠቃሚ አሳቦች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል:: እነርሱም:-

☞ የሥራውን አስፈላጊነት አስቀድሞ ማወቅ መልካም ነው:: ይህም የሚቻለው ስለሥራው በቂ መረጃ በመሰብሰብ ነው:: የሥራው አስፈላጊነት ከታመነበት በኋላ ተገቢውን ውሳኔ ወዲያውኑ መወሰን ያስፈልጋል::

☞ በጸጥታ መንፈስ ውስጥ ሆኖ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በጸሎት መፈለግና ማወቅ ሥራው የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ ቶሎ ለመመለስ ይረዳል:: የእግዚአብሔርን አሳብ ደግሞ ልብን ከፍቶ ማዳመጥ ያስፈልጋል:: ከዚያ በኋላ ሥራውን በሙሉ ኃይል መሥራት ይቻላል::

☞ ሥራው እንዲረሳ የሚያደርግ ወይም እንዳይሠራ የሚያደርግ የተሰወረ ዓላማ ካለ መፈተሽ አስፈላጊ ነው:: አገልጋይ ሥራውን ቶሎ መሥራት የማልፈለገው ለምንድነው? ብሎ ራሱን በመጠየቅ ትክክለኛውን ምላሽ ሊያገኝ ይገባል::

☞ የሥራው ጥራት ማጣትን በጊዜ እጥረት ለማስተባበል ብሎ ሥራውን እስከ መጨረሻው ወቅት ማቆየት መልካም አለመሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: አንዳንድ ሰዎች የተሰጣቸውን ሥራ በሚገባ እንደማይሠሩት ሲገባቸው ሥራውን ሆን ብለው ያቆዩትና ጥቂት ጊዜ ሲቀራቸው ይሠሩና ሥራቸው ጥራቱ የጎደለው ሆነው ሲጠየቁ ቶሎ ቶሎ ስለተሠራ ነው ይላሉ:: ይህ ደካማ የሆነ አካሄድ ስለሆነ ሊታረም ይገባል:: ሥራውን መሥራት ካልቻሉ መሥራት ለሚችል ሰው መስጠት ያስፈልጋል:: ጊዜንም ለመጠቀምና ጥራት ያለው ሥራም እንዲሠራ ያደርጋል::

☞ አንድን ሥራ በአንድ ጊዜ ሠርቶ ለመጨረስ ከማሰብ ይልቅ ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ጥቂት በጥቂቱ መሥራት የተሻለ ነው:: የሚፈለገው ሥራ ብዙ ሳያስጨንቅ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል::



*6. ጊዜን ከነጣቂዎች መዋጀት*

ጊዜን በሚገባ ለመጠቀም ጊዜን ሊያባክኑ ከሚችሉ ነገሮች መቆጠብ ያስፈልጋል:: ጆን ካልቪን «ጊዜው የተበላሸ በመሆኑና ዲያብሎስም ስለሚዋጋ ጊዜን ሳይዋጁ ለእግዚአብሔር መስጠት አይቻልም:: ጊዜን ለመዋጀት ደግሞ ዋጋው ምንድነው? ብለው በመጠየቅ ጊዜ ለእግዚአብሔር እንዳይዋጅ እንቅፋት ከሚሆኑ ከማናቸውም ፈተናዎች መራቅ፣ ራሳችንን ዓለም ለምትሰጠው ምቾት አለመስጠትና በአጭር ንግግር ማንኛውንም መሰናክል ማውገዝ ነው» በማለት ምዕመናን ጊዜያቸውን ለእግዚአብሔር ክብር እንዲጠቀሙበት ይመክራቸዋል::[11] በዚህ ዘመን ዲያብሎስ የአገልጋዮችን ጊዜ እንደ ልቡ እየተጠቀመበት ይገኛል:: አገልጋዮች ለእግዚአብሔር ሥራ የተቀጣጠለ ልብ እንዳይኖራቸው ስልቹዎች እንዲሆኑ በማድረግ እንዲሁም ከእርስ በርሳቸውና ከቤተክርስቲያን መሪዎች ጋር እንዳይስማሙና አንዱ ስለሌላው ክፋት እያወራ እግዚአብሔር የሰጣቸውን ጊዜ እንዲያባክኑ እያደረጋቸው ነው:: ስለዚህ የክፋውን ዓላማ ባለመዘንጋት በጸሎት እየተዋጉ ጊዜን ለእግዚአብሔር በጎ ሥራ ላይ ማዋል ትልቅ ብድራት ይኖረል::

*7. እምቢ ማለትን መማር*

አገልጋይ አላስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለመሥራት ፈቃደኛ ባለመሆን ጊዜውን በመልካም ነገሮች ላይ ማዋል ይችላል:: አገልጋይ ለአንዳንድ አገልግሎቶች ለምንና እንዴት እምቢ ማለት እንዳለበት ከመመልከታችን በፊት እምቢ ማለት ምን እንደሆነና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አሳብ መሆኑን በማየት እንጀምራለን::

እምቢ ማለት ለአገልግሎት ወሰን ወይም ገደብ ማበጀት ማለት ነው:: በምድራችን ላይ የብስና የውኃ አካላት ወሰን አላቸው:: ሀገራት የየራሳቸው ወሰን አላቸው:: በድንበር ይገባኛል ጥያቄ ብዙ ጦርነቶች ተደርገዋል:: አንዱ የሌላውን ወሰን ጠብቆ ሲኖር በሀገራት መካከል ሰላም ይኖራል:: ለመልካም ጉርብትናና ግንኙነት ወሰንን ማክበር አስፈላጊ ነው:: በሕይወት ውስጥም ወሰን አስፈላጊ ነው:: አንድ ሰው መሆንና መሆን የማይችለውን እንዲሁም ማድረግ የሚችለውንና የማይችለውን ነገር ለይቶ ማወቅ የራሱን ገደብ ወይም ወሰን እንዲያውቅ ያግዟል:: አገልጋይ በአገልግሎቱ ከየት እስከ የት መሄድ እንደሚችል ሲያውቅና ያን ገደብ ሲያከብር ብዙ ይጠቀማል::

እምቢ ማለት ወይም ለአገልግሎት ወሰን ማበጀት አስፈላጊ የሆነበትን እንዳንድ ነጥቦችን መጥቀስ ይቻላል:: እነርሱም:-

- አገልጋይ ሳይባክን አገልግሎት መስጠት ይችላል:: የራሱን ጸጋና ኃይሉን በመጠበቅ ማገልገል ይችላል:: በአንድ ጊዜ ውልቅልቁ ሳይወጣ በሕይወት ዘመኑ አገልግሎቱን ይሰጣል::

---

[11] Parker, T.HL. *Calvin's Commentaries*. Grand Rapids, MI: Wm.B. Eerdmans Publishing Company, 1965, p. 202-203.

ያለበት ለምን ዓይነት ሥራ ነው፡ ለትምህርት ዝግጅት፣ ለጉብኝት፣ ለማማከር፣ ለጸሎት፣ ለአስተዳደራዊ ሥራዎች ወይስ ለምንድነው? አገልጋይ ከእነዚህ ሥራዎች ቅድሚያ ሰጥቶ ለመሥራት በራሱ መወሰን ይችላልን? አገልጋይ ከመሪዎች የተሰጡትን ሥራዎች የሚተገብር ነው ወይስ በራሱ ቅድሚያ ሊሰጡ የሚገባቸውን ነገሮች መርጦ መሥራት ይችላል? አገልጋይ እንዲሠራቸው የተሰጡት ሥራዎች ቅደም ተከተል አላቸውን? የቤተክርስቲያን መሪዎችና ምዕመናን አገልጋይ ከሁሉም በላይ መሥራት አለበት ብለው የሚያስቡት ሥራ ምንድነው? አገልጋዩ ራሱስ ምን በቅድሚያ መሥራት እንደሚገባው ያስባል? ለአንድ ሥራ ቅድሚያ ለመስጠት እነዚህ ጥያቄዎች ተገቢውን ምላሽ ሊያገኙ ይገባቸዋል።

አገልጋዮች በተጠሩበትና በተሠማሩበት አገልግሎት በኬታማ የሚሆኑት በአገልግሎቱ የሚጠበቅባቸውን ቀዳሚ ሥራ በቅድሚያ መሥራት ሊችሉ ነው። ለምሳሌ ከመጋቢው የሚጠበቀው ለምዕመናን ተመጣጣኝ የሆነ መንፈሳዊ ትምህርት አዘጋጅቶ ማስተማርና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዋህዱ በግልም ከእነርሱ ጋር መነጋገር፣ መጸለይና ወደ እግዚአብሔር ፍጹም አሳብ እንዲያድጉ ማገዝ ቢሆንና መጋቢው ግን አገልግሎቴ ነው ብሎ የያዘው ፕሮግራም ማውጣትና አገልጋዮችን እየጋበዘ መመደብ፣ በብሰባዎችን ማካሄድና መካፈል፣... ከሆነ የሚጠበቅበትን አገልግሎት አገልግለዋል ለማለት አዳጋች ነው።

አንድ አገልጋይ ለየትኛው አገልግሎት ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባው ካላወቀና ካላደረገ ጊዜውን እንዲሁ ያባክናል። አገልግሎትን ይሰጣል ነገር ግን የሚሰጠው አገልግሎት እርሱ ከፍተኛ ትኩረት ሊያደርግበት የሚገባ ሳይሆን ይቀራል። ሰዎች ከእርሱ የሚጠብቁትንና የአገልግሎት ሥፍራው ከእርሱ የሚፈልገውን ነገር ሳያከናውን ሌሎች ነገሮችን ሊሠራ ይከርምና ውጤቱን መገምገም ሲጀምር ጠብ የሚል ነገር ሳይሠራ መቅረቱን ይረዳል። አገልጋይ እግዚአብሔርና ቤተክርስቲያን ባስቀመጠችው ቦታ መሥራት የሚገባውን ሥራ ለመሥራት በአገልግሎት ቦታው ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውን ለይቶ ማወቅና ማድረግ አለበት።

በአገልግሎቱ ምን ዓይነት ሥራ መቅደም እንደሚገባ ያላወቀ ወይም እያወቀ ተግባራዊ የማያደርግ አገልጋይ ሰነፍ ነው ማለት አይደለም። በአብዛኛው ለየትኛው ሥራ ቅድሚያ መስጠት እንዳለበት የማያውቅ አገልጋይ ብዙ ሥራዎችን ይሠራል። ጉልበቱንና ኃይሉን አይቆጥብም። የሚመለከተውንና የማይመለከተውንም ሥራ ይሠራል። የሚሠራው ሥራ ለቤተክርስቲያን ከሚኖረው ጥቅም አኳያ አይመረጥም። ትጉ ሠራተኛ ነው። ከእርሱ ጋር የሚያገለግሉ ሌሎች አገልጋዮች እንደ እርሱ የማይተጉ ከሆነ በተለይም እርሱ ትኩረት በሰጠባቸው ሥራዎች ላይ ትኩረት የማያደርጉ ከሆኑ ይነጫነጫል። ከዚህም የተነሳ ከእነርሱ ጋር ያለው ግንኙነት ይሻከራል።

እንግዲህ ሚዛን የጠበቀ አገልግሎት ለመስጠት ጊዜን በሚገባ መጠቀም መቻል ከፍተኛ ድርሻ አለው። ጊዜ ውድ ነው። አገልጋይ ይህን መልሶ ሊያገኝ የማይችለውን ውድ ጊዜ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎች መታነጽ፣ ለግል የሕይወት ዓላማ በኬት ለመጠቀም እግዚአብሔር በሕይወታችን ለማከናወን የሚፈልገውን ዋነኛ ዓላማ ማወቅና ለዚህም ተግባራዊነት ራስን በሥርዓት መምራት እጅግ አስፈላጊ ነው።



<u>ተከታዮቹን ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሩ።</u>

1. *አገልጋይ ጊዜውን በሚገባ ተጠቅሞበታል የሚባለው ወይም አልተጠቀመበትም የሚባለው ጊዜውን እንዴት ሲጠቀምበት ነው?*
2. *የአገልጋይን ጊዜ የሚነጥቁ ነጣቂዎች ምን ምን ናቸው?*
3. *አገልጋይ ተገቢ ነው ብሎ ለሚያስባቸው ሥራዎች ወይም ጥያቄዎች እምቢ ማለትን የሚፈራበት ምክንያቶች ምንድናቸው?*

እንግዲህ አገልጋይ እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ ሥርዓት ባለው መንገድ የማይጠቀምበት ከሆነ የእግዚአብሔርን ዓላማ ሳይፈጽም ከመቅረቱም በላይ ዛሬ በምድር ባለው አገልግሎቱና ሕይወቱ ከፍተኛ ኪሣራ ይደርስበታል። ከጊዜ አጠቃቀምና አገልግሎትን ሚዛን ባልጠበቀ ሁኔታ ማገልገል በሕይወት፣ በቤተሰብና በአገልግሎት ፍሬያማነት ላይ ሊያመጣ የሚችላቸውን ችግሮች፣ የችግሮቹ ምልክቶች እንዲሁም በዚህ ችግር ውስጥ የገቡ አገልጋዮች እንዴት መውጣት እንደሚችሉ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ እንመለከታለን።

## ምዕራፍ 8

### በአገልግሎት መዳሸቅን መከላከል

አንዳንድ ጊዜ አገልግሎት መልካም ቢሆንም በሚዛን ካልተያዘ በስተቀር ሕይወትን ሊያዳሽቅ ይችላል። በመንፈሳዊ አገልግሎት ውስጥ በአብዛኛው ከባድና አስቸጋሪ ሆነው ከሚታዩ ችግሮች መካከል አንዱ ዘወትር ለአገልግሎት ንቁና ትጉ ሆኖ አለመገኘት ነው። አንዳንድ አገልጋዮች መንፈሳዊ አገልግሎት በጀመሩበት የተነቃቃ መንፈስና ስሜት አይዘልቁም። በሂደት በድካም ነፋስ ይመቱና በፊት የነበረው መነቃቃታቸውና የልብ መነሳሳታቸው ይቀዘቅዝባቸዋል። ከዚያም እንኳን ሌሎች ሰዎችን ማገልገል ቀርቶ በግል ሕይወቱም ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት ይበላሽበታል። እንደዚህ ዓይነት አገልጋይ ስለወደፊት ሲያስብ ተስፋ አይታየውም። እነዚህ ምልክቶች አንድ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ምን ማለት ነው? በአገልግሎት መዳሸቅ በአገልግሎት ከመወጠር የተነሳ የሚከሰት አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ስሜታዊና መንፈሳዊ ዝለት ነው። በአገልግሎት መዳሸቅ እንደ ባሎን ራስን መወጠርና መፈንዳት ነው። ባሎን ከመጠን በላይ በአየር ተሞልቶ ሲወጠር በቀላሉ ይፈነዳል። ውጥረቱ እየጨመረ ሲሄድ አደጋ የመከላከል አቅሙ እየተዳከመ ይሄዳል። አገልጋይም መሄድ ከሚገባው ገደብ በላይ በአገልግሎት ሲወጠር ተመሳሳይ ዕድል ፈንታ ይገጥመዋል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ማለት ለማገልገል የሚያስፈልገውን ኃይልና ብርታት ማጣት ነው። ዱሮ ለመሥራት የሚቻለውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችል ኃይል ይከዳና ባዶ መሆን ነው። አንድ ሰው መነሳትና መቀመጥ ይችል ነበር። አሁን ግን ከተቀመጠ በኋላ ለመነሳት ኃይል ያጣል። በአገልግሎት መዳሸቅም አንድ አገልጋይ እንደ በፊቱ ስማገልገል የሚችልበትን ጸጋ ማጣት ነው።

አገልጋይ ስአገልግሎት ያለው ትጥቅ ምን ያህል እንደሆነ አስቀድሞ ሳይገምትና ምን ያህል እንደተጠቀመበት ሳይከታተል ይቀርና በአገልግሎት ላይ እያለ ትጥቆቹ ያልቁበትና ነዳጅ እንዳለቀበት መኪና ያለቦታው ይቆማል። አንዳንድ ጊዜ በተለይም ተሳፋሪ በሚበዛበት ጧትና ማታ የከተማ ታክሲ ሹፌሮች ቶሎ ቶሎ ሠርቶ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ ነዳጅ ሳይቀዱ ይቀራሉ። አሳባቸው ሠርቶ በሚያገኙት ገንዘብ ላይ እንጂ በታክሲው ደህንነት ላይ አይደለም። ታክሲው እየሄደ ድንገት ቀጥ ይላል። ችግሩ ምንድነው ተብሎ ሲታይ ነዳጅ የለውም። ምናልባት በአቅራቢያው የነዳጅ ማደያ ከሌለ «ወያላው» ትንሽ ጃርኬን ይዞ ወደ ነዳጅ ማደያ ጣቢያ ይሮጣል። ይህ ሲሆን ተሳፋሪዎች በታክሲው ውስጥ ይቀመጣሉ ወይም ከቸኩሉ ገንዘባቸውን ከስረው በሌላ ታክሲ ይሄዳሉ።

ትጥቆቹን እንደገና ማግኘት የሚችልበት ሁኔታ ቢኖርም ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ በአገልግሎት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው። ምዕመናን ከአገልጋዩ በጊዜው ማግኘት የሚፈልጉትን ነገሮች ማግኘት አይችሉም። ለእነርሱ የሚሰጠውን ነገር ከስጪው አልተቀበሰም ወይም ከመንፈሳዊ ማደያ አልቀዳም። ምዕመኑ መድረስ ከሚፈልግበት ግብ ድረስ ሳይደርስ



ሲቀር ደግሞ ይነጫነጫል። ይህ ደግሞ በአገልጋይና በምዕመኑ መካከል ግጭት እንዲፈጠርም ምክንያት ይሆናል።

በአገልግሎት መዳሸቅ እንደ ብረት ዝገት ነው። ዝገት ብረትን በአንድ ጊዜ አያበላሸውም። ነገር ግን ብረት ስተከታታይ ጊዜያት ለዝገት ከተጋለጠ ከጥቅም ውጭ ሲሆን ይችላል። ማንኛውም መሣሪያ ተገቢውና አድሳት ካልተደረገለት በስተቀር እየተበላሸ በመጨረሻ ላይ ደግሞ ጥቅም ሲሰጥ በማይችልበት ደረጃ ላይ ይደርሳል። በተመሳሳይ መልኩ በአገልግሎት ውስጥም አገልጋይ እያገለገለ እያለ ለራሱ ተገቢውን እንክብካቤ የማይሰጥ ከሆነና ሕይወቱን የሚያድስበት ልምምድ ከሌለው ቀስ በቀስ ከጥቅም ውጭ ይሆናል። በአገልግሎት ንቁ ሆኖ ለመቀጠል በአካል፣ በአዕምሮ፣ በስሜትና በመንፈሳዊ ሕይወት እየታደሱ መኖር አስፈላጊ ነው። እንዲህ ካልሆነ ዝገት ብረትን እንደሚያበላሽ ሁሉ በአገልግሎት አየባከኑ ራስን መጣልም የዛገ ብረት ያህል ተቀባይነት ያሳጣል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ውጫዊና ውስጣዊ ይዘት አለው። ውጫዊ ገጽታው በአካል ላይ በሚታየው ዝለት ሲገለጥ ውስጣዊው ደግሞ የሥነልቡና ምላሾችን ለምሳሌ የስሜት፣ አመለካከት፣ ዓላማና ተስፋ በአሉታዊ ጎን መለወጥን ያመለክታል።

በማንኛውም ሥራ ውስጥ እንደሚኖር ሁሉ ከፍታና ዝቅታ በአገልግሎት ሕይወት ውስጥም ያጋጥማል። አገልጋይ በአገልግሎቱ ውስጥ ካጋጠመው ስኬት የተነሳ ራሱን እንደ «አምላክ» የሚቆጥርበት እንዲሁም ምዕመናን «እንደ እርሱ ያለ አገልጋይ የለም» እስኪሉ ድረስ የሚደርሱበት ጊዜ አለ። በዚህ ጊዜ አገልጋይ በኃይል የተሞላ፣ ከራሱ ተርፎ ለሌሎች ጸጋን የሚሰጥ መልዕክት ያለው፣ መልዕክቱን ለማቅረብ ጸጋና ጥበብ የተሞላ ይሆናል። በተቃራኒው ደግሞ አገልጋይ ባዶነት ተሰምቶት እንኳን ለሌሎች የሚበቃ ጸጋ ያለው መሆን ቀርቶ ለራሱም የሚደርቅበት ጊዜ ያጋጥማል። ከዚህም የተነሳ «ለምን ወደዚህ አገልግሎት ገባሁ» «በዚህ ሁኔታ እንዴት አገልጋይ ሆኜ መቀጠል እችላለሁ?» «ይህን ውርደት እንዴት መሸከም እችላለሁ?» እያለ ጭንቀትና ግራ መጋባት ውስጥ ይገባል።

በአገልግሎት መዳሸቅና በዝቅታ ውስጥ መሆን ምን እንደሚመስል ለማሳየት የአንድ አገልጋይ ሕይወትን እንመልከት። ጌታን ማገልገል ከጀመረ ወደ ሃያ ዓመታት አስቆጥሯል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በውስጡ እንግዳ የሆነ ስሜት እየተሰማው መጣ። አገልግሎት ሲሰጠውም ለማገልገል ፈቃደኛ አይደለም። ሰዎች ቀድሞ የነበረውን መልካም ነገሩን እያሰቡ ይጋብዙታል። እርሱ ግን አሁን ያለበት ሁኔታ በቀድሞ ሥፍራ ሳይሆን ለራሱም ምን እንደሆነ በማያውቅበት ሁኔታ ነው። «በአጥቢያዬ የእሁድ ስብከት ሲሰጠኝ በጣም አዝናለሁ። ሰዎች ልቤን አያውቁም እንጂ እኔ በግራ መጋባት ውስጥ ነኝ። እነርሱ እንደ ቀድሞ ዘመን ትጉና በውስጤ በመንፈስ የምቃጠል ይመስላቸዋል። የተሰጠኝን አገልግሎት እምቢ ማለት ደግሞ ሌላ ችግር ሊያመጣብኝ ይችላል በማለት ብቻ እሺ ብዬ አገልግሎትን እቀበላለሁ። መጽሐፍ ቅዱስ ከፍቼ ማንበብ ስጀምር ከዚህ ቀደም ያየሁትና መልዕክት ያገኙበት መሆን ቀርቶ አንድም ቀን ከፍቼ ያነበብኩት ዓይነት መጽሐፍ አይመስለኝም። ዱሮ ከፍቼ ማንበብ ስጀምር በውስጤ የሚፈሰው መልዕክት አሁን የለም። ደረቅ ይሆንብኛል። ስጸሎት ስንበረከክ

የምጸልይበትንም ርዕስ አላገኘም። እንደ ነገሩ ከዚህም ከዚያም አሳቦችን በመለቃቀም ሰአሁድ ስብከት ዝግጅት አደርኩና ወደ ጸሎት ቤት ሄድኩኝ። በጸሎት ቤት ጢም ብሎ ሞልቶ ካለው ምዕመን ፊት ለፊት ከእግዚአብሔር ለእነርሱ መልዕክት እንዳለው አገልጋይ በቀመጥ ውስጡ ይረበሻል። ሕዝበ ባሬ እግዚአብሔር ይናገረኛል ብሎ ያስባል። እኔ ግን ከእግዚአብሔር ምንም መልዕክት የለኝም። የስብከት ጊዜው ሳይደርስ የሆነ እንግዳ ነገር መጥቶ ሳልሰብክ ብቀር ደስ ይለኝ ነበር። ግን ማምለጫ በሰሌሰኝ ለመስበክ ወጣሁ» በማሰት ይናገራል።

ይህ አገልጋይ እንዲህ ዓይነት በሜት እንዲሰማው ያደርገው እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠው ጸጋ በሚገባ መፍሰቅ የሚችልበትን ዓውድ ባለማዘጋጀቱ ነው። እግዚአብሔር ለአገልጋይ የሰጠው ስጦታ የሚያድገው በአገልግሎት በመባከን ሳይሆን በጸጥታና በእርጋታ በእግዚአብሔር ፊት በመሆን፣ አካሄድን በመፈተሽና ስጦታን በተገቢው ሥፍራ በመጠቀም ነው። በአገልግሎት ስም መባከን በአገልግሎት የሚያቆይ ሳይሆን ሁለንተናዊ ሕይወትን በማሳሽቅ ባዶ የሚያስቀር፣ ሕይወትን ትርጉም የለሽ የሚያደርግና የሕይወትን አቅጣጫ የሚያጠፋ ይሆናል።

## በአገልግሎት የመዳሽቅ ምልክቶች

በአገልግሎት መዳሽቅና የመንፈስ መለሳቸት ተመሳሳይነት አላቸው። በሁለቱም ውስጥ ለአገልግሎት ኃይል ማጣት፣ ቀድሞ የሚወዱትን አገልግሎት ለማገልገል የልብ መነሳሳት ማጣት፣ የአለመቻል ስሜትና ተስፋ ቢስነት ይታያሉ። ሆኖም የመንፈስ መበሳቸት የሕይወት ገጽታን ሁሉ የሚነካና ብዙ መንስኤዎች ሲኖሩት በአገልግሎት መዳሽቅ ግን በአብዛኛው ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ ነገር ነው። በአገልግሎት መዳሽቅ ከሚታወቅባቸው ምልክቶች ጥቂቶቹ እንደሚከተሰው ተጠቅሰዋል። እነርሱም:-

በአገልግሎት የዳሸቀ አገልጋይ ሰውነቱ ይደክሟል። ብዙ ጊዜ ከፍተኛ የድካም ስሜት ይሰማዋል። በቀን ውስጥ ብዙ ሰዓታትን በአገልግሎት ላይ ያሳልፋል። አንድ ሰው በተከታታይ ሲሸከመው ከሚችሰው በላይ በአገልግሎት ይወጠራል። ከዚህም የተነሳ አካሉን የሚያሳርፍበት ጊዜ የሰውም። እንኳን ለማረፍ ምግብንም በተገቢው ሰዓት አይመገብም። ምሳውን መብላት የሚገባው በምሳ ሰዓት ሆኖ አያለ እርሱ ግን በከሰዓት በኋላ በመክሰስ ጊዜ ይመገባል። ብዙ ጊዜ የጨጓራ ሕመም እንዳለው ይናገራል። ሰውነቱ ከመዛሉ የተነሳ ማታ አምሽቶ ወደ ቤት ሲገባ እንቅልፍ መተኛት አይችልም። እንቅልፍ አይወስደውም። ማለዳ ላይ ከአልጋው ላይ ለመነሳት በጣም ይቸገራል። ሰውነቱ እንደሚገባ ባሰማረፉ የማይሰቀው የራስ ምታት ይሰማዋል። በእብዛኛው ጤነኛ እንደሆነ አይሰማውም። እርሱ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ጤንነት እንደማይሰማው ይናገራል።

በአገልግሎት የዳሸቀ አገልጋይ አዕምሮውን ስኬታማ በሆነ መንገድ መጠቀም ይሳነዋል። ቀድሞ አዲስን ነገር ለማወቅና ለመማር የነበረው ጉጉት ይጠፋበታል። በአገልግሎት ውስጥ የሚያጋጥሙትን ጉዳዮች እያነሳ ከሌሎች አገልጋዮች ጋር ይነጋገር ነበር። አሁን ግን ከሌሎች ጋር መነጋገር፣ መከራከርና የልምድ ልውውጥ ማድረግ ያስጠላዋል። በአገልግሎት ተወጥሮ ጊዜ ከማጣቱ የተነሳ አዳዲስ ጽሑፎችን በማንበብ



አዕምሮውን መገንባት አይታይበትም። አዳዲስ ነገሮችን ተምሮ አገልግሎቱን ለማሻሻል ምንም ትጋት የለውም። በአገልግሎቱና በሕይወቱ ውስጥ ለገጠሙት ተግዳሮቶች ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት ተከታታይነት ያለው ትምህርት ከመፈለግ ይልቅ በአቋራጭ ለችግሩ ጊዜያዊ መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉትን መንገዶች ይፈልጋል። አገልጋዩ አዳዲስ ነገሮችን መማር ቀርቶ እርሱ ቀድሞ የሚያውቃቸው ነገሮች እንኳ ጠፍቶበታል።

በአገልግሎት የባከነ አገልጋይ ብዙ ጊዜውን ለሌሎች ስለሚሰጥ ለራሱ ጊዜ የለውም። በቤተክርስቲያን ውስጥ ችግር ያላቸውን ሰዎች እየተከታተለ አስፈላጊውን እንክብካቤ ይሰጣቸዋል። ዘወትር የሚያስበው ስለሌሎች ሰዎች ነው። ከዚህም የተነሳ የራሱን ውስጣዊ ስሜቶች የሚያዳምጥበት ጊዜ የለውም። ለራሱ ምን እንደሚፈልግ አያውቅም። የራሱን ፍላጎት አለማወቁ ደግሞ ከጊዜ በኋላ ስሌሎችም ትኩረት እንዳይሰጥና ግድየለሽ እንዲሆን ያደርጓል። አገልግሎቱ ውስጣዊ እርካታ እያሳጣው ሲሄድ ቀስ በቀስ ስሌሎች ሰዎች ጉዳይ ቀዝቃዛ የሆነ ምላሽ መስጠት ይጀምራል። ከምዕመናን ጋር የማይገናኝበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ያደርጋል።

አገልጋዩ ስለራሱና ስለሌሎች ሰዎች ያለው አመለካከት አሉታዊ ይሆናል። በአገልግሎቱ እንደ ቀድሞ ትጋት በማጣቱ ራሱን ይኮንናል። በአገልግሎቱ አንድ መልካም ነገር እንደሠራ ስለማይታየው ለራሱ የሚሰጠው ዋጋ ይቀንሳል። «አሁን እኔ የምጠቅም አገልጋይ አይደለሁም» «የእኔ ጊዜ አልፏል» ብሎ ሲናገር ይሰማል። አገልግሎት ለእርሱ ማንነት ዋጋ ማግኘት ምንም አስተዋጽኦ እንደሌለው ስለሚያስብ በተቻለ መጠን ከአገልግሎት ራሱን ለማግለል ይፈልጋል።

በአገልግሎት መዳሸቅ ውስጥ የገባ አገልጋይ ስለአገልግሎት ከጓደኞቹና ከቤተሰብ አባላት ጋር መነጋገርን አይፈልግም። ጓደኞቹ ስለአገልግሎት ሲጠይቁት አገልጋዩ ምንም ለመናገር ፈቃደኛ አይሆንም። በተቻለ መጠን ስለአገልግሎቱ እንዲናገር የሚያደርጉትን ርዕሶች ወደ ሌላ ጉዳይ ለመቀየር ጥረት ያደርጋል። ስለአገልግሎት መናገር የማይፈልገው በውስጡ ስለአገልግሎት የነበረው አመለካከት ስለተለወጠ ነው።

አገልጋይ ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄድ እርሱ ወጣ ብሎ በነበረበት ወቅት ሰልክ የደወሉ ሰዎች መኖራቸውን አይጠይቅም። ከዚህ በፊት ከቢሮ ወጣ ብሎ ሲመለስ ሰዎች መደወላቸውን ይጠይቅና ደውለው እርሱን ላጡት ሰዎች መልሶ ይደውልላቸው ነበር። አሁን ግን እንዲህ ለማድረግ ፍላጎት የለውም። እርሱን የፈለጉት ሰዎች ምንም የሚያስደስት ነገር እንደማያመጡለት ነገር ግን ሁላቸውም ሰራሳቸው ጥቅም እንደሚፈልጉት በማሰብ ይዘጋቸዋል። ለእርሱ በማሰብ የሚፈልገው ሰው እንደሌለ ያስባል። ሰዎች ለእርሱ ሸክም እንደሆኑ ይገምታል። ስለዚህ ማን እንደፈለገው ለማወቅ ክትትል አያደርግም።

ምዕመናን በተመደበላቸው ፕሮግራሞች መገኘት አለመቻላቸውን ሲገልጹ ወይም በሆነ ምክንያት ፕሮግራም ሲሰረዙ ደስ ይለዋል። ሳያውቅ በውስጡ «ጌታ ሆይ ተመስገን!» ይላል። ይህ ማገልገል ምን ያህል እንደሰለቸው ያመለክታል።

አገልጋዩ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ውስጥ *ጥቃቅንና ትላልቅ ችግሮች ይከሰታሉ*፡፡ ምዕመናን በፊት የነበራቸውን ሕይወት በመልቀቅ በሕይወታቸው ግራ መጋባት ውስጥ በመግባት ከእግዚአብሔርና ከእርስ በርሳቸው ጋር ያላቸው ችግሮች መብዛት የአገልጋዩ ሕይወት ነጸብራቅ ነው፡፡ የምዕመናኑ ሕይወት መልካም አለመሆን የአገልጋዩ ሕይወትና አገልግሎት መዳከምን ያሳያል፡፡ ምዕመናን አገልጋዩ ሳያውቅ ከእርሱ ተስፋ መቁረጥን፣ መነጫነጭን፣ ምክንያት እየፈጠሩ አስፈላጊ ነገሮችን አለማድረግንና የመሳሰሉትን ነገሮች ከእርሱ ይማራሉ፡፡ ስለዚህ ምዕመናን ያሉበት የሕይወት አቋም የአገልጋዩ ሕይወት ግልባጭ ነው፡፡

አገልጋይ *በተከታታይ በሐሳብ ይዋጣል*፡፡ ቁጭ ብሎ ለብዙ ደቂቃዎች ያስባል፡፡ በአዕምሮው ውስጥ ብዙ ነገሮችን ያወጣና ያወርዳል፡፡ ቢሮ ገብቶ ቁጭ ብሎ ስመሥራት ሲያስብ አንድ ሐሳብ ብልጭ ይልበትና ዓይኑ በተተከለበት ሥፍራ ፍንክች ሳይል ለደቂቃዎች ይቆያል፡፡ እርሱ ዘንድ ለማማከር የሚመጡ ሰዎች ከፊቱ ቁጭ ብለው እያሉ እርሱ በሐሳቡ ሌላ ቦታ ይሄድባቸዋል፡፡ ሐሳቡ በአንድ ቦታ አይያዝለትም፡፡ አንድን ነገር ለመሥራት ትኩረት ለማግኘት ይቸገራል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በሐሳቡ ወደኋላ ይመለስና በአገልግሎቱ ፍሬያማ የሆነበትን ጊዜ ያስባል፡፡ አዕምሮው በዚህ ከመያዙም የተነሳ ስለእነዚያ የቀድሞ ዘመናት ማውራትን ይወዳል፡፡ የአሁኑ ነገር እንዲነሳበት አይፈልግም፡፡

አገልጋዩ *ጊዜውን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም አይችልም*፡፡ ተኝቶ ከአልጋ ላይ መነሳት በራሱ ትልቅ ተግዳሮት ይሆንበታል፡፡ ቶሎ ከእንቅልፍ ላለመነሳት ብዙ ምክንያቶችን ይደረድራል፡፡ ወደ አገልግሎት ሥፍራው ከሄደም በኋላ ፍጥነት የለውም፡፡ ነገሮችን በዝግታ ለማድረግ ይፈልጋል፡፡ ብዙም ሳይሠራ የድካም ስሜት ይሰማዋል፡፡ ሥራውን አቋርጦ ቡና ፍለጋ ይሄዳል፡፡ ከመደበኛ አገልግሎቱ ውጭ የሆኑትን ነገሮች በማድረግ ብዙ ጊዜን ያጠፋል፡፡ ቡና ሲጠጣ እያወራ ሰዓታትን ያባክናል፡፡ በዚህም ምንም ቅር አይለውም፡፡

አገልጋዩ *ለምዕመናን መልካም ያልሆኑ ነገሮችን መናገር ይጀምራል*፡፡ እርሱ የሚያገለግላቸው ምዕመናን ተምረው እውነትን ወደማወቅ የማይደርሱ፣ በሕይወታቸው ለውጥ የማይታይባቸው፣ ብዙ ደካማ ጎኖች እንዳሉአቸው ይናገራል፡፡ የምዕመኑን ደካማ ጎን ከመሸፈን ይልቅ ለሌሎች ገልጦ በማሳየት ይስቅባቸዋል፡፡ ለምዕመኑ ተገቢ ያልሆኑ ቀልዶችን ይናገራል፡፡

አገልጋዩ ሲያገለግል *አገልግሎቱ ሕያው እንቅስቃሴ የለውም*፡፡ እርሱም ለእግዚአብሔር መቅናት አይታይበትም፡፡ ሲያስተምር ወይም ሲሰብክ የነበረው ደስታ አሁን የለም፡፡ ምዕመናን ዝም ብለው ይሰማሉ፡፡ ብዙ እንቅስቃሴ አይታይም፡፡ ሳቅ የለም፡፡ የአገልጋዩ ድምጽ ተመሳሳይ ነው፡፡ የሰለቸውና የደከመው ሰው ድምጽ ይመስላል፡፡ ምዕመናን ከአገልግሎቱ ሲወጡ «የዛሬ ሰዓት እንዴት ረዘመ?» «እቤት ሲደክም» «ዛሬስ በጣም ተጫጫነኝ» ይላሉ፡፡

አገልጋዩ *በአገልግሎቱ ወደኋላ ይቀራል*፡፡ እርሱ መሥራት የሚገባቸው ሥራዎች በወቅቱ አይሠሩም፡፡ ደብዳቤዎች በጊዜው ምላሽ አይሰጣቸውም፡፡ ከመሪዎች የተሰጡትን ሥራዎች አይሠራም፡፡ ለምን



እንደሆነ ሲጠየቅ ሰበብ ያበዛል፡፡ ከእርሱ ጋር የሚያገለግሉ አገልጋዮች በነገሩ ግራ ይጋባሉ፡፡

አገልጋዩ *ለብቻው ማሳለፍን ይፈልጋል*፡፡ ከጓደኞቹ ጋር ሆኖ አንድን ነገር ከመሥራት ወይም ከመዝናናት ይልቅ እቤቱ ውስጥ ሆኖ ቴሌቪዥን ያያል ወይም ገጠር ከሆነ ደግሞ ጫካ ውስጥ ገብቶ ቁጭ ይላል፡፡ ከሰዎች ጋር የሚያገናኘውን ጉዳይ ይረሳል፡፡ የተሰጠውን መንፈሳዊ ፕሮግራሞችን ይረሳል፡፡ ስብሰባ እንዲመጣ ሲነገረው በመርሳት ሳይሄድ ይቀራል፡፡ ከቤተሰብ ጋርም በፊት የነበረውን መልካም ግንኙነት ያጣል፡፡ በቤተሰብ ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ ከመግባትና የራሱን ኃላፊነት ከመወጣት ይልቅ የዳር ተመልካች መሆንን ይመርጣል፡፡

አገልጋዩ ያለበትን ትክክለኛ ሁኔታ በመገንዘብ *ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የተለያዩ ምክንያቶችን እየጠቀሰ ለችግሩ ውስጥ ይመላለሳል*፡፡ በአገልግሎት የነበረውን ደስታ የወሰደበትን ምክንያት በትክክል ከመፈለግ ይልቅ ሌሎች ሰዎችን ተጠያቂ ያደርጋቸዋል፡፡ ሌሎች ሰዎችን መክሰስ መፍትሔ ባይሆንም ይህን ሲያደርግ ይታያል፡፡ በችግር ውስጥ የወደቁትን ሰዎች በረዳበት መንገድ ራሱን መርዳት ያቅተዋል፡፡ «ቡዳ ስለራሱ አያውቅም» እንደሚባለው ይሆናል፡፡ በዚህ ወቅት የሚደርሰለት የቅርብ ጓደኛ ወይም መንፈሳዊ ሞግዚት ከሌለው ከብዙ ሰዎች ጋር በመጋጨት እንዲሁም ሕይወቱ በማጉረምረም ይሞላና ከፍሬያማ ሕይወት ውጭ ይሆናል፡፡

## በአገልግሎት የመዳሽቅ መንስኤዎች

በአገልግሎት መዳሸቅ እንዲሁ በድንገት የሚመጣ ክስተት አይደለም፡፡ አገልጋይ ሚዛኑን ባልጠበቀ ሁኔታ አገልግሎት ሲጀምር ቀስ በቀስ ራሱንና አገልግሎትን ሲያጣ ወደሚችልበት ሁኔታ ውስጥ እየገባ ይሄዳል፡፡ ስለዚህ በአገልግሎት መዳሸቅ ረጅም ሂደት ያለው ሲሆን ቶሎ ካልተነቃበት በስተቀር የውስጥን ኃይል በእዝጋሚ ሁኔታ እየበላ በመጨረሻ ላይ ሕይወትንና አገልግሎትን አደጋ ላይ ይጥላል፡፡ የአገልግሎት መዳሸቅ በተለያዩ ምክንያቶች ሊመጣ ይችላል፡፡ አንዳንዶቹ ምክንያቶች ከአገልጋዩ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ አገልጋዩ ከሚያገለግልበት አውድ ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡

1. በአገልግሎት መዳሸቅ የሚመጣው አገልጋዩ በሚቀበለውና በሚሰጠው መካከል ልዩነት ሲፈጠር ነው፡፡ አገልጋይ ሌሎችን የሚያገለግለው ከእግዚአብሔር በመቀበል ነው፡፡ የአገልግሎት ኃይል ምንጭ እግዚአብሔር ነው፡፡ አገልጋይ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው እርሱ ለሰዎች ከሚሰጠው አንሶ ከተገኘ አገልጋዩ እያለቀ ይሄዳል፡፡ እናት ለወለደችው ሕጻን በቂ የጡት ወተት ለመስጠት ከፈለገች በቂ ምግብ መመገብ ይኖርባታል፡፡ ለራስዋ በቂ ምግብ ሳትመገብ ሕጻኑዋን ማጥባት ከቀጠለች ሰውነትዋ እየተጎዳ ይሄዳል፡፡ የምትጎዳው እርስዋ ብቻ ሳትሆን ሕጻኑዋም ጭምር ነው፡፡ እናት ተገቢውን ምግብ ካላገኘች የሁለቱም ሁኔታ አስጊ ይሆናል፡፡ አንዳንድ እናቶች በሕጻንነት ብቻ ሳይሆን ልጆቻቸው ካደጉ በኋላም ለራሳቸው ምግብ መመገብ ትተው ለልጆቻቸው በመስጠት ይጎዳሉ፡፡

«የእናት ምግብ መቀነትዋ ነው» እየተባለ ለራሳቸው ትኩረት አይሰጡም። ከዚህም የተነሳ በበሽታ ይጠቁና «ያለጊዜያቸው» ይሞታሉ።

አገልጋይም ከእግዚአብሔር ሳይቀበል ለምዕመናን የሚሰጠው ነገር የለም። ስለዚህ ለምዕመኑ የሚሆነውን ነገር ከእግዚአብሔር ዘወትር ሊቀበል ይገባል። እርሱ ከእግዚአብሔር የሚቀበለው ነገር ለራሱና ለሌሎች የሚበቃ ካልሆነ አገልጋዩ ይራባል፤ ለሌሎችም የሚያጠግብ መንፈሳዊ ምግብ መስጠት አይችልም። በትንሽ ቧንቧ ወደ ቤት ውስጥ የሚመጣን ቧንቧ ትልቁ ቢገጠምለት ተገቢ አይሆንም። በትንሽ ቧንቧ ውስጥ የመጣው ውኃ በትልቁ ውስጥ ይጠራቀማል እንጂ ኃይል አግኝቶ አይወጣም። እንደዚሁም አገልጋይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለራሱ በቅቶ ለሌሎች የሚተርፍ ነገር ካልተቀበለ ከእርሱ አልፎ ሌሎችን የሚባርክና የሚገነባ መልዕክት ማስተላለፍ ይሳነዋል።

2. በአገልግሎት ውስጥ የሚያረካና ትርጉም ያለው ነገር ማጣት ነው። አገልጋዩ እያገለገለ እያለ በውስጡ የነበረው ደስታና እርካታ እየተሟጠጠ ያልቃል። ለመንፈሳዊ አገልግሎት ኃይል የሚገኘው አገልግሎቱ ለአገልጋዩ ውስጣዊ መንፈሳዊ እርካታ በማምጣቱ ላይ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ሆኖ ይህን መንፈሳዊ ሥራ በመሥራቱ ያገኝ የነበረው ትርጉም ሲያጣ ለአገልግሎት የሚያነሳሳው ኃይል ይጠፋል። ይህ ሲሆን ደግሞ ጥቂት የሚባለውን ሥራ እንኳ ለመሥራት ከባድ ሸክም ይሆናል።

3. አገልግሎት ተዳጋጋሚና ተመሳሳይ ዓይነት እንዲሁም ተግዳሮት የሌለበት ሲሆን ነው። ተመሳሳይ የሆነ ሥራ ሁልጊዜ ሲሠራ ይሰለቻል። አገልግሎቱ በፊት የነበረውን የማስደሰት ኃይል ያጣል። አገልጋይ በመጀመሪያ በአገልግሎት ላይ ሲሠማራ የሚሠራቸው ሥራዎች ሊያስደስቱት ይችላሉ። በአገልግሎት ውስጥ ሲቆይ ግን ተደጋጋሚ የሆኑ ሥራዎች ይበዛሉ። በየዕለቱ ትናንት፤ ከሳምንት በፊት የሠራቸው ሥራዎችን ይሠራል። አገልጋይ ምዕመናንን ይጎበኛል፤ ስብከትና ትምህርት ያዘጋጃል፣ ይሰብካል፤ ያስተምራል፤ ሥርዓቶችን ይፈጽማል፤ እነዚህ ነገሮች ዘወትር ተመሳሳይ ከመሆናቸው የተነሳ ይሰለቹታል።

4. ምዕመናን አገልግሎት ለመቀበል ፈቃደኛ ሳይሆኑ ሲቀሩ ወይም በአገልግሎቱ ፍሳንት ሲያጡ ተስፋ ያስቆርጣል። ምዕመናን ቀድሞ ሲያገለግላቸው ከነበረው አገልጋይ ይልቅ ሌሎችን እየመረጡ ሲሄዱ በፊት ከእነርሱ ጋር የነበረው አገልጋይ የነበረው የአገልግሎት ፍሳንትና የልብ መነሳሳት ይወድቃል።

5. አገልጋዩ ወደ አገልግሎት ሲገባ እንደሚያገኝ ጠብቆ የገባውን ነገር ሳያገኝ ሲቀር ወይም ሲዘገይበት ተስፋ ይቆርጣል። አንዳንድ ጊዜ አገልጋዩ ጠብቆ የገባው ነገር ተጨባጭ ሆነው ሳይገኙ ሲቀሩ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከተግዳሮቶች ብዛት የተነሳ የተጠበቀው ነገር ሳይገኝ ይቀራል። የጠበቁትን አለማግኘት ደግሞ ስሜትን ይጎዳል። አገልጋይ ቤተክርስቲያን ወይም እርሱ ራሱ ከራሱ የሚጠብቀው ውጤት ተጨባጭ ካልሆነ የራሱን ሁኔታ ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር በማቀናጀት ፍሬያማ አገልግሎት መስጠት አይችልም። አገልጋዩ ከፍተኛ ውጤት እንደሚያመጣ ለራሱ ዓላማ አድርጎ ቀንና ሌሊት እየሠራ ወደሚፈልገው ግብ ሊደርስ ይችላል። ሆኖም ይህ በተከታታይ ሲሆን አገልጋዩን ማዳሸቁ አይቀርም።



አገልጋይ በመጀመሪያ ወደ አገልግሎት ሲገባ ለእግዚአብሔር ክብር ለመዋል፤ ምዕመናን ለማነጽ እንዲሁም አዳዲስ ነፍሳትን ወደ ጌታ ለማምጣት ነው። ይህ በዓላማ ደረጃ ያለውን አሳብ ተግባራዊ ማድረግ ትልቅ ትግልን ይጠይቃል። አንዳንድ ጊዜ አገልግሎት አገልጋዩ እንደሚፈልገው ሳይሄድለት ይችላል። በዚህ ወቅት አስቀድሞ የነበረው ዓላማ በአገልጋዩ ውስጥ እየሞተ ይሄዳል። የራእዩ መሞት ደግሞ የአገልጋዩንም ማንነት ይጎዳል። ሕይወት ራእይ ከሌላት ወይም ራእይዋ ካልተሳካለት ትርጉም ታጣለች። አገልጋይ ራእዩውን ለመተግባር የተለያዩ ነገሮችን አድርጎ ካልተሳካለት ባዶነት ይሰማዋል። አገልግሎትና ለሕይወቱ የሚሰጠው ዋጋ ተያያዥነት ስለሚኖራቸው አገልግሎት አልተሳካም ማለት ሕይወትም ትርጉም ስለምታጣ ቢኖርም ባይኖርም ዋጋ እንደሌለው ማሰብ ይጀምራል።

6. በተፈጥሮ በአገልግሎት ውስጥ የድካምና የትጋት ጊዜያት ያጋጥማሉ። በሕይወትና በአገልግሎት ውስጥ የሚመጡትን ቀውሶች በመቋቋም ማለፍ ካልተቻለ ቀውሶቹ ሥፍራን የሚያስለቅቁ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ እንደ አገልጋዩ የመንፈስ ጥንካሬና ችሎታ ይለያያል።

7. አገልጋዩ በሚያገለግልበት ቤተክርስቲያን ውስጥ ለረጅም ጊዜ ይሠራበት የነበረ የአሠራር ሁኔታ ሲለወጥና አዲስና እንግዳ የሆነ አሠራር ሲተካ ቀድሞ የነበረው አገልጋይ ከዚህ ከአዲሱ አሠራር ጋር ለመልመድ ይቸገራል።

8. የአገልጋዩ የስብዕና አቋም፡ በቀላሉ የሚረበሽ፣ ችግርን ለመቋቋም የሚቸገርና ግትር አቋም የሚይዝ ሲሆን ሁኔታው ከሰዎች ጋር እንዲጋጭ ያደርገዋል።

9. አገልጋዩ የበኩሉን ድርሻ እየተወጣና በትጋት እያገለገለ ነገር ግን ቤተክርስቲያን ዕድገት ሳታሳይ ትቀራለች። አዳዲስ ምዕመናን ወደ ቤተክርስቲያን የማይጨመሩ ከሆኑ የአገልጋይ የውስጥ መነሳሳት እየወረደ ይሄዳል። አገልጋይ በአገልግሎቱ ፍሬ የማያይ ከሆነ ብዙ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይጀምራል። «ምናልባት እግዚአብሔር አልጠራኝ ይሆንን?» «እግዚአብሔር ከእኔ ጋር የለምን?» «በዚህ ሥፍራ መሆኔ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለምን?» ብሎ መጠየቅና መጠራጠር ይጀምራል። ለእነዚህ ጥያቄዎች ከእግዚአብሔር ዘንድ ግልጽ በሆነ መንገድ መልስ ካላገኘ ለአገልግሎት ያለው መነሳሳት ይጠፋል።

10. በቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልጋዮችና በመሪዎችም አካባቢ የሚታየው የከፍተኛ ሥፍራ፤ የሥልጣን፣ የተቀባይነት ፍለጋ በግልጽና በስውር የሚደረገው ትግል እውነተኛ መንፈሳዊ ለሆነ አገልጋይ እንቅፋት ነው። ምሳሌ መሆን የሚገባቸው አገልጋዮች በዚህ ተራ በሆነ ትግል ውስጥ ገብተው ሲያይ መንፈሱ ይረበሻል። ከዚህ ሁኔታ እንዴት ማምለጥ ይቻላል? ከእነዚህ ሰዎች ጋርስ እንዴት ማገልገል ይቻላል? የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይጀምራል። ይህ ደግሞ በቀላሉ መልስ የማያገኙ ነገሮች ባለመሆናቸው የአገልጋዩን መንፈሳዊና የአገልግሎት ትጋት ክፉኛ ያጎዳል። ስለቆዩት መንፈሳዊ አገልጋዮችና ስለቤተክርስቲያን የነበረው መልካም

# ክፍል ሁለት

## የክርስቲያን ሕይወት

በክፍል አንድ ውስጥ አገልጋይ እንዴት አድርጎ ሚዛናዊ ሕይወትና አገልግሎት ሊኖረው እንደሚችል ተመልክተናል። በዚህ ክፍል ውስጥ ስለአገልጋይ አብዛኛዎቹ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎች ለማንኛውም በክርስቶስ አምኖ የእርሱ ተከታይ ለሆነ ሰው ሊሠራ እንደሚችል የታመነ ነው። አገልግሎትን እንደ ማንኛውም ሥራ ብናበብ መርሆዎቹ ለማንም መሥራት ይችላሉ። ሆኖም በእግዚአብሔር ተጠርቶ የወንጌልን ሥራ መሥራት በዓለም ውስጥ ሰነዎችን ብለን ከምንሠራው ሥራ በዓይነትና በአሠራሩ የተለየ ነው። በመሆኑም የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ ላልሆኑ ክርስቲያኖች ሕይወት፣ ትዳርና ሥራ እንዲሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጡትን መንፈሳዊ አገልግሎት በሚዛናዊነት ስለመጠበቅ ጥቂት ነገሮችን ማንሳቱ ተገቢ ነው።

ከዚህ ቀጥለው የሚኖሩት ሁለት ምዕራፎች ማንኛውንም ክርስቲያን በሚመለከት ሁኔታ ላይ ትኩረት በማድረግ ስለግል ሕይወት፣ ትዳር፣ ሥራና መንፈሳዊ አገልግሎት ሚዛናዊነት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ማብራሪያ ይሰጣል።

የመጀመሪያ ምዕራፍ ማለትም ምዕራፍ ዘጠኝ ትኩረት ያደረገው በዚህ ዓለም ስለሚሠራው የተለያዩ ሥራዎች ክርስቲያኖች ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖራቸው እንደሚገባ፣ ለምን መሥራት እንደሚገባቸው፣ ምን ዓይነት ሥራ እንዲሁም በሥራ ላይ ሊያሳዩ የሚገባቸውን ባሕርያት መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ያብራራል።

ምዕራፍ አሥር ደግሞ ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የሆነውን ሥራ በትጋት በሚሠሩበት ወቅት ለግል ሕይወታቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም በቤተክርስቲያን ውስጥ ለሚሰጡት መንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ ሊሰጡ ይገባቸዋልን? ክርስቲያኖች ከላይ ለተጠቀሱ ነገሮች በቂ ጊዜ መስጠት እንደሚገባቸው መናገር ይቻላል። ነገር ግን ለእያንዳንዱ የሚበቃው ጊዜ ምን ያህል ነው? ጊዜውን ምን ዓይነት የቅደም ተከተል አሰጣጥ መርሕ በመከተል መስጠት ይገባቸዋል? ተከታዩ ምዕራፉ ለእነዚህና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል።



# ምዕራፍ 9.

## ክርስቲያንና ሥራ

በዚህ ክፍል ውስጥ ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸውን አመለካከት ስመዳሰስ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ የሚለውን አሳብ እንመለከታለን። ሥራ የሚለው አሳብ ሰዎች ለኑሮአቸው የሚያከናውኑትን ማንኛውንም በአእምሮ ወይም በአካላዊ ኃይል የሚተገበሩ ድርጊቶችን ያጠቃልላል።

አንድ ጊዜ ከአንድ ክርስቲያን ወንድም ጋር ተገናኘን። የተለመደውን ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ሻይ እየጠጣን ስለሕይወቱና ሥራው መጠየቅ ጀምርኩ። ይህ ወንድም በቀለም ትምህርት ከፍተኛ ትምህርት ያለው ሰው ነው። የሚሠራው ብዙ ሰዎች መሥራት የሚመኙበት መሥሪያ ቤት ውስጥ ነው። «ሥራ እንዴት ነው? በሥራህ ምን ያህል ደስተኛ ነህ?» ብዬ ለጠየኩት ጥያቄ «ምን ዋጋ አለው፣ እኔ እየሠራሁ ያለሁት ለምታልፈው ዓለም ነው» ብሎ መለሰልኝ። ለጠየኩት ጥያቄ እንዲህ ያለ ምላሽ ይመልሳል ብዬ አልጠበኩትም ነበር። ምላሹ በጣም ስለገረመኝ አሳቡን በጥልቀት ለመረዳት ተጨማሪ ጥያቄዎችን ጠየኩት። በእርሱ እይታ በዓለማዊ መሥሪያ ቤት ውስጥ መሥራት ለሰይጣን መንግሥት እንደ መሥራት ያህል እንደሆነ ገለጸልኝ። እግዚአብሔር የሚከብርበት ሥራ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሠራ ሥራ እንደሆነ ገለጸልኝ። የዚህ ወንድም አመለካከት ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት ይኖረዋል ብላችሁ ታስባላችሁ?

ክርስቲያኖች ስለሥራ የሚኖራቸው አመለካከት ትክክለኛ መሆኑ የሚለካው የእግዚአብሔር ቃል ከሚያስተምረው ትምህርት ጋር መጣጣሙ ምን ያህል እንደሆነ በመገምገም ነው። ሰዎች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት የሚመነጨው በሥራ ቦታቸው ከሚገጥማቸው ሁኔታ ላይሆን ከልባቸው ውስጥ ነው። በልባቸው ውስጥ ስለሥራ ያላቸው አሳብ ደግሞ አእምሮአቸውን ከሞላው መረጃ ይመነጫል።

*እስቲ ለተወሰኑ ደቂቃዎች ጊዜ እንውሰድና ስለሥራ ያለንን አመለካከት እንፈትሽ። ሥራ የኃጢአት ውጤት ነው ወይስ ኃጢአት ወደ ዓለም ባይገባም ይኖር ነበር?*

በመካከለኛው ዘመን የነበሩ እንዲሁም በአሁኑ ዘመንም አንዳንድ ክርስቲያኖች ሥራ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ለኃጢአታቸው መቀጫ የሰጣቸው እንደሆነ አድርገው ያስባሉ። ይህ ፍጹም የተሳሳተ አመለካከት ነው። ሥራ እግዚአብሔር ሰዎች ኃጢአት በመሥራታቸው የተሰጣቸው ፍርድ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ሥራ የተፈጠረው የሰው ልጅ በኃጢአት ከመውደቁ በፊት እንደሆነ በግልጽ ይናገራል።

ክርስቲያኖች ስለህብት በሚያስቡበት ወቅት ሁለት ነገር በአእምሮአቸው ውስጥ ይመላለሳል። የመጀመሪያው ነገር ክርስቲያን እግዚአብሔር በሰጠው መልካም ዕድል ሁሉ ተጠቅሞ ሀብት ማፍራት አስፈላጊ ነው የሚል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጌታ ቶሎ ሲመጣ

ስለሚችልና ዘመኑ አጭር በመሆኑ ብዙ ሀብት ማፍራትን ወደ ጎን በመተው ለዕለት የሚበቃቸውን ያህል እያገኙ መኖር ያስፈልጋል የሚል ነው።

ክርስቲያን ከሥራ ተለይቶ የሚኖርበት ወቅት አይኖርም። አንዳንድ ምዕመናን የዓለም ነገር አስጠልቶአቸው በቅድስና ለመኖር ወደ ገዳም ሲገቡ እንኳ ሥራ ይሠሩ ነበር። በገዳም ውስጥ የሚኖሩ ምዕመናን ከመንፈሳዊ ሥራ በተጓዳኝ ለራሳቸው የሚሆነውን የዕለት ጉርሻ ለማግኘት በትጋት ይሠሩ ነበር።

ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት መልካም ወይም መጥፎ እንደሆነ ለመናገር ያስችል ዘንድ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ የሚያስተምረውን መሠረታዊ እውነት መመልከት አስፈላጊ ይሆናል። የእግዚአብሔር ቃል ስለሥራ ምን ያስተምራል?

*መጽሐፍ ቅዱስ ስለሥራ ምን ይላል?*

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የመጀመሪያው ሠራተኛ እንደሆነ ያስተምራል። ሥራን የፈጠረው እግዚአብሔር ራሱ ሥራን የሚወድና የሚሠራ ትጉህ ሠራተኛ ነው። እግዚአብሔር ሥራን ሲሠራ አይደክምም፣ ኃይሉ በምንም ተዓምር አያልቅበትም። እግዚአብሔር በሚሠራው ሥራም ይደሰታል።

እግዚአብሔር ሰውን የፈጠረው በኤደን ገነት ውስጥ እንዲንፈላሰስ ብቻ ሳይሆን እርሱ ባስቀመጠው ሥፍራ ኃላፊነት ተሰምቶት እንዲሠራም ነው። እግዚአብሔር ሰውን ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፣ ሁለቱም ይኖሩበት ዘንድ፥ በተሰጣቸው ምድር ላይ ሥራ ሠርተው ይኖሩ ዘንድ ኃላፊነትን ሰጣቸው። «ምድርን... ግዙአትም» (ዘፍ.1:28) የሚል ትዕዛዝ ሰጣቸው።

> *እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሥራ እንዲሠራ የፈለገበት ምክንያት ምን ነበር? እግዚአብሔር ሰው እንዲሁ ቁጭ ብሎ ማለትም ምንም ሥራ ሳይሠራ እንዲኖር ለምን አላደረገም?*

እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ሥራን የሰጠበት ዓላማው ለበረከት እንጂ ለመርገም አልነበረም። ምክንያቱም ሥራ ለሰው ልጅ የተሰጠው ሰው በኃጢአት ከመውደቁ በፊት ነበር። አዳም በኤደን ገነት ውስጥ እንዲቀመጥ ሲያደርግ «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በኤደን ገነት አኖረው» (ዘፍ2:15) በማለት ተናግሯል። እግዚአብሔር ለአዳም ሔዋንን የፈጠረበትም አንዱ ምክንያት እርሱ ብቻውን እንዳይሆንና በሥራውም እርሱን እንድታግዝ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው የመጀመሪያው ሥራ የግብርናና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ እንደሆነ እንመለከታለን። ብዙዎች የግብርና ሥራ የሚሠሩ ሰዎች አፈር መግፋትን እንደ እርግማንና ከሥራ ሁሉ በታች እንደሆነ ቢያስቡትም ይህ ግን ለሰው ልጅ የተሰጠ የመጀመሪያው ሥራ ነበር።



ከፍጥረት ታሪክ መጀመሪያ የምንረዳው አንድ እውነት ሥራ መርገም ሳይሆን ለሰው ልጅ የተሰጠ በረከት እንደሆነ ነው። እንደዚሁም እግዚአብሔር አምላክ በመሆኑ ለሰው ልጅ የሚያስፈልገውን ነገር በየዕለቱ እየሰጠው ሰው ግን ቁጭ ብሎ እንዲጸልይ ማድረግ ይችል ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር እንዲህ አላደረገም። እግዚአብሔር የሰው ልጅ ሠርቶ መኖር እንዲችል የሚያስፈልጉ የሥራ ግብአቶችን አዘጋጀ፣ ለሰው ልጅም የማወቅ፣ የመመራመር፣ የመፈልሰፍና የመፍጠር ችሎታ ሰጠው። ከዚያም አእምሮውንና ጉልበቱን በመጠቀም በአካባቢው ያሉትን ግብአቶችን በማቀናጀት ለኑሮው የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት እንዲሠራ ኃላፊነት ሰጠው። በዚህ አሠራሩም እግዚአብሔር የሰው ልጅ በእግዚአብሔር በመታመን እርሱ በሰጠው ነገር ራሱን እንዲመራ ኃላፊነት ተሰጥቶታል።

በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ሰው ሆኖ መሥራት ጤናማ ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች ሥራን አለመሥራት ግን ከጤናማ ሕይወት መውጣት ነው። ሥራ የጤናማ ሕይወት ምልክት ነው። እያንዳንዱ ሰው ለድስት ቀን መሥራት እንዳለበት ታዟል። ይህም ከጧት እስከ ምሽት ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል። «ሰው ወደ ተግባሩ፣ እስኪመሽም ድረስ ወደ ሥራው ይወጣል» (መዝ.104:23)። እግዚአብሔር ጠዋት ፀሐይን ሲያወጣ «ወደ ሥራ ሂዱ« ማለቱ ሲሆን ምሽት ላይ ፀሐይ እንድትጠልቅ ሲያደርግ ደግሞ «አሁን ከሥራው እረፉ» ማለቱ ነው። ተፈጥሮ ራሱ የሰው ልጅ መሥራትም ማረፍም እንዳለበት ታስተምራለች። እያንዳንዱ ሰው በየዕለቱ መሥራት የሚገባው ነገር አለ። ይህን ሥራው ከጠዋት እስከማታ ድረስ ይሠራል። ሌሊት ደግሞ አርፎ በነጋታው ደግሞ ወደ ሥራው ይሄዳል። ይህ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የፈጠረው የተፈጥሮ ውደት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በስንፍና ምክንያት አለመሥራትን ወይም ታካችነትን እጅግ ይቃወማል። የመጽሐፈ ምሳሌ ጸሐፊ ታካችነት ማለትም ያለሥራ መኖርን መፈለግ፣ አእምሮን ያለምንም ሥራ ማስቀመጥ፣ ራስን ዓላማ ካለው ተግባር ጋር ሳያያይዙ፣ አንድ ለውጥ ለማምጣት ጥረት ለማድረግ መነሳሳት ማጣትን፣ ለሥራ ግድየለሽ መሆንንና ያለሥራ መዝናናትን መሻትን ይኮንናል። ታካችነት ወይም ስንፍና የድህነት ዋነኛ መንስኤ ነው። ደሃ ለመሆን ከስንፍና የተሻለ መንገድ የለም። በተቃራኒው ደግሞ ሲታሰብ ከድህነት ለመውጣት ተግቶ መሥራት ዓይነተኛ መንገድ ነው። ታካችነትን ለማስተማር ከተሰጡት ምሳሌዎች መካከል የሚከተለው ክፍል አንዱ ነው።

አንተ ታካች ወደ ገብረ ጉንዳን ሂድ
መንገድዋንም ተመልክተህ ጠቢብ ሁን።
አለቃና አዛዥ ገዢም ሳይኖራት
ምግብዋን በበጋ ታሰናዳለች
መኖዋንም በመከር ትሰበስባለች።
አንተ ታካች እስከ መቼ ትተኛለህ?
ከእንቅልፍህ መቼ ትነሣለህ?
ጥቂት ትተኛለህ፣ ጥቂት ታንቀላፋለህ
ትተኛም ዘንድ ጥቂት እጅህን ታጥፋለህ
ችጋርህም ለይፍ እንደ ታጠቀ ሰው ይመጣብሃል። (ምሳ.6:6-11)

በስንፍና መንፈስ የተያዘ ሰው ከዚህ ባሕርይው ለመላቀቅ መማር ይኖርበታል፡፡ በዚህ ክፍል ታካች እንዲማር የተመከረው ከገብረ ጉንዳን ነው፡፡ የሰው ልጅ በተፈጥሮም ሆነ በትምህርት ከእንስሳት የተሻለ ነው፡፡ የሰው ጥበብ ከእንስሳት ጥበብ ይልቃል፡፡ ሆኖም የሰነፍ ሰው ጥበብ ከገብረ ጉንዳንም ያነሰ እንደሆነ መመልከት ይቻላል፡፡ ሰው ሆኖ ከገብረ ጉንዳን ለመማር ወደዚህ ነፍሳት መሄድ ውርደት ነው፡፡ ከደረጃ በታች ሄደው እንደመማር ያህል ነው፡፡ ሰነፍ ሰው ከገብረ ጉንዳን እንዲማር መጠየቁ ከደረጃ በታች ሄደው እንደመማር ቢቆጠርም ለራሱ መልካም ትምህርት ከእነርሱ መማር ይችላል፡፡

ከገብረ ጉንዳን ለመማር ከፍተኛ ትኩረት መስጠትን ይጠይቃል፡፡ ገብረ ጉዳን የምትሠራውን ሥራ በሚገባ መመልከትና ማስተዋል ከእርስዋ ጥበብን ለመማር መሠረታዊ እርምጃ ነው፡፡ የሰነፍ ሰው ችግሩ ሁኔታዎችን በትኩረትና በጥልቀት አለመመልከቱ ነው፡፡ ጠቢብ ለመሆን ደግሞ አንዱ ዓይነተኛ መንገድ ሁኔታዎችን በማስተዋል መመልከት ነው፡፡ ሰነፍ በጥሞና መመልከት ቢችል እግዚአብሔር ከፈጠራቸው ከእነዚህ ነፍሳት ብዙ ቁምነገሮችን መቅሰም ይችላል፡፡

ሰዎች መልካምን ነገር መማር ከሚችሉባቸው መንገዶች አንዱ ሌሎች ሰዎች የሚያደርጉትን መልካም ሥራዎችን በመመልከት የእነርሱን ምሳሌነት መከተል ነው፡፡ የሌሎችን ሰዎች መልካም ሕይወትና ድርጊት አይቶ መከተል መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥበብ መማሪያ መንገድ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስም ምዕመናን የእርሱንና እርሱን የሚመስል ሕይወት የሚኖሩትን አገልጋዮች ሕይወትና ድርጊት እንዲከተሉ ምዕመናንን ይመክራቸው ነበር፡፡ «ወንድሞች ሆይ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፣ እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ እንዲሁ የሚመላለሱትን ተመልከቱ» (ፊልጵ.3፡17) ይላል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ለሥራ ከማስተማርም በተጨማሪ በመሥራትም ለሌሎች ሰዎች መልካም ምሳሌ እንደነበር በቀደሙት ምዕራፎች ውስጥ ተመልክተናል፡፡

ሌሎች የሚያደርጉትን መልካም ነገር ተመልክቶ ለመማር የሚያስፈልጉ እርምጃዎች አሉ፡፡ እነርሱም፡-

- የሚደረገውን መልካም ነገር በትኩረት መመልከትና ማስተዋል፣
- ያስተዋሉትን ነገር በአእምሮአቸው መያዝና ማስታወስ መቻል፣
- ያገኙትን ወይም የቀሰሙትን መልካም ነገር በድርጊት መግለጽ፣
- በልባቸው ተነሳሽነት ድርጊቱ ሁልጊዜ እንዲቀጥል ማድረግ ናቸው፡፡

እንግዲህ ሌሎችን ተመልክቶ መማር አንድ የመማሪያ መንገድ እንደሆነ ከተረዳን ሰነፍ ሰው ከገብረ ጉንዳን እንዲማር የተፈለገው ነገር ምንድነው? የትምህርቱ ይዘት ምንድነው? ሰነፍ ገብረ ጉንዳንን አይቶ ጠቢብ እንዲሆን ነው የተፈለገው፡፡ ስለዚህ እንዲማር የተፈለገው ጥበብን ነው፡፡ ምናልባት ጥበብ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡ ጥበብ ከእውቀት ያለፈ ነገር ነው፡፡ ስለአንድ ነገር ማወቅና አንድን ነገር ለማድረግ የሚያስችል ስልት እውቆ ተግባራዊ ማድረግ በተለያዩ ደረጃዎች የሚመጡ



ናቸው፡፡ ጥበብ አንድን ነገር አስተውሎ በመረዳት ያንን እውቀት ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል ብቃት ማግኘት ነው፡፡

ሰነፍ ገብረ ጉንዳንን በመመልከት የሚማረው ጥበብ ምንድነው? ገብረ ጉዳን አለቃና አዛዥ ሳትፈልግ ማድረግ የሚገባትን ነገር በወቅቱ ታደርጋለች፡፡ የምታደርገው ነገር ለራስዋ እንደሚጠቅማት በሚገባ ታውቃለች፡፡ በሥራዋም ሌላ አካል እንዲያዛት አትፈልግም፡፡ በራስዋ ተነሳሽነት ከራስዋ የሚጠበቅባትን ተግባር ማንም ሳያዛት ታከናውናለች፡፡ የምትሠራውን ነገር የምትሠራው ለራስዋ በማለት እንጂ በሌላ አካል ለስታዘዘች አይደለም፡፡ በዚህ ሁኔታ አለቃ ቢኖርም ባይኖርም ሥራው በወቅቱ ይሠራል ማለት ነው፡፡ ለሥራዋ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶአት ትሠራለች፡፡

በሥራው ትጋት የሌለው ሰው ከገብረ ጉንዳን በመማር ለራሱ ለሚያስፈልገው ነገር ሌላው ሰው ሳይነግረውና ሳያዘው በራሱ ተነሳሽነት መሥራት አለበት፡፡ አሠሪን ወይም የሥራ መሪን በመፍራት መሥራት ከአንድ ትጉ ሠራተኛ የሚፈለግ ባሕርይ አይደለም፡፡ ትጉ ሠራተኛ በተለይም ክርስቲያን የሆነ ሰው ሰውን ፈርቶ ሳይሆን ለሕሊናው በመታዘዝ ሥራውን በትጋት መሥራት ይጠበቅበታል፡፡ በዓውዳችን በአብዛኛው ሰዎች ሥራን በትጋት የሚሠሩት አሠሪው በአጠገብ ሲኖር ነው፡፡ አሠሪ ዘወር ሲል ሠራተኞቹ እንዲሁ ጊዜውን ያጠፋሉ፡፡ ደመወዝ ሲከፈል ግን በትጋት እንደሠራ ሠራተኛ ደመወዝ ይቀበላሉ፡፡ ይህ ከሰው ልጅ የሚፈለግ ባሕርይ አይደለም፡፡ ሰው መፍራትና መታዘዝ ያለበት ሕሊናውን ሊሆን የተገባ ነው፡፡ የትጉ ሠራተኛ አለቃው ሕሊናው ነው፡፡ ሕሊናውን በመታዘዝ የሚሠራ ሠራተኛ ሥራውን የሚሠራው መሥራት ኃላፊነቱ መሆኑን በመገንዘቡ ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሰው ያለውን ችሎታ፣ እውቀትና ልምድ በመጠቀም የሚቻለውን ሁሉ በማድረግ የሚሠራው ሥራ ፍሬያማ እንዲሆን ጥረት ያደርጋል፡፡

> *አንዳንድ ሰዎች ሕይወታቸውን የሚጠቅመውን ሥራ በትጋት እንዲሠሩ ሲመከሩ ምክሩን ተግባራዊ አድርገው ኑሮአቸውን ከማሻሻል ይልቅ «ለምን እንዲህ ይለኛል?» ብለው ያኮርፋሉ፡፡ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ ከምን የሚመነጭ ይመስላችኋል? እንዲህ ዓይነት ባሕርያቸውንም እንዲለውጡ ምን መደረግ አለበት?*

ገብረ ጉንዳን ምግቧን በበጋ ታሰናዳለች፡፡ ገብረ ጉንዳን በበጋ እንደ ልብዋ በመንቀሳቀስ ምግብዋን ማሰናዳት ትችላለች፡፡ በበጋ ወቅት ያሰናዳችውን ምግብ በሙሉ በአንድ ጊዜ በልታ አትጨርሰውም፡፡ ነገር ግን ለክረምት መቀመጥ የሚገባው ምግብ ይቀመጣል፡፡ ገብረ ጉንዳን እንኳ ለሰወደፊቱ በማሰብ በዕቅድ ትመራለች ማለት ነው፡፡ ዓላማዋ ለዕለታዊ ኑሮዋ የሚያስፈልገውን ነገር መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ከዕለታዊው ፍጆታ ያለፈውን ቀስ በቀስ በመቆጠብ ለክፉ ቀን ታስቀምጣለች፡፡

> *አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጭምር በትጋት እየሠሩ ገቢ ያገኛሉ፡፡ ነገር ግን ያገኙትን ነገር በቁጠባ ባለመጠቀማቸው ኑሮአቸው ከቀን ወደ ቀን ሲሻሻል አይታይም፡፡ እንደ ክርስቲያን ስለቁጠባ ያለን አመለካከትና ልምምድ ምን ይመስላል? ለነገ ብሎ መቆጠብ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለውን? ካለው እንዴት መቆጠብ እንችላለን?*

ሰነፍ ሰው ከገብረ ጉንዳን የሚማረው ሌላው ትምህርት በምቹ ጊዜ በትጋት በመሥራት ለኑሮ የሚያስፈልገውን ነገር ማግኘት ነው። ሰነፍ ጊዜው ምቹ ሆኖ ሳለ መሥራት ይጠበቅበታል። በምቹ ጊዜ መሥራት ብቻም ሳይሆን የሥራውን ፍሬ በአንድ ጊዜ በልቶ መጨረስ የለበትም። ነገር ግን ለዕለት የሚያስፈልገውን ነገር እየተጠቀመ፣ ለነገም ማበቀመጥን መማር ይገባዋል። ከድህነት የመውጫው መንገድ አንዱ ተግቶ መሥራት ሲሆን ከዚህ ባልተናነሰ ሁኔታ ሌላው አስፈላጊ ነገር ደግሞ መቆጠብ ነው። በትጋት መሥራትና በዕቅድ መቆጠብ የእድገት መርሆዎች ናቸው። በትጋት ሠርቶ ብዙ ፍሬ ማፍራት የቁጠባ ባሕል ካልታከለበት ዘላቂነት ያለውን የእድገት ሰውጥ ማምጣት አይቻልም። ቁጠባ ለነገ ከመጨነቅ የተነሳ የሚደረግ ሳይሆን በሥራ የተገኘው ፍሬ ዛሬውን ማሰቅ እንደሌለበት መረዳትና አርቆ የማሰብ ውጤት ነው። አንድ ሰው እውቀትና የሥራ ልምድ ቢኖረውም መሥራት የማይችልበት ወቅት ሲመጣ ይችላል። ይህም ከአካባቢ ሁኔታ የተነሳ ወይም ከዕድሜ ማርጀት ወይም ከሌሎች ሁኔታዎች ሲሆን ይችላል። በዚህ ወቅት መጠቀም የሚቻለው በቁጠባ የተቀመጠውን ህብት ነው። ሰነፍ ይህን አያደርግም። ከገብረ ጉንዳን የሚማር ሰው ግን ይህን ማድረግ የሚያስችለውን ጥበብ ይማራል።

በበጋ መሥራት ድካም አለው። በጋ የሙቀት ወቅት ስለሆነ በዚያ ሙቀት በትጋት ከመሥራት ይልቅ አቤት ውስጥ ወይም ጥላ ሥር ማረፍ ደስ ይላል። አስቸጋሪ ነገር ቢኖርም ግን የሥራ ወቅት ነው። በዚህ ወቅት በትጋት በመሥራት ለክረምት ጊዜ የሚበቃን ምግብ ማከማቸት ይቻላል። ሥራውን በመተው በተለይም ባለው አካባቢያዊ ሁኔታ በማላበብ ጊዜው ካለፈ ቢፈለግም መሥራት የማይቻልበት የክረምት ወቅት ይመጣል። «ሙሉ በጋ ስትዘል ከርማ ሳታስብ ወደኋላ፣ ክረምት ገባ ጉዱዋ ፈላ» እንደሚባለው መሆን ይመጣል። ክርስቲያን በማንኛውም የዕድሜ ደረጃ ላይ ቢገኝ ለመሥራት ያለውን ዕድል ሳይጠቀም መቅረት የለበትም።

ሰነፍ ከገብረ ጉንዳን መማር ያለበት ሌላው ትምህርት ደግሞ ከሌሎች ሰዎች ጋር በትብብር መሥራት መቻልን ነው። ገብረ ጉንዳን በመተባበር ለጋራ ዓላማና ጥቅም ትሠራለች። አንድ ጉንዳን አንድ ትልቅ ለምግብ የሚሆን ነገር ተሸክማ የምትሄድ ከሆነች ሌላዋ መጥታ ትረዳታለች። በመተባበር ያን ትልቅ ነገር ወደ መጋዘን ያስገባሉ። የሚጠቀሙበት ጊዜ ሲደርስ ደግሞ በጋራ ይጠቀሙበታል። ሰነፍ ሰው ከሌሎች ሰዎች ጋር በመተባበር ለጋራ ዓላማ መሥራት አይፈልግም። ከዚህ ዓይነት አንድነት የሚሸሸውም ሥራ እንዳያሠሩት ነው። ወደ አንድነቱ ቢገባም ሥራውን በተለያዩ መንገዶች በመለገም ሥራው ከሚፈለግበት ግብ እንዳይደርስ ምክንያት ይሆናል። ከዚህም የተነሳ ትጉ ሠራተኞች ሰነፍ ሰውን አያስጠጉትም።

> *«አንድነት ኃይል ነው» ይባላል። በዓውዳችን ክርስቲያኖች ምን ያህል በኅብረት ሠርተው ኑሮአቸውን ለመለወጥ ጥረት እያደረጉ ነው? በመሠረተ አሳብ ደረጃ ክርስቲያኖች ከሌሎች ሰዎች ይልቅ የሚያስተሳስራቸው የክርስቶስ ፍቅርና ሥልጣን ኢያለ አነርሱ ግን በኅብረት ለመሥራት ሲቸገሩ ይታያል። ይህ ለምን እንዲህ ይሆናል? በኅብረት ሠርተው ፍሬያማ በመሆን ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን ምን ቢያደርጉ ይሻላል?*



ከዚህ ክፍል መረዳት እንደሚቻለው ለሥራ ምቹ በሆነበት ወቅት ተገቢውን ዋጋ በመክፈል በትጋት መሥራት ከቀረ ችጋር ወይም ድህነት መሣሪያ እንደ ታጠቀ ወንበዴ ድንገት ይመጣል። ድህነት ጨካኝ ወንበዴ ነው። የድህነት ሰይፍ የሚበላው የማይሠራውን ሰው ነው። ከዚህ ሰይፍ ከታጠቀ ወንበዴ ማምለጥ የሚቻለው ተግቶ በመሥራት ነው። መሥራት በሚገባበት ወቅት ያለሥራ መቀመጥ የታጠቀ ወንበዴ መጥቶ አደጋ እንዲያደርስ መፍቀድና ቀጠሮ መስጠት ነው። ክርስቲያን ለዚህ ወንበዴ ራሱን መስጠት እንዲሁም ሌሎች ሰዎችም ራሳቸውን እንዲሰጡ መስጠት የለበትም። ይህንን ለማድረግ ራሱ ተግቶ በመሥራት ለሌሎች ሰዎች መልካም ምሳሌ በመሆን ማሳየት ይጠበቅበታል።

> *«የክርስቲያን ደሴት» በሚባል አገር ውስጥ እያለን በዓለም ግን በድህነታችን የታወቅነው ለምን ይሆን? እግዚአብሔር ስለማይወደን ወይስ በዓለም ካሉት ሕዝቦች ሁሉ ኃጢአተኞች በመሆናችን ወይስ ለሥራ ያለን አመለካከት ትክክል ባለመሆኑ ወይስ በትጋት መሥራት የሚገባንን ያህል ስለማንሠራ ወይስ ሌላ? እንደ ክርስቲያን የድህነታችን ምንጭ ምንድነው ብለን መናገር እንችላለን? ተደጋግፈን በትጋት ብንሠራ ከድህነት ሰይፍ ማምለጥ የምንችል አይመስላችሁምን?*

ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ተከታዮች በሥራ መትጋት እንደሚገባቸው በግልጽ ያዛቸዋል። አማኞች በትጋት ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን እንዲሁም ከዚያ አልፈው ሌሎች ሰዎችን መርዳት እንደሚገባቸው ይመክራቸውና ያዛቸዋል። በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ዳግመኛ የተወለዱ ሰዎች መልካም ያልነበረውን ባሕርያቸውን በመተው በአዲስ የሕይወት ዘይቤ መመላለስ ይገባቸዋል። የባሕርይ ለውጥ ማሳየት ከሚገባቸው ነጥቦች አንዱ በሥራ ላይ ባላቸው አመለካከትና ትጋት ነው። ሐዋርያው «የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፣ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም» (ኤፌ.4:28) በማለት ይናገራል።

የክርስቶስ ተከታይ የሆነ ሰው ውስጣዊ ሕይወቱ ማለትም አእምሮው ሲታደስ የቀድሞ ባሕርይውን እርግፍ አድርጎ መተው ይጠበቅበታል። በራሱ ጥረት ቢሆንም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ለጥቅም የሚሆን ነገር መፈለግ የለበትም። በኃይልም ሆነ በጥበብ ተገቢ ያልሆነ ሥራ መሥራት የለበትም። በማንኛውም መልኩ በስርቆት ተግባር ላይ መሳተፍ አይገባውም። ባለው ሥልጣን ወይም ጥበብ በመጠቀም በሕጋዊ መንገድ የእርሱ ያልሆነውን ንብረት መውሰድ ወይም መጠቀም አይገባም።

ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የሰዎችን/የድርጅቶችን ህብት አለመውሰድ በራሱ አንድ መልካም ነገር ቢሆንም በቂ ግን አይደለም። ይህ የክርስቶስ ተከታይን ባሕርይ ለማሳየት ግማሽ መንገድ የመሄድ ያህል ነው። እንደ ክርስቲያን ኃጢአት የሚባለውን ነገር መተው በራሱ ሙሉ ለውጥን

አያመለክትም። አንድ የሚቀር መሠረታዊ ነገር አለ። ይኼውም በፊት ይሠራ የነበረው ድርጊት ተቃራኒ የሆነ ነገር መሥራት ነው። ከላይ በተጠቀሰው ክፍል ውስጥ እንደተጠቀሰው ይሰርቅ የነበረ ሰው የክርስቶስ ተከታይ ከሆነ በኋላ አለመስረቁ መልካም እርምጃ ነው። በስርቆት ላይ ተሰማርቶ ለነበረ ሰው መስረቅን ማቆም ሙሉ ለውጥን አያሳይም። ሌሎች የሚቀሩት አዎንታዊ እርምጃዎች አሉ።

የሥነልቦና ችግር ካሳጋጠማቸው በስተቀር በአብዛኛው ሰዎች በስርቆት ላይ የሚሰማሩት ባለመሥራታቸው ማለትም ሥራ ሠርተው ለራሳቸው ኑሮ የሚበቃቸውን ነገር ካለማግኘታቸው የተነሳ ነው። በመካከለኛው ዘመን የነበረ አንድ መንፈሳዊ መሪ «ስርቆት የሥራ መፍታት ውጤት ነው» በማለት ተናግሮ ነበር። *ሥራ* የማይሠሩ ሰዎች ለኑሮ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማግኘት ከሚጠቀሙባቸው መንገዶች አንዱ መለመን ነው። ነገር ግን በሰዎች ታይተው ይሉኝታን ሰብረው፣ ለማኝ መባልን በመቻል በዚህ ተግባር ላይ መሰማራት ያሸማቅቃቸዋል። ከዚህም የተነሳ የሰዎችን ንብረት ወደ መስረቅ ይሄዳሉ። ይህ ግን ዘለቄታ ያለው መፍትሔ አይሆንም። የእግዚአብሔር ቃል መፍትሔው ተግቶ መሥራት እንደሆነ ያስተምራል። በተለያዩ መንገዶች የሚደረገውን ስርቆት በማቆም ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል። ስለዚህ ቀድሞ ይሰርቅ የነበረ ሰው ዳግመኛ እንዳይሰርቅ ስርቆትን ማቆም ብቻ ሳይሆን በእጆቹ ተግቶ መሥራትን መጀመር ይኖርበታል። ዳግመኛ ወደ ስርቆት ተግባር ሳለመመለስ ዓይነተኛ ው መንገድ ሠርቶ ሀብት ማፍራት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህም በላይ አንድ እርምጃ እንደሚቀር ያመለክታል። ሠርቶ ንብረትና ሀብት ማፍራት ብቻ ሳይሆን በመሥራት ራሳቸውን መቻል ያልቻሉትን/የማይችሉትን ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ ችግር ውስጥ የሚገኙትን ሌሎች ሰዎችን መርዳት መጀመር ነው። ይህ ሲሆን ወደ ቀድሞ መጥፎ ባሕርይ መመለስ ይቀራል። በሕይወት ውስጥ የተጀመረው ለውጥም ሙሉ ይሆናል።

> *ከድህነት ለመውጣት ክርስቲያኖች መጸለይ ወይም የእግዚአብሔርን በረከት መጠበቅ ወይም ተዓምራዊ ተሐድሶ መመኘት ብቻ በቂ ነውን? ከጸሎት በተጨማሪ ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? በገዛ እጆቻችን በሥራ መድከም ምን ያህል ድርሻ ይኖረዋል?*

ጳውሎስ ከምክርና ከትዕዛዝም አልፎ መሥራት እየቻሉ በትጋት ሠርተው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የማይረዱ አማኞች ከቤተክርስቲያን ኅብረት እንዲገለሉና ቤተክርስቲያን ለእንዲህ ዓይነት ሰዎች ምንም ዓይነት እርዳታ ማድረግ እንደማይገባት አጥብቆ ይናገራል (2ተሰ.3:6፣14፣ 3:10)።

ጳውሎስ እንዲህ ዓይነት ትዕዛዝ በድፍረት የሚሰጠው ሠርቶ ራስንና ሌሎች ሰዎችንም መርዳት እንደሚቻል ራሱም ምሳሌ ሆኖ በማሳየት ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ትጉህ የወንጌል መልዕክተኛ ከመሆንም በተጨማሪ ትጉህ ሠራተኛ ነበር (2ተሰ.3:7-9፣ የሐዋ.20:33-35፣ 1ተሰ.2:9)።

ከእነዚህ ከተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለሥራ የምንማራቸው ጠቃሚ አሳቦች አሉ። ከእነዚህም የመጀመሪያው *ሥራ* መልካምና ለሰው ልጅ የሚጠቅም መሆኑ ነው። *ሥራ* መርገም ሳይሆን በረከት ነው። *ሥራ* ለሚሠራው ሰው እንዲሁም ለኅብረተሰቡ ይጠቅማል።



የሰው ልጅ በሚሠራበት ጊዜ ለኑሮ የሚያስፈልገውን ማለትም የሚበላውንና የሚጠጣውን ነገር ከማግኘቱም በላይ *ሥራው* ራሱ ደስታን ይሰጠዋል። ሰው የማይሠራ እንዲሁም በሥራው የማይደሰት ከሆነ ትርጉም ያለውን ሕይወት መምራት አይችልም። እግዚአብሔር የሰው ልጅ *ሥራን* እንዲሠራና በሥራውም እንዲደሰት ዕድል ፈንታ ሰጥቶታል። ይህ የሚያሳየው *ሥራ* መልካምና ደስታን ሊሰጥ የሚችል ነገር ሲሆን የሰው ልጅ ያለሥራ እንደ ሰው ሕይወትን በሙላት መኖር አለመቻሉን ነው። በመጽሐፈ መክብብ ውስጥ «... ሰው እግዚአብሔር በሰጠው በሕይወቱ ዘመን ሁሉ ይበላና ይጠጣ ዘንድ ከፀሐይ በታችም በሚደክምበት ድካም ሁሉ ደስ ይለው ዘንድ ነው፣ ይህ እድል ፈንታው ነውና» (መክ.5:18) የሚል ቃል ይነበባል።

ሁለተኛው *ሥራ* ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተሰጠ ኃላፊነት ነው። ሠርቶ መኖር ለሰው ልጅ የተሰጠ ሞራላዊ ግዴታው ነው። *ሥራን* ሳይሠራ የሰው ልጅ የራሱን ፍላጎት የሚያረካበት ሌላ አማራጭ መንገድ ከእምላክ ዘንድ አልተሰጠም። የሰው ልጅ በዚህ በተሰጠው ምድር ላይ የሚፈልገውን አግኝቶ መኖር ከፈለገ በትጋት መሥራት ይኖርበታል። እግዚአብሔር ሰውን በገነት ውስጥ አስቀምጦም «ሁሉን ነገር አደርግልሃለሁና አንተ ቁጭ ብለህ ብቻ ብላ፣ ጠጣ፣ ተዝናና» አላለውም። እንኳን ከዚህ በኃጢአት በተበላሸ ዓለም ቀርቶ እግዚአብሔር ሰው በኤደን ገነትም ሠርቶ እንዲኖር አዞታል። ስለዚህ አማኞች «እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፣ እርሱ የምንፈልገውን ነገር ይሰጠናል፣ ዋናው ነገር መጸለይ ነው...» እያሉ በሥራ ሳይተጉ መቅረታቸው ወደሚመኙት ገነት ሳይሆን በዓለም በምድረ በዳ ውስጥ እንደሚኖር ሰው እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል። በትጋት ሠርቶ መኖር እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ዕቅድ ስለሆነ አይሻርም። በዚህ ውስጥ እግዚአብሔር አማኞች ሳይሠሩ እንደሚባርካቸው፣ በተዓምር እንደሚያኖራቸው እንዲሁም ሌሎች ሰዎች ሠርቶላቸው እነርሱም እንዲሁ የሚበሉበትንና የሚጠጡበትን ተስፋ አልሰጠም። አማኞች እንደማንኛውም ሰው መሥራት ይገባቸዋል። እንደ እግዚአብሔር ሰው መሥራታቸው ግን ልዩነትን ያመጣል። ይህን በተመለከተ በኋላ እንመለስበታለን።

አለመሥራት መብት አይደለም። *ሥራን* መሥራት ግዴታ ነው። ቢጠላም ቢወድም አማኝ *ሥራን* መሥራት ይኖርበታል። ካልሠራ ይሞታል። አንድሪው ሙሬ የሚባለው ታዋቂው የወንጌል መምህር *ሥራን* በተመለከተ፦

> በእርግጥ *ሥራ* የመኖር ከፍተኛው ደረጃ ነው። ሕይወት ድርጊት ናት። ሕይወት ራስዋን የምትገልጠው በምትሠራው *ሥራ* ነው። አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ መንፈሳዊ፣ የማህበራዊና ብሔራዊ ሕይወት እያንዳንዳቸው የሚለኩት በሥራዎቻቸው ነው። የሚሠራው *ሥራ* ባሕርይና ጥራት የሚለካው በሚሠራው ሕይወት ነው። *ሥራ* የሕይወት ውጤት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ሕይወት በሥራ ላይ ጥገኛ ናት። ከዚህ ውጭ የሕይወት ሙሉ እድገት፣ መግለጫ እንዲሁም ፍጹምነት አይኖርም። ሕይወት የሥራ ውጤት ናት።
> ...

ሥራ በሕይወት ላይ ጥገኛ ነው። እንዲሁም ሕይወት ስማደግና ፍጹም ለመሆን በሥራ ላይ ጥገኛ ናት። ሕይወት ሁሉ ግብ አላት። ሕይወት ያለሥራ ዓላማዋን ከግብ ማድረስ አትችልም። ሕይወት ወደ ፍጹምነት የምታድገው በሥራ ነው። የሕይወት የተደበቀው ባሕርይዋና ኃይልዋ የሚገለጥበት ዋነኛው መንገድ በምትሠራው ሥራ ነው። ስለዚህ ሥራ የተደበቀው የክርስትና ሕይወት ውበትና መለኮታዊ ኃይል መገለጫ ትልቅ መሣሪያ ነው[12] በማለት ጽፏል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሰው አሳብ ሥራና የሰው ልጅ ሕይወት ከፍተኛ ቁርኝት እንዳላቸው ያመለክታል። ሰው ሥራን ሲሠራ ራሱንም ይለውጣል። ያለሥራ የሰው ልጅ ሕይወት አይለወጥም። የሰው ልጅ ሕይወት መለወጥ ደግሞ ሥራን ይለውጣል። ሥራ ሰውን፣ ሰውም ሥራን እየለወጠ ሂደቱ ይቀጥላል። አንዱ ለማደግ ሌላውን ይፈልጋል። ሥራ ሠሪዋን ትመስላለች፣ ሠሪዋም ሥራውን ይመስላል። ስለሆነም የሰው ልጅ ከሥራ ተለይቶ መኖር የሚችልበትና እግዚአብሔር ወዳቀደለት ግብ የሚደርስበት መንገድ የለም።

ስለዚህ ሰው የሚሠራውን ሥራ ቢወድም ባይወድም መሥራቱ የግድ ነው። የሰው ልጅ የሚመሳለለው ሥራን እንደ ራሱ ግዴታ በመቀበሉ ላይ እንጂ በሚሠራው ሥራ እኩል ደስታና እርካታ በማግኘቱ አይደለም። ብዙዎች በሥራዎቻቸው ደስተኞች ላይሆኑ ይችላሉ፣ ነገር ግን ሥራውን ይሠራሉ። ምክንያቱም ሳይሠሩ መኖር አይችሉም። በተለይ ደግሞ እንደ ክርስቶስ ተከታይ ሥራን ሳይሠራ አንድ ሰው እንዴት መኖር ይችላል? ምናልባት «እግዚአብሔር በተዓምር ያኖራል» እያለ በተለያዩ ዘዴዎች መንፈሳዊ ነገሮችን እየቀላቀለ ካልሰረቀ፣ ካላጭበረበረ ወይም ካልለመነ በስተቀር ክርስቲያናዊ ሥነምግባርን በጠበቀ ሁኔታ እንዴት ገቢ ሊያገኝ ይችላል?

የሰው ልጅ መልካም ኅብረተሰብን ለመፍጠር ኃላፊነት ተሰምቶት መሥራት ይጠበቅበታል። በኅብረተሰብ ውስጥ የማይሠራ ሰው እንደ መልካም ዜጋ አይቆጠርም። ምክንያቱም ለመልካም ኅብረተሰብ ግንባታ የበኩሉን አስተዋጽኦ እያደረገ ባለመሆኑ ነው። ለኅብረተሰቡ ማበርከት የሚገባውን ነገር አለማበርከት ለኅብረተሰቡ ሸክም ያደርጋል። መሥራት እየቻለ በትጋት ሠርቶ ራሱን የማይችል ሰው ወላጅም፣ ቤተሰብም፣ ማኅበረሰብም አይወዱትም። ይህ ማለት ሥራን አለመሥራትና በትጋት አለመፈጸም በኅብረተሰቡ ዘንድም ተቀባይነትን ሲያሳጣ በተቃራኒው ደግሞ ሥራን በትጋት መሥራት በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነትንና ክብርን ያስገኛል።

መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአት ወደ ዓለም መግባቱ ሰዎች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት እንዲለወጥ እንዳደረገ ይናገራል። ኃጢአት ወደ ዓለም በመግባቱ ሰዎች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ኃላፊነት ተግባራዊ ለማድረግ ችግር ገጠማቸው። ለሥራ ያላቸው አመለካከት ተለወጠ። ሥራ ከባድና የማያስደስት ሆነባቸው። በመጀመሪያ መልካም የነበረች መሬት ከኃጢአት የተነሣ ተረገመች። ከዚያም እሾህንና አሜከላን አበቀለች (ዘፍ.3:18)። የሥራ ሁኔታ አስቸጋሪ መሆን ደግሞ ሰዎች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት

[12] Murray, A. (1983). *How to Work for God.* Whitetaker House. Pp28-29



ከእግዚአብሔር አሳብ ውጭ እንዲሆን አንዱ ምክንያት ሆነ። ኃጢአት ወደ ዓለም ከገባ በኋላ ሥራ ለሰው ልጅ የሚገባውን ደስታና እርካታ መስጠት አልቻለም። «በፊትህ ወዝ እንጀራህን ትበላለህ» (ዘፍ.3:19) ተብሎለታል።

- ✓ ሰዎች ሥራን መናቅና ከተቻለ ደግሞ ሳይሠሩ እንዲሁ መኖር የሚችሉበትን ሁኔታ ማፈላለግ ተጀመረ።
- ✓ ሰዎች ሥራን ለራሳቸው ጥቅም ብቻ መጠቀም ጀመሩ። የራሳቸውን ጥቅም ለማግኘት ደግሞ የሌሎች ሰዎችን መብትና ጥቅም መርገጥ ጎልቶ ይታያል። ሥራን ለግል የማበልጸጊያ መንገድ ማድረግ ከእግዚአብሔር አሳብ ያፈነገጠ ነው (ሉቃ12:15-21)
- ✓ ሥራን እንደ ጣዖት ማምለክም የኃጢአት ውጤት ነው። ለሥራ ከተገቢ በላይ የሆነ ሥፍራ መስጠት ጥሩ ቢመስልም ዘላቂነት ያለው ጥቅም አይኖረውም። ለሥራ ከፍተኛ ሥፍራ ከመስጠት የተነሣ ለብዓዊ ግንኙነት ክፉኛ ይጎዳል።

*በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ በመንፈስ ቅዱስ ዳግም ልደት ማግኘትና የኃጢአት ስርየት መቀበል ክርስቲያኖች ስለሥራ የሚኖራቸው አመለካከትና ድርጊት እንዲለወጥ ማድረግ ይችላልን?*

ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት ሲበላሽ በሥራ አማካኝነት ለሕይወት ትርጉምና እርካታ ለማግኘት ሙከራ ያደርጋሉ። ሥራ ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ መሆኑ ቢታወቅም ለሰው ልጅ እግዚአብሔርን የመተካት አቅም የለውም። እግዚአብሔር የሚሰጠውን የሕይወት ትርጉምና ዘላቂነት ያለውን እርካታ ሥራ መስጠት አይችልም። ከኃጢአት የተነሳ ለሰው ልጅ የተፈጠረበትን ያህል ደስታና እርካታ መስጠት ያልቻለው ሥራ ከክርስቶስ ጋር መልካም ግንኙነት ሲኖር የደስታ ምንጭ ይሆናል። ምክንያቱም ሥራን እግዚአብሔርን የማገልገያ መንገድ እንደሆነ በመቀበል እንደ ግዳጅ ሳይሆን በፍላጎት በመሥራት ነው።

### ክርስቲያኖች ምን ዓይነት ሥራ መሥራት አለባቸው?

ሥራ በዚህ ዓለም ብቻ የሚኖር ሳይሆን በመንግሥተ ሰማያትም እንደሚኖር ተጠቅሷል። ክርስቲያኖች ሊመጣ ባለው የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ ምን ዓይነት ሥራ እንደሚሠሩ ባይታወቅም አብዛኛው በዚህ ዓለም ከሚሠራው ሥራ ለየት ያለ እንደሆነ ማሰብ ይቻላል። ከኃጢአት ተጽዕኖ ነጻ በመሆን እግዚአብሔርን የሚያስደስት ሥራ እንደሚሠሩ ይታመናል (ራእይ22:3)። በመንግሥተ ሰማያት አማኞች ሥራ ይኖራቸዋል። ይህም ሥራ እግዚአብሔርን ማምለክ ሲሆን ቀንና ሌሊት ይደረጋል (ራእ7:15)። ያለ ሥራ ለዘላለም መኖር ትርጉም የለውም። በዚህም ዓይነቱ ይለያይ እንጂ ሥራ ዘላለማዊ ባሕርይ ያለው እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

ሥራ ከሰው ልጅ ጋር አብሮ የተፈጠረ ነገር እንደሆነና በዚህ ምድር ላይ ሳይወሰን ሊመጣ ባለውም ዓለም እንደሚቀጥል ተመልክተናል። እንግዲህ ክርስቲያኖች ሥራ መሥራት የሚገባቸው ከሆነ ምን ዓይነት ሥራ መሥራት ይገባቸዋል? እግዚአብሔር እያንዳንዱ ክርስቲያን መሥራት የሚገባውን የሥራ መስክ ለይቶ እንደሚገልጽ በግልጽ የተነገረ ቃል የለም።

ሆኖም እግዚአብሔር አንዳንድ ሰዎችን ለተለየ *ሥራ* ሲጠራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንመለከታለን።

> *ክርስቲያኖች በዚህ ዓለም እንደ ማንኛውም ሰው መሥራት እንዳለባቸው ተመልክተናል። ነገር ግን ምን ዓይነት ሥራ መሥራት አለባቸው? ክርስቲያኖች ሥራን መምረጥ ያለባቸው በምን መሥፈርት ነው?*

ክርስቲያኖች እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ማንኛውንም *ሥራ* *መሥራት* ይችላሉ። ለ*ሥራ* የተለያየ ደረጃ በመስጠት አንዳንዱን *ሥራ* መልካም፣ ሌሎችን ደግሞ መጥፎ በማለት በመፈረጅ *ሥራዎችን* ከማበላለጥ ይልቅ በቃሉ ውስጥ ከተጠቀሱት የእግዚአብሔር ሕግጋት ጋር የማይጋጩትን *መሥራት* ይችላሉ። ክርስቲያኖች የሚሠሩት *ሥራ* ቃሉን የማይቃረን፣ ከ*ሥራው* የሚገኘው ውጤት (ምርት) ከክርስቲያን *ሥነምግባር* ጋር የሚጣጣም፣ በማንኛውም መልኩ ኅብረተሰብን የማይጎዳ፣ እንደ ሠራተኛ ለቤተሰብ የሚሰጠውን ጊዜ የማይሻማ እንዲሁም ሰውነትን የማይጎዳ ሊሆን ይገባል።

ከእግዚአብሔር አጠቃላይ እሳብ ጋር የሚጣጣም ማንኛውንም *ሥራ* *መሥራት* ለክርስቲያን የተፈቀደ ነው። በግለሰብ ደረጃ የሚስማማን *ሥራ* ለመምረጥ ወይም ለ*መሥራት* እእምሮን ለእግዚአብሔር ማስገዛት፣ የራስን ፍላጎት ለይቶ ማወቅ፣ በወጣትነት ዕድሜ ከሆነ የተለያዩ *ሥራዎችን* ሞክሮ ማየት፣ ከችሎታ ጋር የሚመጥን *ሥራን* መሻት፣ የሌሎች ሰዎችን ምክር ማግኘት፣ ለሚፈለገው *ሥራ* በትምህርት ራስን ማዘጋጀት፣ ከግል ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚጣጣምን *ሥራ* ለማግኘት በትዕግሥት መፈለግ፣ ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሰጥና ሰዎችን ለማገልገል ከፍተኛ ዕድል የሚሰጥ *ሥራን* መምረጥ ይቻላል።

ክርስቲያኖች ለምን ይሠራሉ?

በዚህ ዓለም እንደሚኖሩ ሰዎች ክርስቲያኖችም ለመኖር *መሥራት* ይኖርባቸዋል። ለመኖር ለእነርሱ የተለየ አማራጭ መንገድ የለም። ስለዚህ ክርስቲያኖች ለምን ይሠራሉ? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነውን? በእርግጥ ክርስቲያኖች ለመኖር ማለትም ለኑሮአቸው አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማግኘት *መሥራት* የግድ ነው (ምሳ.12:11፣ 14:23፣ 16:26፣ 1ተሰ 4:12)። ክርስቲያኖች የራሳቸውን የግልና የቤተሰብ *መሠረታዊ* ፍላጎት ለማሟላት *መሥራታቸው* መልካም ቢሆንም አንዳንድ ጊዜ ምኞታቸውን ለማርካትም ሲሠሩ እንደሚችሉ *መታወቅ* አለበት። ምኞትን ለማርካትና *መሠረታዊ* ፍላጎትን ለማግኘት *መሥራት* የተለያየ ነው።

> *እስቲ ጥቂት ጊዜ እንውሰድና ለምን እንደምንሠራ እናስብበት። ለሥራ የሚያነሳሳን ውስጣዊ ወይም ውጫዊ ምክንያቶች ምንድናቸው? ሥራ የምንሠራ ምን ለማግኘት ነው? ይህን ማወቅስ ምን ያህል የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወታችን ከግብ ያደርሳል?*



ክርስቲያኖች የራሳቸውን *መሠረታዊ* ፍላጎት ለማርካት በሚሠሩበት ጊዜ ከራሳቸው የተረፈ ነገር በማግኘት ሌሎች ሠርተው ራሳቸውን *መደገፍ* የማይችሉትን ሰዎች ለመርዳትም በትጋት ይሠራሉ። እግዚአብሔር ለድሆዎች ማሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ይናገራል። ተግተው በ*መሥራት* በአካባቢያቸው ወይም ሩቅ ቦታ ያሉትን ድሆዎች መርዳት በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ ተግባር ነው። ክርስቲያኖች የማያውቁትን ወገን መርዳት እንኳ ቢያቅታቸው የገዛ ችግረኛ ዘመዶቻቸውንና የዘመዶቻቸውን ልጆች ለመርዳት በትጋት *መሥራት* አይገባቸውምን? (1ጢሞ6:18)።

ሆኖም ክርስቲያኖች የሚሠሩት ለመኖር ብቻ ብለው አይደለም። ክርስቲያኖች ሌላ ዓላማ አላቸው። ክርስቲያኖች *ሥራ* የሚሠሩበት ዋነኛው ዓላማ ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ነው። ክርስቲያኖች የሚሠሩት *ሥራ* ለእግዚአብሔር ክብርን ማምጣት የሚችለው ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ *ሥነምግባርን* የሚጠብቅ ሲሆን እንዲሁም ለ*ሥራ* ያላቸው አመለካከት በእግዚአብሔር ፊት አስደሳች ከሆነ ነው።

*ሥራን* *መሥራት* ለኑሮ ብቻም ሳይሆን የ*ሥነ* ልቦና ጥቅም ይሰጣል። እግዚአብሔር የሰጣቸውን ችሎታ በሚጠቀሙበት ጊዜ ሰዎች እርካታንና ደስታን ያገኛሉ። *ሥራ* ለክርስቲያኖች እርካታና ደስታ የሚሰጠው በግዳጅ ሳይሆን በፈቃደኝነት ሲሠሩ ነው። ክርስቲያኖች ለምን *መሥራት* እንደሚገባቸውና *ሥራው* ለሕይወታቸው የሚሰጣቸውን ብድራት በትክክል ሲረዱ ነው። ይህን ዓይነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው ደግሞ መንፈሳዊ መሪዎች ስለ*ሥራ* መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ ትምህርት ሲሰጡአቸው ይጠበቅባቸዋል።

ከዚያም በላይ ለራሳቸው የሚኖራቸው እይታ መልካም ሆኖ ለራሳቸው የሚሰጡት ዋጋ ወይም ክብር ይጨምራል። «እኔ እንዲህ ማድረግ እችላለሁ» ሲሉ ለራሳቸው የሚሰጡት ክብር እየጨመረ ይሄዳል። *ሥራ* ካልሠሩ ግን የሚሰማቸው እንዲህ ያለ ስሜት ሳይሆን «እኔ የተፈጠርኩት በከንቱ ነው፣ ምንም ፍሬ ያለው ነገር ሳልሠራ እኖራለሁ» የሚል ነው። ይህ ደግሞ ሰዎች ስለራሳቸው ያላቸው እይታ ወይም ለራሳቸው የሚሰጡት ክብር ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርጋል። በአገር ደረጃ እንኳ ደሃ በመሆናችን የሚሰማን የበታችነት ስሜት አለ (መክ.2:24፣ 3:13፣ 22፣ 5:18-19)። ከዚህ አንጻር *ሥራ* የማንነትን ክብር ይጨምራል ማለት ነው።

*ሥራ* *መሥራት* የክርስቲያኖች ግዴታ እንደሆነ ተመልክተናል። *ሥራ* ተሠርቶ የሚጠበቀው ስኬት ሲገኝ ደግሞ ለእግዚአብሔር ክብርን መስጠት ተገቢ ነው። ለ*ሥራው* የሚያስፈልገውን ችሎታና መልካም ዕድሎችን የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ በመረዳት ለእርሱ የሚገባውን ክብርና *ምሥጋና* መስጠት ስኬቱ በዘላቂነት ለእነርሱና ለኅብረተሰቡ ጥቅምና በረከት እንዲሆን ወሳኝነት አለው (ዘፍ.26:12፣ 1ቆሮ4:7)። የመልካም በረከት ሁሉ ምንጭ እግዚአብሔር እንደሆነ *መረዳት* ትሕትናን፣ *ምሥጋናን*፣ ኑሮዬ ይበቃኛል የሚለውን መርሕ መከተልንና በእርሱ ላይ *መታመንን* *ያመጣል*። ክርስቶስን ለማይከተሉ ሰዎችም *መሥራት* የሚችሉበትን ችሎታና መልካም ሁኔታ የሰጣቸው እግዚአብሔር ነው። የእነርሱና የክርስቲያኖቹ ልዩነት ስለችሎታውና መልካም ዕድሎቹ ምንጮች

ያላቸው ግንዛቤ ነው። ያላመኑ ሰዎች ችሎታው ከራሳቸው እንደሆነ ሲያስቡ አማኞቹ ግን ችሎታውን ያገኙት ከእግዚአብሔር እንደሆነ መረዳት ለእርሱ ክብርን ይሰጣሉ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች ሥራን የሚሠሩት በዚህ ዓለም በሚኖሩበት ጊዜ ለኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ከማግኘት ያለፈ ነገር አለው። ሥራ ክርስቲያኖች የተፈጠሩበትና የተፈጠሩለት መስክ ነው። ክርስቲያን ሳይሠራ ለሌሎች ሸክም መሆን የለበትም፣ ይልቁን ሠርቶ ለሌሎች ማካፈል ይኖርበታል። እግዚአብሔር ክርስቲያኖች ሀብታሞች እንዳይሆኑ አልከለከለም። ሀብት ግን የሚገኘው በእግዚአብሔር በመታመን በመጸለይ ብቻ ሳይሆን በመሥራት ነው። ተሠርቶ የሚፈለገው ሀብት ሲገኝ ደግሞ ዓይንን በሀብት ላይ ከመጣል ይልቅ ለሥራው የሚያስፈልገውን ኃይልና ችሎታ ለሰጠው ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር መስጠት ይጠበቃል (1ጢ.ሞ.6:17-19)።

## ክርስቲያኖች በሥራ ላይ ሊያሳዩት የሚገባቸው መልካም ባሕርያት

በክርስቶስ ያመኑ ሰዎች ካላመኑ ሰዎች የተለየ ባሕርይ በሥራ ቦታ ማሳየት አለባቸው። ይህ በሚታይ ተግባር ብቻም ሳይሆን በውስጣዊ አመለካከታቸውም ስለሥራ ባላቸው አመለካከት የተለዩ መሆን እንዳለባቸው ያመለክታል። ያመኑ ካለመኑት የግድ የተለየ ነገር ሲኖራቸው ያስፈልጋል ማለት ሳይሆን አማኞች ሲኖራቸው የሚገባ አመለካከትና የሚያሳዩት ባሕርይ መልካምና እንደ እግዚአብሔር ቃል መሆን እንደሚጠበቅበት ለማሳየት ነው። ክርስቲያኖች ማሳየት ከሚገባቸው መልካም አመለካከቶችና ባሕርያት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም:-

ትጋት:- ክርስቲያኖች በሥራቸው ከማንም ሰው በላይ ትጋትን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። አምኞች በተሰጣቸው የሥራ ዕድል ተጠቅመው ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰዎችና ለራሳቸው ጥቅም በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል። ትጋት ጊዜን በሚገባ መጠቀም ያስችላል። ጊዜ ቆሞ አይጠብቅም። ጥበበኞች ግን እግዚአብሔር በሰጣቸው ጊዜ በትጋት በመሥራት ይጠቀሙበታል።

> *ክርስቲያኖች የግላቸው ያልሆነውን ሥራ ማለትም ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት ተቀጥረው የሚሠሩ ከሆነ ከሌሎች ሠራተኞች በተለየ ሁኔታ ትጋት ማሳየት ይጠበቅባቸዋልን? በየወሩ ደመወዝ እስከተከፈላቸው ድረስ ለምን በትጋት መሥራት ያስፈልጋቸዋል?*

ሐዋርያው ጳውሎስ ምዕመናን በትጋት ሥራዎቻቸውን መሥራት እንደሚገባቸው ይመክራቸዋል። «ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ ሁሉ በትጋት አድርጉት፣ ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና» (ቆላ.3:23-24) ይላል። ክርስቲያኖች በሚሠሩት ሥራ ሁሉ ትጋትን ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ለሰው ሳይሆን እግዚአብሔርን እያገለገሉ እንደሆኑ እንዲያስቡና እንዲሠሩ ተመክረዋል። ይህ ማለት በሥራቸው ክብርን የሚሰጡት ለሚያመልኩት አምላካቸው እንደሆነ በመገንዘብ እንደ ቃሉ፣ በልብ ቅንነት እርሱ በሰጣቸው ችሎታ መልካም የሆነውን ነገር ያለመታከት መሥራት አለባቸው ማለት ነው።



ለአሠሪያቸው በትጋት ሲሠሩ እግዚአብሔርን ማክበራቸው ነው። እንዲህ ዓይነት መልካም ሥራ በመሥራታቸውም ካከበሩት ከእግዚአብሔር ዘንድ ብድራታቸውን ያገኛሉ።

ታማኝነት - ክርስቲያኖች ለሚሠሩት ሥራ ታማኞች መሆን ይገባቸዋል። ማንም ሰው የታዘዘውን ነገር በታማኝነት በሚሠራበት ጊዜ አዛዡ በጣም ደስ እንደሚለው የታወቀ ነው። ሠራተኛ በታማኝነት ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ አሠሪ በጣም ይደሰታል፣ በሠራተኛው ሥራ እርካታን ያገኛል እንዲሁም ለሠራተኛው ተገቢውን ብድራት ለመስጠት ያስባል። ሐዋርያው ጳውሎስ በቀርጤስ ቤተክርስቲያንን ይመራ ለነበረው ቲቶ በጻፈው መልዕክት ውስጥ እንደ ቤተክርስቲያን መሪ ቲቶ የቤተክርስቲያን አባላት ሆነው በተለያየ ቦታ በወቅቱ ባሪያዎች ሆነው ለሚሠሩ ምዕመናን እንዲህ የሚል መልዕክት ጽፎ ነበር።

> ባሪያዎች ስለመድኃኒታችን ስለእግዚአብሔር የሚሆነውን ትምህርት ሁሉ ነገር ያስመስግኑ ዘንድ ለገዛ ጌቶቻቸው እንዲገዙ በሁሉም ደስ እንዲያሰኙ ሳይቃወሙና ሳይሰርቁም በጎ ታማኝነትን ሁሉ እንዲያሳዩ ምከራቸው (ቲቶ2:9-10)።

ሐዋርያው ጳውሎስ በተለያየ ሥራ ላይ ተሠማርተው የሚኖሩ በወቅቱ ባሪያዎች የነበሩ ሰዎች በኅብረተሰቡ ውስጥ ዝቅተኛ ሥፍራ ቢኖራቸውም ይህ ግን ለእግዚአብሔር አሳብ ከመታዘዝ ነጻ እንደማያደርጋቸው ይናገራል። የክርስቶስ ተከታይ የሆነ አማኝ በማንኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ ቢገኝ፣ ምንም ዓይነት ሥራ ቢሠራ በሚገኝበት ሥፍራ ሁሉ የክርስቶስን ሕግ መፈጸምና ሥራውን በፈሪሃ እግዚአብሔር ማከናወን ይጠበቅበታል። ሠራተኞች ለአሠሪያቸው መታዘዝና ሥራቸውን ደግሞ በታማኝነት መፈጸም ይገባቸዋል። ይህ አሠሪን መታዘዝ የሚለው አሳብ እርሱን/እርስዋን በመፍራት አለቃ የሚለውን ነገር መፈጸም ሳይሆን ለአሠሪ የሚገባውን ሥፍራ በመስጠት ከማክበር የመነጨ መታዘዝን ማሳየት ነው። ክርስቲያን የሆኑ ሠራተኞች ለአሠሪያቸው የሚታዘዙት በራሳቸው ፈቃድ በዚያ ሥፍራ ሆነው ለመሥራት በመወሰናቸውና ይህም የእግዚአብሔር አሳብ በመሆኑ ነው። ስለዚህ ጉልበታቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ልምዳቸውንና ጊዜያቸውን ሳይቆጥቡ በታማኝነት ማገልገል ይገባቸዋል። በሚሠሩበት ሥፍራ ታማኝነትን ማጉደል አሠሪያቸውንና ራሳቸውንም ይጎዳል። ከሁሉም በላይ ደግሞ እግዚአብሔርን ያሳዝናል፣ እርሱ በሕይወታቸው እንዳይከብር ያደርጋል።

ክርስቲያኖች በሚሠሩበት ቦታ ተገቢ በሆነ ነገር ሁሉ አሠሪዎቻቸውን ደስ ማሰኘት እንደሚገባቸው ታዘዋል። አሠሪያቸው የሚያዛቸው ከክርስቲያናዊ ሥነምግባር ውጭ ካልሆነ በስተቀር ሥራውን በሚመለከት ለአሠሪያቸው መታዘዝና የታዘዙትን በታማኝነት መፈጸም ተገቢ ነው። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በሆነ መታዘዝ ለአሠሪ መታዘዝ ከአሠሪ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔርም ዘንድ ብድራትን ያስገኛል። ለክርስቲያን ሠራተኞች የአሠሪያቸው የሆነውን ማንኛውንም ነገር ያለፈቃድ ለራሳቸው ጥቅም ማዋል ከሥነምግባር የጎደለ ሥራ ነው። የአሠሪያቸው የሆነን ነገር ያለፈቃድ መጠቀም ብቻም ሳይሆን የአሠሪያቸው ለሆነው ነገር ለራሳቸው ንብረት እንደሚጠነቀቁ ሁሉ መጠንቀቅና በአግባቡ መጠበቅ ይገባቸዋል። አሠሪያቸው እነርሱን በማመን ለሚሰጣቸው ለማንኛውም ነገር

ታማኞች ሆነው መገኘት ደረጃውን የጠበቀ ክርስቲያናዊ ሕይወት የመኖራቸው አንዱ ምልክት ነው።

ክርስቲያን ሠራተኞች የአሠሪያቸውን ንብረት አለመስረቅ ወይም ያለ አግባብ ማባከን መተዋቸው ብቻ በቂ አይደለም። መጥፎ የሆነውን ነገር አለማድረግ መልካም ቢሆንም የክርስቶስ ተከታዮች ግን ከዚያ ያለፈ መልካም ነገር ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በዚሁም መሠረት ክርስቲያን ሠራተኞች አሠሪያቸው አሁን ካለበት ደረጃ በላይ እንዲያድግ ከእነርሱ የሚጠበቀውን ማንኛውንም መልካም ነገር ሁሉ ማከናወን ይኖርባቸዋል። ሌሎች ከእነርሱ ጋር የሚሠሩ ሠራተኞች መጥፎ ነገር ቢያደርጉም «የእኔ መልካም ነገር ማድረግ ምን ለውጥ ሊያመጣ ይችላል?» ብለው ተስፋ ሳይቆርጡ በራሳቸው በኩል ማድረግ የሚችሉትን መልካም ነገር ሁሉ ማድረግ ቀስ በቀስ ለውጥን ያመጣል።

መጥፎ ነገር የአንድን ቡድን ሥርዓት ወደ መጥፎ ሁኔታ መለወጥ እንደሚችል ሁሉ መልካም የሆነ ነገር በሥርዓቱ ውስጥ ሲከናወንም ሥርዓቱን ወደ መልካም ሁኔታ መለወጥ ይችላል። «እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ... መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን እባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ» (ማቴ.5:14-16) ብሎ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለተከታዮቹ የተናገረውን ቃል ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስም የክርስቶስ ተከታዮችን «በመጥፎና በጠማማ ትውልድ መካከል ያለ ነቀፋ የዋሆችም ነውርም የሌለባቸው የእግዚአብሔር ልጆች እንድትሆኑ ሳታንጎራጉሩ ክፉም ሳታስቡ ሁሉን አድርጉ በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ» (ፊልጵ2:14-16) በማለት መክሮአቸዋል።

> *ብርሃን በብዛት ሳይሆን በማንነቱ ጨለማን የማስወገድ ኃይል አለው። ክርስቲያኖች በሚሠሩበት ሥፍራ ብዛት ባይኖራቸውም በአካባቢያቸው ላሉት ሰዎች ብርሃን መሆን ይችላሉ። እንደ ክርስቲያን በሥራ ቦታችን እንዴት በመልካም ሥራችን ለሌሎች ሰዎች ብርሃን መሆን እንችላለን? በግላችን ብርሃን ሆነን ለእግዚአብሔር ክብር ማምጣት የምንችልባቸው መንገዶች ምንድናቸው?*

ክርስቲያኖች በየትኛውም ሥፍራ በሚሆኑበት ወቅት ብርሃን መሆን ይጠበቅባቸዋል። ፍጥረተ-ዓለም ሲፈጠር በዓለም ትልቅ ልዩነት ያመጣው የብርሃን መፈጠር ነበር (ዘፍ1:3)። ይህ በብርሃን መፈጠር ትርጉም ያገኘው ዓለም ዛሬም የሚኖረው በብርሃን እማካኝነት ነው። የዓለም አዳኝ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ራሱ የዓለም ብርሃን እንደሆነ ተናገሯል (ዮሐ.8:12)። ክርስቲያኖችም እርሱን በመከተላቸው የእርሱ ባሕርይ በሕይወታቸው ውስጥ ይንጸባረቃል። ይህን ባሕርይ ደግሞ በዓለም በሚሆኑበት በማንኛ ውም ሥፍራ ማሳየትና ብልሹ ሥርዓት ባለበት ዓውድ ውስጥ መልካም ሥራዎችን በመሥራት መልካም ለውጥን የሚያመጣ አቅጣጫን ማሳየት ይገባቸዋል። የክርስቶስ ተከታዮች ሙስናና ብልሹ አሠራር ባለበት ሥርዓት ውስጥ ሆነው መልካም ነገርን እያደረጉ ለውጥ ማምጣት ካልቻሉ ዓለም ምን ተስፋ ሊኖራት ይችላል?



ከተነሳንበት ርዕስ አንጻር ክርስቲያኖች በሥራ ቦታዎቻቸው ያለው ሥርዓት ታማኝነትን የማያበረታታ ቢሆንም ተስፋ ሳይቆርጡ መልካም ሥራን ሁሉ እየሠሩ በሥርዓቱ ውስጥ እንደ ምልክት መታየት ቢችሉ እንደ ተራራ የማይገፋ የሚመስለው መልካም ያልሆነው የሰዎች አመለካከትና ድርጊት ይለወጣል። ክርስቲያኖች በሰዎች ዘንድ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚታዩትን ነገሮች ባለመፈጸማቸውና ራሳቸውን በክርስቲያናዊ ሥነምግባር ማስገዛታቸው ከውጭ ሆነው ለሚመለከቱ ሰዎች የተለያየ ትርጉም ሊኖረው እንደሚችል የታወቀ ነው። ቢሆንም ክርስቲያኖች ከሥነምግባር የጎደለ ድርጊት ጋር ባለመተባበራቸው ሌሎች እንደሚፈልጉት እንዳያደርጉ እንቅፋት በመሆናቸው ደስ ሊላቸው ይገባል። እንዲሁም የሚበጃቸውን የማያውቁ፣ ከሞት በኋላ መልካም ብድራት ለማግኘት ብለው በተሰጣቸው ዳግመኛ ዕድል በማይኖራቸው በዚህች ዓለም ምስኪን ኑሮ የሚኖሩ ምኞች፣ ጠባብ አእምሮ ያላቸው፣ አጉል ጽድቅ የሚፈልጉና የመሳሰሉት እያሉ ማጥላላታቸው እንደሚኖር መገንዘብ መልካም ነው።

በተቃራኒው ጥቂቶች ደግሞ ክርስቲያኖቹ ለራሳቸው ጥቅም ሳይሸነፉ ራሳቸውን በመግዛት የተሰማሩበትን ሥራ በታማኝነት ሲያከናውኑ በማየታቸው ያደንቁአቸዋል፣ እነርሱንም ለመከተል ፍላጎት ይኖራቸዋል። አንድ ነገር እርግጠኛ መሆን ይቻላል፣ እርሱም ክርስቲያኖች መልካም ሥነምግባራቸውን ጠብቀው በታማኝነት ሥራዎቻቸውን ሲሠሩ በሚሠሩበት ዓውድ ውስጥ በጨለማ ውስጥ እንዳለች ጭል ጭል እንደምትል ብርሃን መሆናቸው ነው። እነዚህ ጭል ጭል የሚሉ ብርሃናት አንድ ላይ ሲመጡ ደግሞ ምድራችንን ወደ መልካም ሁኔታ መለወጥ የሚችል ኃይለኛ ብርሃን ይሆናሉ።

ስለሆነም ክርስቲያኖች በሚሠሩበት በማንኛውም ሥራ ቦታ ክርስቲያናዊ ሥነምግባራትን በመጠበቅ በሚሠሩት ሥራ ስኬታማ ከመሆንም አልፈው ለእግዚአብሔር ትልቅ ክብር የሚያመጣ ለውጥን ማምጣት ይችላሉ። እንዲህ እንዲሆን «ክርስትና በልብ ነው» የሚለውን ፈሊጥ በመተው ክርስቲያን መሆናቸውን በእንደበትና በተግባር መግለጽ ይገባቸዋል። ካልሆነ መብራት አብርቶ ከመቅረዝ ላይ ሳይሆን በዕንቅብ ሥር ማስቀመጥ ይሆናል። ብርሃኑን ለማየት ለሚፈልጉ ሰዎች መብራት አይችልም። ክርስቶስን ባላመኑ ሰዎች መካከል በክርስቲያናዊ ሥነምግባር የማይመላለሱ ክርስቲያኖች በስም እንጂ በተግባር ለሌሎች ሊበራ የሚችል ብርሃን የላቸውም። ጨለማው እነርሱንም ውጦአቸዋል። ለሕዝቡ አቅጣጫን የምያሳይ ብርሃን በአካባቢው የለም ማለት ነው። በክርስቲያናዊ ሥነምግባር የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ግን በሚሠሩበት አካባቢ ምንም ያህል ቢጠሉም በተራራ ላይ እንዳለች ከተማ ሊሰወሩ አይችሉም። ለሕዝብ ሁሉ ምልክት ይሆናሉ፣ ሊመጣ ባለው ዓለም ብቻ ላይሆን በዚህም ሕይወት ከሰማዩ አባታቸው ብድራታቸውን ያገኛሉ።

> *እንደ ክርስቲያን ማድረግ የሌለብን እንደሆነ እያወቅን ነገር ግን ምንም አይደለም ብለን ከክርስቲያናዊ ሥነምግባር የጎደለ በሥራ ቦታ የምናደርጋቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው? እነዚህንስ ነገሮች እንዴት ማስወገድ እንችላለን?*

ክርስቲያኖች በሚሠሩበት የሥራ ቦታ መልካም ያልሆነ ድርጊታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች ማጽደቅ የለባቸውም። በአብዛኛው ያላመኑ ሰዎች ምንም ሳይሰማቸው የሚያደርጉአቸው ነገሮች አሉ። ክርስቲያኖች እነዚያን ነገሮች ማድረግ አይገባቸውም። ለምሳሌ ያህል የሚከተሉትን ነገሮች ማድረግ ለክርስቲያን ተገቢ አይደለም:-

- ✓ ምንም አይደለም እየተባለ ትንሽ ሐሰት የሆነ ነገር መናገር ወይም ለሰዎች ማውራት፣
- ✓ ለአሠሪያቸው፣ ለአብሮ ሠራተኞች ወይም ለተገልጋዮች የገቡትን ቃል አለመጠበቅ፣
- ✓ በሥራ ቦታ አሠሪን፣ ሌሎች ሠራተኞችን ወይም ሌሎች ሰዎችን ማማት፣
- ✓ ከሥራ ለመቅረት አስበው ሳይታመሙ ታመምን ብለው ቤት መዋል፣ የሐኪም ማስረጃ የሚያስፈልግ ከሆነ ደግሞ ከዘመድ ወይም ከጓደኛ ወይም በሌላም መልክ የሐኪም ፈቃድ ለማግኘት መሞከር፣
- ✓ የመሥሪያ ቤቱን ስልክና ንብረት ያለአግባብ ለግል ጥቅም ማዋል፣ አንዳንድ ሰዎች ክርስቲያኖችንም ጨምሮ የመሥሪያ ቤታቸውን ስልክ ያለአግባብ ለራሳቸው ሲጠቀሙበት ይታያሉ። አንዳንዶች እንደ ስልክ ቤት ሠራተኛ ቀኑን ሁሉ ስልክ እየደወሉ ይውላሉ።
- ✓ መሥራት ከሚችሉት በታች መሥራትና ሥራን መሰገምና ተገቢ ያልሆነ ውጤት ማምጣት፣

ከላይ የተጠቀሱትንና ተመሳሳይ ነገሮችን ማድረግ ለእግዚአብሔር፣ ለአሠሪ፣ ለተሰጣቸው ኃላፊነትና ንብረት እንዲሁም ለጊዜ ታማኝ አለመሆንን ያመለክታል። ክርስቲያኖች ለአሠሪያቸው ታማኝነታቸውን ከሚገልጡባቸው መንገዶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው። እነርሱም:-

- የአሠሪን ማንኛውንም ንብረት ያለፈቃድ አለመጠቀም፣
- በተገቢው ጊዜ ተገቢ የሆነው ውጤት ማምጣት፣
- ችሎታን፣ ልምድንና እውቀትን ያለመሰገም ተጠቅሞ መሥራት፣
- ተገቢ የሆነውን የአሠሪን ትዕዛዝ ለማስተናገድ ዝግጁ በመሆን፣
- የሥራን ጊዜ በሚገባ ማክበር፣
- አሠሪው በምስጢር እንዲጠበቅ የሚፈልጋቸውን መረጃዎች በምስጢር መጠበቅ፣
- በኃላፊነት የተሰጣቸውን ማንኛውንም ነገር ለአሠሪው ጥቅም መጠቀም፣
- አሠሪውን ሊጎዳ የሚችል ማንኛውንም መረጃ ቶሎ መናገርና የመሳሰሉት የሚጠቀሱ ናቸው።

እንግዲህ ክርስቲያኖች በሥራቸው በክርስቶስ ላላመኑት ሰዎች ብርሃን መሆን ከሚችሉባቸው መንገዶች አንዱ በታማኝነት የተሰጣቸውን ሥራ መፈጸማቸው ነው። በፈሪሃ እግዚአብሔር የሚመላለሱ የክርስቶስ ተከታዮች ታማኞች በመሆን ትውልድን ወደ ታማኝነት ጎዳና ማራመድ ይችላሉ።

ፍትሕ:- ክርስቲያኖች በተለይ አሠሪ ወይም ተጠሪ ሆነው ሌሎች ሠራተኞችን የሚመሩ ሲሆን በአመራራቸው ውስጥ ፍትሕ ጎልቶ መታየት



ይኖርበታል። ሠራተኞች ፍትሐዊ የሆነ አመራርን ይፈልጋሉ። ይህን ዓይነት አመራር ለመስጠት ብቃት ያለው ደግሞ ፍትሕ ከተሞላበት ከእግዚአብሔር ጋር መልካም ግንኙነት ያለው ሰው ነው። በዚህ ዓለም በተለይ ደግሞ በዓውዳችን በሥራ ቦታ ፍትሕ አይታይም። አሠሪዎች ወይም የሥራ መሪዎች መሥሪያ ቤቱ በሚተዳደረው መመሪያ ሳይሆን በሚፈልጉበት አቅጣጫ በመሄድ ሠራተኞችን ይበድላሉ፣ ተገቢ የሆነ ጥቅማ ጥቅሞችን ይከለክላሉ፣ ዝቅተኛ ክፍያ ይከፍሉአቸዋል፣ የደመወዝ ጭማሪ ይከለክላሉ፣ አንዱን ሠራተኛ ከሌላው በማበላለጥ ለአንዱ የማይገባውን ጥቅም ሲሰጡ፣ ሌላውን ደግሞ ያለአግባብ ሲበድሉና የመሳሰሉትን ኢፍትሐዊ ድርጊቶችን ሲፈጽሙ ይሰማል/ይታያል።

አንዳንድ አሠሪዎች ለሠራተኛው የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም ለመስጠት ከራሳቸው ንብረት እንደሚሰጡ ያህል በማሰብ ሠራተኛው ለመብቱ ሲጠይቅ ይከፋቸዋል። አንዳንዶች ደግሞ ራሳቸው በትጋት ሳይሠሩ ሌላውን ሠራተኛ በማሠራት በሥራው ውጤት ግን ራሳቸውን ለማስተዋወቅ ይፈልጋሉ። አንዱ በሠራው ሌላው ይመሰገናል፣ ጥቅምም ያገኛል። ለአንድ የሥራ ቦታ/ደረጃ ወደዚያ ደረጃ ሊያድግ የሚችል ሠራተኛ መሥሪያ ቤት ውስጥ እያለ ዘመድ ወይም ጓደኛን ለመቅጠር ማስታወቂያ ያወጣል። ከዚያም መሥፈርቱን እንዲያመጣ በተፈለገው ዘመድ ሁኔታ በመቅረጽ ዘመዱን ይቀጥራል። እነዚህ ነገሮች ፍትሕ የጎደላቸው ሥራዎች ናቸው (ኤፌ.6:9)። ክርስቲያን አሠሪ ወይም የሥራ መሪ እንዲህ ዓይነት ነገሮችን በፍጹም ማድረግ የለበትም።

> *ክርስቲያን የሥራ መሪ በሚመራበት ጊዜ የትኛውን ዓይነት የአመራር ዘይቤ መብት-መርሕ፣ ሥራ-መርሕ ወይስ ሰው-መርሕ ወይስ ሁሉንም መከተል አለበት? የትኛው መርሕ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት አለው? ለሠራተኛውና ለሥራው ስኬት ይጠቅማል?*

ክርስቲያን አሠሪ ወይም የሥራ መሪ ሠራተኞች መብታቸውን በማክበር መምራት ይጠበቅበታል። ከሥራ ይልቅ ለሠራተኞች ሰብዓዊ መብቶች ቅድሚያ መስጠት ይኖርበታል። ሥራ የሚሠራው ለሰው በመሆኑና ውጤታማ ሥራ የሚሠራው ደግሞ አመራሩ ለሠራተኞች ዋጋ እንደሚሰጣቸው ሲረዱ በመሆኑ ነው። ሠራተኞችን በክርስቲያናዊ ትሕትናና በጎነት መያዝ መልካም ነው። በክርስቲያን የሥራ መሪና ክርስቲያን ባልሆነው የሥራ መሪ መካከል ለሠራተኛው ፍትሕን በማድረግ ልዩነት ከሌለ የክርስቶስ ተከታይ መሆን ወዴት አለ? ያሰኛል። ለክርስቲያን አሠሪዎች መጽሐፍ ቅዱስ ምክርና ተግሳጽ አለው (ያዕ5:1-6፣ ቆላ3:24)።

ክርስቲያን የሥራ መሪዎች የሠራተኞችን መብት ማክበርና ማስከበር እንዳለባቸው ቢታወቅም እንኳን በዓለማዊ መሥሪያ ቤት የሥራ መሪ ሆነው በቤተክርስቲያንና በክርስቲያናዊ ድርጅት ውስጥ በተለያየ ደረጃ የሥራ መሪ ሆነው የሚመሩ ክርስቲያኖች የሠራተኞችን መብት እንደሚገባ አያከብሩም። ሠራተኛው ለመብቱ ጥያቄ ሲያቀርብ ክርስቲያን አሠሪዎች «ብርቱ ክርስቲያን ለመብቱ አይከራከርም፣ ለእግዚአብሔር ብቻ ይናገራል እንጂ» እያሉ ዝም ለማሰኘት ጥረት ያደርጋሉ። ሠራተኛው ደግሞ በመንፈሳዊ መንገድ በመሄድ «እኛ ክርስቲያኖች አይደለንም ወይ? ይህ ነገር

ስምን እንዲህ አልተደረገም» ብሎ ሲጠይቅ የመሥሪያ ቤቱን ደንቦች መጥቀስ ይጀምራል:: ክርስቲያን አሠሪ በተለይ ክርስቲያኖችን ሲመራ ክርስቲያኖች የመብት ጉዳይ ሲያነሱ በመንፈሳዊ አቀራረብ በመቅረብ ዝም ያሰኛቸዋል:: እነርሱ በመንፈሳዊ አቀራረብ ሲቀርቡት ደግሞ «ዓለማዊ» ይሆንባቸዋል:: ክርስቲያኖች በክርስቲያኖች ላይ በደል ለመፈጸም መንፈሳዊ አቀራረብ ወይም ቋንቋን ሲጠቀሙ ከማየት በላይ የሚያሳዝን ምን አለ? እንዲህ እየተደረገ ክርስቲያን እንዴት የዓለም ብርሃንና ጨው መሆን ይችላሉ? ለሌላው መልካምነታቸው ከመውጣቱ በፊት ለእርስ በርሳቸው መልካምነታቸው መታየት አይኖርበትምን?

> *ክርስቲያን የሥራ መሪ/አሠሪን ከሌሎች ካላመኑ የሥራ መሪዎች/አሠሪዎች ልዩ የሚያደርጉት ዋና ዋና መለያ ምልክቶች ምንድናቸው? እነዚህን ባሕርያት እንዴት ማሳደግ ይቻላል?*

እንግዲህ ክርስቲያን አሠሪዎች ለሠራተኞች የሚገባውን ነገር ሁሉ በማድረግ በሁለንተናዊ ሕይወታቸው ማደግ እንዲችሉ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል:: በእነርሱና በሠራተኞች መካከል ባለው ግንኙነትና አሠራር ሁሉ ፍትሕ መታየት አለበት:: እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክ በመሆኑ እርሱን የሚከተሉ ሰዎችም ከሌሎች ሰዎች ጋር ባላቸው ማንኛውም ግንኙ ነት ፍትሕን በተግባር ማሳየት መለያቸው ሊሆን ይገባል::

*ሥራን እንደ አገልግሎት መቁጠር:-* ሥራን መንፈሳዊና ዓለማዊ እያሉ መከፋፈል መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም:: ዶ/ር ክላውድና ዶ/ር ታምንሴንድ የተባሉ ክርስቲያን ጸሐፊዎች ሥራ መንፈሳዊ እንደሆነና ለባሕርይ ቀረጻም አስፈላጊ እንደሆነ እንዲህ በማለት ተናግረዋል::

> ሥራ መንፈሳዊ ነው:: በሥራችን እግዚአብሔርን ወደ መምሰል እናድጋለን፣ ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱ ሠራተኛ፣ ሥራ አስኪያጅ፣ ፈጣሪ፣ አሳዳጊ፣ ባለአደራና ፈዋሽ ነው:: ክርስቲያን መሆን ማለት በሰብዓዊ ማህበረሰብ ውስጥ ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ ሠራተኛ መሆን ነው:: ... ሥራ ለዘላለም እንድንሠራው ለሚጠብቀን ሥራ ባሕርይያችንን እየቀረጸ የሚያዘጋጀን ሥፍራ ነው::[13]

በዚህ አሳብ መሠረት ሥራ እግዚአብሔር በሰጠን ስጦታ ሠራተኛ የሆነውን የእግዚአብሔርን ምሳሌነት በመከተል መሥራት፣ መምራት፣ መፍጠር፣ ማሳደግ፣ ባለአደራነትን መፈጸምና ፈውስ የሚያስፈልገውን መፈወስ ነው:: እነዚህንም ነገሮች በመሥራት ሕይወታችን እያደገና ባሕርያችንም እግዚአብሔርን በመምሰል ያድጋል:: በዚህ ዓለም ሥራ መሥራት ባሕርያችንን በመቅረጽ በሚመጣው ዓለም ለዘላለም ለሚሠራው ሥራ ያዘጋጀናል::

ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ሥራ በሚሠራበት ጊዜ ሥራውን እንደ አገልግሎት ሲያስብ ለሥራው የሚኖረው አመለካከትና

[13] Cloud, H. & Townsend, J. (1992). *Boundaries*. Zondervan Publishing House, PP.194-195.



የሚያሳየው ትጋት የተለየ ይሆናል:: መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖች ሥራ ሲሠሩ ለአሠሪያቸው ብቻ እንደሚሠሩ ሳይሆን ለክርስቶስ እንደሚሠሩ በማሰብ በትጋት መሥራት እንዳለባቸው ተመልክተናል (ኤፌ6:5-8፣ ቆላ.3:23-24፣ 1ጢሞ6:1-2)::

በመሠረተ አሳብ ደረጃ የክርስቶስ ወንጌል የሰዎችን ሕይወት ከለወጠ ሰዎች ስለሥራ ያላቸውም አመለካከት ይለወጣል:: በሥራ ውስጥ ድካም እንዳለ የታወቀ ነው:: ለመልካም ነገር መድከም ግን ውጤት አለው:: ክርስቲያኖች ሆነው ስለሥራ ያላቸው አመለካከትና በሥራ ቦታ የሚያሳዩት ባሕርያት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ የሰዎቹን በወንጌል መለወጥና የአእምሮአቸውን መታደስ መጠርጠር ያስፈልጋል:: ሰዎች ስለአንድ ነገር የነበራቸው አመለካከትና ባሕርይ ቶሎ ብሎ እንደማይለቃቸው ቢታወቅም ቀስ በቀስ የወንጌል በሕይወታቸው ፍሬ ማፍራት ወደ እግዚአብሔር አሳብ እንዲያደርሳቸው ይጠበቃል:: ይህ ፍሬ በሥራም ላይ መታየት እንዳለበት መታወቅ አለበት::

ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እንዳይሆን ያደረገው አንዱ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው ሚዛን ያልጠበቀ መንፈሳዊ ትምህርት ነው:: ቤተክርስቲያን በዓውዳችን ክርስቲያኖች ስለሥራ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ እያበረከተች ያለው አስተዋጽኦ ከቁም ነገር ገብቶ የሚቆጠር አይመስልም:: ቤተክርስቲያን በምትሰጣቸው መንፈሳዊ ትምህርቶች ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው ግንዛቤ እንዲዛባ ማድረግዋን ከሚታየው ተጨባጭ ነገር በመነሳት መናገር ይቻላል:: ከቤተክርስቲያን ምስባክ የሚሰማው ሥራ ዓለማዊና ምድራዊ እንደሆነ በተቃራኒው ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎት መስጠት ደግሞ የተቀደሰ ሥራና መንፈሳዊ እንደሆነ ነው:: ከሥራዎች ሁሉ የሚበልጠው መንፈሳዊ ሥራ መሆኑ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ይነገራል:: በእርግጥ ይህ አሳብ በአንድ በኩል እውነትነት ቢኖረውም ሰዎች ግን ለኑሮአቸው በርትተው እንዳይሠሩ እንቅፋት ሊሆን አይገባም::

በቤተክርስቲያን በኩል የሚታየው ሌላው ችግር ደግሞ በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት ሰዎች በዚህ ዓለም በእቋራጭ መንግሥተ ሰማያትን በምድር እንዲኖሩ የሚያደፋፍር ነው:: የዘመኑ ክርስቲያኖች በቤተክርስቲያን ውስጥ በአምልኮ ላይ ሳሉ መንግሥተ ሰማያት የገቡ ይመስላቸዋል:: በስሜታቸው ነፋስ ላይ ሲከንፉ ውለው የዕለቱ የጉባኤ አምልኮ ተጠናቅቆ ከቤተክርስቲያን ሕንጻ ሲወጡ ደግሞ ወደ ምድር ይመለሱና ተመልሰው በቀድሞው ሕይወታቸው ውስጥ ይገባሉ:: መንፈሳዊ ትምህርቱ እንደ ሕመም ማስታገሻ መድኃኒት ሆኖላቸዋል:: ቤተክርስቲያን መሄድ ለጊዜው ከዚህ ዓለም ችግር «ነጻ» ሆነው በስሜታቸው እፎይታን የሚሹበት መንገድ ሆኗል::

ከዚህም በተጨማሪ በቤተክርበቲያን የሚሰጠው መንፈሳዊ ትምህርት ክርስቲያኖች ከሚኖሩበት ተጨባጭ ዓለምና ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ባለመሆኑ ምዕመናን ቤተክርስቲያን ሲሄዱ የዕለት ኑሮአቸውን በምን ዓይነት ሁኔታ በመኖር ወደ እግዚአብሔር አሳብ ሙላት መድረስ እንደሚችሉ በቂ እውቀት አያገኙም:: ምዕመናን ያሉበት ሁኔታ በድህነትና በጉስቁልና ሆነው ሳለ የሚሰበከው ግን ከድህነትና ጉስቁልና እንዴት መውጣት እንደሚቻል ሳይሆን ስለበረከትና የድል ሕይወት ነው:: ምዕመናን ቤተክርስቲያን ውስጥ

ሲሆኑ ስለድህነታቸው እንዲያስቡም አይፈለግም፣ እርሱን መርሳት እንዳለባቸው ይነገራቸዋል። የሚሰበከው ስለምድር ሳይሆን ስለሰማይ ነው። እንዴት ከምድር ተነስቶ ሰማይ መድረስ እንደሚቻል ግን ተጨባጭ የሆነ ምክርና መመሪያ አይሰጥም።

በተመሳሳይ ሁኔታ ምዕመናን በእርሱ ላይ እምነት ቢኖራቸው እግዚአብሔር ሁሉን ነገር መልካም እንደሚያደርግ ተደጋግሞ ይነገራል። በዚህ ሂደት ማለትም ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ሲታመኑና እግዚአብሔር ለመባረክ ሲያስብ በሚሰጠው ትምህርት ውስጥ ሰብዓዊ ድርሻ ምን እንደሆነ አይጠቀስም። ይህን መንፈሳዊ ትምህርት የሚሰማው ምዕመን ለጊዜው እውነት ነው ብሎ ተቀብሎ ወጣ ብሎ ከተጨባጩ ዓለም ጋር ሲገናኝ ከፉውን ዓለም እንዴት ማሸነፍ እንደሚችል ምንም ዋስትና የለውም። ኑሮውን ለማሻሻል እንድ እውነት የተማረ መስሎት ነበር፣ ነገር ግን የሰማው ትምህርት ከሕይወት ጋር ተዋሕዶ የሚጠቅመው ሳይሆን ለጊዜው ስሜትን የሚያግል ሆኖ ያገኘዋል። መንፈሳዊነቱ ሁለንተናዊ ሕይወቱን ሲለውጥ አይታይም።

ምዕመናን በቤተክርስቲያን የሰሙትን ትምህርት ተግባራዊ ለማድረግ ሊያስቡ ሁለት ተቃራኒ የሆኑ ምላሾችን ይሰጣሉ። የመጀመሪያው የሰሙት ትምህርት በዕለት ተዕለት ኑሮ ውስጥ ተግባራዊ ሊደረግ የማይችል እንደሆነ በማሰብ መንፈሳዊውንና ዓለማዊውን የሕይወት ገጽታ በመለየት ሁለቱን በማለያየት ለመኖር ጥረት ማድረግ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የሰሙት ትምህርት ቅዱስና እውነተኛ ትምህርት ሆኖ እያለ በሕይወት ተግባራዊ እንዳይሆን ለሚው ኃጢአተኛ በመሆኑ ወይም እምነት ስለሌለው እንደሆነ በማሰብ ራስን እየኮነኑ መኖር ነው።

> *ክርስቲያኖች በዓለም የሚሠሩትን ሥራዎቻቸውን እንደ አገልግሎት በመቁጠር ለእግዚአብሔር ክብር በሚሆን መልኩ እንዲሠሩ ቤተክርስቲያን እንደ ተቋም ምን ማድረግ ይጠበቅባታል?*

ቤተክርስቲያን ምዕመናንን ስለሥራ መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ያደረገ ትምህርትና ምክር ልትሰጣቸው ይገባታል። ሆኖም ግን ስለሥራ በምታስተምርበትና በምታነሳሳበት ጊዜ ደግሞ ከሁለት ጽንፈኛ አመለካከቶች መጠበቅ ይኖርባታል። የመጀመሪያው ለሥራ ከፍተኛ ሥፍራ በመስጠት እግዚአብሔር በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ የሚኖረውን የአምላክነት ሥፍራ እንዳይወስድ ነው። ክርስቲያኖች እንደ ማንኛውም ዓለማዊ ሰው የሕይወትን ደስታና እርካታ ማግኘት የሚችሉት በሥራ ብቻ እንደሆነ እንዲያስቡ የሚጋብዝ ትምህርት መስጠት የለበትም። ክርስቲያኖች ለሥራ ክብርን የሚሰጡት መንፈሳዊነታቸውን በመጠበቅ ሊሆን ይገባል። ሥራውንም መሥራት የሚገባቸው ክርስቲያን ሆነው ነው። በሥራ ሀብትን ማግኘት፣ በትምህርት መጥቆ መሄድ የሚበረታታ ጉዳይ ነው። ቤተክርስቲያንም ምዕመናን በማንኛውም መስክ ክርስቲያኖች ቀድመው እንዲገኙ ማስተማር፣ ማደፋፈርና መደገፍ ይገባታል። ግን ስኬት መልካም ጣዕም እንዲሁም ዘላቂነት ያለው እርካታና ደስታ የሚኖረው ከክርስቶስ ጋር እንደሆነ ደግሞ አበክሮ ማሳየትና ክርስቲያኖች ስኬት ሲያገኙ እንዴት ክርስቶስን አክብረው መኖር እንደሚችሉ ማሳየት ተገቢ ነው።



ሁለተኛው ጽንፈኛ አመለካከት ደግሞ የብልጽግና ወንጌል ነው። ክርስቲያኖች ሥራ ከሠሩ በሥራቸው ስኬትን ሊያገኙ ይችላሉ። በክርስቶስ ማመን ግን በራሱ ሰዎችን ባለጠጋ አያደርጋቸውም። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ላይ እምነት ቢኖራቸው ምድራዊ በረከትንም ማግኘት ይችላሉ፣ ክርስቲያን ድሃ መሆን የለበትምና የመሳሰሉት አሳቦች መጽሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ ሁኔታ ከመተርጎም የመነጨ አሳብ ነው። በዓውዳችን ምስባኮችም በአብዛኛው የሚነገረው መንፈሳዊ መሣሪያዎችን በመጠቀም ምድራዊ በረከቶችን ማግኘት ነው። «እግዚአብሔር መኪና እንዲሰጠኝ ሦስት ዓመት ጸለይኩና ጌታ ጥሩ መኪና ሰጠኝ» «ለአገልግሎት ሙሉ ጊዜዬን ከመስጠቴ በፊት ቤት አልነበረኝም፣ ለአገልግሎት ከወጣው በኋላ ግን እግዚአብሔር ግማሽ ሚልዮን የሚያወጣ ቤት ሰጠኝ» የሚሉና የመሳሰሉ አባባሎች ምዕመናን እግዚአብሔርን ቢጠይቁ የሚፈልጉትን ነገር እንደሚቀበሉ እንዲሁም ሠርቶ ከማግኘት ይልቅ በትጋት መጸለይ የተሻለ ውጤት እንዳለው ያመለክታል። እግዚአብሔር የምንፈልገውን ነገር ሳይሆን የሚያስፈልገንን ነገር ይሰጠናል። ያለ ሥራ ቁጭ ብሎ ከመጸለይ ይልቅ እየጸለዩ መሥራት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው።

ቤተክርስቲያን ምዕመናን ስለሥራና ስለሀብት ሊኖራቸው የሚገባቸውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት ዘወትር በትጋት ማስተማር ይገባታል። ወደ ሥራ ዓለም የሚገቡ ወጣቶች እንዴት እግዚአብሔርን የሚያስደስትና ከችሎታቸው ጋር የሚዛመድ ሥራ መያዝ እንደሚችሉ ምክርና ትምህርት በመስጠት አቅጣጫ ማሳየት ይጠበቅባታል። የቤተክርስቲያን መሪዎች ሚዛኑን የጠበቀ መልካም የሥራ ሥነምግባር ያላቸው ምዕመናን ሊሆኑ ይገባቸዋል። በመንፈሳዊና የሥራ ሥነምግባራቸው የተመሰከረላቸው ምዕመናን ለሌሎች ማስተማር የሚችሉበትንም ሁኔታዎች ማመቻቸት ተገቢ ነው።

ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው አስተሳሰብና የሚያደርጉትን ነገር እንደ እግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለመፈተሽ ራሳቸውን እንዲፈትሹ የሚረዱ አሳቦች እንደሚከተለው ተጠቅሰዋል። እነርሱም:-

- ✓ *ለሥራ ያነሳሳቸውና ሥራ የሚሠሩት በምን ምክንያት ነው? ገንዘብ ለማግኘት፣ ኃላፊነት ስለሆነ፣ በፍርሃት መንፈስ ተይዘው ወይስ* ለእግዚአብሔር ክብርን ለማምጣት ወይስ ሁሉም?
- ✓ *ሥራ ለምሥራት ኃላፊነት ሲሰጣቸው ከሥራው ቶሎ ለመገላገል አቋራጭ መንገዶችን ይፈልጋሉ ወይ? አንድን ሥራ በአቋራጭ መንገድ ለመሥራት ሲታሰብ ውጤታማ ሥራ ሳይሠራ ይችላል። ሥራው ቶሎ* ካለቀ ደግሞ የተረፈው ጊዜ ምን ላይ ይውላል? ጊዜን በጥሩ ሁኔታ ለመጠቀም ሥራዎችን ሁሉ ቶሎ ቶሎ ብሎ መሥራት የሚደገፍ ነው። ሆኖም ቶሎ ቶሎ ሠርቶ ለመገላገል ማሰብ ትክክለኛ ዓላማ አይደለም።
- ✓ በሥራ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶችን እንዴት ያስተናግዳሉ? ማንኛውም ሰው በሥራ ላይ ስህተት ሲፈጽም ይችላል። ምዕመናን በሥራ ላይ ስህተት ሲሠሩ በተለይ ስህተታቸው ሌሎች ሰዎችን የሚጎዳ ሆነው ሲያገኙት ምን ዓይነት እርምጃ ይወስዳሉ? ስህተቱ በሕይወታቸው ወይም በሥራቸው ዋስትና ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በመፍራት ይደብቃሉ? ወይም ሰዎች ምን ይሉኛል፣ ስህተቴን አምኜ እንዴት እዋረዳለሁ? በማለት ስህተታቸውን ለመሸፈን ይሞክራሉ?

- ✓ ከአሠሪያቸው ወይም ተጠሪያቸው ጋር ግጭት ውስጥ ሲገቡ ምን ያደርጋሉ? ስለአሠሪው ወይም ተጠሪው ክፋትና ስህተት ስሌሎች ሰዎች ያወራሉ ወይስ ቀጥታ ወደ የሚመለከተው በመሄድ ያነጋግሩታል?
- ✓ ሳይታመሙ ነገር ግን ሥራን ላለመሥራት በሕመም በማሳታከክ ይቀራሉን?
- ✓ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጡ ሥራውን ይተዋሉን?

በአጠቃላይ እያንዳንዱ ክርስቲያን እንደሚኖርበት ዓውድ ስለሥራ የሚኖረው አመለካከት የተለያየ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ ስንመለከተው ሥራ የሰው ልጅ ለራሱ የፈጠረው ክስተት ሳይሆን ከእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሚሰጠው ትዕዛዝ ደግሞ ተግባራዊ ሲሆን ሰውን በሁለንተናዊ መልኩ የሚጠቅም እንጂ የሚጎዳ ነገር የለውም። አለመሥራት በእግዚአብሔር ዘንድ የማይፈለግ ባሕርይ ሲሆን ለሰው ልጅ መርገምን እንጂ በረከትን አያመጣም። የስንፍና ፍሬው ድህነትና ጉስቁልና ነው።

በክርስቶስ ኢየሱስ አምነው ዳግም የተወለዱ ምዕመናን ስለሥራ ያላቸው አመለካከትና በሥራ ላይ የሚያሳዩት ባሕርይ የተለወጠ ሊሆን ግድ ነው። ምክንያቱም ዳግም ልደት በሁለንተናዊ ሕይወታችን ላይ መልካም ለውጥ ሊያመጣ ይገባል። ይህ ለውጥ ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተጠቀሱትን ትዕዛዛትን ተግባራዊ በማድረግ ይገለጣል። ለክርስቲያን መሥራት መብት ሳይሆን ግዴታ ነው። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ «ሊሠራ የማይወድ አይብላ» (2ተሰ3፡10) በማለት ስለሚያዝ ነው። ክርስቲያን እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነውን ማንኛውንም ሥራ መሥራት ይችላል። በማንኛውም በተሠማራበት ሥራ ላይ ክርስቲያን ታታሪ፣ ታማኝ፣ ፍትሕን የሚያደርግና ሥራውን እንደ አገልግሎት በመቁጠር ለእግዚአብሔር ክብር የሚሠራ ሊሆን ይገባል።

ክርስቲያን እግዚአብሔር የሰጠውን ጊዜ በመልካም ሁኔታ በመጠቀም ሥራውን በትጋት መሥራት አለበት ሲባል ግን ለራሱ ሕይወት፣ ለቤተሰቡና ለመንፈሳዊ አገልግሎት ጊዜ መስጠት የለበትም ማለት አይደለም። በሥራ፣ በግል ሕይወትና በመንፈሳዊ አገልግሎት መካከል ሚዛን የጠበቀ አሠራር መኖር አለበት። ይህ እንዴት መሆን እንደሚችል በሚቀጥለው ምዕራፍ ውስጥ በሰፋት እንመለከታለን።



## ምዕራፍ 10.

## ሥራን፣ ክርስቲያናዊ ሕይወትንና መንፈሳዊ አገልግሎትን በሚዛን መጠበቅ

ሥራ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጅ የተሰጠ መልካም ኃላፊነት እንደሆነ ተመልክተናል። ሥራ መልካም ቢሆንም ገደብ ሊኖረው ይገባል። ሰዎች ፍሬያማ የሆነ ሁለንተናዊ ሕይወት እንዲኖራቸው ከፈለጉ ለሥራና ለእረፍት ጊዜ መመደብ ይጠበቅባቸዋል። እንደ ክርስቲያን በቀን ወይም በሳምንት ስንት ሰዓት መሥራት አለብን? ለዚህ ጥያቄ እያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ምላሽ የተለያየ እንደሚሆን የታወቀ ነው። አንዳንዶች ሥራን ከመጠን በላይ በመውደድ እንደ ጣዖት በማምለክ ዘወትር በሥራ ሊጠመዱ ሌሎች ደግሞ ሲያመልኩት ሌሎች ደግሞ ሥራን ከመጠን በላይ ከመጥላታቸው የተነሣ ከሥራ መቅረት ወይም ሥራ መሥራትን ማስወገድ የሚችሉበትን ማንኛውንም አማራጭ መንገድ ለመጠቀም ይሞክራሉ። በዓውዳችን ክርስቲያኖች ስለሥራ ያላቸው አመለካከት ሌሎች ሰዎች ስለሥራ ካላቸው አመለካከት እምብዛም የተለየ እንዳልሆነ ማሰብ ይቻላል። ሁለቱም ዓይነት ሰዎች ባመኑትና ባላመኑት ውስጥ እንደሚገኙ የታወቀ ነው። ከዚህ በላይ ስለሥራ የተጠቀሱት ሁለቱ አመለካከቶች ጽንፈኛ ናቸው። በሁለቱም መካከል ሚዛን ሊኖር ይገባል።

### ሥራና እረፍት

መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ሥራን በትጋት መሥራት እንዳለበት ቢያስተምርም በሥራ መካከል እረፍት አስፈላጊ እንደሆነም በግልጽ ይናገራል። ስለሆነም ሥራና እረፍት ተያይዘው የሚሄዱ ነገሮች ናቸው። ከሥራ በኋላ እረፍት ሊኖር እንደሚገባ እግዚአብሔር በራሱ ምሳሌ አሳይቶናል። እግዚአብሔር ኃይሉ ባይደክምም፣ የሚፈልገውን ነገር ለማድረግ የሚችል ቢሆንም ግን ሥራዎቹን የሚሠራው በዕቅድ ነው። በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር ፍጥረታትን ደረጃ በደረጃ ማለትም በአንድ ጊዜ አንድ ነገርን እየፈጠራቸው ፍጥረታትን ወደ ሙላት እንዳመጣቸው እንመለከታለን። በወቅቱ መሥራት የሚገባውን ሥራ ከጨረሰ በኋላ ደግሞ እግዚአብሔር እንዳረፈ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። እግዚአብሔር ለምን ከሥራው አረፈ? እግዚአብሔር ከሥራው ያረፈው ስለደከመው አይደለም። ነገር ግን በጊዜው መሥራት የሚገባውን ሥራ በማጠናቀቁና እርሱ ከሥራው እረፍት በማድረግ የሰው ልጅም የእርሱን ምሳሌ በመከተል ለተወሰነ ጊዜ ሥራን ሠርቶ ከዚያ ደግሞ ለጥቂት ጊዜ ማረፍ እንደሚገባው ለማሳየት ነው።

እግዚአብሔር ከሥራው ያረፈበትን ቀን ሰንበት ብሎ ሰየመው። «እግዚአብሔርም የሠራውን ሥራ በሰባተኛው ቀን ፈጸመ፤ በሰባተኛውም ቀን ከሠራው ሥራ ሁሉ ዐረፈ። እግዚአብሔርም ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም፤ እግዚአብሔር ሊያደርገው ከፈጠረው ሥራ ሁሉ በእርሱ ዐርፎአልና» (ዘፍ.2፡2-3)። እግዚአብሔር ከሥራው ሲያርፍ ምን አደረገ? የእረፍት ጊዜውን በምን ላይ አዋለ? እግዚአብሔር ያረፈው በሠራው ሥራ የድካም መንፈስ ይዞት ወይም ሰውነቱ ዝሎ ሳይሆን የሠራውን ሥራ አይቶ ለመደሰት ነው። ስለዚህ እግዚአብሔር በዚህ የሰንበት ቀን ስለሠራው ሥራ እያሰበ ይደነቅ ነበር ማለት ይቻላል።

እረፍት ለሰዎች ለራሳቸው የፈጠሩት ጊዜ ሳይሆን እግዚአብሔር ለሰዎች ያዘዘው አሳብ ነው፡፡ ሠርቶ ማረፍን ያስተማረው እግዚአብሔር ራሱ ነው፡፡ እግዚአብሔር ፍጥረተ-ዓለምን ፈጥሮ በየቦታቸው አድርጎ ሂደቱ እንዲቀጥል ካደረገ በኋላ ከሥራው ዐረፈ፡፡ ይህ የሰንበት ቀን የተባረከና የተቀደሰ ቀን ነው፡፡ በሳምንት ውስጥ ስድስት የሥራ ቀናትና አንድ የእረፍት ቀን ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጅ ተሰጥቶአል፡፡ እግዚአብሔር ለሕዝቤ እስራኤል በሰጠው ሕግ ውስጥም ሕዝቡ የሰንበትን ቀን እንዲያከብር ትዕዛዝ ሰጥቶአቸዋል (ዘጸ 20:11)፡፡ በዚህ ዕለት ማንኛውም የቤተሰብ አባል *ሥራ መሥራት* የለበትም፡፡ እግዚአብሔር ሰዎች ስድስት ቀን ሠርተው አንድ ቀን ግን እንዲያርፉ ያዘዘው ለምንድነው?

> ሰዎች ለኑሮአቸው የሚያስፈልገውን ነገር ለማግኘት ስድስት ቀን ሲደክሙ ከርመው በሰንበት ቀን ደግሞ ስለአምላካቸው *ሥራ* እንዲያስቡና እርሱን እንዲያመሰግኑና እንዲያመልኩ፣
> የሚያስፈልገውን *ሥራ* ለመሥራት ስድስት ቀን በቂ ስለሆነና ለሚቀጥለው የሥራ ቀናት ደግሞ በአዲስ መንፈስና ኃይል ለመዘጋጀት ጊዜ መውሰድ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ክርስቲያኖች በሥራ መትጋት እንደሚገባቸው ተጠቅሷል፡፡ እረፍት የሚገባው ጊዜውን በሚገባ ተጠቅሞ ተገቢ የሆነ *ሥራ* ለሠራ ሰው ብቻ ነው፡፡ አንድ ሰው ሳይሠራ ስለእረፍት እንዴት ማንሣት ይችላል? ስለዚህ እረፍት ሲታሰብ በቅድሚያ መምጣት ያለበት *ሥራ* ነው፡፡ ሠርቶ ማረፍ አምላካዊ ትዕዛዝ ነው፡፡ ሳይሠሩ መዝናናት መፈለግ ግን የስንፍና አንዱ ምልክት ነው፡፡

በትጋት ለሚሠሩ ሰዎች ግን እረፍት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ሰዎች ሲፈጠሩ እረፍት ማድረግ እንደሚገባቸው ሆነው ተፈጥረዋል፡፡ ስለዚህ ያለእረፍት ጤናማ የሆነ ሕይወት መምራት አይቻልም፡፡ ያለእረፍት ለሥራ ብቻ ተጠምዶ መኖር ማለብ ሰብዓዊ ላለመሆን ጥረት ማድረግ ሲሆን ውጤቱ ጉዳት እንጂ ጥቅም የለውም፡፡ ለሥራ የሚሰጠው *ሥፍራ* በሚዛን ካልሆነ ለሰው ልጅ ሕይወት የሚሰጠውን እርካታና ደስታ መስጠት አይችልም፡፡ *ሥራ* እንደ ሱስ ሆኖ ሕይወትን ሊያጠፋ የሚችል ባሕርይ አለው፡፡ አንዳንዶች *ሥራን* እንደ ጣዖት አድርገው ለራሳቸው፣ ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለእግዚአብሔር መስጠት የሚገባቸውን ጊዜ ባለመስጠታቸው ሕይወታቸው ይናጋል፡፡ ክርስቲያኖች *ሥራን* አያመልኩትም፡፡ ለክርስቲያን *ሥራ* በእርሱና በአምላኩ መካከል መግባት የለበትም፡፡ ከዚያም አልፎ *ሥራ* ቤተሰብንና ትዳርን ለማፍረስ ምክንያት ሊሆን አይገባም፡፡ *ሥራ* ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ግንኙነት የሚያዛባ እንዲሁም ትዳርንና ቤተሰብን ለማፍረስ ምክንያት የሚሆን ከሆነ ምኑ ተወደደ?

ለሥራ ምን ያህል ትኩረትና ጊዜ መስጠት አለበት? በአንድ በኩል ለሥራ ትጋትን ማሳየት ሲጠበቅ በሌላ በኩል ደግሞ መንፈሳዊ አገልግሎትና ቤተሰብ መረሳት የለባቸውም የሚለውን አሳብ በሚዛን መጠበቅ የክርስቲያን የሁልጊዜ ፈተና ወይም ውስጣዊ ትግል ነው፡፡ ብአብዛኛው ወደ አንዱ አቅጣጫ ማዘንበል ይታያል፡፡ በሥራ፣ በቤተሰብና መንፈሳዊ አገልግሎት መካከል ያለውን ሚዛን መጠበቃቸውን ለመፈተሽ ክርስቲያኖች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ራሳቸውን መጠየቅ ይችላሉ፡-



- ✓ የምሠራው *ሥራ* መጽሐፍ ቅዱስ እንዳላነብ፣ እንዳልጸልይ፣ ቤተክርስቲያን ሂጄ እንዳላመልክ ወይም መንፈሳዊ አገልግሎት እንዳልሰጥ እያደረገኝ ነው ወይ?
- ✓ አብዛኛውን ጊዜ የማስበው ስለምንድነው? ብዙ ጊዜ ከአእምሮዬ የማይጠፋው አሳብ ምንድነው? *ሥራ*፣ ቤተሰብ፣ መንፈሳዊ አገልግሎት ወይስ ሌላ?
- ✓ ለሥራ ወይም ለመንፈሳዊ አገልግሎት የምሰጠው ጊዜ ከትዳር ጓደኛዬና ከቤተሰቤ ጋር ባለኝ ግንኙነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ወይ?
- ✓ *ሥራ* በማልሠራበት ጊዜ ምን ዓይነት ስሜት ይሰማኛል? ከሥራ እረፍትን ሳደርግ በውስጤ የመረበሽና የመጨነቅ ስሜት ይሰማኛል ወይ? እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች በመጠየቅ ለሥራና ለሌሎች ኃላፊነቶች ተገቢው *ሥፍራ* መሰጠቱን መፈተሽ ይቻላል፡፡

ከላይ ለተጠቀሱት ጥያቄዎች «አዎን» የሚል ምላሽ ከተሰጠ *ሥራ* ሕይወትን እያፈረሰ እንጂ እየገነባ እንዳልሆነ መመልከት ቀላል ነው፡፡

## *ሥራና መንፈሳዊ አገልግሎት*

*ሥራንና* መንፈሳዊ አገልግሎትን በተመለከተም ሚዛን መጠበቅ አለበት፡፡ ሆኖም ይህን በተመለከተ በተለያዩ ዘመናት የተለያዩ አመለካከቶች ተንጸባርቀዋል፡፡ በመካከለኛው የቤተክርስቲያን ታሪክ ቶማስ አኩኔስ የተባለ የሥነመለኮት ምሁር ለተለያዩ *ሥራዎች* ደረጃ ሰጥቶአቸው ነበር፡፡ በዚህ መሠረት እርሻ የቀዳሚነት *ሥፍራ* ሲይዝ የዕደ ጥበብ *ሥራዎችና* ንግድ በሁለተኛና በሦስተኛ ደረጃ ላይ ተመድበው ነበር፡፡ እነዚህ ሁሉ *ሥራዎች* ግን ዓለማዊ *ሥራዎች* ይባሉ ስለነበር መንፈሳዊ *ሥራ* ማለትም የቤተክርስቲያን *ሥራ* ከእነዚህ *ሥራዎች* የላቀ እንደሆነ ይታመን ነበር፡፡ በቤተክርስቲያን በተለይም በገዳም ውስጥ መጸለይና ስለእግዚአብሔር ማሰላሰል ወደር የለሽ *ሥራ* በመሆኑ ከሁሉም *ሥራዎች* ልቆ ይታይ ነበር፡፡ *ሥራ* መንፈሳዊና ዓለማዊ በመባል ለሁለት ይከፈል እንጂ በማንኛውም ዓለማዊ *ሥራ* ላይ የተሠማራም ክርስቲያን ያን *ሥራ* ያገኘው በእግዚአብሔር ጥሪ እንደሆነ ስለሚታሰብ እያንዳንዱ ክርስቲያን *ሥራውን* በትጋት እንዲሠራና የሚሠራውንም *ሥራ* ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ ለልጆቹ ማስተማር እንደሚገባ ይበረታታ ነበር፡፡

በዚያን ዘመን ሰዎች *ሥራን* የሚሠሩት ለዕለት ኑሮአቸው የሚያስፈልጋቸውን ነገር ለማግኘት እንዲሁም ያለሥራ መቀመጥን ለማስወገድ ነበር፡፡ ክርስቲያን ያለሥራ ቢቀመጥ ወደ ኃጢአት የሚያመራውን ነገር ያስባል እንዲሁም ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ክርስቲያኖች *ሥራን* እንዲሠሩ ይደረጋል፡፡ ይህም የሚያሳየው *ሥራ* ለኑሮ የሚሆን ነገር ለማግኘትና ከኃጢአት እንዲከላከል በማሰብ እንጂ *ሥራ* በራሱ እርካታን ወይም ደስታን እንደሚሰጥ በማሰብ አይሠራም ነበር፡፡

ክርስቲያኖች በማንኛውም *ሥራ* ላይ ተሠማርተው በሚሠሩበት ወቅት *ሥራቸውን* እንደ አገልግሎት መውሰድ ይችላሉ፡፡ እንደ እግዚአብሔር ቃል የሆነ ማንኛውም *ሥራ* እንደ አገልግሎት ይቆጠራል፡፡ ይህም የሚሆነው ሠራተኛው *ሥራውን* ለእግዚአብሔር ክብርን እየሰጠና

ለሰዎች ጥቅም እንዲሆን አውቆ ሲሠራው ነው:: በአንድ በኩል ሥራን አገልግሎት ወይም ለጥቅም ማግኛ የሚሠራ ሥራ የሚያደርገው ሥራውን የሚሠራው ሠራተኛው እንደሆነ መናገር ይቻላል:: የሚሠራውን ሥራ እንደ ገቢ ማግኛ ብቻ አድርጎ የሚያስብ ሰው ሥራው ለእርሱ ጥቅም የሚያመጣ ብቻ ስለሆነ ሥራ ነው እንጂ አገልግሎት አይደለም:: ምክንያቱም በሥራው ውስጥ ጎልቶ የሚታየው የሠራተኛው ጥቅም ነው:: ሥራውን እንደ አገልግሎት የሚያስበው ሠራተኛ ደግሞ ሥራውን የተቀበለው ከእግዚአብሔር እንደሆነ በማመን በመጀመሪያ ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሚሠራላቸውን ሰዎች ለመጥቀም በመጨረሻም ከሁለቱ ውጤት የተነሣ ለራሱም ይጠቀማል:: በዚህ አሳብ መሠረት ሥራን አገልግሎት ወይም «ተራ» ሥራ የሚያደርገው የሠራተኛው የውስጥ አሳብና ዓላማ እንደሆነ መመልከት ይቻላል::

ሐዋርያው ጳውሎስ የክርስቶስ ተከታዮች የሚያደርጉትን ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲያደርጉት ይመክራቸው ነበር:: «በቃል ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢየሱስ ስም አድርጉት» (ቆላ.3:17 ይላል:: ክርስቲያኖች ሥራቸውን እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ ያስቀመጠውን መመሪያ በመከተል፣ የአሠሪያቸውን ብቻ ሳይሆን የክርስቶስን ሥልጣን በመፍራት፣ የሚሠሩት ከእርሱ ባገኙት እውቀትና ችሎታ እንደሆነ በመረዳትና በማሳወቅ ከሁሉም በላይ አምላካቸውን ለማክበር በሚሠሩበት ጊዜ ሥራቸው «ተራ» ሥራ መሆኑ ይቀርና አገልግሎት ይሆናል:: ክርስቲያኖች «ይህን ሥራ የሰጠኝ እግዚአብሔር ስለሆነ ለእርሱ ክብርን ለማምጣት መሥራት አለብኝ» ብሎ የመጀመሪያ ተጠያቂነታቸውን ለእግዚአብሔር ሲያደርጉ ሥራቸው አገልግሎት ይሆናል:: በኢየሱስ ስም የተደረገ መልካም ሥራ አገልግሎት ነው:: ሥራን በኢየሱስ ስም ማድረግ ማለት በጸሎት መጀመር ብቻ እንዳልሆነ ሊታሰብበት ይገባል:: ሥራውን ለጌታ ኢየሱስ ክብርን ለማምጣት በተነሳሳ ልብ ማድረግ ነው::

ብዙ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው መንፈሳዊ ሥራ ማለትም በቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነው ሙሉ ጊዜን ሰጥቶ (ወንጌላዊ፣ መጋቢ፣ የወንጌል አስተማሪ የመሳሰሉት በመሆን) ማገልገል እንደሆነ ያስባሉ:: መንፈሳዊ ሥራዎች እንጂ በዓለም የሚሠሩ ሌሎች ሥራዎች አገልግሎት እንደሆኑ አያስቡም:: በቤተክርስቲያን ወንጌል ሲሰበክም የእግዚአብሔርን ፈቃድ እያደረጉ ያሉ ክርስቲያኖች መንፈሳዊ ሥራዎችን የሚሠሩ እንደሆነ ነው:: አንድ ሰው በአንድ ሥፍራ ወንጌልን ሲያስተምር ቀድሞ ይሠራ በነበረበት ድርጅት ውስጥ ሲሠራ አንድ ቀን «ጌታ ሆይ! እንደ በሬ በልቼና ጠጥቼ የምኖረው እስከ መቼ ነው?» ብሎ እግዚአብሔርን እንደጠየቀ ይናገር ነበር:: አሁን እግዚአብሔር ከዚያ አውጥቶ መንፈሳዊ አገልጋይ እንዲሆን እንዳደረገው ይመሰክራል:: ሰዎች የራሳቸውን አሳብ ለመግለጽ የሚጠቀሙበት አገላለጽ ፍጹም አለመሆኑ ቢታወቅም ይህ አባባል መንፈሳዊ አገልግሎትን በከፍታ ሥፍራ ላይ አስቀምጦ መንፈሳዊ የማይባለውን ሥራ መሥራትን ደግሞ እንደ በሬ ለመብላትና ለመጠጣት ብቻ እንደ መኖር የሚያስቆጥር ነው:: ይህና እነዚህን የሚመስሉ አባባሎች የሚሰማ ክርስቲያን የሚሠራውን ሥራ እግዚአብሔር የሰጠው አገልግሎት እንደሆነ እንዲያስብ የሚያበረታቱ አይደሉም::

የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ማለት በቤተክርስቲያን ውስጥ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን ብቻ እንደሆነ የሚታሰብ ከሆነ



ክርስቲያኖች ሌሎች ሥራዎችን መሥራት የለባቸውም ማለት ነው:: በእርግጥ እያንዳንዱ ክርስቲያን በግሉ ሲጠየቅ ክርስቲያን ማንኛውንም ለእግዚአብሔር ክብርን የሚሰጥ ሥራ መሥራት ይችላል የሚል ምላሽ ይሰጣል:: ነገር ግን የወንጌል ስብከትና ትምህርት ቅኝቱ ግን አሁንም ያዘነበለው ሰዎች ሁሉ እግዚአብሔር ባስቀመጣቸው ሥፍራ ለእርሱ ክብር እንዲኖሩ ሳይሆን ሰባኪዎቹ መንፈሳዊ ነው ወደሚሉት ሥራ እንዲያዘነብሉ ነው:: ይህን ለማረጋገጥ በየሥፍራው የሚሰጡትን መንፈሳዊ ትምህርቶችና ስብከቶችን መገምገም ይቻላል::

## ምን ዓይነት አገልግሎት ለቤተክርስቲያን መስጠት ይቻላል?

የሙሉ ጊዜ አገልጋይ ያልሆነ ክርስቲያን ወይም ወንጌልን ለማስተማር በቂ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የሌለው ወይም እንዲህ ጎላ ብለው የወጡ የመንፈስ ቅዱስ የጸጋ ስጦታዎች የለኝም የሚል ክርስቲያን ምን ዓይነት መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተክርስቲያን ውስጥ መስጠት ይችላል? መልካም ሥራ የሚባለው የሙሉጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን እንደሆነ መታሰብ የለበትም:: ሥራን መንፈሳዊና ሥጋዊ ብለው የከፈሉት ክርስቲያኖቹ ናቸው እንጂ ቃሉ እንዲህ ዓይነት አሳብ አይሰጠንም::

ችሎታን በተፈጥሮም ወይም በትምህርት ተገኘ ቢባል ምንጩ እግዚአብሔር ነው:: በዚህ ችሎታ የሚሠሩ እንደ ቃሉ የሆኑ ሥራዎች ሁሉ አስፈላጊ ናቸው:: እያንዳንዱ ሥራ የሚያስፈልግበት ቦታ አለው:: እንዱ ሌላውን የሚያግዝ ነገር አለው:: በከተማ ውስጥ ኤሌክትሪክ የሚሠራ ሠራተኛ ባይኖር የኤሌክትሪክ ብልሽት ቢያጋጥም ማን ሊያስተካክል ይችላል? ኤሌክትሪክ ባይኖር መንፈሳዊ ሥራዎች ሊቋረጡ ይችላሉ:: የኤሌክትሪክ ሙያ ያለው ሰው ቢመጣና ብልሽቱን ቢያስተካክል ለእግዚአብሔር ሥራ እገዛ አደረገ ማለት ነው:: እንደ ክርስቲያን አንዱ ሥራ ከሌላው እንደሚበልጥ ከማሰብ ይልቅ ሥራዎች ሁሉ በፈሪሃ እግዚአብሔር ከተሠሩ የሚደጋገፉና ለእግዚአብሔር ክብር የሚሰጡ መሆናቸውን ማሰብ የተሻለ ነው:: ማንኛውም ተገቢ ሥራ በታማኝነትና በትጋት ለእግዚአብሔር ክብርን ለመስጠት ቢሠራ መልካም ነው::

አንዳንድ ጊዜ ጥቃቅን የሆኑ አሳቦች ወደ ክርስቲያኖች አእምሮ ውስጥ ገብተው አመለካከታቸውን ያበላሻሉ:: ጥቃቅን ቢሆኑም ውስጥ ለውስጥ እየቦረቦሩ አቅጣጫን ያስለውጣሉ:: እንደ ክርስቲያን በሥራና ለሥራ ሥነምግባር ላይ ማመቻመች ማለትም እንደ እግዚአብሔር ቃል አለማድረግ ቀስ በቀስ እያደገ ይሄድና ሕይወትን ይወርሳል:: ሰይጣንም በክርስቲያኖች ሕይወት ውስጥ መግባት የሚችለው ጥቂት ትክክለኛ ያልሆነ አሳብ አስቀድሞ በማስገባት ነው:: አንድ ጊዜ ከትክክለኛው አስተሳሰብ ካለወጣ ትክክለኛ ወዳልሆነ ድርጊት ይመራል:: ክርስቲያናዊ ያልሆነ ድርጊት ሲፈጸም ደግሞ የበደለኛነትን ስሜት ያስከትላል::

እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ የወንጌል አገልጋዮች እንዲሆኑ አልጠራም:: ሁሉም የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ እንዲሆን አልተጠራም:: ነገር ግን እያንዳንዱ በክርስቶስ ያመነ ሁሉ በዓለም ውስጥ የክርስቶስ ምስክር እንዲሆን ተጠርቷል:: ለወንጌል አገልግሎት የተጠሩ አገልጋዮች በትጋት የወንጌልን ሥራ እንዲሠሩ እንዲሁም ለወንጌል አገልግሎት የሚያስፈልገው ሀብት እንዲገኝ ምዕመናን ተግተው ሠርተው

ለወንጌል አገልግሎት መስጠት ይችላሉ:: ይህ የማይሆን ከሆነ የታላቁ ተልዕኮ እንደሚገባ ከግብ አይደርስም:: የክርስቶስ ተከታዮች በሁለት መልኩ ለታላቁ ተልዕኮ ስኬት አስተዋጽኦ ያደርጋሉ:: የመጀመሪያ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ሠርተው ከሚያገኙት ገቢ በገንዘብና በቁሳ ቁስ በመደገፍ ሲሆን ሁለተኛ ደግሞ ሥራቸውን በትጋት በመሥራት ለሌሎች ሰዎች ምሳሌ ሆነው በተግባር ምስክርነት በመስጠት ነው (1ጢሞ6:1፣ ቲቶ2:9፣10)::

ክርስቲያኖች አንድ ማወቅ የሚገባቸው አሳብ አለ:: ይኼውም እያንዳንዱ ክርስቲያን ከዚህ ከጨለማው ዓለም ሥርዓትና የሕይወት ዘይቤ የተጠራው የእግዚአብሔርን በጎነት እንድነግር ነው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ለምዕመናን እንዲህ የሚል መልዕክት ጽፎላቸዋል::

> እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትነግሩ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ» (1ጴጥ2:9) ይላል::

እግዚአብሔር ሰዎችን ከዚህ ከጨለማው ሥርዓት በልጁ ደም ገዝቶ ነጻ ያወጣቸው የእርሱን በጎነት እንዲነግሩ ነው:: ምዕመናን የእግዚአብሔርን በጎነት የሚናገሩት ለምዕመናን ሳይሆን እነርሱ ከመጡበት በጨለማው ዓለም ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች ናቸው:: እግዚአብሔር በሕይወታቸው ያደረገውን ለውጥ በአንደበትና በድርጊት ይናገራሉ:: ይህ ሥራ የእያንዳንዱ ከጨለማ ወጥቶ ወደ ብርሃን የመጣ አማኝ ኃላፊነት ነው:: ይህን ኃላፊነት ለመወጣት ደግሞ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን አያስፈልግም:: ምዕመናን ተበታትነው ባሉበት በማንኛውም ሥፍራ ለክርስቶስ ኢየሱስ ምስክሮች መሆን ይችላሉ:: ስለዚህ ወደ ቤተክርስቲያን በመምጣት እርስ በርስ ለመሟሟቅ መቻላቸውን እንደ ትልቅ መንፈሳዊነትና አገልግሎት መቁጠራቸውን መተው ይገባቸዋል:: ብርሃናቸው ደምቀው የሚታየው እንዲሁም ሰዎችን ከጨለማው ዓለም ወደ ወንጌል ብርሃን ማምጣት የሚችሉት ባላመኑ ሰዎች መካከል ሲሆኑ ነው:: ካላመኑ ሰዎች ጋር ለመሆን አንዱ ምቹ ሥፍራ ደግሞ የሥራ ቦታ ነው::

እግዚአብሔር ለወንጌል አገልግሎት በልዩ ጥሪ ከጠራቸው ሰዎች ውጭ ሌሎች ምዕመናን እንደ እግዚአብሔር ቃል በሆነ ሥራዎቻቸው እግዚአብሔርን ማክበር ይገባቸዋል:: ሥራዎቻቸው መንፈሳዊ እንዳልሆኑ አስበው መስነፍ አይገባቸውም:: መንፈሳዊ አገልግሎት የሚባለው የግድ ወንጌልን መስበክ፣ መንፈሳዊ ፕሮግራም መምራት፣ የመዘምራን አባል ሆኖ መዘመር፣ ዲያቆን ሆኖ የአስተዳደር ሥራ መሥራት፣ ብቻ አይደለም::

ሥራ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ መንፈሳዊ የሆነና መንፈሳዊ ያልሆነ ተብሎ ሳይሆን ከተገለጠው ከእግዚአብሔር አሳብና ፈቃድ ጋር የማይቃረን ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰው ልጆች ጥቅምና መታነጽ ከተሠራ መልካም ነው:: በተለያየ ሙያ በተለያየ ዓለማዊ ወይም ክርስቲያናዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሠሩ ክርስቲያኖች በሙያቸው ቤተክርስቲያንን ቢያገለግሉ እግዚአብሔር በሰጣቸው ችሎታና በተማሩት እውቀት እግዚአብሔርንና ሕዝቡን አገልግለዋል ማለት ነው:: ለምሳሌ መሐንዲሶች ለምዕመናን የአምልኮ ቤት ዲዛይን ቢሠሩ፣ ግንበኞች ቤቱን ቢገነቡ፣ የኤሌክትሪክ ባለሙያዎች ኤሌክትሪክ መስመር ቢዘረጉ፣ የቧንቧ ሠራተኞች በቤቱ ውስጥ ቧንቧውን ቢዘረጉ፣ አናጢው ቆርቆሮውን ቢመታ፣



እንዲሁም ሌሎችም ቤቱ እስኪያልቅ ድረስ የሚያስፈልገውን ነገር ቢያደርጉ ይህ አገልግሎት አይደለምን? የግድ እነዚህ ሰዎች መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት መጽሐፍ ቅዱስን ማስተማር ወይም የሆነ መንፈሳዊ ኮሚቴ ውስጥ መግባት አለባቸውን? የለባቸውም::

እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሲፈጥር የሠራቸው ሥራዎች መንፈሳዊ የሆኑ ወይስ መንፈሳዊ ያልሆኑ ናቸው? እግዚአብሔር ፍጥረታትን ሲፈጥር የወንጌል ስብከት አላደረገም:: ለነገሩ የሰው ልጅ ስላልተፈጠረ ለማን ይሰብክ ነበር! ሥራዎቹን ሠርቶ ከጨረሰ በኋላ ግን የሠራቸው ሥራዎች ሁሉ እጅግ መልካም እንደሆኑ ተናግሯል (ዘፍ.1:31):: እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ የሰው ልጅ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ብቻ እንዲጎለብት የሚጠቀሙ ድርጊቶች ብቻ አልነበሩም:: የእርሱ ሥራዎች ሁለንተናዊ ጥቅም አላቸው:: እግዚአብሔር ሥራዎችን ሲሠራ ሥራዎቹ ሁሉ በእምነት (መዝ.33:4)ና በጥበብ (መዝ.104:24) ይሠራሉ::

በዚህ ዓለም ላይ የሰው ልጅ የሚሠራው ሥራዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት መልካም አይደሉም:: አንዳንድ ሥራዎች መልካም ሲሆኑ ሌሎቹ ግን ክፉዎች ናቸው:: የክርስቲያኖች ሥራ ግን መልካም ሥራ ሲሆን እንደሚገባ ታዞዋል:: ክርስቲያኖች ክፉ ሥራዎችን ለሚሠሩ ሰዎች መልካምን ሥራ ሠርተው ማሳየት እንደሚገባቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ አስተምሯል:: ክርስቲያኖች ክርስቶስን ባላመኑ ሰዎች መካከል ሲኖሩ በሚሠሩት ሥራ ትጋትን፣ ታማኝነትንና ፍትሕን በማሳየትና ክርስቶስን የሚመስል ባሕርያት በማሳየት ሰዎች እግዚአብሔርን በእነርሱ ሕይወት ውስጥ እንዲመለከቱ በማድረግ ነው:: ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ከክርስቲያኖች ጋር የሚደረጉትን ሥራዎችንማ የት ያዩታል?

> *ክርስቲያኖች የሚሠሩትን ማንኛውንም እንደ ቃሉ የሆነ ሥራ እንደ አገልግሎት መቁጠር የሚችሉ ከሆኑ መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተክርስቲያን መስጠት ያስፈልጋቸዋልን? በሁለቱም ሥፍራ ከሚወጠሩ አንዱን ብቻ በተገቢ ሁኔታ ቢሠሩ ምን ችግር አለው?*

ክርስቲያኖች የክርስቶስ አካል ብልቶች በመሆናቸው ለአካሉ ማስትም ለቤተክርስቲያን መታነጽ እያንዳንዳቸው ስጦታ አላቸው:: ይህ ስጦታቸው ምን እንደሆነ ለይተው በማወቅ በሙያቸው ወይም እግዚአብሔር በውስጣቸው ባስቀመጠው ማንኛውም ስጦታ ማገልገል ይችላሉ:: ከላይ ለመጥቀስ የተሞከረው ሁሉም ክርስቲያን «መንፈሳዊ» የሚባሉትን ሥራዎች ለመሥራት ከማሰብ የተነሣ እግዚአብሔር እንዲሠራ የሚፈልገውን ሥራ ሳይሠራ መቅረት እንደሌለበት ነው:: በዓለም ውስጥ በሚሠሩት ሙያና ስጦታ ወይም በተለየ ልዩ ስጦታ ቤተክርስቲያንን በሚያገለግሉበት ጊዜ ክርስቲያኖች ሚዛን መጠበቅ ይገባቸዋል::

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅደም ተከተልን የሕይወት መርሕ ማድረግ

ለአንድ መንፈሳዊ አገልጋይ የተጠቀሱ መርሆዎች ለምዕመናንም ተግባራዊ ይሆናሉ:: ከሁሉም በላይ ቅድሚያ የሚሰጠው በግል ከእግዚአብሔር ጋር ተራክቦ ለማድረግ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የሚመጣው

ደግሞ ለቤተሰብ አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት ነው። ከቤተሰብ ቀጥሎ የሚመጣው ጉዳይ ሥራ ነው። በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት የሚመጣው ከዚህ በኋላ ነው። አንድ የክርስቶስ ተከታይ የሚሠራው ሥራና በቤተክርስቲያን የሚሰጠው አገልግሎት የቤተሰብን ሕይወት የሚያንጽ እንጂ በቅርብ ወይም በረጅም ጊዜ የሚጎዳ ሊሆን አይገባም። ስለሆነም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የሚሰጠው ጊዜ ሥራንና የቤተሰብ ሕይወትን ከዚያም በግል ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን የጥሞና ጊዜ እስከማይጎዳ ድረስ ነው።

አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲሰጥ የዕለት ሥራውን ይሠራል። አንድ ምዕመን ግን መንፈሳዊ አገልግሎት በቤተክርስቲያን በሚሰጥበት ጊዜ በየዕለቱ ከሚሠራው ሥራ በተጨማሪ ሌላ ሥራ ይሠራል። ይህ ደግሞ በሕይወቱ ላይ ጫናን እንደሚያመጣ የታወቀ ነው። ቀን ሥራ እየሠሩ ውለው ማታ ወይም ሳምንቱን ሁሉ ሥራ ሲሠሩ ከርመው በሰንበት ቀን በመንፈሳዊ አገልግሎት ይጠመዳሉ። ይህ በግል ሕይወታቸው ከእግዚአብሔር እንዲሁም ከቤተሰባቸው ጋር የሚኖራቸውን ጊዜ እጅግ ይሻማል። ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውና የቤተሰባቸው ሕይወታቸው ይናጋል። በቤተክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎትን መስጠት በራሱ የግል መንፈሳዊ ሕይወትን አያሳድግም እንዲሁም ቤተሰብን እግዚአብሔርን የሚያስከብር ቤተሰብ አያደርግም። ሁለቱም ጊዜ በመስጠት መሥራትን የሚጠይቁ ጉዳዮች ናቸው።

እንግዲህ ክርስቲያን ሥራን በትጋት መሥራት ይኖርበታል። የሚሠራው ሥራ በዘላቂነት ፍሬያማ እንዲሆንና የሠራተኛውን ሁለንተናዊ ሕይወት በሚጠቅም ሁኔታ እንዲሆን እረፍት ያስፈልጋል። ክርስቲያን እንደ ማንኛውም ሠራተኛ ቢሠራም በቤተክርስቲያንም ድርሻ አለው። ይህንንም ድርሻውን ደግሞ ሥራውን፣ ቤተሰቡንና ሕይወቱንም በማያዳሽቅ ሁኔታ በሙያው በማገልገል ወይም ሠርቶ ከሚያገኘው ገቢ ለታላቁ ተልዕኮ መሳካት ድጋፍ በመስጠት መወጣት ይችላል። ከሁሉም በላይ ግን በሚሠራበት ሥፍራ ባላመኑ ሰዎች መካከል በቃልና በተግባር የሚመሰክርለት በመሆን ያገለግላል። በክርስቶስ ባላመኑ ሰዎች መካከል ብርሃን የመሆንን ተልዕኮ ትቶ በቤተክርስቲያን ውስጥ ብዙ «መንፈሳዊ» አገልግሎቶችን በመስጠት መባከን በእግዚአብሔር ፊት ሚዛን የሚደፋ አይሆንም።



## Bibliography


Adams, J. (1972 ). *Christian Living in the Home*. NJ: Phillipsburg, Presbyterian and Reformed Publishing Company.

Adams, J. (1975). *Shepherding God's Flock*. Grand Rapids, MI: Zondervan Publishing House

Cloud, H. & Townsend, J. (1992). *Boundaries*. Zondervan Publishing House.

Fernando, A. (1985). *Leadership Life Style*. Wheaton, IL: Tyndale House Publishers, Inc

Miles, R.L. (1999). *The Pastor as Moral Guide*. MN, Fortress Press.

Murray, A. (1983). *How to Work for God*. Whitetaker House.

Parker, T.HL (1965). *Calvin's Commentaries*. Grand Rapids, MI: Wm.B. Eerdmans Publishing Company.

Shawchuck, N. and Heuser, R. (1993). *Leading the Congregation: Caring for Yourself While Serving Others*. Nashville, Abingdon Press.

Stott, J. (1989). *The Message of Ephesians*. Inter varsity Press.

Stott, J. (1996). *The Message of 1Timothy and Titus*. Inter varsity Press

Sugden, H.F. and Wiersbe, W. W. (1980). *Confident Pastoral Leadership*. Cbicago, Moody Press.

ከበደ በከሬ (1997). *ልጆቻችንን እንዴት እናሳድጋቸው?* አአ

ከበደ በከሬ (1997). የስኬታማ አገልግሎት መርሆዎች። አአ